ከኢሰላም መርሆዎች

ክፍል ሁለት

ማውጫ

ምዕራፍ አንድ

ከተላቀው ቁርኣን ጋር 7

سورة الأَعْلَى (የበላይ አሸናፊው ምዕራፍ) 8

የመጀመሪያው ክፍል 10

ሁለተኛው ክፍል 17

سورة الغاشية (የሸፋኝቱ ምዕራፍ) 19

የመጀመሪያው ክፍል 19

ሁለተኛው ክፍል 23

سورة الفجر (የጎህ ምዕራፍ) 27

ክፍል አንድ 28

ክፍል ሁለት 32

سورة البلد (የሀገር ምዕራፍ) 37

سورة الشمس (የፀሐይ ምዕራፍ) 44

سورة الليل (የሌሊት ምዕራፍ) 50

سورة الضحى (የረፋዱ ምዕራፍ) 57

ምዕራፍ ሁለት

አል-ሑዲሱ ሸሪፍ 60

ስድስተኛው ሑዲስ 61

ሐላልና ሐራም 61

የቃላትና ሐረጎች ፍቺ 62

ጥቅል ትርጓሜ 63

ሰባተኛ ሑዲስ 67

ዲን ነሲሐ (ምክክር) ነው 67

የሑዲሱ አሳሳቢነት 67

የቃላትና ሐረጎች ትርጓሜዎች 68

አጠቃላይ ትርጓሜ 68
ከሑዲሱ የምንቀስመው ትምህርት 72
ስምንተኛው ሑዲስ 74
የመልሊም ደም ጥበቅነት 74
የሑዲሱ አስፈላጊነት 74
የቃላትና ሐረጎች ፍቺዎች 75
ጥቅል ትርጓሜ 75
ከሑዲሱ የምንቀስመው ትምህርት 77
ዘጠኛው ሑዲስ 78
ማብራሪያና አለማክረር 78
የሑዲሱ አሳሳቢነት 78
ሑዲሱ የተነገረበት ሰበብ 79
የቃላትና ሐረጎች ፍቺዎች 79
ጥቅል ትርጓሜ 80
አስረኛው ሑዲስ 83
መልካም የሆነ ሐላል የተቀባይነት መስፈርት ነው 83
የሑዲሱ አሳሳቢነት 84
የቃላትና ሐረጎች ፍቺዎች 84
ጥቅል ትርጓሜው 85
ከሑዲሱ የምንቀስማቸው ትምህርቶች 86

ምዕራፍ ሦስት

ዐቂዳ 88
ሀለተኛው የእምነት መሠረት 89
በመላእክት ማመን 89
ተግባራዊ እርምጃዎች 91
ሦስተኛው የእምነት መሠረት 93
በአላህ መጻሕፍት ማመን 93

ምዕራፍ አራት

ቆይታከአላህ መልዕክተኛ ታሪክ ጋር 101
የነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ) በሐራእ ዋሻ መላለል/ኸልዋ/ 102
ኸልዋ /አላህን ለመዛት ብቸኝነትን በመምረጥ መልል/ 102
የወሕይ መጀመር 106
ሚከጥራዊው የደዕዋ ሂደት 109
ይፋዊ ጥሪ 113
ጥሪወን ለሞላሽት ጥቅም ላይ የዋሉ ልዩ ልዩ ስልቶች 118

ምዕራፍ አምስት

የሶሐቦች ቅንጭብ ታሪክ 130
ዐሚር ኢብኑ አል-ኹጣብ 131
ታላቅነቱን ከሚያሳዩ ነገሮች መካከል ጥቂቶቹ 139
አቡ ዐብይዳህ ዐምር ኢብኑ አል-ጀራሕ 149
ሰልማን አል-ፋሪሲ(እውነትን ፈላጊው) 157

ምዕራፍ ስድስት

ራስን ወደ ተሸለ ደረጃ መለውጥ..... 160
አጠቃላይ ዓላማ.....168
የመጀመሪያው ዓላማ 168
ሁለተኛው ዓላማ 176
ራስን ወደ ተሻለ ደረጃ የመለውጥ አሳሳቢነትና አስፈላጊነት ሊያብራራ 176
ሦስተኛው ዓላማ 185
የነፍስን ባህሪያትና ጉድለቶቿን ሊገነዘብ 185
አራተኛው ዓላማ 195
ነፍሶችን የማልበቻ ዘዴዎች ግልጽ ሊያደርግ 195
1- አላህን መፍራትና ነፍስን ከስሜቷ መከልከል 195
2- ነፍስን ምርመራ ማድረግ 204
3- ወደ አላህ ተወበት ማድረግ 212
4- ሞትን ማስታወስ 229

5- ዱዓ 233

ምዕራፍ ሰባት

የእስልምና የዕወቀት ምንጭ 240
አጠቃላይ ዓላማ..... 241
የመጀመሪያው ዓላማ 241
የእስልምናን የዕወቀት ምንጭ ግልፅ ማድረግ 241
የሁለተኛው አጠቃላይ ዓላማ 251
እስልምናን ለማንዘብ በዲን ዕወቀት በተሻሉ ሰዎች መታገዝ አስፈላጊ ስለመሆኑ 251
የሦስተኛው አጠቃላይ ዓላማ 262
እስልምናን ከምንጩ ለመመቅ አላህን ፈሪና በእወቀቱ የተሻለ መሆኑን በሚያምንበት ሰው ሊታገዝ 262
የአራተኛው አጠቃላይ ዓላማ 276
የመልክተኛውንና (ሰ.ዐ.ወ) የቀደምት መልካም ሰለፎችን ፈለግ በማኛወም ሁኔታው ተግባራዊ ሊያደርግ 276
የመጀ ምንጮች..... 282

ምዕራፍ አንድ

ከተካቀው ቁርኣን ጋር

سورة الأَعْلَى

(የበላይ አሸናፊው ምዕራፍ)

ኢማም አሕመድ እንደዘገቡት ኢማም ዐሊይ (ከረመላሁ ወጅሀሁ) “የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ‹ሰብቢሒ-ስመ ረብቢከል-አዕላ› የተሰኘችውን ይህችን ምዕራፍ ይወዷት ነበር።” ብለዋል።

ሙስሊም ሶሒሕ የሐዲስ ጥራዛቸው ላይ እንዳሰፈሩት ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በሁለቱ ዒዶችና በጁሙዓ ሶላቶች ውስጥ ‹ሰብቢሒ-ስመ ረብቢከል-አዕላ› እና ‹ሀል አታከ ሐዲሡ-ል-ጋሺያ› የተሰኙትን ምዕራፎች ያነቡ ነበር። አንዳንዴ በዓላቱና የጁሙዓ ሶላት አንድ ቀን ላይ ሲውሉ በሁለቱም ሶላቶች ያነቧቸው ነበር።

በርግጥ የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) የፍጥረተ ዓለሙን በሙሉ የበላይ ጌታቸውን ከየአቅጣጫው ተገቢ ካልሆኑ ስያሜዎች ያጠራበት ዘንድ ወደ አምልኮ ስፍራ የምትለውጠውን፣ በውዳሴና በማጥራት የታጀበችውን ይህችን ምዕራፍ መውደድ ይገባቸው ነበር።

﴿سَبِّحِ ٱسْمَ رَبِّكَ ٱلْأَعْلَى ۝١ ٱلَّذِى خَلَقَ فَسَوَّىٰ ۝٢ وَٱلَّذِى قَدَّرَ فَهَدَىٰ ۝٣ وَٱلَّذِىٓ أَخْرَجَ ٱلْمَرْعَىٰ ۝٤ فَجَعَلَهُۥ غُثَآءً أَحْوَىٰ ۝٥﴾ الأعلى: ١ - ٥

“ከሁሉ በላይ የኾነውን ጌታህን ስም አሞግስ፣ የዚያን (ሁሉን ነገር) የፈጠረውን፣ ያስተካከለውንም፣ የዚያን የወሰነውንም (ለተፈጠረለት ነገር) የመራውንም፣ የዚያን ግጦሽን (ለምኣም አድርጎ) ያወጣውንም፣ (ከዚያ) ደረቅ ጥቁር ያደረገውንም (አምላክ ስም አሞግስ)።” (አል-አዕላ፡ 1-5)

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) የታላላቅ ጉዳዮች ብስራት የያዘችላቸውን ይህችን ምዕራፍ በእርግጥ መውደድ ይገባቸው ነበር። ጌታቸው ጥሪውን የማድረስና የማስታወሱን ኃላፊነት እንዲወጡ አዟቸዋል፡-

﴿سَنُقْرِئُكَ فَلَا تَنسَىٰٓ ٦ إِلَّا مَا شَآءَ ٱللَّهُۚ إِنَّهُۥ يَعْلَمُ ٱلْجَهْرَ وَمَا يَخْفَىٰ ٧ وَنُيَسِّرُكَ لِلْيُسْرَىٰ ٨ فَذَكِّرْ إِن نَّفَعَتِ ٱلذِّكْرَىٰ ٩﴾ الأعلى: ٦ - ٩

"[ቁርአንን] በእርግጥ እናስነብበሃለን፣ አትረሳምም፤ አላህ ከሻው ነገር በስተቀር፡፡ እርሱ ግልጽን፣ የሚሸሸገውንም ሁሉ ያውቃልና፡፡ ለገሪቱም [ህግጋት] እንገጥምለን፡፡ ግሣጼይቱ ብትጠቅም [ሰዎችን] ገሥጽም፡፡"
(አል-አዕላ፡ 6-9)

ልቦናቸው ቁርኣንን ጠብቆ እንደሚይዝ ዋስትናውን ይወስድላቸዋል፡፡ ከዚህም ባሻገር በሁሉም ሁኔታዎቻቸውና በዚህ ጥሪያቸው ምንጊዜም ገር ወደሆነው አቅጣጫ እንደሚመራቸው ዋስ ሆኖላቸዋል፡፡ ይህ እጅግ የላቀ ጉዳይ ነው፡፡

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ይህችን ምዕራፍ መውደድ ይገባቸው ነበር፡፡ ምክንያቱም ይህች ምዕራፍ ፈጣሪን አንድ የማድረግን፣ መለኮታዊ ረዕይን ማረጋገጥን፣ በወዲያኛው ዓለም (አኺራ) በሥራ መመንዳትን ማረጋገጥ የመሳሰሉ *መሠረታዊ የእምነት (ዐቂዳ)* መመሪያዎች ማረጋገጫ በውስጧ ስለያዘች ነው፡፡ ይህች ምዕራፍ የመጀመሪያው እምነት ማጠናከሪያ ነች፡፡ ከዚያ ይህን እምነት ሩቅ ከሆኑት የእምነት ዘርፎች እና ካለፉት ነገረ ሥሮች፣ ዘመናትን ተሻግሮ የሚያልፍ ጥልቅ ስረ-መሰረት ጋር ታያይዛለች።

﴿إِنَّ هَٰذَا لَفِى ٱلصُّحُفِ ٱلْأُولَىٰ ١٨ صُحُفِ إِبْرَٰهِيمَ وَمُوسَىٰ ١٩﴾ الأعلى: ١٨ - ١٩

"ይህ በፊተኞቹ መጻሕፍት ወስጥ ያለ ነው፤ በኢብራሂምና በሙሳ ጽሑፎች ወስጥ፡፡" (አል-አዕላ፡ 18-19)

ምዕራፏ የዚህን ዐቂዳ፣ ለሕዝብ የሚያደርሰውን መልዕክተኛ እንዲሁም የተሸካሚውን ትውልድ ጸባይ በምስል ከማቅረቧ ይበልጥ የገርነትንና የይቅር ባይነትን ጸባይ በተገቢው ሁኔታ አስቀምጣለች፡፡

የመጀመሪያው ክፍል

(አንቀጽ: 1-13)

﴿ سَبِّحِ ٱسۡمَ رَبِّكَ ٱلۡأَعۡلَى ١ ٱلَّذِي خَلَقَ فَسَوَّىٰ ٢ وَٱلَّذِي قَدَّرَ فَهَدَىٰ ٣ وَٱلَّذِيٓ أَخۡرَجَ ٱلۡمَرۡعَىٰ ٤
فَجَعَلَهُۥ غُثَآءً أَحۡوَىٰ ٥ سَنُقۡرِئُكَ فَلَا تَنسَىٰٓ ٦ إِلَّا مَا شَآءَ ٱللَّهُۚ إِنَّهُۥ يَعۡلَمُ ٱلۡجَهۡرَ وَمَا يَخۡفَىٰ ٧ وَنُيَسِّرُكَ
لِلۡيُسۡرَىٰ ٨ فَذَكِّرۡ إِن نَّفَعَتِ ٱلذِّكۡرَىٰ ٩ سَيَذَّكَّرُ مَن يَخۡشَىٰ ١٠ وَيَتَجَنَّبُهَا ٱلۡأَشۡقَى ١١ ٱلَّذِي يَصۡلَى
ٱلنَّارَ ٱلۡكُبۡرَىٰ ١٢ ثُمَّ لَا يَمُوتُ فِيهَا وَلَا يَحۡيَىٰ ١٣ ﴾ الأعلى: ١ - ١٣

"ከሁሉ በላይ የኾነውን ጌታህን ስም አሞግሥ፡ (1) የዚያን (ሁሉን ነገር) የፈጠረውን ያስተካከለውንም፡ (2) የዚያንም የወሰነውን፡፡ (ለተፈጠረለት ነገር) የመራውንም፡ (3) የዚያንም ግጦሽን (ለምለም አድርጎ) ያወጣውን፡፡ (4) (ከዚያ) ደረቅ ጥቁር ያደረገውንም (አምላክ ስም አሞግስ)፡፡ (5) (ቁርአንን) በእርግጥ እናስነብበሃለን፤ አትረሳምም፡ (6) አላህ ከሻው ነገር በስተቀር፡፡ እርሱ ግልጹን የሚሸሸገውንም ሁሉ ያውቃልና፡፡ (7) ለገሪቱም (ሕግጋት) እንገጥምለን፡፡ (8) ግሣጼይቱ ብትጠቅም (ሰዎችን) ገሥጽም፡ (9) (አላህን) የሚፈራ ሰው በእርግጥ ይገሣጻል፡፡ (10) መናጢውም ይርቃታል፡፡ (11) ያ ታላቂቱን እሳት የሚባው፡ (12) ከዚያም በእርሷ ወስጥ አይሞትም ሕያውም አይኾንም፡ (13)"

የትምህርቱ ዝርዝር ዓላማዎች

1. ይህች ምዕራፍ በአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ ያላትን ቦታ እንዲገልጽ ማስቻል፡፡
2. የኃያሉን አላህ የአፈጣጠር ችሎታ በማስተንተን እንዲያጠራውና እንዲያወድሰው ማስቻል፡፡
3. ምዕራፏ ለአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እና ከእሳቸው ሕልፈት በኋላ ለሚመጣው ሕዝብ ያዘለችውን ብስራት እንዲገልጽ ማስቻል፡፡
4. ምዕራፏ ያመለከተችውን ወደ አላህ መንገድ ጥሪ የሚያደርግ አንድ ሰው ሊኖረው የሚገባውን ኃላፊነት እንዲጠቅስ ማስቻል፡፡

5. በተግሳፅ ተጠቃሚ የሚሆንና የማይሆንን እንዲጠቅስ ማስቻል።

[ከሁሉ በላይ የኾነውን ጌታህን ስም አሞግሥ፡ (1) የዚያን (ሁሉን ነገር) የፈጠረውን ያስተካከለውንም፡ (2) የዚያንም የወሰነውን፡፡ (ለተፈጠረለት ነገር) የመራውንም፡ (3) የዚያንም ግጦሽን (ለምለም አድርጎ) ያወጣውን፡፡ (4) (ከዚያ) ደረቅ ጥቁር ያደረገውንም (አምላክ ስም አሞግስ)፡፡]

“ተስቢሕ” ማለት ማላቅ፣ ማጥራት፣ ለአላህ (ሱ.ወ) ብቻ የተገቡ ባሕሪያትንና ትርጓሜዎችን በአእምሮ እንዲመጡ ማድረግና በልቦና ውስጥ ማስረፅ ማለት ነው፡፡ እንጂ እንዲያው በአንደበት “ሱብሓነሏህ” የተሰኘውን ቃል መደጋገም ማለት ብቻ አይደለም፡፡ (ከሁሉ በላይ የሆነውን ጌታህን አጥራ)

“ረብ (ጌታ)” ደግሞ ተንከባካቢና ጠባቂ ማለት ነው፡፡ “አል-አዕላ” (ከሁሉ የበላይ የሆነው) መገለጫ ደግሞ ፍጻሜ የለሽ ወደሆነው አጽናፍ ነፍስ እንድትመለከት የሚያደርግና አላህን እስከወዲያኛው እንድታሞግስ… አላህን እንድታወድስ ነፃ የሚያደርግ ነው፡፡

ከሁሉ በላይ የኾነውን ጌታህን ስም አሞግስ፤” የሚለው አገላለጽ በመጀመሪያ መልዕክቱ የተላለፈው ለአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ሲሆን ከጌታቸው የመጣ ትእዛዝ ነው፡፡ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) በቅድሚያ ይህን ትእዛዝ ያነቡና ከዚህኛው ወደ ሌላኛው የምዕራፉ አንቀጽ ከመሸጋገራቸው በፊት በቀጥታ ለትእዛዝ ምላሽ በመስጠት አንቀጹን ያሰርጉት (ይቋጩት) ነበር፡፡ በዚህ መሠረትም ትእዛዙን አንብበው ካጠናቀቁ በኋላ፣ سبحان ربي الأعلى” “ከሁሉ በላይ የኾነው ጌታዬ ጥራት (ሙገሳ) ተገባው” ይሉ ነበር፡፡

﴿ٱلَّذِى خَلَقَ فَسَوَّىٰ ۝٢ وَٱلَّذِى قَدَّرَ فَهَدَىٰ ۝٣﴾ الأعلى: ٢ - ٣

“የዚያን (ሁሉን ነገር) የፈጠረውን፥ ያስተካከለውንም፤ የዚያንም የወሰነውን፥ (ለተፈጠረለት ነገር) የመራውንም፤” (አል-አዕላ፡ 2-3)

ያ ሁሉንም ነገር የፈጠረና ያስተካከለውን፣ ስሪቱንም ምሉዕ ያደረገውን ከአፈጣጠሩ ጋር የሚስማማውን የምሉእነት ደረጃ ላይ ያደረሰውን፣ ያ ለእያንዳንዱ ፍጥረት ሥራውንና ትልሙን የወሰነውን ወደ ተፈጠረለት ዓላማ የመራውን፣ የመገኘቱን ዓላማ ያለበሰውን፣ ለሚኖርበት ጊዜ የሚጠቅመውን ነገር የወሰነለትን፣ ወደዚሁ የመራውን ጌታውን እንዲያሞግስ (እንዲያመሰግን) ታዟል። ይህ ደግሞ ወደ ሁሉም ግኝት ያዘነበለ ታላቅ እውነታ ከመሆኑ ባሻገር ለግኝቱ ሁሉም የሚመሰክሩለት ሁኔታ ነው።

(የዚያን ግሶሽን (ለምላም አድርጎ) ያወጣውንም፤ (ከዚያ) ደረቅ ጥቁር ያደረገውንም (አምላክ ስም አሞላስ)... "ግሶሽ" የሚለው ቃል ማንኛውንም ዕፅዋት ያጠቃልላል። ፍጡር ጥቅም ላይ እንዲውል ታስቦ ቢሆን እንጅ ያለ ጥቅም የተፈጠረ የለም። ዕፅዋት በመጀመሪያ ደረጃ አረንጓዴ ሆኖ ይወጣል። ከዚያም በሂደት ይጠወልግና ይደርቃል። ቀለሙም ወደ ጥቁርነት አድልቶ የገረጣ ይሆናል። የዕፅዋት የሕይወት ደረጃ (አስተዳደግ) እዚህ ላይ መጠቀሱ ሌላ ድብቅ ምስጢር እንድናስተውል ያስችለናል። ይኸውም ማንኛውም አዝመራ ወደ መሰብሰብ እንደሚያመራ ሁሉ ማንኛውም ሕይወት ያለው ሁሉ ፍጻሜ እንዳለው ያመላክታል። ይህም ቅርቢቱ ዓለም ሕይወትና ስለ ወዲያኛው ዓለም ሕይወት ከተነገረው ነገር ጋር የሚጣጣም ነው።

ከዚህ በኋላ ምዕራፏ ለአላህ መልክተኛ ከእርሳቸው በኋላ ለሚመጡት ህዝቦች በሙሉ እንደሚከተለው ታላቅ ብስራትን ይዛ ትመጣለች፡-

﴿ سَنُقْرِئُكَ فَلَا تَنسَىٰٓ ٦ إِلَّا مَا شَآءَ ٱللَّهُ ۚ إِنَّهُۥ يَعْلَمُ ٱلْجَهْرَ وَمَا يَخْفَىٰ ٧ وَنُيَسِّرُكَ لِلْيُسْرَىٰ ٨ فَذَكِّرْ إِن نَّفَعَتِ ٱلذِّكْرَىٰ ٩ ﴾ الأعلى: ٦ - ٩

"[ቁርኣንን] በእርግጥ እናስነብበሃለን፣ አትረሳምም፤ አላህ ከሻው ነገር በስተቀር፡፡ እርሱ ግልጹን፣ የሚሸሸገውንም ሁሉ ያውቃልና፡፡ ለገሪቱም [ህግጋት] እንገጥምለን፡፡ ግሣጼይቱ ብትጠቅም [ሰዎችን] ገሥጽም" (አል-አዕላ፡ 6-9)

የብስራቱ ጅማሮ መልዕክተኛው ቁርአን ከልቦናዬ እንዳይጠፋብኝ የሚል ስጋታቸውንና ልፋታቸውን የጭንቀት ሸክም ከጫንቃቸው በማውረድ ነበር።

([ቁርአንን] በእርግጥ እናስነብብሃለን፣ አትረሳምም) አላቸው፡፡ የርሳቸው ኃላፊነት ከጌታቸው የወረደውን ማንበብ ብቻ ነው፡፡ ከዚያ በኋላ በልቦናቸው ውስጥ የመጠበቁን ዋስትና ጌታቸው ወስዷል፡፡ ስለዚህ ያስነበባቸውን ፈጽሞ አይረሱም፡፡ ***"አላህ ከሻው ነገር በስተቀር"*** የሚለው የአንቀጹ ክፍል እርሳቸው በእርግጥ እንደማይረሱ እውነተኛ ቃል ከተገባላቸው በኋላ ያለውን መለኮታዊ የመጠበቅ ፍላጐትን አረጋጋጭ ነው፡፡

(إنه يعلم الجهر وما يخفى)

(እርሱ ግልጹን፣ የሚሸሽገውንም ሁሉ ያውቃልና)

በርግጥ አገላለፁ ከዚህ በላይ የተቀመጠውን በልቦና ላይ የማሳረፍ፣ የመጠበቅና እርሱ ከፈለገው በስተቀር እንደማይሆን የተነገሩትን እውነታዎች እንደሚወሰን ሁሉ እነዚህ እውነታዎችም ባጠቃላይ ግልጹንም ሆነ ድብቁን አዋቂ ወደሆነው ወደ እርሱ ብቸኛ ጥበብ ተመላሽ እንደሆኑ ያብራራል፡፡

ሁለተኛውና አጠቃላይ የሆነው ብስራት ደግሞ

(ونيسرك لليسرى) ..

(ለገሪቱም [ህግጋት] እንገጥምለን) የሚለው ነው፡፡)

ይህ አንቀጽ ለመልክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) እና ከኋላቸው ላለው ሕብረተሰብ የተቸረ ብስራት ከመሆኑ ባሻገር የዚህን ሃይማኖት ባህሪና የዳዕዋውን እውነታ፣ በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ የሚኖረውን ሚና፣ በህይወት ሥርዓት ውስጥ ያለውን ስፍራ አረጋጋጭ ነው፡፡ በእርግጥ አላህ ገርነትን ባህሪው ያደረገለት ሰው ሕይወቱን በሙሉ ቀላልና ገር ሆኖ ይቀጥላል፡፡ ገርነት በእጁ፣ በአንደበቱ፣ በእርምጃው፣ በተግባሩ፣ በእይታው፣ በአስተሳሰቡ፣ ጉዳይን በሚወስድበት፤ ለችግሮች መፍትሔ በሚሻበት፣ከራሱም ይሁን ከሌላው ጋር ሲኖር ገርነት አብሮት ይገኛል፡፡

የአላህ መልክተኛም በተጨባጭ ሁለንተናቸው እንዲሁ ገር ነበሩ::ሁለት ጉዳዮች በምርጫነት ሲቀርቡላቸው ገር የሆነውን እንጅ አይመርጡም:: ዐቂዳና ኃላፊነቶቹ በግንባር ቀደምነት ተቀምጠው በሌሎች ጉዳዮች ላይ ግን ገርነትን፣ ይቅር ባይነትንና ለስላሳነትን ስለመምረጥ የሚያነሳሱ ሐዲሶች በቁጥር ብዙ ናቸው::

ከነዚህም ውስጥ:- *"ይህ ዲን ገር ነው፣ አንድ ሰው (ዲኑ እርሱን) የሚሸንፈው ቢሆን እንጅ ከልክ በላይ አያጠበቀወም::* *"አማራሩ እንጂ፣ አታስጠብቁ"* (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)

የለት ተለት ውሎን በተመለከተ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ):- *"ሲሸጥ፣ ሲገዛና ሲፋረድ ይቅር ባይነትን የተላበሰ ሰው አላህ ይዘንለት::"* ብለዋል:: (ቡኻሪ ዘግበውታል) *"አጥብቀው ተከራካሪ የሆኑ ሰዎች አላህ ዘንድ በጣም የተጠሉ ናቸው::"* (ቡኻሪ ዘግበውታል)

የአላህ መልክተኛ (ሰዐወ) የሕይወት ታሪክ ገፅ በሙሉ በይቅር ባይነት፣ በገራገርነት፣ በለስላሳነትና ባጠቃላይ ነገሮችን ከገርነት ጋር በማስማማት ላይ የተሰደሩ ናቸው::

(فذكر إن نفعت الذكرى)..

(ግሣጼይቱ ብትጠቅም [ሰዎችን] ገሥጽም) ...

ለማስታወስ እድል፣ ወደ ልብ ለመግባት ክፍተት እንዲሁም መልእክቱን የማድረሻ ዕድል እስካገኘህ ድረስ አስታውስ:: [ግሣጼይቱ ብትጠቅም] የሚለው መጠቀሱ ማስታወስ ሁልጊዜም ጠቃሚ መሆኑን ነው:: በዛም አነሰም በማስታወስ የሚጠቀም አይጠፋም:: ምንም ያህል ሰዎች ቢበላሹ፣ ልቦናቸው ብትደርቅና የወንጀል ዝገት በላይዋ ላይ ግርዶሽ ቢጥልባትም፣ ሰምቶ የሚጠቀም ከትውልድም ሆነ ከምድረ ገጽ በፍፁም አይታጣም!

የመልዕክተኛው ኃላፊነት ማስታወስ ብቻ ነው:: ለፍፃሜው ከተነሱ የተጣለባቸውን ግዴታ ተወጥተዋል:: ከዚህ በኋላ ሰዎች የራሳቸው ኃላፊነት ነው:: መስተጋብራቸው እንደሚለያይ ሁሉ ጉዟቸውም ይለያያል:: ለትውስታዋ የሚሰጡትን መልስ መነሻ አድርጎ አላህ በነርሱ ላይ የፈለገውን ይፈጽማል::

(سيذكر من يخشى ، ويتجنبها الأشقى ، الذي يصلى النار الكبرى ، ثم لا يموت فيها ولا يحيا . قد أفلح من تزكى ، وذكر اسم ربه فصلى) ..

[አላህን የሚፈራ ሰው በእርግጥ ይገሰጻል፡፡ መጥፎም ይርቃታል፤ ያ ታላቂቱን እሳት የሚባው፡፡ ከዚያም በእርሷ ወስጥ አይሞትም፡ ህያውም አይሆንም፡፡ የተጥራራ ሰው በእርግጥ ዳነ ፤ የጌታውንም ስም ያወሳና የሰገደ፡፡]

አስታውስ...[በማስታወስህ የሚፈራው ይገሰጻል፡፡]ያ ልቦናው የአላህን ፍራቻ የተገነዘበለት ሰው፤ የአላህን ቁጣና ቅጣት ይጠነቀቃል፡፡ ይህ ዓይነቱ ሲገሰጹት ይገሠጻል፤እንዲመለከት ከተደረገ ይመለከታል፤ከተመከረ ከምክሩ አንዳች ነገር ይወስዳል፡፡

(ويتجنبها الأشقى)

[መጥፎም ይርቃታል...]

መናጢ (መጥፎ) የሆነ ሰው በእርግጥም ግሣጼን ይርቃል፣ አይሰማም፣ ከእርሷም አይጠቀምም፡፡ ስለዚህ እርሱ መናጢ ነው...የመናጢነትን የመጨረሻ ቁንጮ ላይ የደረሰ መናጢነት... ይህ ሰው በዱንያው ባዶነት በሞላት፣ በሞተችና የቂልነት ጫካ በወረሳት ነፍሱ ዕድለቢስ ሲሆን በአኼራውም ደግሞ ገደቡ የማይታወቅ በሆነ ቅጣት ነፍሱ የምትሰቃይበት ዕድለቢስ ነው፡፡

(الذي يصلى النار الكبرى . ثم لا يموت فيها ولا يحيا) ..

[ያ ታላቂቱን እሳት የሚባው፡፡ ከዚያም በእርሷ ወስጥ አይሞትም፤ ህያውም አይሆንም፡]

ታላቂቱ እሳት የተባለችው የጀሀነም እሳት ናት፡፡ በብርታቷም፣ በቆይታዋም፣ በግዝፈቷም ታላቅ ናት፡፡ በእርሷ ውስጥ የሚቆይበት ጊዜ ይረዝማል፡፡ ሞቶም የሞትን እረፍት ማጣጣም አይችልም፤ወይም ሕያው ሆኖ የሰላምን እረፍት አይጎናጸፍም...በእርግጥም ዘላለማዊ ቅጣት ነው፡፡

የመጠዘኛ ጥያቄዎች

1- ምዕራፉ በአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ ያለውን ስፍራ ግለፅ፡፡

2- አላህ በአፈጣጠሩ ውስጥ ያለውን ታላቅነት የምታስተነትንበት የዘወትር ልምድ አለህን?

3- ምዕራፉ ለአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እና ከእሳቸው በኋላ ላለው ኡመታቸው የያዘውን ብስራት ግለፅ፡፡

4- በምዕራፉ ባመለከተው ዓይነት የአንድ ዳዒ (ወደ አላህ መንገድ ተጣሪ) የሆነ ሰው ኃላፊነት ምን እንደሆነ ግለፅ፡፡

5- በማስታወስ ማን እንደሚጠቀምና በእርሷ የማይጠቀመው ማን እንደሆነ ለይተህ አስቀምጥ፡፡

ሁለተኛው ክፍል

(ሱንቁጹ 14-19)

﴿قَدۡ أَفۡلَحَ مَن تَزَكَّىٰ ١٤ وَذَكَرَ ٱسۡمَ رَبِّهِۦ فَصَلَّىٰ ١٥ بَلۡ تُؤۡثِرُونَ ٱلۡحَيَوٰةَ ٱلدُّنۡيَا ١٦ وَٱلۡأٓخِرَةُ خَيۡرٞ وَأَبۡقَىٰٓ ١٧ إِنَّ هَٰذَا لَفِي ٱلصُّحُفِ ٱلۡأُولَىٰ ١٨ صُحُفِ إِبۡرَٰهِيمَ وَمُوسَىٰ ١٩﴾ الأعلى: ١٤-١٩

"የተጥራራ ሰው በእርግጥ ዳነ፡፡ (14) የጌታውንም ስም ያወሳና የሰገደ፡፡ (15) ይልቁንም ቅርቢቱን ሕይወት ትመርጣላችሁ፡፡ (16) መጪዪቱ (ሕይወት) በላጭ ሀል ጊዜ ዘወታሪም ስትኾን፡፡ (17) ይህ በፊተኞቹ መጻሕፍት ወስጥ ያልለ ነው፡፡ (18) በኢብራሂምና በሙሳ ጽሑፎች ወስጥ፡፡ (19)"

የትምህርቱ ዝርዝር ዓላማዎች

1. በአንቀጾቹ ውስጥ በተገለጸው መሠረት የመዳኛና የስኬት መንገድ ምን እንደሆነ ግልጽ እንዲያደርግ ማስቻል፡፡
2. ጠፊ ከሆነው ዘላለማዊ የሆነውን ሊያስበልጥ፡፡
3. በመለኮታዊ የመልእክት ሽግግር ታሪክ የዐቂዳን አንድነት እንዲያብራራ ማስቻል፡፡

በክፍል አንድ መጨረሻ ላይ ለተገለጸው እድለቢስነት ተቃራኒ አሁን ደግሞ መዳንና ስኬት ከመፅዳትና ከመገሠፅ ጋር የተቆራኘ እንደሆነ እናያለን [የተጥራራ ሰው በእርግጥ ዳነ ፤ የጌታውንም ስም ያወሳና የሰገደ...]

መጥራራት ማለት ከሁሉም ዓይነት ቆሻሻና ርክሰት መፅዳት ማለት ነው፡፡ ጥራት የተገባው አላህ (ሱ.ወ) ያ የተጥራራና የጌታውን ስም ያወሳ፣ የእርሱን ኃያልነት በልቡ ያሳደረ... ያ -የጸዳ፣ ያስታወሰና የሰገደ... እርሱ በእርግጥ ስኬታማ እንደሆነ ያረጋግጣል፡፡ ይህ ሰው በዱንያው ስኬታማ ነው፡፡ ከጌታው ጋር ያለው ትስስሩ ሳይቋረጥ፣ ልቦናውም ሕያው ሆኖ፣ የፈጣሪውን ጉድኝትና እርሱን የማውሳት ጥፍጥና እንዳጣጣመ ይኖራል፡፡ በአኼራውም እንዲሁ ስኬታማ ነው፡፡

ከታላቋ እሳት ድኗል። ከዚያም የጀነትን ፀጋና የፈጣሪውን ውዴታ ተጎናፀፏል... *ከመጨረሻም እንዲህ ያለ ያማረ መጨረሻ የታለ? ከመዳረሻም እንዲህ ያለ ያማረ ምን ሊይነት መዳረሻስ የታለ?*

ለመናጢ ታላቋ እሳት እንደምትጠብቀውና ለተጽዳዳ ስኬትና መዳንን እንደሚጎናጸፍ ከገለጸልን በኋላ መናጢዎቹ የእድለቢስነታቸውን መንስኤንና የዝንጉነታቸውን መነሻ ወደ መግለፁና ማናገሩ ይመለሳል።

(ይልቁንም ቅርቢቱን ሕይወት ትመርጣላችሁ፤ ሜጪሻይቱ [ሕይወት] በላጯ ሀልጊዜም ዘውታሪ ስትሆን)... የጥፋት ሁሉ መሠረት ምድራዊ ሕይወትን ማስበለጥ ነው። ከተግሳጹ መዞር መነሻም ይሄው ምድራዊ ሕይወትን ማስበለጥ የሚያስከትለው አባዜ ነው።... ምክኒያቱም ከአኼራ ይልቅ ምድራዊ ዱንያ ትሻላለች የሚል እሳቤን ያስይዛቸዋልና። እነሱ ዱንያን ይፈልጋሉ፣ ከሁሉም ነገር ያስበልጧታልም። ሜጪሻይቱ [ሕይወት] በላጭና ሀልጊዜም ናት፡ ... በዓይነቷ በላጭ ናት... ጊዜዋም ዘውታሪ ነው። በዚህ እውነታ ስር ዱንያን ከአኼራ ማስበለጥ ምን አይነት ቂልነትና የተሳሳተ ልኬት እንደሆነ ግልጽ ይሆናል። ማሰብና ማስተዋል የሚችል በአኺራ ላይ ምንም ዓይነት ነገር አያስቀድምም።

በመጨረሻም የዚህችን መለኮታዊ ጥሪ (ደዕዋ) ጥንታዊነት፣ የጅምሯን ስርፀት፣ በዘመናት ቅርንጫፍ የሥሮቿን ጥልቀት እንዲሁም ከዘመንና ከቦታ በስተጀርባ የተውሂድ መሠረቷን አንድነት ይጠቁማል። [ይህ በፊተኞቹ መጻሕፍት ውስጥ ያለ ነው። በኢብራሂምና በሙሳ ጽሑፎች ውስጥ]... ይህ ነው እንግዲህ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ታላቁን የዐቂዳ መሠረት አካቶ የወረደው...ያ በመጀመሪያዎች መጻሕፍት የነበረው!... [በኢብራሂምና በሙሳ ጽሑፎች!...] እርሱ ብቸኛው እውነታ ነው፣ መሠረቱም አንድ ነው።

የመጨረሻ ጥያቄዎች

1- በምዕራፉ ውስጥ እንደተገለፀው የመዳኛና የስኬት መንገዶች አብራራ።

2- ጠፊ ከሆነው ይልቅ ዘላለማዊ የሆነውን ታስበልጣለህን? በተግባር ካሳለፍከው ክስተት ጋር አያይዘህ አብራራ።

3- በመለኮታዊ የመልእክት ሽግግር ዘመን ታሪክ የዐቂዳን አንድነት ግልጽ አድርግ።

سورة الغاشية

(የሸፋኝቱ ምዕራፍ)

ይህች ምዕራፍ በጣም ጥልቅና በተረጋጋ ድባብ ምት ከሚያሳርፉ ምዕራፎች አንዷ ስትሆን ወደማስተዋልና ወደ ማስተንተን፣ ወደ መከጀልና ወደ ተስፋ፣ ወደ ፍራቻና ስጋት፣ ለመተሳሰቢያው ቀን ወደ መሥራት የምታነሳሳ ምዕራፍ ናት።

የመጀመሪያው ክፍል

(ስንቀጽ: 1-16)

﴿ هَلۡ أَتَىٰكَ حَدِيثُ ٱلۡغَٰشِيَةِ ١ وُجُوهٞ يَوۡمَئِذٍ خَٰشِعَةٌ ٢ عَامِلَةٞ نَّاصِبَةٞ ٣ تَصۡلَىٰ نَارًا حَامِيَةَۢ ٤ تُسۡقَىٰ مِنۡ عَيۡنٍ ءَانِيَةٖ ٥ لَّيۡسَ لَهُمۡ طَعَامٌ إِلَّا مِن ضَرِيعٖ ٦ لَّا يُسۡمِنُ وَلَا يُغۡنِي مِن جُوعٖ ٧ وُجُوهٞ يَوۡمَئِذٖ نَّاعِمَةٞ ٨ لِّسَعۡيِهَا رَاضِيَةٞ ٩ فِي جَنَّةٍ عَالِيَةٖ ١٠ لَّا تَسۡمَعُ فِيهَا لَٰغِيَةٗ ١١ فِيهَا عَيۡنٞ جَارِيَةٞ ١٢ فِيهَا سُرُرٞ مَّرۡفُوعَةٞ ١٣ وَأَكۡوَابٞ مَّوۡضُوعَةٞ ١٤ وَنَمَارِقُ مَصۡفُوفَةٞ ١٥ وَزَرَابِيُّ مَبۡثُوثَةٌ ١٦ ﴾ الغاشية: ١ - ١٦

"የሸፋኝቱ (ትንሣኤ) ወሬ መጣህን? (1) ፊቶች በዚያ ቀን ተዋራጆች ናቸው። (2) ሠሪዎች ለፊዎች ናቸው። (3) ተኳሰን እሳት ይገባሉ። (4) በጣም ከፈላች ምንጭ ይጋታሉ። (5) ለእነርሱ ዶሪዕ ከሚበል (እሾሃም) ዛፍ እንጅ ሌለ ምግብ የላቸውም። (6) የሚሰባ ከረሃብም የሚብቃቃ ከኾነ ው። (7) ፊቶች በዚያ ቀን ተቀማጮች ናቸው። (8) ለሥራቸው ተደሳቾች ናቸው። (9) በከፍተኛ ገነት ወስጥ ናቸው። (10) በወስጧ ወድቅን ነገር አይሰማም። (11) በወስጧ ፈሳሾች ምንጮች አልሉ። (12) በወስጧ ከፍ የተደረጉ አልጋዎች አልሉ። (13) በተርታ የተኖሩ ብርጭቆዎችም። (14) የተደረደሩ መከዳዎችም። (15) የተነጠፉ ስጋጃዎችም (አልሉ)። (16)"

የትምህርቱ ዝርዝር ዓላማዎች

1. የሸፋፂን ዕለት ትዕይንቶችና በእሷ ውስጥ የሚከሰቱ ኹነቶችን እንዲያብራራ ማስቻል።
2. ሰዎች በዕለተ-ቂያማ የመጨረሻ ዕጣ-ፋንታቸው ምን እንደሆነና የምንዳቸውንም ትዕይንት እንዲገልፅ ማስቻል ናቸው።

1) (የሸፋኝቱ [ትንሳዔ] ወሬ መጣህን?)

ምዕራፏ ልቦች ወደ አላህ እንዲመለሱ በመፈለግ፣ በመኖር ውስጥ ስላለው ተአምር ልታስታውሳቸው፣ በመጨረሻው ዓለምም መተሳሰብና ምንዳ መክፈሉ የተረጋገጠ መሆኑን ልታሳስባቸው በዚህ መጠይቃዊ ዐረፍተ ነገር ትጀምራለች። በዚህ መጠይቃዊ መልእክት ውስጥ የአላህን ታላቅ ችሎታ ከማስገንዘቡም ባሻገር የአኼራ ጉዳይ ቀድሞ የተረጋገጠና የማስጠንቀቅ ሥራም የተሰሠራበት መሆኑን ያመላክታል። የትንሳዔ ዕለትም (**ሸፋኝቱ!**) በተሰኘችው አዲስ ስያሜም በክስተቷ ሰውን ሁሉን የምትሸፍንና የምታጥለቀልቅ የሆነች ነች ማለት ነው።

መልእክቱ ይህንን ቁርአን ለሚሰማ ሁሉ የተላለፈ ከመሆኑ ጋር ይህ “መጣህን?” የሚለው መልዕክት ሲያደምጡ የአላህ መልክተኛ ከጌታቸው ለመጀመሪያ ጊዜ ራሳቸውን በቀጥታ እያናገራቸው መሆኑን እንዲያስቡ ያደርጋቸው ነበር። የሸፋኝቱ ቀን ወሬ በቁርአን ውስጥ በተደጋጋሚ የተነገረ ነው። ልክ ነፍስ ፈጣሪዋን እንድትከጅል፣ የእርሱን ከለላ እንድትሻና ወደ እርሱ እንድትንጠለጠል እንደገፋፋት ሁሉ በእርሱ አስጠንቅቆበታል፤ አብስሮበታልም። ልቦና በፍርሃት እንድትሰጋ፣ ጥንቁቅ እንድትሆንና፣ ፍርሃት እንዲነግስባት አድርጐባታል። ከዚህም ባሻገር ልቦና በቁመናዋ ሳትሞትና ሳትዘነጋ ሕያው ሆና እንዲትኖር ያስችላታል።

(የሸፋኝቱ [ትንሳዔ] ወሬ መጣህን?)...

ከዚያም ስለ ሸፋኝቱ ቀን ክስተት ጥቂት ነገሮችን ያብራራል፡-

[ፊቶች በዚያ ቀን ተዋራጆች ናቸው፡]

...እዚህ ላይ በእርግጥ እሱ (አላህ) ከፀጋ ትእይንት በፊት የቅጣት ትዕይንትን አስቀድሟል። ያኔ -በዚያን ወቅት በፍርሃት የተሞሉ፣ የተዋረዱ፣ የደከሙና በጭንቀት ጽልመት የተዋጡ ፊቶች አሉ። ሠርተዋል፣ ለፍተዋል። ነገርግን ሥራቸው አልተመሰገነም፤ ፍጻሜውም አልተወደደም። ጥፋትንና ክስረትን እንጅ ሌላን አልታደሉም። ይባስ ብሎ በተቃራኒው ጽልመትንና ድካምን ጨምረዋል። እነኝህ ፊቶች፡ (**ሠሪዎች ለፊዎች**) ናቸው... ከአላህ ውጭ ለሆነ አካል ሥራ ሠርተዋል፤ ከእርሱ ውጭ በሆነ መንገድ ለፍተዋል።... ከዚያም የሥራቸውንና የልፋታቸውን ውጤት አግኝተዋል። በምድራዊው ዓለም የፈፀሙት ሥራቸውና ልፋታቸው ስንቅ እድለ ቢስነት ሆኖ አገኙት። በአኼራ ደግሞ ለቅጣት የሚዳርግ ጥላሸት ሆኖ አገኙት። ከዚያም የመጨረሻውን ውርደት የተከናነበ፣ ጭንቀት የነገሰበትንና ተስፋው የተሟጠጠን መከራ ይጋፈጣሉ!

ከዚህ ውርደት፣ ጭንቀት፣ ቅጣትና ህመም ጋር (ተኳሳን እሳት ይገባሉ)- يَصْلَىٰ نَارًا ذَاتَ لَهَبٍ(በጣም ከፈላች ምንጭ ይጋታሉ)... ግለቷም ጫፍ የደረሰ ነው።... (ለእነርሱ ዶሪዕ ከሚባል (እሾሃም) ዛፍ እንጅ ሌላ ምግብ የላቸውም። የማያሰባ ከረሃብም የማያብቃቃ ከኾነው)...'ዶሪዕ' በጀሀነም ውስጥ ከእሳት የሆነ ዛፍ ነው ተብሏል... እንዲሁም ከእሾህ ዓይነትም ነው።... አረንጓዴ ሳለ ግመሎች ይበሉታል...በደረቀ ጊዜ ዶሪዕ ይባላል። በዚህ ጊዜ ግመሎችም መብላት የማይችሉት መርዛማ ይሆናል።

በሌላ በኩል ደግሞ፡ (ፊቶች በዚያ ቀን ተቀማጣዮች ናቸው። ለሥራቸው ተደሳቾች ናቸው።)... ጸጋን የተንበሻበሹ ፊቶች አሉ፤ ከነርሱም ደስታ ይፈልቃል...በላቀ መንፈሳዊ ስሜትም ደስታን ያጣጥማሉ። ይህ ስሜት ሥራቸውን አላህ እንደወደደላቸው ከማየት የመነጨ ነው። መቼስ ለልቦና በጥሩ ከመረጋጋትና መጨረሻው ያማረ፣ በቸሩ አላህም ዘንድ ውዴታን ከማግኘት፣ በፀጋውም ከመንበሽበሽ የበለጠ እርጋታን የሚሰጥ ነገር አይኖርም። ከዚያም ቁርአን ጀነት ውስጥ ያለውን የደስታ ዓይነት፣ ምቾትና ድሎት በመቀጠል ያቀርባል።

ለእነኝህ በደስታ ለሚያበሩ ፊቶች ስለ ጀነት ምንነትና በውስጧም ስለያዘችው ፀጋ እንዲህ ይገለጽላቸዋል። (በከፍተኛ ገነት ውስጥ ናቸው)... ጀነት

በራሷ ከፍ ያለች፤ በደረጃዋም ልዕልና የተቸራትና ትልቅ ግምት የተሰጣት ናት፡፡ (በውስጧ ውድቅን ነገር አይሰሙም) ...ይህ አባባል የተረጋጋና የሰከነ አየር መኖሩን ይገልፃል...ከማንኛውም ጥሩ ነገር ከሌለውና ጤናማ ካልሆነ ውዳቂ ንግግር የጸዳና የላቀ ቦታ!...ይህ ብቻውን ትልቅ ፀጋ ነው!...ይህ ገለፃ ሙእሚኖች በምድር ሲኖሩ ከክርክርና ዛዛታ መራቃቸው በጀነት ከሚኖራቸው ሕይወት አካል እንደሆነና ለዚያ ለተከበረው የፀጋ አገር ቅድመ ዝግጅት እያደረጉ መሆኑንም ያመላክታል፡፡ ከዚያም ስሜትንና ህዋሳትን የሚያስነመዝቱ የፀጋ አይነቶች ይመጣሉ፡፡ (በውስጧ ፈሳሾች ምንጮች አልሉ)...የሚፈልቁና የሚንቧቡ! ውብ እይታን ሰብስቦ የያዘ አገላለፅ! ባጠቃላይ እንቅስቃሴው፣ መንቧቧቱና ፍሰቱ የሚማርክ! (በውስጧ ከፍ የተደረጉ አልጋዎች አልሉ)... ከፍታው ንጹሕ የመሆኑንና ከቆሻሻ የጠራ የመሆኑንን ስሜት ይጭራል፡፡ (በተርታ የተኖሩ ብርጭቆዎችም)... የተሞሉና ለመጠጣት ዝግጁ የሆኑ! መጠየቅም ሆነ ማዘጋጀት የማያስፈልገው! (የተደረደሩ መከዳዎችም)... ነማሪቅ የሚለው የዐረበኛ ቃል ለማረፍ የተመቸ ትራስና መደገፊያ ማለት ነው! (የተነጠፉ ስጋጃዎችም)... በውበት ያሸበረቁ እዚህም እዚያም የተዘረጉ ምንጣፎች!

ሁሉም የተዘረዘሩት ፀጋዎች የሰው ልጅ በምድር ሲኖር የሚያቸው አምሳያዎች ናቸው፡፡ ...ነገር ግን እውነተኛ ማንነታቸውና የፀጋነት ሙሉ ቅርፃቸው እዚያ አገር(ገነት ውስጥ) ለማጣጣም እንዲመቹ ተደርገው የተሠሩ ናቸው፡፡ እንግዲህ ለእድለኞቹ አላህ በዚህ መልኩ ሊያጣቅማቸው ቃል ገብቷል፡፡

የመወያዘሻ ጥያቄዎች

1. የሸፋኟን ዕለት ትዕይንቶችና የሚከሰቱ ኩነቶችን አብራራ፡፡
2. ሰዎች በዕለተ-ቂያማ የመጨረሻ ዕጣ-ፋንታቸው ምን እንደሆነና የምንዳቸውንም ትዕይንት ምዕራፉ እንደገለፀው አብራራ፡፡

ሁለተኛው ክፍል

(ሰንቂዱ: 17-26)

﴿ أَفَلَا يَنظُرُونَ إِلَى ٱلْإِبِلِ كَيْفَ خُلِقَتْ ﴿١٧﴾ وَإِلَى ٱلسَّمَآءِ كَيْفَ رُفِعَتْ ﴿١٨﴾ وَإِلَى ٱلْجِبَالِ كَيْفَ نُصِبَتْ ﴿١٩﴾ وَإِلَى ٱلْأَرْضِ كَيْفَ سُطِحَتْ ﴿٢٠﴾ فَذَكِّرْ إِنَّمَآ أَنتَ مُذَكِّرٌ ﴿٢١﴾ لَّسْتَ عَلَيْهِم بِمُصَيْطِرٍ ﴿٢٢﴾ إِلَّا مَن تَوَلَّىٰ وَكَفَرَ ﴿٢٣﴾ فَيُعَذِّبُهُ ٱللَّهُ ٱلْعَذَابَ ٱلْأَكْبَرَ ﴿٢٤﴾ إِنَّ إِلَيْنَآ إِيَابَهُمْ ﴿٢٥﴾ ثُمَّ إِنَّ عَلَيْنَا حِسَابَهُم ﴿٢٦﴾ ﴾ الغاشية: ١٧ - ٢٦

"(ከሓዲዎች) አይመለከቱምን? ወደ ግመል እንዴት እንደተፈጠረች! (17) ወደ ሰማይም እንዴት ከፍ እንደ ተደረገች! (18) ወደ ተራራዎችም እንዴት እንደ ተቸከሉ! (19) ወደ ምድርም እንዴ እንደተዘረጋች (አይመለከቱምን?) (20) አስታውስም፤ አንተ አስታዋሽ ብቻ ነህና። (21) በእነርሱ ላይ ተቧሚ (አስገዳጅ) አይደለህም። (22) ግን (ከእውነት) የዞረና የካደ ሰው፤ (23) አላህ ታላቁን ቅጣት ይቀጣዋል። (24) መመለሻቸው ወደእኛ ብቻ ነው። (25) ከዚያም ምርመራቸው በእኛ ላይ ብቻ ነው። (26)"

የትምህርቱ ዝርዝር ዓላማዎች

1. አንቀጾቹ እንዳስቀመጡት የተብራራውን የአላህን ችሎታና የማስተናበር ብቃት እንዲያብራራ ማስቻል።
2. ወደ አላህ ተጣሪ የሆነ ዳዒን የሥራ ድርሻና ኃላፊነት ምን እንደሆነ እንዲዘረዝር ማስቻል።

ባሳለፍነው የመጀመሪያ ክፍል ሲያስነበኝን የነበረውን የሌላኛውን ዓለም ቅኝት ቆም አድርጎ አሁን ወዳለንበት ተጨባጭና ቅርብ ዓለም ይመልሰናል። ከዚያም ቻይ የሆነውን አምላክ ብቃትና የማስተናበር ችሎታ ያስታውሰናል፦

(አይመለከቱምን? ወደ ግመል እንዴት እንደተፈጠረች!

((ከሓዲዎች) አይማከቱምን? ወደ ግሜል እንዴት እንደተፈጠረች!)..
ወደ አፈጣጠሯና ቅንብሯን አይመለከቱምን? ከዚያም እንዴት በዚህ መልኩ ተፈጠረች? ለተሰጣት ተልዕኮ የተመቻቸችና የተፈጠረችበትን ዓላማ የምታሳካ ሆና እንዲሁም ከምትኖርበት አካባቢና ባጠቃላይም ከተጣለባት የሥራ ድርሻ ጋር ተስማሚ ተደርጋ እንዴት እንደተፈጠረች አያስተነትኑም? በእርግጥ እነርሱ አልፈጠሯትም! ወይም ደግሞ በራሷ አልተፈጠረችም፡፡ እርሷ ግኝቶችን በብቸኝነት ፈጣሪ እንዳለ ከማመላከት ካስገኘና ከሠራ አካል ግኝቶች መካከል ነች ከሚለው ሃሳብ በስተቀር ሌላ የሚቀር ነገር የለም፡፡ ይህ አፈጣጠሯ ልክ ችሎታውንና ማስተናበሩን እንደሚያመለክት ሁሉ የእሱን መኖር በግልጽ ያረጋግጣል፡፡

(ወደ ሰሜይም እንዴት ከፍ እንደተደረገች!)... ልቦና ስለ ሰማይ እንዲያስተነትን የመገፋፋቱ መልእክት ቁርአን ውስጥ ይደጋገማል...ወደ እርሷ አይመለከቱምን? እንዴት ከፍ እንደተደረገች አያስተውሉምን? ያለ ዋልታ ማንስ ከፍ አደረጋት? ለቁጥር የሚያዳግቱ ከዋክብትን ማንስ በእርሷ ውስጥ በተናቸው? እንዲህ በሚያስገርም አኳኋንና በሚያስደንቅ ውበት ማንስ አደራጃት? በእርግጥ እነርሱ ከፍ አላደረጓትም፣ ወይም ደግሞ ራሷን ከፍ አላደረገችም፡፡ ስለዚህም የግዴታ ከፍ ያደረጋትና ካልነበረችበት ያስገኛት ኃይል መኖር አለበት፡፡

(ወደ ተራራዎችም እንዴት እንደተቸከሉ!)... ተራራዎችን መመልከት በሰው ልጅ ነፍስ ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ ያሳድራል-ተራሮች ባጠቃላይ አገላለፅ-ግዙፍና አስፈሪ ናቸው፡፡ በዚህም የሰው ልጅ ራሱን ከተራራ ጋር ሲያነጻጽር በጣም ኢምንት መሆኑን የመረዳትና በግዝፈታቸው የመዋጥ ስሜት ይፈጥርበታል፣ ከባድ በሆነ ሐፍረትም ይሸማቀቃል፡፡

(ወደ ምድርም እንዴት እንደተዘረጋች)... ምድር ለእይታ የተዘረጋች፣ ለሕይወት የተነጠፈች፣ ለጉዞ የተመቻቸችና ለሥራ የተገራች ናት፡፡ ወደ እርሷም አይመለከቱምን? ከበስተጀርባዋ ስላለው እውነታ አያስተነትኑምን? ለመሆኑ ማን ዘረጋት፣ እንደዚህስ ለሕይወት ተስማሚ ትሆን ዘንድ ማን አስተካከላት (አመቻቻት) የሚለውን ጥያቄ ራሳቸውን ለምን አይጠይቁም?

አሁን ደግሞ ወደ መልክተኛው ይዞራል፡፡...የተጣለባቸውን የኃላፊነት ወሰንና የሥራቸውን ባህሪ ያመላክታቸዋል፡፡... ልቦቻቸውን በሚያባንን መልእክት እንዲያስታውሳቸው፡ (አስታወስም፤ አንተ አስታዋሽ ብቻ ነህና፡፡ በእነርሱ ላይ ተቧሚ (አስገዳጅ) አይደለህም) . . አስታውስ!... በአኼራና በእርሷ ውስጥም ባለው ነገር አስታውሳቸው፡፡ በዩኒቨርሱና በውስጡ ባለው ሁሉ አስታውሳቸው፡፡ በእርግጥ አንተ አስታዋሽ ብቻ ነህ፡፡ የሥራ ድርሻህም ወሰን ይህ ነው፡፡ በዚህች ደዕዋ (ጥሪ) ላይ ያንተ ሚናም ይኼው ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ያለፈ መብትም ሆነ ግዴታ የለብህም፡፡ የተጣለብህ አደራም ማስታወስ ነው፡፡ ለዚህ ተግባር የተገራህ ነህ፣ በእርሱም ላይ ኃላፊነት አለብህ፡፡

(በእነርሱ ላይ ተቧሚ (አስገዳጅ) አይደለህም)... አንተ በልቦቻቸው ጉዳይ ላይ በጉልበት አሸንፈህ ለእምነት እንዲንበረከኩ የማድረግ ምንም ስልጣን የለህም፡፡ ልቦች በአር-ረሕማን ጣቶች መካከል ናቸው፡፡ የሰው ልጅ በነርሱ ላይ ምንም አቅም የለውም፡፡ ይህ መልክተኛው በዚህ ደዕዋ ጉዳይ ከማስታወስና ከማድረስ በቀር ሌላ ምንም ነገር የሌላቸው መሆኑን ማስገንዘቢያ ሲሆን በቁርአን ውስጥ ለተለያዩ ምክንያቶች ሲባል ተደጋግሞ ተገልጿል፡፡ የመጀመሪያው ምክንያት መልክተኛው ከማድረስ ባሻገር የነበረባቸውን የደዕዋ ጭንቀት ለማንሳት ነው፡፡ ይህንንም ኃላፊነት አላህ ለራሱ የተወውና እርሱ እንደፈለገው የሚያደርገው ጉዳይ ሆኗል፡፡ ነገር ግን ምንም እንኳን የመልክተኛው ኃላፊነት በዚህ ቢወሰንም ነገሩ በዚህ ደረጃ ብቻ ይቋጫል ማለት አይደለም፡፡ አስተባባዮች ስኬታማ ሆነው በሰላም ሊያጠናቅቅ በፍፁም አይችሉም፡፡ እውነታው ከዚህ ጉዳይ ጀርባ አላህ እንዳለና ነገሩም ሁሉ ወደ እርሱ እንደሚመለስ ነው፡፡

(ግን [ከእነሱ] የዞረና የካደ ሰው፤ አላህ ታላቁን ቅጣት ይቀጣዋል)... ወደ አላህ ብቻ መመለሳቸው ቁርጥ ነው፣ እርሱም ብቻ እንደሥራቸው የሚመነዳቸው መሆኑ አይቀሬ ነው፡፡

(መሻሻቸው ወደ እኛ ብቻ ነው፡ ከዚያም ምርመራቸው በእኛ ላይ ብቻ ነው)... እንግዲህ መልክተኛው በዚህች ደዕዋ ያላቸው ሚና በዚህ ይወሰናል፡፡ ከእርሳቸው በኋላም ያሉ ዳዒዎች የሥራ ድርሻ ይኼው ብቻ ነው፡፡ በእርግጥ አንተ ማስታወስ ብቻ ነው፣ ከዚህ በኋላ የመተሳሰባቸው ጉዳይ አላህ ዘንድ ነው፡፡

ወደ እርሱ ከመመለስ መሸሻም የላቸውም፣ ከእርሱ ሂሳብና ምንዳም ማምለጫ የላቸውም።

የመጠዘኛ ጥያቄዎች

1. አንቀጾቹ እንዳስቀመጡት የአላህን ችሎታና የማስተናበር ብቃት ምሳሌ አብራራ።
2. ወደ አላህ ተጣሪ የሆነ ዳዒን የሥራ ድርሻና ኃላፊነት ምን እንደሆነ ጥቀስ።

سورة الفجر

(የጎህ ምስራቁ)

ይህች ምዕራፍ ባጠቃላይ በዚህኛው ክፍል ውስጥ የሰው ልጅ ልቦና ወደ እምነትና ወደ ፍራቻ እንዲያቀና፣ እንዲነቃና እንዲያስተነትን ተፅእኖ ከሚፈጥሩት ምዕራፎች የምትመደብ ናት። ከፊሉ ገጽታዋ ውብ፣ የተረጋጋና እዝነት የተሞላበት ልዩ የሆነ ድምጸት ያለው ነው። ከዚህ አኳያ በመግቢያዋ ላይ የተገለጸው ረቂቅ ተፈጥሯዊ ክስተትና በዚህ ወቅት ለሚከናወነው ሂባዳና ሶላት የሚደረገው ጥድፊያ ተጠቃሽ ናቸው።

(በጎህ እምላለሁ፤ በአሥር ሌሊቶችም፤ በጥንዳም በነጠላዋም፤ በሌሊቱም በሚሄድ ጊዜ)

ከፊሉ ገጽታዋ ደግሞ ብርቱና አስከፊ የሆነ መልእክትን አዝሏል... እንደዚያ ከባድና አስፈሪ እንደሆነው የቂያማ ክስተት...

(ተወ፤ ምድር ደጋግማ በተሰባበረች ጊዜ፤ መላእክትም ሠልፍ ሠልፍ ቆመው ጌታህ ትእዛዙ በመጣ ጊዜ፤ ገሀነም በዚያን ቀን በተመዘች ጊዜ፤ በዚያን ቀን ሰው ጥፋቱን ይገነዘባል፤ መገንዘብም ለርሱከየቱ? ዋ! እኔ ምን ነው በሕይወቴ! መልካምን ሥራ ባስቀደምኩ ኖሮ ይላል። በዚያን ቀንም የርሱን አቀጣጥ ማንም አይቀጣም፤ የርሱንም አስተሣሰር ማንም አያሥርም)

በሌላኛው ገጽታዋ ደግሞ እዝነትና ውደታ የነገሰበትና መረጋጋትን የሚያሰፍን ጥሪ ይስተዋልበታል..ልክ በመጨረሻዋ ላይ እንዳለው አንቀጽ፡

[(ለአማኞች ነፍስም) አንቺ የረካሽው ነፍስ ሆይ! ወዳጅ ተወዳጅ ሆነሽ ወደ ጌታሽ ተመለሽ። በባሮቼም መስጥ ግቢ፣ ገነቴንም ግቢ (ትባላለች)]

ክፍል ስንድ

(ስንቀጽ: 1-14)

﴿ وَٱلۡفَجۡرِ ١ وَلَيَالٍ عَشۡرٖ ٢ وَٱلشَّفۡعِ وَٱلۡوَتۡرِ ٣ وَٱلَّيۡلِ إِذَا يَسۡرِ ٤ هَلۡ فِي ذَٰلِكَ قَسَمٞ لِّذِي حِجۡرٍ ٥ أَلَمۡ تَرَ كَيۡفَ فَعَلَ رَبُّكَ بِعَادٍ ٦ إِرَمَ ذَاتِ ٱلۡعِمَادِ ٧ ٱلَّتِي لَمۡ يُخۡلَقۡ مِثۡلُهَا فِي ٱلۡبِلَٰدِ ٨ وَثَمُودَ ٱلَّذِينَ جَابُواْ ٱلصَّخۡرَ بِٱلۡوَادِ ٩ وَفِرۡعَوۡنَ ذِي ٱلۡأَوۡتَادِ ١٠ ٱلَّذِينَ طَغَوۡاْ فِي ٱلۡبِلَٰدِ ١١ فَأَكۡثَرُواْ فِيهَا ٱلۡفَسَادَ ١٢ فَصَبَّ عَلَيۡهِمۡ رَبُّكَ سَوۡطَ عَذَابٍ ١٣ إِنَّ رَبَّكَ لَبِٱلۡمِرۡصَادِ ١٤ ﴾ الفجر: ١ - ١٤

"በነህ እምላለሁ፡፡ (1) በዐሥር ሌሊቶችም፡፡ (2) በጥንዱም በነጠላውም፡፡ (3) በሌሊቱም በሚሸድ ጊዜ፡፡ (4) በዚህ (ማሉላ) ለባለ አእምሮ ታላቅ ማሉላ አለበትን? (5) ጌታህ በዓድ እንዴት እንደ ሠራ አታውቅምን? (6) በአረም በባለ ረዣዥሙ አዕሞር፡፡ (7) በዚያች ብጠዋ በአገሮች ወስጥ ያልተፈጠረ በኾነ ችው፡፡ (8) በሰሞድም በእነዚያ በሸለቆው ቋጥኝን የቆረጡ በኾኑት፡፡ (9) በፈርዖንም ባለ ችካሎች በኾነው፡፡ (10) በእነዚያ በአገሮች ላይ ግፍ የሠሩ፡፡ (11) በእርሷም ወስጥ ጥፋትን ያበዙ በኾኑት (እንዴት እንደሠራ አታውቅምን?) (12) በእነርሱ ላይም ጌታህ የቅጣትን አለንጋ አወረደባቸው፡፡ (13) ጌታህ በማጠበቂያ ላይ ነውና፡፡ (14)"

የትምህርቱ ዝርዝር ዓላማዎች

1. በአንቀጾቹ ውስጥ የተማለባቸውን ነገሮች ትሩፋት እንዲጠቅስ ማስቻል፡፡

2. ምዕራፏ ስላወሳቻቸው እንቢተኛ አመጸኞች መጨረሻ እንዲያብራራ ማስቻል፡፡

...ይህ በዚህች ምዕራፍ መግቢያ ላይ የተጠቀሰው መሃላ የሚከተሉትን ተፈጥሯዊ ክስተቶችና ሁኔታዎች አካቷል፡-

(ነህ)... ሕይወት በቀላሉ የምትተነፍስበት ጊዜ ነው፡፡ (አሥር ሌሊቶች) በማለት የተቀመጡት ቁርኣናዊ ዐረፍተ ነገሮችን በተመለከተ የተለያዩ ዘገባዎች ተወስተዋል፡፡... እነርሱም የዙል-ሒጃ አሥር ቀናቶች ናቸው ተብሏል፡፡ የሙሐረም አሥር ቀናት ናቸው ተብሏል፡፡ የረመዳን አሥር ቀናት ናቸውም

ተብሏል፡፡ እንደዚህ ያልተገደቡ አድርጐ መተው የተሻለና በላጭ ነው፡፡ እነርሱ አላህ የሚያውቃቸው አሥር ሌሊቶች ናቸው፡፡ እነዚህ አሥር ቀናት በእርሱ ዘንድ ልዩ ቦታ አላቸው፡፡ (በጥንቁም በነ ጠለወም)... የሶላትንና የሚባዳን መንፈስ በዚያ በነህ አየር ውስጥ ይረጫሉ...ከጥንድም ከነጠላም የሆኑ ሶላቶችን፡፡

(ሌሊቱም በሜድ ጊዜ)... እዚህ ላይ የምንረዳው ሌሊት ሕያው ፍጡር መሆኑን ነው፡፡ ልክ በጨለማ ውስጥ እንደሚንቀሳቀስ ተጓዥ! ወይም መንገድ እንደሚመርጥ የሩቅ ተጓዥ በዩኒቨርሱ ውስጥ ይጓዛል፡፡

በመጨረሻም (በዚህ ማዙለ ለባለ አእምሮ ታላቅ ማዙለ አለበትን?) በማለት ሃሳቡን ይቋጫል፡፡ ጥያቄው ለማረጋገጥ የመጣ ነው፡፡ በዚህ ውስጥ ንቁ ልብና አእምሮ ላለው ሰው ታላቅ መሐላ አለበት፡፡ መገንዘብና ማስተንተን ለሚችል በርሱ ውስጥ ትልቅ ማረጋገጫ አለለት፡፡

(ጌታህ በዓድ እንዴት እንደሠራ አታውቅምን? በአረም፡ በረጣማሮዎቹ አዕማድ፤)

ይህን መሰሉ መጠይቃያዊ አገላለፅ ሰውን የማንቃትና ዙሪያውን እንዲያማትር የማድረግ ተፅእኖው ከባድ ነው፡፡ ሲጀምር መልዕክቱ ለነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ነው፡፡ ከዚያም የነዚያ ህዝቦች መጨረሻ ለታየውና ለሚያስብ ሁሉ ነው፡፡ ረቡክ (ጌታህ) ከሚለው ቃል በንግግሩ ውስጥ መጨመሩ በተለይም ለነዚያ መካ ውስጥ በአመጸኞችና አምባገነን ሙሽሪኮች የሚደርስባቸውን ግፍና መከራ ለተጋፈጡት፣ ለደዕዋውና ለተከታዮቹ ተጠባባቂ ሆነው መሰዋትነት ለሚከፍሉት ሙእሚኖች እርጋታ፤ አብሮነትና እርካታን ይለግሳል፡፡

አላህ (ሱ.ወ) በእነዚህ አጫጭር አናቅጽ እነዚያ የጥንት ታሪክ ያወቃቸውን ኃይለኛና አምባገነን ህዝቦች መጨረሻቸው ምን እንደሆነ እስፍሯል፡፡

(የዓድ እና ኢረም መጨረሻ)... እነኝህ የመጀመሪያዎች የዓድ ህዝቦች ናቸው፡፡ መኖሪያቸው በደቡብ የመንና በሐድረመውት መካከል በምትገኝ ክፍል በአሸዋ ክምር ውስጥ ነበር፡፡ በአዕማድ ላይ የቆመ ድንኳን ለመጀመሪያ ጊዜ የገነቡ ነበሩ፡፡ ኃይለኛና ብርቱ እንደነበሩ በቁርአን ውስጥ ተጠቅሰዋል፡፡ የዓድ ጎሳ በዘመናቸው ከነበሩት ሁሉ ኃይለኛና የተለዩ ነበሩ፡፡ (በዚያች ብጤዋ በአገሮች ውስጥ ያልተፈጠረ በኾነችው)... በዚያን ዘመን!!

(በሥጋም በነዚያ በሸለቆው ቋጥኝን የቆረጡ በኾኑት)... ሠሙዶች በመዲናና በሻም መካከል በምትገኘው በሰሜን የዐረቢያ ደረቅ ምድር ክፍል ቋጥኝ ፈልፍለው ይኖሩ ነበር። ቋጥኙን ጠርበው ግንብ አድርገውት ነበር። እንደዚሁም ተራራውን ቦርቡረው መጠለያና ዋሻ ይገነቡ ነበሩ።

(በፈርዖን፣ ባለችካሎች በሆነ ወታ... እነኝህ ምናልባትም ዋልታ የሚመስሉትና ምድር ላይ በጠንካራ ሁኔታ የተገነቡት ፒራሚዶች ሳይሆኑ እንደማይቀር ተነግሯል። እዚህ ላይ የተጠቀሰው ፈርዖን በሙሳ (ዐ.ሰ) ጊዜ የነበረው ግፈኛው ፈርዖን ነው።

እነኝህ ሁሉ (በነዚያ ባገሮች ላይ ግፍ የሠሩ፤ በርሷም ወሰጥ ጥፋትን ያበዙ የኾኑት) ናቸው። መቼም ከግፈኛ በስተጀርባ ከጥፋት ውጭ ሌላ አይኖርም። ወሰንን ማለፍ ግፈኛን ያበላሻል። እንደዚሁም ግፍ ያረፈባቸው በሙሉ ይበላሻሉ። ማንኛውም የሕይወት ግንኙነትና ትስስሮችም ይበጠሳሉ። በምድር ላይ ጥፋትን ሲያበዙ መድሃኒቱ የምድርን ገጽታ ከጥፋት ማጽዳት ነበር።

(በነሱ ላይም ጌታህ የቅጣትን አለንጋ አወረደባቸው፤ ጌታህ በማሰብቀ ላይ ነውና)። ጌታህ እነርሱን ተጠባባቂና ተግባራቸውን መዝጋቢያቸው ነው። ጥፋቱ በበዛና በጨመረ ጊዜ የቅጣቱ አለንጋ ዘነበባቸው። [የቅጣት አለንጋ] የሚለው አገላለፅ ቅጣቱ ምን ያህል አስከፊ እንደሆነ ያሳየናል። [አወረደባቸው] የሚለውም ቅጣቱ ተከታትሎ የመውረዱንና ሁሉን ያሰመጠ መሆኑን ያሳያል።... ሕመምና ስቃይ የተሰባሰበበትና አምባገነኖችን የሸፈነበት ክስተት። በነዚያ በምድር ላይ ወሰንን ባለፉትና ጥፋትን ባበዙት ላይ!! ይህ የአምባገነኖች ውድቀት በስተጀርባ በየትኛውም ዘመንና ቦታ አምባገነኖችን በሚፋለሙ አማኞች ልብ ላይ መረጋጋትን ያዘንባል። [ጌታህ በማሰብቂያ ላይ ነው] የሚለው የአላህ ቃል ልዩ መረጋጋትን ይፈጥራል። ጌታህ ተጠባባቂ ኾኖ እዚያ ቦታ አለ። ምንም ነገር አያመልጠውም። ምንም የማያልፈው ተቆጣጣሪ ነው። ጌታው በመጠባበቅ ላይ ስለሆነ... ወሰን አላፊዎችን፣ ተንኮለኞችንና አጥፊዎችን ስለሚጠባበቅ የአማኝን ጭንቀት ያረጋጋል..!!

የመጠዘኛ ጥያቄዎች

1. በአንቀጾቹ ውስጥ አላህ የማለባቸውን ነገሮች ደረጃ ጥቀስ፡፡
2. አንቀጾቹ ውስጥ የተነገረላቸው ሌሊቶች ምን ዓይነት ሌሊቶች ናቸው? ደረጃቸውስ ምንድን ነው?
3. ምዕራፏ ያወሳቻቸው እንቢተኛ አመጸኞች መጨረሻቸው ምን እንደሆነ አብራራ፡፡
4. (ጌታህ በመጠባበቂያ ላይ ነው)... ይህ አንቀጽ ባንተ ውስጥ ምን አሳደረብህ?

ክፍል ሁለት

(ሰንቂጽ: 15-20)

﴿ فَأَمَّا ٱلۡإِنسَٰنُ إِذَا مَا ٱبۡتَلَىٰهُ رَبُّهُۥ فَأَكۡرَمَهُۥ وَنَعَّمَهُۥ فَيَقُولُ رَبِّيٓ أَكۡرَمَنِ ١٥ وَأَمَّآ إِذَا مَا ٱبۡتَلَىٰهُ
فَقَدَرَ عَلَيۡهِ رِزۡقَهُۥ فَيَقُولُ رَبِّيٓ أَهَٰنَنِ ١٦ كَلَّاۖ بَل لَّا تُكۡرِمُونَ ٱلۡيَتِيمَ ١٧ وَلَا تَحَٰٓضُّونَ عَلَىٰ
طَعَامِ ٱلۡمِسۡكِينِ ١٨ وَتَأۡكُلُونَ ٱلتُّرَاثَ أَكۡلٗا لَّمّٗا ١٩ وَتُحِبُّونَ ٱلۡمَالَ حُبّٗا
جَمّٗا ٢٠ كَلَّآ إِذَا دُكَّتِ ٱلۡأَرۡضُ دَكّٗا دَكّٗا ٢١ وَجَآءَ رَبُّكَ وَٱلۡمَلَكُ صَفّٗا صَفّٗا ٢٢ وَجِاْيٓءَ
يَوۡمَئِذِۭ بِجَهَنَّمَۚ يَوۡمَئِذٖ يَتَذَكَّرُ ٱلۡإِنسَٰنُ وَأَنَّىٰ لَهُ ٱلذِّكۡرَىٰ ٢٣ يَقُولُ يَٰلَيۡتَنِي قَدَّمۡتُ لِحَيَاتِي
٢٤ فَيَوۡمَئِذٖ لَّا يُعَذِّبُ عَذَابَهُۥٓ أَحَدٞ ٢٥ وَلَا يُوثِقُ وَثَاقَهُۥٓ أَحَدٞ ٢٦ يَٰٓأَيَّتُهَا ٱلنَّفۡسُ ٱلۡمُطۡمَئِنَّةُ ٢٧
ٱرۡجِعِيٓ إِلَىٰ رَبِّكِ رَاضِيَةٗ مَّرۡضِيَّةٗ ٢٨ فَٱدۡخُلِي فِي عِبَٰدِي ٢٩ وَٱدۡخُلِي جَنَّتِي ٣٠ ﴾ الفجر: ١٥ - ٣٠

"ሰውማ ጌታው በሞከረው ጊዜ፣ ባከበረውና ባጣቀመው (ጊዜ) «ጌታዬ አከበረኝ (አበለጠኝ)» ይላል። (15) በሞከረውና በእርሱ ላይ ሲሰዩን ባጠበበ ጊዜማ «ጌታዬ አሳነሰኝ» ይላል። (16) ይከልከል፤ ይልቁንም የቲምን አታከብሩም። (17) ድኻንም በማበላት ላይ አትታዘዙም። (18) የወፎስንም ገንዘብ የማብሰብን አበላል ትበላላችሁ። (19) ገንዘብንም ብዙን መውደድ ትወዳላችሁ። (20) ተወ፤ ምድር ደጋግማ በተሰባበረች ጊዜ፤ (21) መላእክትም ሰልፍ ሰልፍ ኾነው ጌታህ (ትዕዛዙ) በመጣ ጊዜ፤ (22) ገሀነምም በዚያ ቀን በተመጣች ጊዜ በዚያ ቀን ሰው (ጥፋቱን) ይገነዘባል። መገንዘብም ለእርሱ ከየቱ? (23) «ዋ እኔ! ምን ባሕይወቴ (መልካምን ሥራ) ባስቀደምኩ ኖሮ» ይላል። (24) በዚያ ቀንም የርሱን አቀጣጥ አንድም አይቀጣም። (25) የእርሱንም አስተሳሰር አንድም አያስርም። (26) (ለአማች ነፍስም) «አንቺ የረካሺው ነፍስ ሆይ! (27) «ወዳጅ ተወዳጅ ኾነሽ ወደ ጌታሽ ተመለሺ። (28) «በባሮቼም ውስጥ ግቢ። (29) ገነቴንም ግቢ፤» (ትባላለች)። (30)"

የትምህርቱ ዝርዝር ዓላማዎች

1. በአንቀጾቹ ውስጥ የሰፈሩትን የሰው ልጅ መገለጫዎች እንዲያብራራ ማስቻል።

2. የሰው ልጅ ለመሰጠትና ለመነፈግ ያለውን እይታ እንዲያብራራ ማስቻል፡፡
3. የቂያማ (የትንሳኤ) እለት ከሚከሰቱ የፍጥረተ ዓለሙ መገለባበጥ ክስተቶች እንዲጠቅስ ማስቻል፡፡
4. የቂያማ (ትንሳኤ) እለት ወንጀለኛ ሰው የሚደረስበትን ኪሳራና ጸጸት እንዲገልጽ ማስቻል፡፡
5. የቂያማ እለት ሁሉም የሰው ልጅ ዓይነቶች መጨረሻቸው ምን እንደሆነ ግልጽ እንዲያደርግ ማስቻል፡፡

ሰመማ ጌታው በሞከረው ጊዜ፣ ባከበረመና ባጣጭመው ጊዜ ጌታዬ አከበረኝ [አበለጠኝ] ይላል፡፡ በሞከረመና ሲሰዩን ባጠበበ ጊዜማ ጌታዬ አሳነሰኝ ይላል)

...እንግዲህ አላህ በተለያየ ሁኔታ በፈተነው ጊዜ የሰው ልጅ አመለካከት እንደዚህ ነው፡፡ በመስጠትና በመንሳት ይፈትነዋል፡፡ ሲሳዩን በማስፋትና በማጥበብ እንዲሁ ይፈትነዋል፡፡... ነገር ግን ይህ ለፈተናና በዚህ ላይ ተመስርቶ በመጨረሻ ለሚከፈለው ምንዳ መሆኑን አያውቅም፡፡ እንዲያውም ይህ የተሰጠኝ ሲሳይና ምኞት ከአላህ ዘንድ ክብር ስለሚገባኝ ነው ብሎ ያስባል፡፡ አላህ እርሱን የመምረጡና ያላቀው መሆኑ ምልክት ይመስለዋል፡፡ ፈተናን ምንዳ፣ ሙከራውን ውጤት አድረጎ ያያል፡፡ አላህ ዘንድ ያለን ክብር በዚህች በቀረበለት ነገር ይለካል፡፡ አላህ ደግሞ ከሰጠው ሲሳይ በማጣበብ ይፈትነዋል፡፡ በዚህን ጊዜም ፈተናውን ምንዳ ነው ብሎ ያስባል፡፡ ሙከራውን ቅጣት ነው ብሎ ይደመድማል፡፡ የሪዝቁን (የሲሳዩን) መጥበብ አላህ እንዳዋረደው አድርጎ ይስላል፡፡ ውርደቴን ባይፈልግ ኖሮ ሲሳዬን ባላጠበበብኝ ነበር ይላል፡፡

እርሱ (የሰው ልጅ) በሁለቱም ሁኔታ በአመለካከቱም ስህተተኛ ነው፤ በግምቱም ስህተተኛ ነው፡፡ የሲሳይ መስፋትም ይሁን መጥበብ አላህ እነርሱ በተሰጣቸው ጸጋ ምስጋናን ያቀርባሉ ወይንስ ኩራት ይሰማቸዋል የሚለው ግልጽ ይሆንለት ዘንድ፤ እንደዚሁም ዘቅዘቅ ሲልባቸው ትእግስትን ይላበሳሉ ወይንስ ተስፋ ይቆርጣሉ የሚለውን ለመለየት ባሪያውን የሚፈትንበት ነው፡፡ በርግጥ በምድር ላይ ያለ ስጦታም ይሁን ክልከላ ምንዳ አይደለም፡፡ አንድ ባሪያ አላህ

ዘንድ ያለው ዋጋ ከዱንያ ሀብት ላይ አይንጠለጠልም፡፡ የአላህ ውዴታውም ይሁን ቁጣው በዚህች ምድር ላይ በመሰጠትና በመከልከል አይገለጽም፡፡

(ይከልከል! ይልቁንም የቲምን አታከብሩም፤ ድኻንም በማበላት ላይ አትተዛዙም፤ የወሮስንም ገንዘብ የሚብሰብን አበላል ትበላላችሁ፤ ገንዘብንም ብዙን መዉደድ ትወዳላችሁ)

በፍጹም! የሲሳይ መስፋት በአላህ ዘንድ የመከበር ማስረጃ አይደለም፡፡ የሲሳይ መጥበብም የውርደትና የክስረት ማስረጃ አይደለም፡፡ እውነታው በመስጠት ግደታ ላይ አትወሳሱም፣ በገንዘባችሁ ላይ ያለባችሁን ኃላፊነት አትሞሉም፣ እናንተ ያን አባቱን ባጣ ጊዜ ጠባቂውንና ተንከባካቢውን ያጣ ደካማ የቲምን አታከብሩም፣ እርስ በርስም ያንን ፈላጊ መሆኑ ለጥያቄ የሚቀርብ ያልኾነውን ምስኪንን በማብላት ላይ አትመካከሩም፡፡ እናንተ የፈተና ትርጉም አልገባችሁም፡፡ የቲምን በመንከባከብና ምስኪኖችን በማብላት ላይ መመካከር፣ ከእርሱም ስኬታማ ለመሆን ጥረት አታደርጉም፡፡ እንዲያውም እናንተ በተቃራኒ ታደርጋላችሁ፡፡... ውርስን በመሰብሰብ ተስገብግባችሁ ትበላላችሁ፡፡ ገንዘብን ያለመጠን ትወዳላችሁ፡፡ ነፍሳችሁ ውስጥ ምንም አይነት የመርካትና ፈላጊዎችን የመንከባከብም ሆነ የመመገብ ቅሪት አይታይም፡፡ እነኝህ አንቀፆች በሰው ልጅ ነፍስ ውስጥ ያለውን እውነታ ይፋ ከማድረግም ባሻገር እሳቤውን የመንቀፍና ተግባሩን የማንቋሸሽ መልእክት ይንጸባረቅባቸዋል፡፡ የሰዎችን የተጠላ ውስጣዊ እውነታ ይህን ያህል ካጋለጠ በኋላና ለፈተና፣ ለመሰጠትና ለመከልከል ያላቸው አመለካከት ስህተት መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ከፈተናና ከውጤት በኋላ አይቀሬ የሆነውን የመተሳሰቡን ቀን አስፈሪነት ያስቀምጣል፡፡

(ይከልከል፤ ምድር ደጋግማ በተሰባበረች ጊዜ፤ መላእክትም ሠልፍ ሠልፍ ኾነው ጌታህ ትእዛዙ በመጣ ጊዜ፤ ገሀነም በዚያን ቀን በተመዘች ጊዜ፤ በዚያን ቀን ሰው ጥፋቱን ይገነዘባል፤ መገንዘብም ለርሱ ከየቱ?)

የምድር መንኮታኮት፣ የመሠረቶቿ መፈራረስና መስተካከል በትንሣኤ ዕለት ከሚከሰቱ የፍጥረተ-ዓለሙ መገለባበጥ ክስተቶች አንዱ ነው፡፡ መላእክት በሠልፍ በሠልፍ ኾነው ጌታህ ይመጣል የሚለው የሩቅ ጉዳይ ነው፡፡ እኛ ምድር ላይ ሆነን በምን መልኩ እንደሚከሰት የማናውቀው ነገር ነው፡፡ እንደዚሁም የገሀነም አመጣጥን እንዴት እንደሚሆን አናውቅም፡፡ ከዚህ መልእክት ገሀነም ለእነርሱ ቅርብ እንደሆነችና

የሚቀጡትም ለእርሷ ቅርብ መሆናቸውን መውሰዱ በቂ ነው። በዚያን ወቅት ስለሚከሰተው ነገርና የሚከሰትበት ሁኔታ ከአላህ የሩቅ ዕውቀት ነው።

(በዚያን ቀን ሰው ጥፋቱን ይገነዘባል፤ መገንዘብም ለርሱ ከየቱ?)... ያ በመስጠትና በመንሳት ላይ የተመረኮዘውን የአላህን የመፈተኛ ጥበብ የረሳው፤ ውርስን ሳያቅማማ የበላው፤ ገንዘብን ከልክ በላይ የሚያፈቅረው፤ የቲምን የማያከብረውና ምስኪኖችን ለመመገብ የማይነሳሳው...የዚያን ጊዜ ያስታውሳል። እውነቱን ያስታውሳል፣ በሚያየውም ይመከራል...ነገር ግን ጊዜው ያለፈበት መመከር ነው፡ (መገንዘብም ለርሱ ከየቱ?)... የመመከሪያው ጊዜ በእርግጥ አልቋል... በዚያ ምንዳ በሚከፈልበት አገር አንድም ሰው እንደገና ሊመለስ አይችልም! በርግጥ በዚህች የሥራ አገር በሆነችው በዱንያ ምድር ላመለጠው እድል የክስረት ጸጸት ናት።

ይህ እውነታ በተገለጸለት ጊዜ (ዋ፡ እኔ! ምነው በሕይወቴ [መልካምን ሥራ] ባስቀደምኩ ኖሮ) ይላል። ዋ! ምነው በዱንያ ላይ ሳለሁ ለሕይወቴ የሚሆን ነገር አስቀድሜ በነበር። አዎ! በርግጥም ሕይወት የሚለው ስም የሚገባት የሆነችው እውነተኛ ሕይወት...ወይ ጥፋቴ...ግልጽ ክስረት የሚታይበት ትካዜ፣ ይህ የሰው ልጅ በአኼራ ሊያደርገው የሚችለው የመጨረሻ አቅሙ ነው!!

ከዚህ አስደንጋጭ ክስረትና የጨለመ ተስፋ በመቀጠል የጉዞው ፍፃሜ ምን እንደሚሆን ያስቀምጣል። (በዚያ ቀንም የርሱን አቀጣጥ አንድም አይቀጣም)... በርግጥም እርሱ ያ ኃያሉና ብርቱው አላህ ነው በዚያን ጊዜ አምሳያ የሌለው ቅጣቱን የሚቀጣው! እንደርሱ ያለን ቅጣት ምንም መቅጣት የማይችል ሲሆን፣ ያ ማንም የማያይዘው የሆነውን ብርቱ አያያዙን የሚይዘው ነው። በዚህ አስፈሪና አስጨናቂ ሁኔታ ውስጥ፣ በዚያ ቅጣትና ብርቱ አያያዝ መሃል ያች የተረጋጋች የሆነችው ነፍስ ከላይኛው ዓለም ጥሪ ይደረግላታል።

(አንቺ የረካሽው ነፍስ ሆይ! ወዳጅ ተወዳጅ ሆነሽ ወደ ጌታሽ ተመለሺ። በባሮቼም ወስጥ ግቢ፤ ገነቴንም ግቢ [ትባላለች])

እንደዚህ በእዝነትና በቅርበት፡ [አንቺ ሆይ!]፣ በመንፈሳዊነትና በክብር [አንቺ ነፍስ ሆይ!]፣ በማወደስና በማረጋጋት [አንቺ የረካሽው ነፍስ ሆይ!]

በማለት ይጠራታል፡፡... በዚያ በጭንቅና በእሥር መሃል ይህች ከጭንቅ የምትገላግል ጥሪ ታስተጋባለች፡ [ወደ ጌታሽ ተመለሽ]... ከምድር እንግድነትና ከዘመናት መለየት በኋላ ወደ መጀመሪያ መነሻሽ ተመለሺ፡፡በዚህ ዓይነት የእዝነትና የውዴታ አየርን በሚያሰፍን ጥሪ... [ወዳጅ ተወዳጅ ሆነሽ]፡፡ [በባሮቼም ወስጥ ግቢ]... ቅርብና ምርጥ የኾኑት ቅርበታቸውን ያጣጥሙ ዘንድ በጥበቃየና በእዝነቴ [ገነቴንም ግቢ]...፡፡

የመጨረሻ ጥያቄዎች

1. በአንቀጾቹ የተቀመጠውን የሰው ልጅ የነፍስ ልዩ መገለጫዎች አብራራ፡፡
2. የሰው ልጅ ለመሰጠትና ለመነፈግ ያለውን እይታ አብራራ፡፡
3. የቂያማ (የትንሣኤ) እለት ከሚከሰቱ የፍጥረተ ዓለሙ መገለባበጥ ክስተቶች ጥቀስ፡፡
4. የቂያማ (የትንሣኤ) እለት ወንጀለኛ ሰው የሚደረስበትን ኪሳራና ጸጸት አመልክት፡፡
5. የቂያማ (የትንሣኤ) እለት ሁሉም ዓይነት የሰው ልጅ መጨረሻቸው ምን እንደሆነ አብራራ፡፡

سورة البلد

(የዘገር ምዕራፍ)

﴿ لَآ أُقۡسِمُ بِهَٰذَا ٱلۡبَلَدِ ١ وَأَنتَ حِلُّۢ بِهَٰذَا ٱلۡبَلَدِ ٢ وَوَالِدٖ وَمَا وَلَدَ ٣ لَقَدۡ خَلَقۡنَا ٱلۡإِنسَٰنَ فِي كَبَدٍ ٤ أَيَحۡسَبُ أَن لَّن يَقۡدِرَ عَلَيۡهِ أَحَدٞ ٥ يَقُولُ أَهۡلَكۡتُ مَالٗا لُّبَدًا ٦ أَيَحۡسَبُ أَن لَّمۡ يَرَهُۥٓ أَحَدٌ ٧ أَلَمۡ نَجۡعَل لَّهُۥ عَيۡنَيۡنِ ٨ وَلِسَانٗا وَشَفَتَيۡنِ ٩ وَهَدَيۡنَٰهُ ٱلنَّجۡدَيۡنِ ١٠ فَلَا ٱقۡتَحَمَ ٱلۡعَقَبَةَ ١١ وَمَآ أَدۡرَىٰكَ مَا ٱلۡعَقَبَةُ ١٢ فَكُّ رَقَبَةٍ ١٣ أَوۡ إِطۡعَٰمٞ فِي يَوۡمٖ ذِي مَسۡغَبَةٖ ١٤ يَتِيمٗا ذَا مَقۡرَبَةٍ ١٥ أَوۡ مِسۡكِينٗا ذَا مَتۡرَبَةٖ ١٦ ثُمَّ كَانَ مِنَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَتَوَاصَوۡاْ بِٱلصَّبۡرِ وَتَوَاصَوۡاْ بِٱلۡمَرۡحَمَةِ ١٧ أُوْلَٰٓئِكَ أَصۡحَٰبُ ٱلۡمَيۡمَنَةِ ١٨ وَٱلَّذِينَ كَفَرُواْ بِـَٔايَٰتِنَا هُمۡ أَصۡحَٰبُ ٱلۡمَشۡـَٔمَةِ ١٩ عَلَيۡهِمۡ نَارٞ مُّؤۡصَدَةُۢ ٢٠ ﴾ البلد: ١ - ٢٠

"በዚህ አገር (በመካ) እምላለሁ፡ (1) አንተ በዚህ አገር ሰፋሪ ስትሾን፡፡ (2) በወላጀም በወለዳቸውም ሰዎች (በአዳምና በዘሮቹ ሁሉ እምላለሁ)፡፡ (3) ሰውን ሁሉ በእርግጥ በልፋት ወልጥ ኾኖ ፈጠርነው፡ (4) በእርሱ ላይ አንድም የሚቸል መሾኑን ይጠረጥራልን? (5) «በዙን ገንዘብ አጠፋሁ» ይላል፡፡ (6) አንድም ያላየው መሾኑን ያስባልን? (7) ለእርሱ ሀለት ዓይኖችን አላደረግንለትምን? (8) ምላስንና ሀለት ከንፈሮችንም፡ (9) ሀለትን መገዶችም አልመራነ ወምን? (10) ዐቀበቲቱንም አልወጣም፡ (11) ዓቀበቲቱም (መውጣቲ) ምን እንደኾነች ምን አሳወቀህ? (12) (እርሱ) ጫጄን መልቀቅ ነው፡ (13) ወይም የረኃብ ባለቤት በኾነ ቀን ማበላት፡፡ (14) የዝምድና ባለቤት የኾነን የቲም (15) ወይም የዐፈር ባለቤት የኾነን ድኻ (ማበላት ነው)፡፡ (16) (ዐቀበቲቱን አልወጣም)፡፡ ከዚያም ከነዚያ ከአሚትና በመታ አደራ ከተባባሉት፣ በማዘንም አደራ ከተባባሉት ሰዎች አልኾነም፡ (17) እነዚያ (ይህንን የፈጸሙ የቀኝ ጓዶች ናቸው፡ (18) እነዚያም በአንቀጾቻችን የካዱት እነርሱ የግራ ጓዶች ናቸው፡ (19) በእነርሱ ላይ የተዘጋች እሳት አልለች፡፡ (20)"

የትምህርቱ ዝርዝር ዓላማዎች

1. በዚህ ሀገር በማለት አላህ (ሱ.ወ)የማለበትን ጥበብ እንዲጠቅስ ማስቻል፡፡
2. ምዕራፏ በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ያካተተችውን መሠረታዊ እውነታ ግልፅ እንዲያደርግ ማስቻል፡፡
3. ከኃይል በኩል አላህ በሰጠው ጸጋ ላይታለልና ሁልጊዜም አላህ በእርሱ ላይ ያለውን የበላይነት እንዲያስታውስ ማስቻል፡፡
4. በምዕራፏ ውስጥ የተገለጸችው ‘ዐቀባህ’ ወይም ዳገት የምትለው ቃል ምንን ለመግለፅ ተፈልጎ እንደተቀመጠ እንዲጠቅስ ማስቻል፡፡
5. ይህችን ዳገት በአላህ መንገድ ሊወጣ የሚችልበትን መንገድ እንዲያብራራ ማስቻል፡፡
6. በምዕራፏ አንቀፆች የተብራሩትን ሁለት የሰው ልጅ ምድቦችን፣ ተግባራቸውንና ፍፃሜያቸውን ግልፅ እንዲያደርግ ማስቻል፡፡

ይህች ትንሽ ምዕራፍ በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ የሚንፀባረቁ የመሠረታዊ እውነታዎችን ስብስብ በክንፏ አቅፋ ይዛለች፡፡ በርግጥ የተከበረው ቁርአን ስለሆነ እንጂ እነዚህን ሁሉ እውነታዎች በዚህች ትንሽ ምዕራፍ ማካተቱ አስቸጋሪ በሆነ ነበር፡፡ ቁርአን በሰው ልጅ የልብ ትርታ ላይ ይህን አይነት ፈጣንና ጥልቅ ምቱን ለማሳረፍ የልዩ ስልት ባለቤት ነው፡፡ ምዕራፏ የሰው ልጅ በሕይወት እስካለ ድረስ በማይሻር እውነታ ላይ ባተኮረ ትልቅ ጉዳይ በመማል ትጀምራለች፡

[በዚህ ሀገር እምላለሁ፤ አንተ በዚህ ሀገር ሰፋሪ ስትኾን፤]

..ሀገር የተባለው በምድር ላይ ለመጀመሪያ ለአምልኮ የተገነባው ቤት መካ ነው፤ ክልክል የሆነው የአላህ ቤት፡፡ ለነርሱ ጌታቸውን ማምለኪያና ሰላም ይሆንላቸው ዘንድ፡፡ ከዚያም የዐረቦችና የሙስሊሞች ሁሉ አጠቃላይ አባት የሆኑት የእስማኢል ወላጅ፣ የኢብራሂም ቤት ነው፡፡ አላህ ነቢዩን የሀገሩን ጥበቅነት በሚያነላና የእርሳቸውንም ክብር በሚጨምር አገላለጽ በዚህ ማስታወሻው ያከብራቸዋል፡፡ በዚህ ሀገር ያላቸውን ሁኔታና ነዋሪነት ይጠቁማቸዋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) በዚህ ሀገርና በእርሱም ውስጥ ነዋሪ በሆነው ብሎ ሲምል በእርግጥ በነቢዩና በክብራቸው ላይ የበለጠ ክብርን ያጎናፅፋቸዋል፡፡ እነዚያ እኛ የተከበረው

ቤት ባለቤቶችና በኢብራሂም የእምነት ጎዳና ላይ ነን ብለው የሚፎክሩትን አጋሪዎች በከፋ ነቀፌታ ያዋርዳቸዋል፡፡ [በወላጆቻቸው በወለዳቸውም] . . . የሚለው አንቀጽ ትርጉም ወደ ኢብራሂም ወይም ወደ እስማኢል (ሰላም በእነርሱ ላይ ይውረድና) በተለይ የሚያመለክት ይመስላል፡፡ ይህም በሀገሩና ነዋሪ በሆነው ነቢይ የተጀመረውን መሐላ የመጀመሪያውን የመካ ሀገር ልጅና ትውልዶቹን በማካተት ሙሉ ይሆናል፡፡ ይህ አገላለፅም 'በአዳምና በዘሮቹ ሁሉ እምላለሁ!' ለማለት ተፈልጎ ነው ከሚለው አገላለፅ ጋርም ተቃርኖ የለውም፡፡

(ሰውን ሁሉ በእርግጥ በልፋት ላይ ኾኖ ፈጠርነው)... በድካምና በችግር፣ በትግልና በእንግልት፣ በፍልሚያና እና በውጣ ውረድ፣... ይህ የዱንያ ሕይወት ተፈጥሯዊ ልፋት ነው፡፡ ዓይነቱና ምክንያቱ ቢለያይም መጨረሻው ያው ልፋት ነው፡፡ እዚህ ላይ ከከሳሪዎች ሁሉ ከሳሪው ከዱንያ ልፋትና ድካም ወደ ከፋ የአኼራ ሕይወት የተሸጋገረ ነው፡፡ ስኬታማ ከሆኑት ሁሉ የበለጠ ስኬታማው ደግሞ የሕይወት ልፋቱ የሚቋጭበትና ጌታውን በመልካም ለመገናኘት በሚያደርሰው መንገድ ላይ የሚያዘጋጀውን ተግባር ዛሬ ላይ የሚለፋ ነው፡፡ ጉዞውም በአላህ ጥላ ሥር በታላቅ እረፍት ትደመደማለች፡፡ ይህንን ተፈጥሯዊ የሰው ልጅ የሕይወት እውነታ ካረጋገጠ በኋላ በቀጣይነት የሰውን ልጅ እይታና ለእንቅስቃሴው ያለውን አመለካከት እንደሚከተለው ይዳስሳል፡፡

(በርሱ ላይ አንድም የሚቸል መሾኑን ይጠረጥራልን? ብዙን ገንዘብ አጠፋሁ ይላል፤ አንድም ያላየው መሾኑን ያስባልን?)... ይህ ለልፋት የተፈጠረው የሰው ልጅ የተፈጠረበትን እውነታ ረስቶ ፈጣሪው በቸረው ሀይልና ችሎታ ይታለላል፡፡ በሚሠራው ሥራ ተጠያቂ እንዳልሆነ አስቦ እንደፈለገ ይንቀሳቀሳል፡፡ አንድም አካል ከበላይ ሆኖ ይተሳሰበኛል የሚል ግምት የለውም፡፡ ከዚያም ለጥሩ ነገር ሲጠራና ገንዘቡን እንዲያወጣ ሲጠየቅ (ብዙን ገንዘብ አጠፋሁ ይላል).. ከዚህ በፊት ብዙ ገንዘቤን አፍስሻለሁ፣ የሰጠሁትና መስዋእትነት የከፈልኩት ይበቃኛል ብሎ ይሞግታል፡፡ (አንድም ያላየው መሾኑን ያስባልን?) . . . የአላህ አይን እንደሚከታተለውና በእውቀቱም እንደሚያካብበው ይረሳል፡፡ እርሱ በእርግጥ ምን እንደለገሰና ለምን እንደሰጠ ተመልካች ነው፡፡ ለዚህ ለተታለለው ሰው ቁርአን አላህ (ሱ.ወ) በራሱ ላይ የዋለለትን ጸጋና በተለይም በራሱ አፈጣጠር ሂደት ላይ ያሟላለትን በመጥቀስ ይገዳደረዋል፡፡

(ለርሱ ሀለት አይኖችን አላደረግንለትምን? ምላስንና ሀለት ከንፈሮችንም፤ ሀለትን መንገዶችም አልመራነ ወምን?)

የሰው ልጅ እርሱ ዘንድ ባለው ኃይሉ ይታለላል። ነገር ግን ኃይልን ለክቶ የሰጠው አላህ (ሱ.ወ) ነው። በገንዘቡም ይመካል። ነገር ግን ይህንንም ገንዘብ የሰጠው አላህ (ሱ.ወ) ነው። አይመራም፣ እንዲሁም አያመሰግንም። በርግጥ የስሜት ዓለምን ሊመራበት የሚያስችሉትን የስሜት ህዋሳት አድርጎለታል። በጥበብና በጥንቃቄ የተዘጋጁ፣ ለማየት ብቃት ያላቸው ሁለት አይኖችን አድርጎለታል። መናገርና ንግግርን መለየት እንዲችል አድርጎታል። ለዚህ ተግባርም ምላስንና ሁለት ከንፈሮችን አዘጋጅቶለታል። ከዚያም ነፍሱ ጥሩና መጥፎውን፣ ቅኑንና ጠማማውን፣ እውነትና ውሸቱን መለየት የምትችልበትን ብቃት ችሯታል (ሀለትን መንገዶችም አልመራነ ወምን?)... ከሁለቱ የፈለገውን መምረጥ እንዲችል። እነዚህ ሁሉ ጸጋዎች ይህ የሰው ልጅ በእርሱና በጀነት መካከል ግርዶሽ የሆነችውን ዳገት መውጣት አላስቻሉትም። የዚህችን ዳገት ምንነት አላህ በሚቀጥለው አንቀፅ ያብራራልናል።

(ዐቀበቲቱንም አልወጣም፡ ዐቀበቲቱንም መውጣቱ ምን እንደኾነ ምን አሳወቀህ?)

እንግዲህ የሰው ልጅ የተጋፈጣትና መውጣት ያልቻላት ዐቀበት ይህች ናት።... በኢማን ካልታገዘ በስተቀር በጀነትና በእርሱ መካከልም ግርዶሽ የሆነችው ዳገት ይህችው ናት። ከዚያም ይህን ትልቅ ጉዳይ ያብራራዋል... (ዐቀበቲቱንም መውጣቱ ምን እንደኾነ ምን አሳወቀህ?)... ይህ በእርግጥ የዓቀበቱን ግዝፈት ለማሳየት ሳይሆን ነገር ግን አላህ ዘንድ ያላትን ትልቅ ግምት ለማሳየት ነው። የሰው ልጅ ተገቢውን ቦታ እንዲሰጣትና ምንም ያክል ትግልና ልፋት ብትጠይቀውም አስቦና አቅዶ እንዲወጣት ነው።

የዐቀበቷ ምንነት ትንታኔ በወቅቱ ደዕዋው (ጥሪው) ተጋፍጧቸው የነበሩ አንገብጋቢ ጉዳዮች ላይ በመንተራስ ይጀምራል። እነኝህ ትናንት አንገብጋቢ የነበሩ ጉዳዮች ባሪያን ነፃ በማውጣት ላይ መተባበርና ለተቸገሩና ምድር ለተራቆተችባቸው ደካሞች መመገብ ናቸው።

‘ፈክ’ የሚለው የዐረብኛ ቃል ባሪያን ነፃ በማውጣት ላይ መደገፍ በሚል የተተረጎመ ሲሆን ሙሉ በሙሉ ነፃ ማውጣት ደግሞ ‘ሺትቅ’ በሚል ይገለጻል፡፡ የትኛውም ትርጓሜ ቢወሰድ ዓላማው ሰዎችን ከባርነት ቀንበር ነፃ ማውጣት ነው፡፡ ይህም በወቅቱ ገዝፎ የነበረ ችግር መሆኑ በአላህ መንገድ ዐቀበትን ለመውጣትና በፅናት ሊተገብሩት የሚገባ የመጀመሪያ ተጠቃሽ ተግባር እንዲሆን አድርጎታል፡፡

(ወይም የረሃብ ባለቤት በሆነ ቀን ማበላት፤ የዝምድና ባለቤት የሆነን የቲም ወይም የአፈር ባለቤት የሆነን ድኻ [ማበላት])

‘መስገባ’ የሚለው የዐረብኛ ቃል ረሀብ ማለት ነው፡፡ ያ የረሀብ አለንጋ በበረታበት ቀንና ምግብ ማጣፊያው ባጠረበት እለት መመገብ በእርግጥም ከኢማን የተሳሰረ ነው፡፡ እንደዚሁም እነዚያን ከችግሩ ብርታት የተነሳ የሚያርፉበት አጥተው ጎናቸው ከመሬት ላይ የተጣበቀ የሆኑትን የአፈር ባለቤት ምስኪኖችን በዚያ በረሃቡ ቀን ማብላት እምነትን ይጠይቃል፡፡ ቁርአን ይህንን ተግባር ዐቀበቷን ለመውጣት ለሚደረገው ጉዞ እንደ ታላቅ እርምጃ አቅርቦታል፡፡ ምክንያቱም ከእምነት የመነጨ እዝነት፣ ርህራሄ፣ ችግርን መጋራትና ከራስ አስበልጦ ሌላውን የመርዳት ስሜትን ስለሚፈለግ፡፡ በቤተሰቦቹ ላይ በአላህ ዘንድ እንዳይጠየቅ የሚያደርገው መጠባበቅ ከእምነት ስለሆነ...በዚያ በብርቱው፣ በረሀቡና ችግር በተደራረበበት እለት!!

ከዚያም (ቁርአን) ቀዳሚና አጠቃላይ በሆነ ጉዳይ ይደመድመዋል፡

(ከዚያም ከነዚያ ካመኑትና በመታገሥ አደራ ከተባባሉት በማዘንም አደራ ከተባባሉት ሰዎች አልኾነም)

እዚህ ላይ ‘ሡመ (ከዚያም)’ የሚለው ቃል ጊዜን አያመለክትም፡፡ ይልቁንም ዐቀበቷን ለመውጣት በሚደረገው እርምጃ ይህ አጠቃላይ፣ ሰፊና ከፍተኛውን ደረጃ እንደሚይዝ ለመግለፅ የተቀመጠ ነው፡፡ ያለዚያማ ባሪያን ነፃ ማውጣትም ሆነ የተራበን ማብላት ያለ እምነት ጥቅም የላቸውም፡፡ እምነት ባሪያን ነፃ ለማውጣት ከመደገፍና ምግብን ከማብላት ቀድሞ የተቀመጠ ግዴታ ነው፡፡ መልካም ሥራ በአላህ ሚዛን ሲለካ ክብደት የሚሰጠው ይህ እምነት ነው፡፡

ትእግስት በአጠቃላይ አገላለፅ አስፈላጊ የሆነ የእምነት አካል ነው፡፡ ዐቀበትን ለመውጣት ደግሞ በተለየ ሁኔታ አስፈላጊነቱ ይጨምራል፡፡ በትእግስት ላይ

መመካከር ደግሞ ከራሱ ከትእግስት በላይ የላቀ ደረጃ ነው። በእምነት ላይ የተመሠረቱ ህብረቶችን የሚያስተሳስር ደረጃ፤ ምክክራቸው ትእግስትን በመላበስ ላይ የሆነ፣ ትብብራቸው በእምነት ኃላፊነቶች ላይ የሆነ፣ እንደዚሁም በመተዛዘን ላይ ያተኮረ መመካከር!! ይህ በእዝነት ላይ ተጨማሪ ተግባር ነው። ይህ በእርግጥ በህብረቱ ውስጥ መተዛዘንን ግደታ የሚያደርግ በምክክር ላይ የተገነባ የስሜት ጮራ ነው። ለዚህ ልዩ ትኩረት የሚሰጥ፣ መመካከርን ቢጋራም ሆነ በግል ግዴታ የሚያደርግ፣ ሁሉም ስለ እርሱ የሚተዋወሱበት፣ ሁሉም በእርሱ ላይ የሚተባበሩበት!!

እነኝህ ዳገቱን የወጡት ሰዎች (እነዚያ ይህንን የፈጸሙ የቀኝ ጓዶች ናቸው) ... በሌላ ስፍራ ላይ እንደተገለጸው የቀኝ ባለቤቶች ናቸው። በሌላ አባባል እድለኞችና ደስተኞች ናቸው። ሁለቱም ትርጓሜዎች ከእምነት ግንዛቤ ጋር የተሳሰሩ ናቸው።

(እነዚያም በአንቀጾቻችን የካዱት እነርሱ የግራ ጓዶች ናቸው፣ በእነርሱ ላይ የተዘጋች እሳት አለች)

እዚህ ላይ ለእድለ-ቢሶቹ ክፍል "እነዚያም በአንቀጾቻችን የካዱት" ከሚለው ውጭ ሌላ ማብራሪያ ወይም ገለጻ አላስፈለገም። ምክንያቱም ከህደት በራሱ የአቋም መጨረሻ ነውና። ከክህደት ጋር ምንም ጥሩ ነገር አይኖርም። ጥፋት ተብሎ ክህደት የማያካትተውና የማይሸፍነው ምንም ነገር የለም። እነዚህ እድለ-ቢሶች ናቸው... ማለትም የግራ ጓዶች፤ የግራ ጫፎችና ያልታደሉ ሊባል ይችላል። ሁለቱም ትርጓሜዎች ተቀራራቢ ናቸው። (በእነርሱ ላይ የተዘጋች እሳት አለች) ... ማለትም የተቆለፈች ናት። አንደኛው ትርጓሜ እነርሱ በቅጣት ውስጥ ታስረው በሮቿ ተቆልፈዋል ለማለት ይሆናል። ወይም ደግሞ የዚህን ቅጣት ዘውታሪነት ለመግለጽም ይሆናል። ይህም ሲባል እነርሱ ከእርሷ ውስጥ አይወጡም፤ በእነርሱ ላይ የተቆለፈች በመሆኗ ምክንያት ከእርሷ ሊወገዱ አይችሉም ለማለት ይሆናል። ሁለቱም አገላለጾች የተቆራኙ ናቸው።

የመጨረሻ ጥያቄዎች

1. አላህ (ሱ.ወ) በዚህ ሀገር የማለባትን ጥበብ ጥቀስ።

2. ምዕራፏ በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ያካተተችውን መሠረታዊ እውነታን አብራራ።

3. ከኃይል በኩል አላህ በሰጠህ እንደ ገንዘብ፣ ጤናና ልጅ በመሳሰሉት ጸጋዎች ትታለላለህን? አላህ በአንተ ላይ ያለውን ችሎታ ሁልጊዜም ታስታውሳለህን? ለመልስህ ማሰረጃ የሚሆን በገቢር የተገበርከው ምሳሌ ካለ ጥቀስ።

4. በምዕራፏ ውስጥ የተገለጸችው 'ዐቀባህ' ወይም ዳገት የምትለው ቃል ምንን ለመግለፅ ተፈልጎ የተቀመጠ እንደሆነ ጥቀስ።

5. በአላህ መንገድ የዐቀበቲቷን የመውጫ መንገዶችን አብራራ።

6. በምዕራፏ አንቀጾች የተብራሩትን ሁለት ምድቦች፣ ተግባራቸውንና ፍፃሜያቸውን ግለፅ።

سورة الشمس

(የፀሐይ ምዕራፍ)

﴿ وَٱلشَّمۡسِ وَضُحَىٰهَا ١ وَٱلۡقَمَرِ إِذَا تَلَىٰهَا ٢ وَٱلنَّهَارِ إِذَا جَلَّىٰهَا ٣ وَٱلَّيۡلِ إِذَا يَغۡشَىٰهَا ٤ وَٱلسَّمَآءِ وَمَا بَنَىٰهَا ٥ وَٱلۡأَرۡضِ وَمَا طَحَىٰهَا ٦ وَنَفۡسٖ وَمَا سَوَّىٰهَا ٧ فَأَلۡهَمَهَا فُجُورَهَا وَتَقۡوَىٰهَا ٨ قَدۡ أَفۡلَحَ مَن زَكَّىٰهَا ٩ وَقَدۡ خَابَ مَن دَسَّىٰهَا ١٠ كَذَّبَتۡ ثَمُودُ بِطَغۡوَىٰهَآ ١١ إِذِ ٱنۢبَعَثَ أَشۡقَىٰهَا ١٢ فَقَالَ لَهُمۡ رَسُولُ ٱللَّهِ نَاقَةَ ٱللَّهِ وَسُقۡيَىٰهَا ١٣ فَكَذَّبُوهُ فَعَقَرُوهَا فَدَمۡدَمَ عَلَيۡهِمۡ رَبُّهُم بِذَنۢبِهِمۡ فَسَوَّىٰهَا ١٤ وَلَا يَخَافُ عُقۡبَٰهَا ١٥ ﴾ الشمس: ١ - ١٥

"በፀሐይና በብርሃኗ እምላለሁ፡፡ (1) በጨረቃም በተከተላት ጊዜ፤ (2) በቀኑም (ፀሐይን) በገለጻት ጊዜ፤ (3) በሌሊቱም በሸፈናት ጊዜ፤ (4) በሰሜቱም በገነባትም (ጌታ)፤ (5) በምድሪቱም በዘረጋትም፤ (6) በነፍስም ባስተካከላትም፤ (7) አመጽዋንና ፍርሃትዋንም ባሳወቃት (አምላክ እምላለሁ)፡፡ (8) (ከኀጢኣት) ያጠራት ሰው ፍላጎቱን በእርግጥ አገኘ፡፡ (9) (በኀጢኣት) የሸፈናትም ሰው በእወነት አፈረ፡፡ (10) ሠሙድ ወሰን በሚፍዋ አስተባበለች፡፡ (11) ጦሟዋ በተንቀሳቀሰ ጊዜ፡፡ (12) ለእነርሱም የአላህ መልክተኛ (ሷሊሕ) «የአላህን ግመል የጠጥ ተራዋንም (ተጠንቀቁ)» አላቸው፡፡ (13) አስተባበሉትም፡፡ (ቋንጃዋን) ወጓትም፡፡ በኀጢኣታቸውም ምክንያት ጌታቸው (ቅጣትን) በእነርሱ ላይ ደጋመጣቸው፤ አስተካከላትም፡፡ (14) ፍጻሜንም (የምታስከትለውን) አያፈራም፡፡ (15)"

ይህች አጭር ምዕራፍ ልዩ ቃናና የዜማ ስልት ያላት ብቸኛ ምዕራፍ ነች፡፡ ብዙ ተጨባጭ ሂደቶችን ትዳስሳለች፡፡ በፍጥረተ ዓለሙ ያሉ ክስተቶችንና ገፅታዎቹን በመጠቆም ትጀምራለች፡፡ ይህንንም ለሌላኛው ታላቅ እውነታ መሸጋገሪያ በማድረግ ትቀጥላለች፡፡ ምዕራፏ ያካተተችው ቀጣዩ እውነታ ስለ ሰው ልጅ ነፍስና ስለ ተፈጥሯዊ ዝንባሌዋ፣ የሰው ልጅ በነፍሱ ላይ ስላለው ሚናና በፍፃሜዋም ላይ ስላለበት ኃላፊነት ነው፡፡ የምዕራፏ ሂደት ከፍጥረተ ዓለሙ ተጨባጭ ባህሪያትና ቋሚ መገለጫዎች ጋር ያስተሳሰረውም ይህንን የሰው ልጅ

ነፍስ እውነታ ነው፡፡ እንደዚሁም ስለ ሠሙድ ህዝቦችና የመልክተኛቸውን ማስጠንቀቂያ ስለማስተባበላቸው፣ ግመሏን ስለማረዳቸው፣ ከዚያም ስለመጥፋታቸውና ስለመወገዳቸው ታወሳለች፡፡ ይህም ታሪክ ነፍሱን ላላጸዳ፣ ለጥመት ለተዋትና በፍራቻም እንዲትዘወትር ላላደረጋት ሰው እንደማሳያ የቀረበ ነው፡፡

የትምህርቱ ዝርዝር ዓላማዎች

1. የፍጥረተ ዓለሙን ክስተቶችና የሰው ልጅ ነፍስ እውነታዋንና ዝንባሌዋን በምዕራፏ ውስጥ እንደተሳለው እንዲስል ማስቻል፡፡
2. የሰው ልጅ በነፍሱ ጉዳይ የሚኖረውን ሚናና በፍፃሜዋም ላይ ያለበትን ኃላፊነት እንዲገልፅ ማስቻል፡፡
3. ምዕራፏ የጠቀሰቻቸውንና ያመላከተቻቸውን ታሪካዊ ምሳሌዎች እንዲጠቅስ ማስቻል፡፡

(በፀሐይና በብርሃኗ እምላለሁ፡ ጨረቃም በተከተላት ጊዜ) አላህ (ሱ.ወ) በነኝህ ፍጥረታትና ፍጥረተ-ዓለማዊ ክስተቶች ይምላል፡፡ እንደዚሁም በነፍስ፣ ባስተካከላትና ባሳወቃትም ይምላል፡፡ ይህ መሃላ ለእነኝህ ፍጥረታት ትልቅ ዋጋ ያላብሳቸዋል፡፡ ልቦናም ወደዚህ እንድታቀና፣ ምን ዋጋ እንዳላቸውና ምንን እንደሚያስረዱ፣ ልዑልና ታላቅ የሆነው አላህ (ሱ.ወ) ሊምልባቸውስ የተገባው ምን ያህል ደረጃ ቢኖራቸው እንደሆነ እንድታስተነትን ይጋብዛል፡፡

እዚህ ጋር አነቃቂ የሆነውንና በፀሐይና በብርሃኗ የተማለውን መሐላ እናገኛለን… ባጠቃላይ በፀሐይ በራሷና በተለይም ደግሞ ረፋድ ላይ ሆና ከአድማስ ከፍ ስትል፣ ቀጥሎም ጨረቃ በተከተላት ጊዜ፤ በዚያ ማራኪና ለስላሳ እንዲሁም አስደናቂና ጽዱ በሆነው ብርሃኑ ቀንም ፀሐይን ሲከተላት!!

ቀኑ ወገግ ሲል ባለውም ሁኔታም ምሏል፡፡ በእርግጥ ይህ መሃላ ከላይ ከተጠቀሰው ከፀሐይ ሂደት ጋር ይያያዛል፡፡ ነገር ግን እዚህ ላይ ቁርአን ሊገልጸው የፈለገው ‘ቀን’ ማለት የዚች ምድር የሕይወት አስኳል መሆኑን ነው፡፡ ቀኑ

ምድርን ግልጽና ይፋ ያደርጋታል፡፡ ቀን በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ ተፅእኖ እንዳለውም ማንም የሚያውቀው እውነታ ነው፡፡

(በሌሊቱም በሸፈናት ጊዜ) … መሸፈን ከላይ የተጠቀሰው የመጉላት ተቃራኒ ነው፡፡ ሌሊት ሁሉን ነገር የሚያለብስና የሚደብቅ ሽፋን ነው፡፡ ይህም እንዲሁ ትልቅ ማስረጃ ነው፡፡ በሰው ልጅ ሕይወት ላይ ልክ እንደ ቀን እኩል በእኩል ተፅእኖ አለው፡፡

በመቀጠለም በሰማይና በግንባታዎቹ ጥበብ ይምላል፡፡ (በሰሜቱም በገነባትም ጌታ) … ሰማይ የሚለው ቃል ሲነሳ ወደ አእምሯችን ፈጥኖ የሚገባው በየትኛውም አቅጣጫ ብንዞር ይህ ከበላያችን እንደ ቁባ የምናስተውለው፣ ያ ከበላያችን የምናየው በደንብ የተሰካካው፣ የማይዛነፈውና የማይናጋው፤ ይፈርሳልም ብለን የማንሰጋበት፤ በፅናቱና በተያያዥነቱ የግንብን ባህሪ ሙሉ በሙሉ ያሟላ፣ ጽኑና በደንብ የተጣመረ የሆነውን ነው፡፡ እንዴት ተገነባ? የተሠራባቸው ክፍሎችስ በህዋ ላይ እየዋኙ ሳለ እንዳይበታተኑ የያዛቸው ምንድን ነው? የሚለው ጥያቄ እኛ የማናውቀው ጉዳይ ነው፡፡ እርግጠኛ ሆነን የምናውቀው ነገር ቢኖር ከሁሉም ነገር በስተጀርባ የአላህ (ሱ.ወ) እጅ ይህንን ግንብ አጥብቆ እንደሚይዘው ነው፡፡ ይህ ደግሞ እርግጠኛ የሚሆንበት ብቸኛው ዕውቀት ነው፡፡

በመቀጠልም በምድርና በዘረጋት ጌታ ይምላል፡፡ (በምድሪቱም በዘረጋትም) በማለት፡፡ መዘርጋት ማለት ማንጠፍ ወይም ለሕይወት ምቹ ማድረግ ማለት ነው፡፡ ይህ ቋሚ የሆነ ባህሪዋ ሲሆን የሰው ልጅም ሆነ የሌላው ፍጥረት የመኖር ህልውና በእርሷ መኖር ላይ የተንጠለጠለ ነው፡፡ ከዚያም ስለ ሰው ልጅ ነፍስ ታላቅ እውነታ ይቀጥላል፡፡ ከተያያዘውና ከተሰናዳው ፍጥረተ ዓለም ምልክቶች መካከል አንዱ ነው፡፡

(በነፍስም ባስተካከላትም፤ አመጽዋንና ፍርሃቷንም ባሳወቃት፤ [ከኃጢኣት] ያጠራት ሰው ፍላጎቱን በእርግጥ አገኘ፤ [ከኃጢኣት] የሸፈናትም ሰው በውኑ አፈረ፤)

ከነዚህና ከሌሎችም ተመሳሳይ የቁርአን አንቀጾች ማብራሪያ እስልምና የሰውን ልጅ ከመሠረቱ በምን ዓይነት መልኩ እንደሚያየው ግልጽ ይሆንልናል፡፡

ይህ ፍጡር ጥንድ ተፈጥሮ፣ ጥንድ ዝግጅትና ጥንድ አመለካከት ያለው ፍጡር ነው። ጥንድ የሚለው ቃል በግልጽ የሚያመለክተው ትርጓሜ የሰው ልጅ ለመልካምና ለመጥፎ ተግባራት በእኩል መጠን ተዘጋጅቶ የተፈጠረ መሆኑን ነው። ይህም ሲባል የሰው ልጅ ራሱን ወደ መልካምና መጥፎ ነገሮች ማዞር እንደሚችለው ሁሉ በመልካምና በመጥፎ ነገሮች መካከል ያለውን ልዩነት መለየት ይችላል። ይህም ችሎታ በሰው ልጅ ተፈጥሮ ውስጥ ተደብቋል።

ከዚህ መረዳት የምንችለው የሰው ልጅ ይህ ድብቅ የሆነ የዝንባሌ ኃይል መሠረታዊ ባህሪው እንደሆነ ነው። ከፈጣሪ የወረዱ መልእክቶች፣ የደዕዋ ጥሪዎችና ውጫዊ ግፊቶች በሙሉ ይህን በውስጥ ተደብቆ ያለ የዝንባሌ ችሎታ ለመቀስቀስና ወደዚህ ወይም ወደዚያ ሂድ ለማለት የታለሙ ነገሮች ናቸው።

ከዚህ ውስጣዊ ዝንባሌ ጎን ለጎን የሰው ልጅ ማንነቱ የሚገለፅበት አንድ ሌላ መሠረታዊ አቅም አለው። ይህንን አቅም ነፍሱን ለማለምለምና ለማፅዳት፣ ለጥሩ ያለውን ዝንባሌ ለማጎልበትና ለመጥፎ ያለውን ዝንባሌ ለማሸነፍ የተጠቀመበት ሰው በእርግጥ ስኬታማ ይሆናል። በተቃራኒው ይህንን የውስጥ አቅም ያጨለመ፣ የደበቀና ያዳከመ ደግም በእርግጥ ይከስራል።

"ከኃጢኣት ያጠራት ሰው ፍላጎቱን በእርግጥ አገኘ፡ ፡ በኃጢኣት የሸፈናትም ሰው በእርግጥ አፈረ" ጥራት የተገባው አላህ ለሰው ልጅ ካደረገው ርህራሄ አንዱ በውስጥ ዝንባሌው ብቻ ወይም በውስጥ አቅሙ ቁጥጥርና እንቅስቃሴ ሳይተወው ቋሚና ጥልቅ የሆኑ መለኪያዎችን ማስቀመጥ እንዲችል መለኮታዊ ራእዮችን አውርዶለታል። ይህም እምነቱን እንዲያድስ በውስጡና በዙሪያው ያሉትን ጥሩ ነገሮች እንዲገለጹለት ይረዳዋል። በተጨማሪም የስሜት ግርዶሽ ይገፈፍለታል፣ እውነትን በትክክለኛ ገጽታው መመልከት ያስችለዋል።

ይህ ነፍስን የማጥራት ሂደት አጠቃላይ እይታ ሲሆን በተርቢያ አቅጣጫ ትልቅ ግምት ያላቸው ጉዳዮች ከርሷ ይመነጫሉ። እነርሱም

አንደኛ፡ – የሰውን ልጅ ዋጋ እንዲኖረውና ደረጃው ከፍ እንዲል ታደርጋለች። ይህም የሚሄድበትን አቅጣጫ በራሱ መወሰን እንዲችልና የተሰጠውን የመምረጥ ነፃነት አስተውሎ እንዲጠቀምበት ታደርገዋለች።

ምርጫውም ያ ይህንን የመምረጥ ነፃነት በቸረው በአላህ መለኮታዊ ፍላጎት ጥላ ሥር ይሆናል።

ሁለተኛ፡ – የአላህ ፍላጎት እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ ፍጡር የመጨረሻ ፍጻሜው ላይ ትኩረት እንዲያደርግ፣ ይህ ጉዳይ በእርሱ እጅ እንደሆነና በስሜቱም ውስጥ ሁል ጊዜ ንቁ፣ ተጨናቂና ፍራቻ ያደረበት እንዲሆን ታስችለዋለች። በተጨማሪም የአላህ ውሳኔ ተፈጻሚ የሚሆነው እርሱ በራሱ ባደረጋቸው እንቅስቃሴዎች ላይ ተመስርቶ እንደሆነ እንዲያውቅ ታደርገዋለች።

ሦስተኛ፡ – ይህ የሰው ልጅ የጸና ወደ ሆነው መለኮታዊ ሚዛን መመለስ ያለበት ባለጉዳይ መሆኑን እንዲሰማው ታደርጋለች። ይህም በስሜቱ አለመታለሉን እርግጠኛ እንዲሆን፣ መንገድ ያልሳተ መሆኑንና ሰዋዊ ፍላጎቱ ወደጥፋት እየመራው አለመሆኑን እንዲሁም ስሜቱን አምላክ አድርጎ በያዘው ሰው ላይ አላህ የወሰነው ቅጣት በእርሱ ላይ እንዳይደርስበት እንዲጠነቀቅ ታደርገዋለች።

ከዚህ በመቀጠልም ነፍሱን ያረከሳትና ቅኑን መንገድ ጋርዶ ያጨለማት መቋጫው ምን እንደሆነ የሚያሳይ ምሳሌ ያቀርባል።

(ሠሞድ ወሰን በሚሏቷ አስተባበለች፤ ጦሞሞ በተንቀሳቀሰ ጊዜ፡ ፡ ለነርሱም የአላህ ሚልክተኛ [ሷሊሕ] የአላህን ግመል የጣጥ ተራዋንም [ተጠንቀቁ] አላቸው፡ ፡ አስተባበሉትም [ቋንጃዋን] ወጓትም፤ በኃጢኣታቸው ምክንያት ጌታቸው [ቅጣትን] በነርሱ ላይ ደመደማቸው፤ አስተካከላትም ፡)

በርግጥ የሠሙድና የነቢያቸው ሷሊሕ (ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ታሪክ በቁርአን ውስጥ በብዙ ቦታ ላይ ተጠቅሷል። እዚህ ላይ የተጠቀሰው ሠሙዶች ወሰን በማለፋቸው ምክንያት ነቢያቸውን አስተባበሉ። ወሰን ማለፍ ብቻውን ለማስተባበላቸው ምክንያት ሆነ። ይህ ወሰን ማለፍም ከመካከላቸው ጠማማን በማፍራት ይመሰላል። እርሱም ያ ግመሏን ያረዳት ነው። ይህ ግለሰብ ጠማማነቱ የበረታና ከፈጸመው ወንጀል ብዛት ክፋቱ ጫፍ የረገጠ ነው። የአላህ መልዕክተኛ (ሠሙድ) ግመሏን ለመግደል ከመንቀሳቀሳቸው በፊት ግመሏን ከመንካትም ሆነ አላህ ለእርሷ አንድ ቀን ለእናንተ ደግሞ አንድ ቀን ያደረገላችሁን የውሃ ተራ

ከመጣስ ተቆጠቡ በማለትም አስጠንቅቀዋቸዋል፡፡ ይህን ቅድመ መስፈርት ያስቀመጡላቸው ተአምር አሳየን ባሉ ጊዜ እና አላህም ይህችን ግመል በማውጣት ተአምር ባደረገላቸው ጊዜ ነበር፡፡ ማስጠንቀቂያውን አስተባብለው ግመሏን ወጓት፡፡ የወጋትም ያ ጠማማው ነው፡፡ ነገር ግን ሁሉም በጋራ ወንጀሉን ተሸካሚ ሆኑ፡፡ በጋራ እንደወጓትም ተቆጠረ፡፡ ምክንያቱም የወጋትን እጁን ይዘው አላስቆሙትም፡፡ እንዲያውም ተግባሩን ጥሩ ሠራህ ብለው አወድሰውታል፡፡

ይህ ከእስልምና አንኳር መርሆች ተጠቃሽ የሆነ በዱንያ ሕይወት ውስጥ በማኅበራዊ ትስስር ላይ ያተኮረ መርህ ነው፡፡ ይህ ከግለሰባዊ ተጠያቂነትና በአኼራ ከሚከፈለው ምንዳ ጋር የማይቃረን መርህ ነው፡፡ አንዱ የሌላኛውን ወንጀል ተሸካሚ አይሆንምና፡፡

በዚህን ጊዜ የኃይል ባለቤት የሆነው የታላቁ አምላክ እጅ ተንቀሳቀሰች፡፡ (በኃጢኣታቸው ምክንያት ጌታቸው [ቅጣትን] በነርሱ ላይ ደጋግማቸው፤ አስተካከላትም) ... ቁጣውና ያስከተለው ብቀላ ተፈጸመባቸው፡፡ **ደመደመ** የሚለው ቃል በራሱ ከበስተጀርባ ያለውን አመላካች ነው፡፡ አላህ ምድራቸውን የላዩን ወደታች በመገልበጥ አስተካከላት፡፡

(ፍጻሜንም አይፈራም) ... ለኃያሉ አምላክ ጥራት ይገባው!! በርግጥስ ማንን ይፈራል? ከምንስ ጉዳይ ይፈራል? መቼስ ይፈራል? ከዚህ ገለጻ የተፈለገው ዘውታሪ የሆነውን ግንዛቤ ነው፡፡ ይህም በሚያደረገው ተግባር ውጤት ማንንም የማይፈራ የሆነው አምላክ በተቆጣ ጊዜ ድንበር የለሽ ቁጣውን ሊያሳርፍ እንደሚችል ነው፡፡ በርግጥም የአላህ ቁጣ እንደዚህ ነው፡፡ በርግጥ የአላህ አያያዝ ብርቱ ነው፡፡

የመጨረሻ ጥያቄዎች

1. በምዕራፏ የተገለጸውን የፍጥረተ ዓለሙን ክስተቶችና የሰው ልጅ ነፍስ እውነታዋንና ዝንባሌዋን አሳይ፡፡
2. የሰው ልጅ በነፍሱ ጉዳይ የሚኖረውን ሚናና በፍፃሜዋም ላይ ያለበትን ኃላፊነት ግለጽ፡፡

3. አንቀጾቹ የስኬትንና የውድቀትን መንገዶች አመላክተዋል። ከሁለቱ የትኛውን መንገዶች መካከል የትኛውን መንገድ ትመርጣለህ? ይህን መንገድ ለመከተል የምትታገዝባቸው ዘዴዎች ምን ምን ናቸው?

4. ምዕራፏ የጠቀሰቻቸውንና ያመላከተቻቸውን ታሪካዊ ምሳሌዎች ጥቀስ።

سورة الليل

(የሌሊት ምዕራፍ)

﴿ وَٱلَّيۡلِ إِذَا يَغۡشَىٰ ١ وَٱلنَّهَارِ إِذَا تَجَلَّىٰ ٢ وَمَا خَلَقَ ٱلذَّكَرَ وَٱلۡأُنثَىٰٓ ٣ إِنَّ سَعۡيَكُمۡ لَشَتَّىٰ ٤ فَأَمَّا
مَنۡ أَعۡطَىٰ وَٱتَّقَىٰ ٥ وَصَدَّقَ بِٱلۡحُسۡنَىٰ ٦ فَسَنُيَسِّرُهُۥ لِلۡيُسۡرَىٰ ٧ وَأَمَّا مَنۢ بَخِلَ وَٱسۡتَغۡنَىٰ ٨
وَكَذَّبَ بِٱلۡحُسۡنَىٰ ٩ فَسَنُيَسِّرُهُۥ لِلۡعُسۡرَىٰ ١٠ وَمَا يُغۡنِي عَنۡهُ مَالُهُۥٓ إِذَا تَرَدَّىٰٓ ١١ إِنَّ عَلَيۡنَا لَلۡهُدَىٰ ١٢
وَإِنَّ لَنَا لَلۡأٓخِرَةَ وَٱلۡأُولَىٰ ١٣ فَأَنذَرۡتُكُمۡ نَارٗا تَلَظَّىٰ ١٤ لَا يَصۡلَىٰهَآ إِلَّا ٱلۡأَشۡقَى ١٥ ٱلَّذِي كَذَّبَ
وَتَوَلَّىٰ ١٦ وَسَيُجَنَّبُهَا ٱلۡأَتۡقَى ١٧ ٱلَّذِي يُؤۡتِي مَالَهُۥ يَتَزَكَّىٰ ١٨ وَمَا لِأَحَدٍ عِندَهُۥ مِن نِّعۡمَةٖ تُجۡزَىٰٓ
١٩ إِلَّا ٱبۡتِغَآءَ وَجۡهِ رَبِّهِ ٱلۡأَعۡلَىٰ ٢٠ وَلَسَوۡفَ يَرۡضَىٰ ٢١ ﴾ الليل: ١ - ٢١

"በሌሊቱ እምላለሁ (በጨለማው) በሚሸፍን ጊዜ፡፡ (1) በቀኑም በተገለጸ ጊዜ፡፡ (2) ወንድንና ሴትን በፈጠረውም (አምላክ እምላለሁ)፡፡ (3) ሥራችሁ በእርግጥ የተለያየ ነው፡፡ (4) የሰጠ ሰውማ ጌታውን የፈራም፡፡ (5) በሚልካሚዟም (እምነት) ያረጋገጠ፤ (6) ለገሪቱ ሥራ እናዘጋጀዋለን፡፡ (7) የሰሰተ ሰውማ የተብቃቃም፤ (በራሱ የተመካ)፤ (8) በሚልካሚዟ (እምነት) ያሰተባበለም፤ (9) ለክፉይቱ ሥራ እናዘጋጀዋለን፡፡ (10) በወደቀም ጊዜ ገንዘቡ ከእርሱ ምንም አይጠቅመውም፡፡ (11) ቅኑን መንገድ መለጽ በእኛ ላይ አለብን፡፡ (12) ሚጨሻይቱም መጀመሪያይቱም ዓለም የእኛ ናቸው፡፡ (13) የምትንቀለቀልንም እሳት አስጠንቀቅኳችሁ (በላቸው)፡፡ (14) ከጦማ በቀር ሌላ የሚገባት የኾነችን፡፡ (15) ያ ያስተባበለና ከትዕዛዝ የሸሸው፡፡ (16) አላህን በጣም ፈሪውም በእርግጥ ይርቃታል፡፡ (17) ያ የሚጥራራ ኾኖ ገንዘቡን (ለድኾች) የሚሰጠው፡፡ (18) ለአንድም ሰው እርሱ ዘንድ የምትመለስ ወለታ የለችም፡፡ (19) ግን

የታላቅ ጌታዉን ወዴታ ለሜለግ (ይህንን ሠራ)፡፡ (20) ወደፊትም በእርግጥ ይደሰታል፡፡ (21)"

የትምህርቱ ዝርዝር ዓላማዎች

1. ምዕራፏ ባስቀመጠች መልኩ በፍጥረተ ዓለሙና እንዲሁም በሰዎች ዘንድ የሚገለጹ ተቃራኒ እውነታዎችን እንዲስል ማስቻል።

2. የሰው ልጅ በነፍሱ ጉዳይ የሚኖረውን ሚናና በፍፃሜዋም ላይ ያለበትን ኃላፊነት እንዲገልፅ ማስቻል።

3. የገሩን መንገድና የጥሙቱን መንገድ እንዲሁም በነዚህ መንገዶች የሚጓዙ ተጓዦች ተግባርና መጨረሻ እንዲስል ማስቻል።

4. እድለ-ቢስ ማን እንደሆናና ጥንቁቅ ማን እንደሆነ፣ እንደዚሁም እነኝህ ሰዎች መጨረሻቸው ምን እንደሆነ እንዲያያብራራ ማስቻል።

(በሌሊት እምላለሁ [ጨለማው] በሚሸፍን ጊዜ፤ በቀኑም በተገለጸ ጊዜ፤ ወንድና ሴትን በፈጠረውም [አምላክ እምላለሁ])

ጥራት የተገባው አላህ በነዚህ ሌሊትና ቀን በተሰኙት ሁለት ተአምራት ይምላል።... ሌሊቱ በስፋት በሚሸፍንበትና በጨለማው ሁሉ ነገር በሚዋጥበት ክስተት፣ ቀኑ ደግሞ ግልጽ ሆኖ በሚወጣበትና ድብቁ ሁሉ ይፋ በሚሆንበት። እነኝህ ሁለት ክስተቶች በሥነ-ፈለኩ ዘውግ ውስጥ የሚስተዋሉ ተቃራኒ ኩነቶች ናቸው። እንደዚሁም በሰው ልጅ ዘንድ ሁለት ተቃራኒ ፆታዎች እንዲኖሩ አድርጎ በመፍጠሩ ይምላል። (ወንድና ሴትን በፈጠረውም) በማለት።... የተቃርኖ መገለጫው እውነታ በሁሉም ላይ የተሟላ ይሆን ዘንድ። አላህ (ሱ.ወ) በእነኝህ በዩኒቨርሱና በሰው ልጅ ላይ በሚገለጹ የተቃርኖ እውነታዎች በመማል ሌላ እውነታን ይፋ ያደርጋል፤ ይኸውም ሰዎች የሚለያዩበት ጉዳይ የተለያየ እንደሆነና መንገዳቸውም እንደሚለያይ፣ ምንዳቸውም እንዲሁ እንደሚለያይ ይገልጻል።

(ሥራችሁ በእርግጥ የተለያየ ነው። የሰጠ ሰውም ጌታውን የፈራም፤ በሚልካሚኑም [እምነት] ያረጋገጠ፤ ለገሪቱ ሥራ እናዘጋጀዋለን። የሰሰተ ሰውም የተብቃቃም [በራሱ የተመካ]፤ በሚልካሚኑ [እምነት] ያስተባበለም፤ ለክፉይቱ ሥራ እናዘጋጀዋለን። በወደቀም ጊዜ ገንዘቡ ከእርሱ ምንም አይጠቅመውም)

የምትለፋበት ነገር (ሩጫህ) የተለያየ ነው፡ በእርግጥም እውነታው የተለያየ ነው፡፡ እንድንሠራው ከውስጥ የሚቀሰቅሰንም ነገር የተለያየ ነው፡፡ አቅጣጫውም የተለያየ ነው፡፡ ውጤቱም እንደዚሁ የተለያየ ነው፡፡ በዚህች ምድር ያሉ ሰዎች ባህሪያቸው የተለያየ ነው፡፡ እይታቸውም ይለያያል፡፡ የሚያሳስባቸውም ጉዳይ ይለያያል፡፡ ይህ ታላቅ እውነታ ነው፡፡ ነገር ግን ከዚህ ያለፈ ሌላ እውነታ አለ፡፡ ይህ እውነታ ሁሉንም የሰው ልጆች ያጠቃለለ የጋራ እውነታ ነው... ይህ እውነታ ሰዎችን ወደ ሁለት ትልልቅ ምድቦች ይከፍላቸዋል፤ ሁለት ተቃራኒ ጐራዎችና አጠቃላይ በሆኑ ሁለት ምድቦች ሥር፡ (የሰጠ፣ ጌታዋን የፈራ፤ በሚልካሚኡም [እምነት] ያረጋገጠ) እና (የሰሰተ፣ የተቧቃቃ[በራሱ የተማካ]፤ በሚልካሚኡ [እምነት] ያስተባበለ)፡፡ ነፍሱንና ገንዘቡን የሰጠ፣ የአላህን ቁጣና ቅጣቱን የፈራ፣ በዚህች እምነትም እውነት ብሎ ያረጋገጠ የመጀመሪያው ጐራ ነው፡፡ ‘ሑስና’ የሚለው የዐረብኛ ቃል ለዐቂዳ የተሰጣት ስያሜ ሲሆን እርሷንም ጠንቅቆ ማወቅን ያካተተ ነው፡፡

በነፍሱና በገንዘቡ የሰሰተ፣ ከአላህና ከቀጥተኛ መንገዱ ቢቃኝ ብሎ በራሱ የተመካው ደግሞ ሌላኛው ጐራ ነው፡፡ ሑስናንም (እምነትንም) አስተባብሏል፡፡ እንግዲህ እነኝህ ሁለት ትልልቅ ጐራዎች ሲሆኑ እያንዳንዱ ጐራ የተለያዩ የነፍስ ዓይነቶችን፣ የተለያዩ ሩጫዎችን (ልፋቶችን)፣ የተለያዩ የሕይወት መመሪያዎችን፣ የተለያዩ ግቦችን ያካትታል፡፡ ለሁሉም ምድቦች በዚህች ሕይወት ውስጥ የራሳቸው የሆነ መንገድ አላቸው፡፡

(የሰጠ ሰውዬ ጌታውን የፈራም፤ በሚልካሚኡም [እምነት] ያረጋገጠ፤ ለገሪቱ ሥራ እናዘጋጀዋለን)

ያ የሰጠ፣ የተጠነቀቀ፣ እምነትንም እውነት ያለ! በርግጥ ይህ ሰው ነፍሱን ለማጽዳትና ቅኑን ጎዳና ለመከተል አቅሙ የፈቀደውን ያህል ጥረት አድርጓል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም ይህ ሰው አላህ በፍላጎቱና በፍቃዱ በራሱ ላይ ግዴታ ላደረገው እገዛና ችሮታ ባለመብት ይሆናል፡፡ አላህ ያገራለት ሰው ደግሞ በርግጥ ካሰበው ይደርሳል፡፡ በገሪቱም ሕይወት ውስጥ (ሳይጨናነቅ) ይኖራል፡፡ ለራሱም ሆነ በዙሪያው ላለ ሁሉ ገርነትን ይለግሳል፡፡ እርምጃውም ገር ይሆናል፡፡ መንገዱም ገር ይሆናል፡፡ ነገሮችንም በሙሉ ሲያስተናግድ ገር ይሆንለታል፡፡

(የሰሰተ ሰወሜ የተቢቃቃም [በራሱ የተመካ]፤ በሚኳካሚ [እምነት] ያስተባበለምፂ ለክፉይቱ ሥራ እናዘጋጀዋለን፡፡ በወደቀም ጊዜ ገንዘቡ ከእርሱ ምንም አይጠቅመውም)

ያ በነፍሱም በሕይወቱም የሰሰተ ሰው፣ ከጌታው እገዛና መቀናት በቃኝ ያለና የሚደረግለትን ጥሪና እንዲሁም ዲኑን ያስተባባለ በእርግጥ ነፍሱን ለጥፋት ቁንጮ ይዳርጋታል፡፡ በዚህም አላህ ሁሉ ነገሩን ከባድ ሊያደርግበት ይገባዋል፡፡ ለችግርም ያጋፍጠዋል፡፡ ገርነት የተባለ ሁሉ በርሱ ላይ እርም ይሆናል፡፡ እያንዳንዱ እንቅስቃሴው በችግርና በጭንቀት ይሞላል፡፡ በዚህም ከቅኑ መንገድ ያፈነግጣል፡፡ ወደ ጥመት ጎዳና ይንጠላጠላል፡፡ በዚህ ሁኔታ ወደ ጌታው ሲመለስም ከመጨረሻው አስከፊ ችግር ውስጥ ይወድቃል፡፡ በዚህ ወቅት ያ የሰሰተው ገንዘቡ አይጠቅመውም፡፡ ከአላህና ከመመሪያው ሲብቃቃ የነበረውም እንዲሁ አያዋጣውምፂ (ገንዘቡ ከእርሱ ምንም አይጠቅመውም) ለተንኮልና ለወንጀል የተገራ መሆኑ ለችግር መገራት ማለት ነው፡፡ እንዲያው በዚህች ምድር ስኬታማ ቢሆን እንኳ ከጀሀነም የከፋ አስቸጋሪ ነገር አለን? እርሷ በርግጥ የከፋችው ችግር ናት!!

ሁለተኛው ክፍል ስለ እነኝህ ምድቦች የመጨረሻ ሁናቴ ይናገራል፡፡ የጉዟቸው ፍፃሜ ምን እንደሆነም ይፋ ያደርጋልፂ ለመልካም ለተገራውም፣ ለችግር ለተገራውም፡-

(ቅኑን መንገድ መገለጽ በእኛ ላይ አለብን፡፡ ሜጪሻይቱም መጀመሪያይቱም ዓለም የኛ ናቸው፡፡የምትንቀለቀልንም እሳት አስጠንቀቅኳችሁ [በላቸው]፡፡ ከጦምባ በቀር ሌላ የሜዛባት የሆነችን፡፡ ያ ያስተባበለና ከትእዛዝ የሸሸው፡ አላህን በጣም ፈሪወም በእርግጥ ይርቃታል፡፡ ያ የሚራራ ኾኖ ገንዘቡን [ለድኾች] የሚሰጠው፡ ለአንድም ሰው እርሱ ዘንድ የምትሚለስ ወለታ የለችም፡ ግን የታላቅ ጌታውን ወዴታ ለሜለግ፣ (ይህንን ሥራ)፡፡ ወደፊትም በእርግጥ ይደሰታል፡፡)

አላህ (ሱ.ወ) ለባሮቹ ባለው እዝነትና ትሩፋት ቅኑን መንገድ ሊገልፅላቸውና ሊያስገነዝባቸው እንዲሁም መልክተኞችንና መልእክቱን በመላክ ሊያብራራላቸው በራሱ ላይ ደነገገ፡፡ ለአንድም ሰው አልተብራራልኝም የሚል መከራከሪያ የለውም፡፡ ማንም ሰው ብዥታ ውስጥ (ጨለማ) ነኝ ሊል አይችልም፡፡ (ቅኑን መንገድ

መገለጽ በእኛ ላይ አለብን)፡፡ ቀጥሎ ያለው እውነታ የሚያስረዳው የሰውን ልጅ አካቦ የያዘውን ቁርጠኛ ጉዳይ ነው፡፡ ከርሱም ውጭ ሌላ መጠጊያን አያገኙም፡፡ (ሜጪሻይቱምᵡ መጂሚያይቱም ዓለም የኛ ናቸው)፡፡ ከአላህ ርቆ መሄድ የፈለገ ወደየትስ ሊሄድ ይችላል? የማካበቡ ቅርንጫፍ የሆነችውን ሌላ እውነታን ያስታውሳቸዋል፡፡ አስጠንቅቄያችኋለሁ፣ ግልፅ አድርጌላችኋለሁ በማለት፡፡ (የምትንቀለቀልንም እሳት አስጠ ቀቅኳችሁ)... መቀጣጠሏ ይጨምራል... ይህች የምትጋጋም እሳት (ከጦማ በቀር ሌላ አይገባባትም)... ከባሮች ሁሉ የመጨረሻ ጠማማው ..ከዚያም ጠማማ የተባለው ማን እንደሆነ ያብራራል፡፡... እርሱ (ያ ያስተባበለና ከትእዛዝ የሸሸው) ነው፡፡ ጥሪውን አስተባበለ፣ ከእርሷም ዞረ፡፡ ከቅኑ መንገድ ሸሸ፡፡ ከጌታው ለሚደረግለት ጥሪም እንቢ አለ...እርሱን ፈልጎ ለሚመጣ ሁሉ ቃል በገባው መሠረት ሊመራው (ሲጠራው አሻፈረኝ አለ፡፡)

(አላህን በጣም ፈሪውም በእርግጥ ይርቃታል)... ይህ የዕድለ-ቢስነት ተቃራኒ የሆነ ደስታ ነው... ከዚያም ጥንቁቅ (አላህን ፈሪ) ማን እንደሆነ ያብራራል... (ያ የሚጥራራ ኾኖ ገንዘቡን [ለድኾች] የሚሰጠው)... ያ በመስጠቱ ራሱን ሊያጸዳ ፈልጎ ገንዘቡን የሚለግሰው...ሲሰጥም ለይዩልኝ ወይም ቸር ለመባልና ራሱን ከሰው በላይ ለማድረግ ያልሆነው... የሚሰጠው በፍላጎት እንጅ ከማንም ሙገሳን ወይም ከማንም ምስጋናን ፈልጎ አይደለም፡፡ የእርሱ ፍላጎት የልዑል-ጌታውን ውዴታ ማግኘት ብቻ ነው፡፡... (ግን የታላቅ ጌታዉን ወዴታ ለሜለግ)... ከዚያስ? ይህ ጥንቁቅና አላህን ፈሪ ምን ይጠብቀው ይሆን? ያ ገንዘቡን ለመጥራራት ገንዘቡን ወጪ የሚያደርገው፣ የታላቅ ጌታውን ውዴታ ፈልጎ? ቁርአን ለዚህች አማኝ ሩሕ የተዘጋጀላትን ይፋ ያደረገው ነገር አስገራሚ፣ ድንገተኛና ያልተለመደ ነው፡፡... (ወደፊትም በእርግጥ ይደሰታል)... እርሱ በርግጥ በዚያ ጥንቁቅ ሰው ልብ ላይ የሚያርፍ ደስታ ነው፡፡ ሩሑን የሚያጥለቀልቅ ደስታ! መላ ሰውነቱን በደስታ የሚሞላ! በሁለመናው የደስታ ብርሃን! ሕይወቱን በሙሉ በደስታ የሚያሸበርቅ!... ምን ዓይነት ምንዳ ነው!! ምን አይነት ታላቅ ጸጋ ነው!! እርሱ በርግጥ ከአላህ በስተቀር ማንም ሊሰጠው የማይችል የሆነ ምንዳ ነው፡፡

የመጨረሻ ጥያቄዎች

1. ምዕራፉ ባስቀመጠው መሠረት በፍጥረተ ዓለሙና እንዲሁም በሰዎች ዘንድ የሚገለጹ ተቃራኒ እውነታዎችን አሳይ።

2. የሰው ልጅ በነፍሱ ጉዳይ የሚኖረውን ሚናና በፍፃሜዋም ላይ ያለበትን ኃላፊነት ግለፅ።

3. የገሩን መንገድና የጥመቱን መንገድ እንዲሁም በነዚህ መንገዶች የሚጓዙ ተጓዦች ተግባርና መጨረሻ ግልፅ አድርግ።

4. እድለ-ቢስ (ጠማማ) ማን እንደሆናና ጥንቁቅ (አላህን ፈሪ) ማን እንደሆነ፣ እንደዚሁም እነኝህ ሰዎች ተግባራቸው ምን እንደሆነና መጨረሻቸውስ ምን እንደሆነ ግለፅ።

5. ሁለቱን መንገዶች ከተረዳህና ሁለቱን ጐራዎች ካወቅክ በኋላ የትኛውን ምድብ እንደምትመርጥና ይህን ምድብ ለመቀላቀል ምን ተግባር ለመፈጸም እንዳሰብክ ግለፅ።

سورة الضحى

(የረፋዱ ምዕራፍ)

﴿ وَٱلضُّحَىٰ ﴿١﴾ وَٱلَّيۡلِ إِذَا سَجَىٰ ﴿٢﴾ مَا وَدَّعَكَ رَبُّكَ وَمَا قَلَىٰ ﴿٣﴾ وَلَلۡأٓخِرَةُ خَيۡرٞ لَّكَ مِنَ ٱلۡأُولَىٰ ﴿٤﴾ وَلَسَوۡفَ يُعۡطِيكَ رَبُّكَ فَتَرۡضَىٰٓ ﴿٥﴾ أَلَمۡ يَجِدۡكَ يَتِيمٗا فَـَٔاوَىٰ ﴿٦﴾ وَوَجَدَكَ ضَآلّٗا فَهَدَىٰ ﴿٧﴾ وَوَجَدَكَ عَآئِلٗا فَأَغۡنَىٰ ﴿٨﴾ فَأَمَّا ٱلۡيَتِيمَ فَلَا تَقۡهَرۡ ﴿٩﴾ وَأَمَّا ٱلسَّآئِلَ فَلَا تَنۡهَرۡ ﴿١٠﴾ وَأَمَّا بِنِعۡمَةِ رَبِّكَ فَحَدِّثۡ ﴿١١﴾ ﴾ الضحى: ١ - ١١

"በረፋዱ እምላለሁ፡ (1) በሌሊቱም ጸጥ ባለ ጊዜ፤ (2) ጌታህ አላሰናበተህም፤ አልጠላህምም፡ (3) ሚጪሻይቱም(ዓለም) ከመጀሚያይቱ ይልቅ ላንተ በላጭ ናት፡፡ (4) ጌታህም ወደ ፊት (ብዙን ስጦታ) በእርግጥ ይሰጥሃል፡፡ ትደሰታለህም፡ (5) የቲም ኾነህ አላገኘህምና አላስጠጋህምን? (አስጠግቶሃል)፡፡ (6) የሳትክም ኾነህ አገኘህ ሚሁህም፡ (7) ድኻም ኾነህ አገኘህ፤ አከበረህም፡ (8) የቲምን ማ አትጨቁን፡፡ (9) ለማኝንም አትገላምጥ፡፡ (10) በጌታህም ጸጋ አወራ፤ (ግለጻት)፡፡ (11)"

የትምህርቱ ዝርዝር ዓላማዎች

1. ይህች ምዕራፍ ለአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) አካታ የያዘችውን ደስታና መፅናኛ እንዲገልጽ ማስቻል፡፡
2. አላህ (ሱ.ወ) ለመልክተኛው ከእርሳቸው በኋላ ላለው ህዝባቸው በምዕራፏ መጨረሻ ላይ ያስቀመጠውን አቅጣጫ እንዲጠቅስ ማስቻል፡፡

ይህች ምዕራፍ በርእሷና በአገላለጿ እንዲሁም በትእይንቷ የእዝነት ዳበሳ ናት! የታመመና በውጋት የቆሰለ ልቦናን በርህራሄ የምትዳስስ እጅ! ቅዝቃዜን፣ መረጋጋትንና እርግጠኝነትን ታፈሳለች! ሁለመናዋ ለነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ) የታሰበችና ከጌታቸው የተቸረች እዝነት፣ ደስታና መፅናኛ፡፡

(በረፋዱ እምላለሁ፣ በሌሊቱም ጸጥ ባለ ጊዜ፡፡)

አላህ (ሱ.ወ) ታላቅ ድምጸትና ጉልህነትን ባዘሉ ሁለት ተጨባጭ ክስተቶች በመማል ይጀምራል። በዚህም የፍጥረተ-ዓለሙን ገፅታ ከነፍስ ስሜት ጋር ያስተሳስረዋል! ያ የሰው ልጅ ልብም ከዚህ ተፈጥሯዊ ሁኔታ ጋር በአብሮነት ስሜት ይኖራል። ባይተዋርነት ወይም እንግዳነት አይሰማውም! በተለይም ደግም በዚህች ምዕራፍ ይህ ክስተት መገለፁ የብቸኝነትን ጥላ ለመግፈፍ የታለመ ነው! የአብሮነት ስሜትን ማስረፅ ዋነኛ ዓላማው ነው።

ይህንን ተፈጥሯዊ ክንዋኔ ተከትሎ የሚመጣው የቀጥታ ማረጋገጫም ይህ ነው፡- (ጌታህ አላሰናበተህም፤ አልጠላህምም) ጌታህ አልተወህም፣ አላራቀህም! ነፍስህ እንድትጨናነቅ፣ ልብህ እንድትቆስልና ህሊናህ እንዲዋልል የፈለጉ ጠላቶችህ እንደሚሞግቱት አይደለም። የፀጋው ምንጭም ሆነ የቸሮታው ፍሰት አልቀነሰም። በመጨረሻው ዓለምም ላንተ ከርሱ ዘንድ መልካም ነገር አለህ። ይህም በዱንያ ከቸረህ ጸጋ ይበልጡን የተሻለ ነው። (ሜጪሻይቱም [ዓለም] ከመጅሚያይቱ ይልቅ ላንተ በላጭ ናት)... መጀመሪያውም ሆነ መጨረሻው ጥሩ የሆነ.. እርሱ በርግጥ የሚያስደሰትህን ነገር ያከማችልሃል። ለጥሪህ (ደዕዋህ) ተሰሚነትን ይገጥምሃል። ከመንገድህ እንቅፋትን ያነሳልሃል፣ መመሪያ መንገድህ አሸናፊ ይሆናል፣ እውነታህ ይፋ ይወጣል። እነኝህ ጉዳዮች በወቅቱ መልክተኛውን (ሰ.ዐ.ወ)ሲያስጨንቁ የነበሩበት ሁኔታ ነበር። ይህ ጊዜ ነቀፌታን፣ ማስተባበልን፣ መከራን፣ ስድብን ተንኮልን የተጋፈጡበትም ወቅት ነበር፡- (ጌታህም ወደ ፊት [ብዙ ስጦታን] በእርግጥ ይሰጥሃል) ያላቸው።

(የቲም ኾነህ አላገኘህምና አላስጠጋህምን? የሳትክም ሆነህ አገኘህ፤ መራህም፡ ድኸም ሆነህ አገኘህ፤ አከበረህም)

አሁን ያለህበትንና ያለፈውን ሁኔታህን አስተውል።..ጌታህ አሰናብቶሃልን? አርቆሃልን? በዚህ ቃል-ኪዳን እስከሚያበስርህስ ድረስ ትቶሃልን? የቲምነትህ እንክብካቤውን አታስታውስህምን? ስህተት ላይ የነበርክበት ቅናቻውን አታስገነዝብህምን? ድህነትህ በቸሮታው አልተሸፈነችምን? የቲም ኾነህ ተወለድክ-ወደ እርሱም አስጠጋህ፣ በሃይማኖትህ ላይ ባልነበረበት እንኳን የአጎትህን የአባ ጣሊብን ልቦና እንድትራራ አገደረገልህ። ድሃም ነበርክ -አላህ ነፍስህን እንድትብቃቃ አደረጋት፣ የልፋትህን ውጤትና የቤተሰቦችህን ገንዘብ በረከት

በመቸር ድህነት እንዳይሰማህና በዙሪያህ ያሉ ሀብታምች ላይ ልብህ እንዳይንጠለጠል አደረገህ፡፡ እይታዎችና እምነቶች በድንቁርና አረንቋ ውስጥ በተዘፈቁበት ማኅበረሰብ አደግክም-ከዚያም አላህ በዚያ ባንተ ላይ ባወረደው ጉዳይ መራህም፤ የምትጓዝበትን መመሪያ ለገሰህም፡፡ ጌታው እርሱን የቲም ሆኖ እንደተንከባከበው፣ ስህተት ላይ ሳለ ቅኑን መንገድ እንደመራውና በድህነት ላይ ሳለ እንዳብቃቃው በጠቀሰበት አጋጣሚ መልክተኛውም ሆነ ተከታዮቹ ሙስሊሞች የቲሞችን ሁሉ እንዲንከባከቡ አቅጣጫ ሰጥቷል፡፡ የተቸገረን ሁሉ መርዳት እንዳለባቸው፣ አላህ በእነርሱ ላይ ያፈሰሰውን ፀጋ እንዳስታውሱና በተለይም ከጸጋዎች ሁሉ የመጀመሪያ ተጠቃሽ የሆነውን ለዚህ ዲን መመራታቸውን እንዲያስተነትኑና እንዲያመሰግኑት አመላክቷል፡፡

(የቲምንማ አትጨቁን፡፡ ለማኝንም አትገላምጥ፡፡ በጌታህም ጸጋ አውራ፤ [ግለጻት])

ይህ አንቀጽ የቲሞችን መንከባከብ አስፈላጊ መሆኑን፣ በእነርሱ ላይ የበላይ መሆን፣ ቅስማቸውን መስበርና አሳንሶ ማየት ክልክል እንደሆነና የተቸገሩ ለማኞችንም በርህራሄና በክብር አይን በማየት መርዳት እንደሚያስፈልግ አቅጣጫ ያስይዛል፡፡ በእርግጥ ይህች ትእዛዝ የመጣችበት ጊዜ ደካሞች ተመልካች ያጡበትና መልካምነት የጠፋበት፣ እንዲሁም ስስት የነገሰበት ብሎም ጉልበት ያለው በሰይፉ ካልሆነ በስተቀር መብቱንና ንብረቱን ማስከበር የማይችልበት መጥፎ ወቅት ነበር፡፡

የአላህን ጸጋ በተለይም ሂዳያንና (ለዲኑ መመራትንና) ኢማንን በየጊዜው ማስታወስ እጅጉን አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ ተግባር ጸጋውን ለሚያጎርፈው፣ በባሮቹ ላይ በደግነቱ ለሚያፈሰው አካል በተግባር የሚገለፅ አንዱ የምስጋና ገጽታ ነው፡፡

የመጨረሻ ጥያቄዎች

1. ምዕራፏ ለመልክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) አካታ የያዘችውን ደስታና መፅናኛ አብራራ፡፡
2. አላህ (ሱ.ወ) ለመልክተኛውና ከእርሳቸው በኋላ ላለው ህዝባቸው በምዕራፏ መጨረሻ ላይ ያስቀመጠውን አቅጣጫ ጥቀስ፡፡

ምዕራፍ ሁለት

የተከበረው ሐዲሥ

ስድስተኛው ሐዲስ

ሐላልና ሐራም

عَنْ أَبِي عَبْدِ اللَّهِ النُّعْمَانِ بْنِ بَشِيرٍ رَضِيَ اللَّهُ عَنْهُمَا، قَالَ: سَمِعْت رَسُولَ اللَّهِ صلى الله عليه وسلم يَقُولُ: "إنَّ الْحَلَالَ بَيِّنٌ، وَإِنَّ الْحَرَامَ بَيِّنٌ، وَبَيْنَهُمَا أُمُورٌ مُشْتَبِهَاتٌ لَا يَعْلَمُهُنَّ كَثِيرٌ مِنْ النَّاسِ، فَمَنْ اتَّقَى الشُّبُهَاتِ فَقَدْ اسْتَبْرَأَ لِدِينِهِ وَعِرْضِهِ، وَمَنْ وَقَعَ فِي الشُّبُهَاتِ وَقَعَ فِي الْحَرَامِ، كَالرَّاعِي يَرْعَى حَوْلَ الْحِمَى يُوشِكُ أَنْ يَرْتَعَ فِيهِ، أَلَا وَإِنَّ لِكُلِّ مَلِكٍ حِمًى، أَلَّا وَإِنَّ حِمَى اللَّهِ مَحَارِمُهُ، أَلَّا وَإِنَّ فِي الْجَسَدِ مُضْغَةً إذَا صَلَحَتْ صَلَحَ الْجَسَدُ كُلُّهُ، وَإِذَا فَسَدَتْ فَسَدَ الْجَسَدُ كُلُّهُ، أَلَا وَهِيَ الْقَلْبُ". رَوَاهُ الْبُخَارِيُّ وَمُسْلِمٌ

ከአቢ ዐብዲላህ ኑዕማን ኢብኑ በሺር (ረዐ) እንደተወራው፦ – የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ)፣ ‹‹ሐላል ግልጽ ነው፡፡ ሐራምም ግልጽ ነው፡፡ በመካከላቸው ብዙ ሰዎች የሚወቋቸው አሻሚ ነገሮች አሉ፡፡ አሻሚ ነገሮችን የተጠነቀቀ ለሃይማኖቱና ለክብሩ መጦራትን ፈለገ፡፡ አሻሚ ነገሮች ወስጥ የወደቀ ሐራም ላይ ወደቀ፡፡ ልክ (ጥበቅ) ድንበር ዙርያ እንደሚጠግድ እረኛ ነው፡፡ (ይህ ሰው) የድንበሩን ክልል አልፎ ሊያስግጥ እንደማቅርብ፡፡ አዋጅ ! በርግጥ ለሁሉም ንጉስ ድንበር አለው፡፡ አዋጅ! የአላህ ድንበር (እርሱ) እርም ያደረገው ነገር (ሁሉ) ነው፡፡ አዋጅ! ሰውነት ወስጥ (አንዲት) ቁራጭ ሥጋ አለች፡፡ እርሷ ከተስተካከለች አካል በሙሉ ተስተካከለ፡፡ እሷ ከተበላሸችም አካል በሙሉ ተበላሸ፡፡ አዋጅ! እርሷም ልብ ናት›› ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ ብለዋል፡፡ (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)

የትምህርቱ አላማ

1. በሐላል፣ በሐራምና በአሻሚ ነገሮች መካከል ያለውን ልዩነት ማብራራት እንዲችል ማስቻል፡፡
2. ሐራም ማለት ምን ማለት እንደሆነ ማብራራት እንዲችል ማስቻል፡፡

3. አሻሚ ነገሮች (ሙሽተቢሃት) ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንዲያብራራ ማስቻል።
4. አሻሚ ነገሮች ያጋጠሙት ሰው ምን ማድረግ እንዳለበት እንዲያብራራ ማስቻል።
5. የሰው ልብ አካል ውስጥ ያለውን ሥፍራ እንዲያብራራ ማስቻል።
6. ሐዲሱ ወዴት እየተጣራ እንደሆነ እንዲያብራራ ማስቻል።
7. ይህንን ሐዲስ በሕይወቱ ውስጥ እንዴት መተግበር እንደሚችል እንዲያብራራ ማስቻል።

የቃላትና ሐረጎች ፍቺ

- ‹‹ግልጽ ነው››፡ – የተብራራና ይፋ የሆነ ነው። ድብቅ አይደለም።
- አሻሚ ነገሮች (ሙሽተቢሃት)፡ – ሐራም ወይም ሐላል መሆኑ ግልጽ ያልሆነ።
- ‹‹ብዙ ሰዎች አያውቋቸውም፡ ››፡ – ብዙሃኑ ብይናቸውን አያውቁም።
- ‹‹አሻሚ ነገሮችን የተጠ ቀቀ››፡ – ከነርሱ የራቀ፣ በርሱና በአሻሚ ነገሮች መሀል መከላከያ ያኖረ።
- ‹‹ለሀይሞቱና ለክብሩ መጥራትን ፈለገ››፡ – ክብሩን ከነውር እምነቱን ከጉድለት ማጽዳት ፈለገ። ዲኑን ከውግዘት ራሱንም ከጉድለት ጠበቀ። በዚህች ንግግር መልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ሰውየው ከሰዎች ጋር እና ከአላህ ጋር ያለውን ግንኙነት የተመለከቱ ጉዳዮችን አመላክተዋል።
- ‹‹ድንበር (ጥበቅ ስፍራ)››፡ – ከባለቤቱ ውጭ የሆነ ሰው የሚከለከልበት ክልል ማለት ነው።
- ‹‹ቁራጭ ሥጋ››፡ – በአፍ መታኘክ በሚችልበት መጠን የሆነ ሥጋ።
- ‹‹ክልሉን አልፎ ሊያስግጥ እንደሚቃርብ››፡ – ያልተፈቀደለት የሰው ድንበር ውስጥ ገብቶ የሰውን ማሳ እንደሚያስበላ ሰው ይመሰላል።

አጠቃላይ ትርጉም

ሐላልና ሐራም ግልጽ ናቸው፡፡ በመሀላቸው ግን አሻሚ ነገሮች አሉ፡፡ የዚህን አጠቃላይ ሃሳብ ትንታኔ ነገሮችን ለሦስት በመክፈል እንጀምር፡፡

ነገራት ሦስት ናቸው፡፡ አንደኛው ግልጽ የሆነ ሐላል፤ መፈቀዱ ድብቅ አይደለም፡፡ ዳቦ እንደ መብላት፣ እንደ ንግግር፣ እንደ መራመድ ወዘተ… ነው፡፡ ሁለተኛው ግልጽ የሆነ ሐራም፤ አልኮል እንደመጠጣት፣ ዝሙት እንደመፈጸምና እነዚህን የመሳሰሉትን ነው፡፡ ሦስተኛው አሻሚ ነገሮች ናቸው፡፡ እነዚህም ሐላል ወይም ሐራም መሆናቸው ግልጽ ያልሆኑ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ብዙሀን ብይናቸውን አያውቁትም፡፡ ዑለሞች ብቻ በተዘገቡ መረጃዎች ወይም በቂያስ (ማመሳሰል) ያውቋቸዋል፡፡

አንድ ነገር ሐላልና ሐራም በመሆን መሀል ካደናገረና ብይን የሚሰጥበት ግልጽ የሆነ መረጃ ወይም የዑለሞች ስምምነት ከሌለ የመተንተን ወይም የኢጅቲሃድ ብቃት ያላቸው ዑለሞች ያጠኑና መረጃን በመጠቀም ከሁለቱ ወደ አንዱ ያስጠጉታል፡፡

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) *«በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነ የጥርጣሬ ስፍራ ላይ ሊይሁን»* ማለታቸው ተዘግቧል፡፡ *«አሻሚ ነገሮች ውስጥ የወደቀ ሐራም ውስጥ ወደቀ»* የሚለው የመልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ንግግርም ለሁለት ነገሮች ይመቻል፡፡ አንደኛ ሰውየው ሐራም መሆኑን ሳይጠረጥር ሐራም ውስጥ ይወድቃል ማለት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ *«ኃጢያት የኩፍር መልእክተኛ ነው»* እንደሚባለው ሐራም ውስጥ ለመግባት ቀርቧል የሚል አንድምታን ያሳልፋል፡፡ «ነፍስ አንድ ኃጢያት ውስጥ ከወደቀች ከሱ ከፍ ወዳለ ርከሰት ከፍ እያለች መምጣቷ አይቀርም» እንደሚባለው ማለት ነው፡፡ ቀጣዩ የቁርአን አንቀጽ ይህን ጉዳይ ያመላክታል፡-

﴿ وَيَقْتُلُونَ ٱلَّذِينَ يَأْمُرُونَ بِٱلْقِسْطِ مِنَ ٱلنَّاسِ فَبَشِّرْهُم بِعَذَابٍ أَلِيمٍ ﴾ آل عمران: ١٢١

"ነቢያትንም ያለ ሕግ ይገድሉ ስለነበሩ ነው፤ ይህ በሞጻቸውና ወሰንን ይተላለፉ ስለነበሩ ነው፡፡" (አል-ዒምራን፡ 112)

ኃጢያትን የመፈጸም እርከን በደረጃ ነቢያትን እስከመግደል ድረስ አደረሳቸው፡፡ ሐዲስ እንዲህ ይላል፡፡ *«እንቁላል ሰርቆ እጁ የሚቆረጥ፤ ገመድም ሰርቆ እጁ የሚቆረጥ ሌባ የአላህ እርግማን ይውረድበት፡፡»*

ከእንቁላል እና ከገመድ ጀምሮ እጆቹን እስከሚያስቆርጠው የገንዘብ መጠን ድረስ የኃጢያት ደረጃው ከፍ ያለ ሰው ለማለት ነው፡፡

የአሻሚ ነገሮችን መተው አላህን በእጅጉ ከመፍራት (ወረዕ) የሚቆጠር ነገር ነው፡፡ ለምሳሌ፡- አሻሚ በሆነ መንገድ ገንዘብ ከሚሠራ ሰው ወይም ወለድ ከሚቀላቅል ሰው ጋር ወይም መተዉ የሚመረጥ የሆነ ሐላል ነገርን አብዝቶ መጠቀም መተው፡፡...

ሐሰን አል-በስሪይ እንዲህ ብለዋል፡- «ተቅዋ (ፈሪሃነት) ፈሪሃዎቹ ሰዎች ብዙ ሐላል ነገሮችን ሐራምን በመፍራት እስከሚተዉ ድረስ ደርሷል፡፡»

ኢብኑ ዑመር(ረ.ዐ) እንዲህ ማለታቸው ተዘግቧል፡- «በእኔና በሐራም መካከል ግርዶሽ የማደርገውና በፍፁም የማልቀድደው የሐላል ሽፋን እንዲኖር እወዳለሁ፡፡»

«ሁሉም ንጉሰ ድንበር አለው፡፡ የአላህም ድንበር ክልክሎቹ ናቸው»

ይህ ምሳሌ የተነሳው ቅርብ በሆነ ነገር የሩቁን ለማንቃትና ለማስገንዘብ ነው፡፡ በሚታየው የማይታየውን ለመግለጽም ነው፡፡የዐረብ ነገስታት ለከብቶቻቸው የግጦሽ ቦታን ይከልላሉ፡፡ ወደነርሱ የሚቀርብን ያስጠነቅቃሉ፡፡ የንጉስን ቅጣት የሚፈራ ድንበሩን አልፎ እንዳይገባ በመስጋት ከድንበሩ ይርቃል፡፡ ቅጣቱን የማይፈራ ሰው ግን ወደ ድንበሩ አስጠግቶ ያስግጣል፡፡ ከምርጫው ውጭም በድንገት ወደ ክልክሉ ውስጥ መግባቱ አይቀርም፡፡ በዚህም ምክንያት ይቀጣል፡፡

አላህም በምድር ውስጥ ወሰኖች አሉት፡፡ ኃጢያቶችና እርም የሆኑ ነገሮች የርሱ ድንበሮች ናቸው፡፡ ከነርሱ አንዱን የሠራ በዱንያም ሆነ በአኼራ የአላህ ቅጣት ያገኘዋል፡፡ አሻሚ ነገሮች ውስጥ በመውደቅም ወደ ሐራም የቀረበ ሰው ከድንበሩ ሊያልፍ ይችላል፡፡ ያኔም በድንገት ሐራም ውስጥ ይገባል፡፡

‹‹በአካል ወስጥ ቁራጭ ሥጋ አለች" የልብ መስተካከል፤ የአካል መስተካከል በልብ መስተካከል የሚወሠን ነው፡፡ ምክንያቱም ከሰው አካል መሃል ዋናው ልብ ነው፡፡ ይህ በህክምናውም ሆነ በሳይንሱ ዓለም ልዩነት የሌለበት ነገር ነው፡፡ ልብ የሰው ልጅ አካላዊ ሕይወት ምንጭ ነው፡፡ ልብ ጤናማ ከሆነም ሥርዓቱን ጠብቆ ደም ይረጫል፡፡ ወደ ሌሎች የሰውነት ክፍሎች በሙሉ ደምን ያሠራጫል፡፡ ያኔም ሰው በመልካም ሁኔታና በጤና ይኖራል፡፡

በሐዲሱ ለመጠቆም የተፈለገው የልብን መንፈሳዊ ጤንነት ነው፡፡ ልብ የሰው ነፍስ መጥራቱን እና ጤናማ መሆኑን ይነግረናል፡፡ ይህን ከአላህ ውጭ ማንም አያየውም፡፡

ጤናማ ልብ አላህ ዘንድ እድልን የማረጋገጫ መንገድ ነው፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡፡

﴿يَوۡمَ لَا يَنفَعُ مَالٞ وَلَا بَنُونَ ٨٨ إِلَّا مَنۡ أَتَى ٱللَّهَ بِقَلۡبٖ سَلِيمٖ ٨٩﴾ الشعراء: ٨٨ - ٨٩

"ገንዘብም ልጆችም በማይጠቅሙበት ቀን፤ ወደ አላህ በንጹሕ ልብ የመጣ ሰው ቢኾን እንጅ፡ ፡" (አሽ-ሹዐራእ፡ 88-89)

የልብ ማማር እና መስተካከል የአካላትን እንቅስቃሴ ያስተካክላል፡፡›› ቀልብ ያማረ እንደሆነ አላህ የሚፈልገውን ከመፈለግ ውጭ ሌላ ምኞት አይኖረውም፡፡ አካላት አላህ ወደሚወደው ነገር እንጂ አይነሳሱም፡፡ አላህን ለማስደሰት ይጣደፋሉ እርሱ ከሚጠላው ነገር ይጠነቀቃሉ፡፡ አላህን ማስቆጣቱ ባይረጋገጥም ከሚጠረጠር ነገርም ይታቀባሉ፡፡ ስለዚህ ዋናው ልብ ነው፡፡

ሐዲሱ ሐላልን ወደ መስራት እርምን ወደ መታቀብ አሻሚ ነገሮችን ወደ መተው ይገፋፋል፡፡ ለዲንና ለክብር መጠንቀቅንም ያስተምራል፡፡ ወደ መጥፎ ጥርጣሬ እና ክትትል ውስጥ ወደ መውደቅ የሚያቀርቡ ነገሮችን እንድንተው ይመክራል፡፡ ሐራምን ብቻ ሳይሆን ወደ ሐራም የሚያደርሱ ነገሮችን መተው፣ የሐራም መዳረሻዎችን መራቅ እንደሚገባ ይጠቁማል፡፡ ልብን ለማስተካከል መትጋት ነፍስንም ከመሠረቱ ማበጀት እንደሚያስፈልግ አበክሮ ያስረዳል፡፡

የመጨረሻ ጥያቄዎች

1. ይህ የተከበረ ሐዲስ ከታላላቅ የዲን መሠረቶች አንዱ እንደሆነ ይነገራል። ለምን?
2. «ሐላል ግልጽ ነው። ሐራምም ግልጽ ነው። በመካከላቸው....» የሚለውን አብራራ። አሻሚ ነገር ማለት ምንድን ናቸው?
3. አሻሚ ነገሮችን በተመለከተ ሙስሊም ሊያደርግ የሚገባው ምንድን ነው? ለምን?
4. ልብ ከሰው ልጅ አካላት መሀል ያለው ስፍራ ምን እንደሆነ ግለፅ።
5. ልብህን ለማስተካከል ያደረግከው ልፋት ይኖር ከሆነ በጥቂቱ ጠቁመን። ምናልባት ለባልደረቦችህ ጥቅም ይኖረዋል።
6. ሐዲሱ ምን እንደሚያስተምር አብራራ።
7. ይህን ሐዲስ በግል ሕይወትህ ውስጥ እንዴት መተግበር እንደምትችል ግለፅ።

ሰባተኛ ሐዲስ

ዲን ነሲሐ (ምክር) ነው

عَنْ أَبِي رُقَيَّةَ تَمِيمِ بْنِ أَوْسٍ الدَّارِيِّ رضي الله عنه أَنَّ النَّبِيَّ صلى الله عليه وسلم قَالَ: "الدِّينُ النَّصِيحَةُ. قُلْنَا: لِمَنْ؟ قَالَ لِلَّهِ، وَلِكِتَابِهِ، وَلِرَسُولِهِ، وَلِأَئِمَّةِ الْمُسْلِمِينَ وَعَامَّتِهِمْ" . رَوَاهُ مُسْلِمٌ.

ከአቢ ሩቀያ ተሚም ቢን አወስ አድ–ዳሪይ እንደተወራው የአላህ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ አሉ ‹‹ዲን (ሃይማኖት) ነሲሐ (ትቡበር) ነው፡ ‹‹(ነሲሐው) ለማን ነው? ›› አልናቸው፡ ነቢዩም(ሰ.ዐ.ወ) ‹‹ለአላህ፣ ለሚልዕከተኛው፣ ለሚስሊም መሪዎች እና አጠቃላያቸው›› በማለት ማለሱ፡፡ ››ሚስሊም ዘግበውታል፡፡

የዚህ ትምህርት አላማዎች

1. የነሲሐን አንገብጋቢነት እንዲያብራራ ማስቻል፡፡
2. ነሲሐ ምን ማለት እንደሆነና የሚይዛቸውን ነጥቦችም እንዲያብራራ ማስቻል፡፡
3. የነሲሐን አደቦች መተንተን እንዲችል
4. እስከ ምን ድረስ ነሲሐን ከነሥነ-ሥርዓቶቹ እንደሚተገብር እንዲያብራራ ማስቻል፡፡
5. ይህንን ሐዲስ በሕይወቱ ውስጥ እንዴት እንደሚተገብር እንዲገልጽ ማስቻል፡፡

የሐዲሱ አሳሳቢነት

ይህ ሐዲስ የመጨረሻው መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ከሌሎች ነቢያት ከተለዩባቸው ክብሮች መካከል አንዱ የሆነውን ጠቅለል ያለ ወይም ሃሳብን በአጭሩ የመግለጽ ድንቅ የንግግር ችሎታ “ጀዋሚዑልከሊም” የሚያንፀባርቅ ሐዲስ ነው፡፡ ጀዋሚዑል-ከሊም ማለት ብዙ ታላላቅ ትምህርቶችንና የላቀ ፋይዳን ያዘሉ በርካታ ጉዳዮችን በአንድ አጭርና ጠቅላይ ገለፃ ማስቀመጥ ማለት ነው፡፡ ገለፃው በግልፅ ከሚያሳየው ነጥብ በተጨማሪ በውስጡ ሌሎች ብዙ ህግጋትንና

ሱናዎችን በመሰረታዊነት አልያም በቅርንጫፋዊ ትንተና ያዘለ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ስለዚህኛው ሐዲስ የኢስላም ምሁራን ሲናገሩ «ይህ ሐዲስ የእስልምና መዘውር የተመሰረተበት ሐዲስ ነው» ብለዋል፡፡

የቃላትና ሐረጎች ትርጉም

- ‹‹ዲን››፡ – (ሃይማኖት) ሲባል እስልምናን፣ኢማንን እና ኢሕሳንን (ማሳመርን) ለማመልከት ነው፡፡

- ‹‹ነሲሐ››፡ – ይህችን ንግግር ነሲሐ ለምታደርገው አካል መልካም መፈለግህን ለመግለፅ የሚጠቅም ንግግር ነው፡፡ ወይም ሌሎች እንደሚተረጉሙት ነሲሐ ልብስ መስፋትን ከሚጠቁም ቃል የተፈለቀቀ ቃል ነው፡፡ ነሲሐ የሚያደርገው ሰው ነሲሐ የሚያደርግለትን አካል ቀዳዳ ለመሸፈን የሚያከናውነው ተግባር ስለሆነ ቃሉም ይህን ለማመሣሠል ጥቅም ላይ ውሏል ማለት እንችላለን፡፡ በሌላ አተረጓጎም ነሲሐ የሚለው ቃል ማርን ከሰሙና ከእንጀራው መለየትን የሚያስይዝ ንግግር ነው፡፡ ህዝብን ከክህደት ማጥራትን ማርን ከማይጠቅመው ቆሻሻ ከማጥራት ጋር አመሳስሉት፡፡

- ‹‹አኢመቲል መኽሊሚ››፡ – አስተዳዳሪዎቻቸው፤ መሪዎቻቸው

- ‹‹ዓመቲሂም›››፡ – ተራው የማኅበረሰብ ክፍል

አጠቃላይ ትርጉም

1. ለአላህ ነሲሐ ሞድረግ፡ – ይህ የሚሆነው በአላህ በማመንና ከርሱ ጋር የሚያጋሩትን ሁሉ በመካድ ነው፡፡ ለአላህ ነሲሓ ማድረግ በባህሪያቱ ላይ ክህደት ከመፈፀም መጠንቀቅን ያካትታል፡፡ እርሱን በተሟሉ በሆኑት ባህሪያት መግለፅን ይይዛል፡፡ ከጉድለት በሙሉ እርሱን በማጥራት፣ አምልኮንም ለእርሱ በማድረግ፣ ለርሱ ብሎ በመውደድ፣ ለርሱ ብሎ በመጥላትም ይገለፃል፡፡ እርሱን የታዘዙትን ወዳጅ በማድረግና እርሱን የነቀፈን በመጥላት ይታወቃል፡፡ ሙስሊም ይህን ሁሉ በንግግርና በተግባሩ መፈፀሙ በዱኒያና በአኼራ ውስጥ

ጥቅሙ ወደርሱ ይመለሳል፡፡ ምክንያቱም አላህ ነሲሐ ከሚያደርጉ ሰዎች ነሲሐ የተብቃቃና ንጹሕ አምላክ ነው፡፡

2. ለአላህ *መጽሐፍት ነሲሐ ማድረግ*፡ – ይህ ከሰማይ በወረዱ መጽሐፍት በሙሉ በማመን፣ ሁሉም ከአላህ ዘንድ መሆናቸውን በመቀበልና ይህ ቁርአንም የሁሉም መደምደሚያና መስካሪ እንደሆነ በማመን የሚተገበር ሥራ ነው፡፡ ለጌታው መጽሐፍ የሚያደርግ የሙስሊም ነሲሐ እንደሚከተለው ይገለጻል፡-

- ማንበብና መሸምደድ፡- ምክንያቱም እርሱን ማንበብ ነፍስን ያጠራል፤ ተቅዋንም ይጨምራል፡፡ ሙስሊም ከአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንደዘገቡት «ቁርአንን አንብቡ፡፡ እርሱ የቂያማ ቀን ለጓደኞቹ አማላጅ ሆኖ ይመጣል፡፡» ብለዋል፡፡ በልብ ውስጥ የአላህን መጽሐፍ መሸምደድ ልብን ልዩ በሆነ የአላህ ብርሃን ያሸበርቃል፡፡ አቡዳውድና ቲርሚዚ ከአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንደዘገቡት «ቁርአንን ለሚያነብ ሰው የቂያማ ቀን እንዲህ ይባላል፡- «አንብብና ደረጃህን ውጣ፤ በዱኒያ ውስጥ ታነብ እንደነበረውም አሳምረህ አንብብ፡፡ የአንተ ደረጃ መጨረሻ ከምታነበው አንቀጽ ዘንድ ነው፡፡»
- ረጋ ብሎ ማንበብ፤ ሲነበብ ድምፅን ማሳመር፡፡
- ትርጉሙን ማስተንተንና አንቀፆቹን ለመረዳት ጥረት ማድረግ፡፡
- ለማኅበረሰቡና ለትውልድ ማስተማር፡፡ ቡኻሪ ከአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንደዘገቡት «ከመሃላችሁ መልካም ሰው ቁርአንን ተምሮ ያስተማረ ነው፡፡» ብለዋል፡፡
- ትክክለኛን ግንዛቤ በመጨበጥና በዚያም ለመስራት መጣር፡፡ ማንበብ ያለግንዛቤ ጥቅሙ እምብዛም ሲሆን ግንዛቤ ያለ ተግባር ደግሞ ፋይዳ ቢስ ነው፡፡

3. *ለአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ነሲሐ ማድረግ*፡ – ይህ የነቢዩን መልእክት በማመን፣ ይዘው የመጡትን ቁርአንና አስተምሮት ሁሉ እውነት ብሎ በመቀበል ይገልፃል፡፡ እርሳቸውን በመውደድና በመታዘዝም ይንፀባረቃል፡፡

﴿ قُلۡ إِن كُنتُمۡ تُحِبُّونَ ٱللَّهَ فَٱتَّبِعُونِي يُحۡبِبۡكُمُ ٱللَّهُ ﴾آل عمران: ٣١

"በላቸው፡ – አላህን የምትወዱ እንደኾናችሁ፥ ተከተሉኝ፤ አላህ ይወዳችኋና፤ "

(አል-ዒምራን፡ 31)

﴿ مَّن يُطِعِ ٱلرَّسُولَ فَقَدۡ أَطَاعَ ٱللَّهَۖ ﴾النساء: ٨٠

"መልእክተኛውን የሚዘዝ ሰው፥ በእርግጥ አላህን ታዘዘ፤" (አን-ኒሳእ፡ 80)

እርሳቸው ከሞቱ በኋላ ለአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ነሲሐ ማድረግ ሙስሊሞች በየቤታቸው የእርሳቸውን ታሪክ እንዲያነቡ፣ መልካም ስብእናቸውን እንዲላበሱ፣ ስርአታቸውንም እንዲከተሉና ፈለጋቸውን አጥብቀው እንዲከተሉ ያደርጋቸዋል። ለጠላቶችና በርሳቸው ላይ ድንበር ለሚያልፉ ተናጋሪዎችም መልስ እንዲሰጡ ይገፋቸዋል።

4. ለመሸለም ሚዎች ነሲሐ ሞጅረግ፡ – የሙስሊሙ መሪዎች ሲባል አስተዳዳሪዎች አሊያም የእነርሱ ምትኮች ሊሆኑ ይችላሉ። ወይም ዑለማዎችና ሷሊሖች ሊሆኑ ይችላሉ።የሙስሊሞች መሪ ከሙስሊሞች ሊሆን ይገባል።እንዲህ ከሆኑ ብቻ እነርሱን መታዘዝ ግዴታ ይሆናል። አላህም እንዲህ ብሏል፡-

﴿ أَطِيعُواْ ٱللَّهَ وَأَطِيعُواْ ٱلرَّسُولَ وَأُوْلِي ٱلۡأَمۡرِ مِنكُمۡۖ ﴾النساء: ٥٩

"አላህን ተገዙ፤ መልክተኛውንና ከእናንተም የስልጣን ባለቤቶችን ታዘዙ፤"

(አን-ኒሳእ፡ 59)

ለእርሱ ነሲሐ ማድረግ ማለት የነርሱን መስተካከል፣ መመራትና ፍትህን መውደድ ማለት ነው። የነርሱን ግል መውደድ ማለት አይደለም። ለነርሱ ነሲሐ በማድረግ በእውነት ላይ እንረዳቸዋለን፤ እንታዘዛቸዋለን፤ ሲረሱ እናስታውሳቸዋለን። በጥበብ፣ በርጋታና በእዝነት እናነቃቸዋለን። መሪዎቹን የማይመክር ሕብረተሰብ ከመልካም የራቀ ነው። በደለኛን ‹አንተ በዳይ!› ብሎ በስሙ የማይጠራ ህዝብም መንገድ የሳተ ነው። ህዝቡን የሚያዋርድ፣የመካሪዎችን

ልሳን የሚዘጋና እውነትን ከመስማት ጆሮውን የሚያደነቁር መሪም መልካምን የተነፈገና ከበጎ የራቀ ነው።

ዑለሞችና ለውጥ ፈጣሪዎች ለአላህ መጽሐፍና ለመልእክተኛው አስተምሮ ነሲሐ በማድረግ በኩል ያለባቸው ኃላፊነት ከባድ ነው። መንገድ የሳተ ዝንባሌን ወደ ቅናት መመለስ የዚህ ኃላፊነት አካል ነው። መሪዎችን በአላህ መጽሐፍና በመልዕክተኛው አስተምሮ እንዲያስተዳድሩ መምከርም ታላቁ ኃላፊነታቸው ነው። መሪን በውሸት ሙገሳ በበደሉ ላይእንዲዘወትር፣ በአባገነንነቱም ላይ እንዲፀና ካደረጉም አላህ በከባድ ሁኔታ ይተሳሰባቸዋል። ጀርባቸውን ለመሪዎች የተመቸ መቀመጫና መጋለቢያ ካደረጉም ይጠየቁበታል። እናም እነርሱን ነሲሐ ማድረግ አለብን ስንል ጫንቃቸው ላይ ያለውን ይህን ኃላፊነታቸውን እንዲያስታውሱ ማድረግ እንዳለብን ለመግለጽ ነው።

5. ለተራው ለሟለም ነሲሐ ሞድረግ፡ – ይህ ተራውን የሙስሊም ማኅበረሰብ በዱኒያና ለአኼራ ጉዳዮቹ ላይ መንገድን በማመላከት ይተገበራል። ነገር ግን በጣም በሚያሳስብ ሁኔታ ሙስሊሞች ይህን ኃላፊነታቸውን ችላ ብለውታል። በተለይም ለአኼራቸው የሚጠቅማቸውን ነገር ከመመካከር ርቀዋል። ጭንቀታቸውን በሙሉም በዱኒያ ጥቅሞቻቸው ላይ ብቻ አትኩረዋል። በተጨማሪም ልንረዳው የሚገባው ነጥብ ነሲሐ በንግግር ብቻ የሚገደብ ሳይሆን ወደ ተግባር መዝለቅም ይገባዋል።

6. ታላቅ የነሲሐ አይነት፡ – በሙስሊሞች መሐል ከሚደረጉ ታላላቅ ነሲሐዎች መሐል በግል ጉዳዩ ላይ ያማከረውን ሰው ነሲሐ ማድረግ ነው። ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላሉ *«ለአንድ ወንድሙ ነሲሐን በጠየቀው ጊዜ ነሲሐውን ሊለግሰው ይገባል።»*

ከዚህ እጅግ የላቀው ደግሞ ወንድሙን በሌለበት ነሲሐ ማድረጉ ነውና እርዳታውንም መለገሱ ነው። ይህ ተግባር ያለውን እውነተኝነትና ታማኝነት ያረጋግጣል። ይህን አስመልክተው ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ አሉ፡- *«በሙስሊም ላይ ከሚኖሩት መብቶች ውስጥ በሌለበት ለርሱ ነሲሐ ማድረጉ አንዱ ነው።»*

7. የነሲሐ ሥነ-ሥርዓት፡- እንደ ኢስላም እምነት አንድ ሙስሊም ወንድሙን ነሲሐ ሲያደርግ በምስጢር ማድረጉ የነሲሐ ሥነ-ሥርዓት (አደብ)ነው፡፡ ፉደይል ኢብኑ ዒያድ እንዲህ ብለዋል፡- ‹ሙእሚን ነውርን ይሸፍናል፤ ይመክራል፡፡ጠማማ (ሙናፊቅ) ነውርን ይገልፃል፤ ያሰራጫል፡፡›

ከሐዲሱ የምንቀስመው ትምህርት

- ነሲሐ ዲን (ሃይማኖት) ነው፡፡ ዲን ንግግር ላይ እንደሚገኝ ሁሉ ተግባር ላይም ይኖራል፡፡
- ነሲሐ ከማኅበረሰብ ውስጥ በቂ ቁጥርና ብቃት ያላቸው ሰዎች ሊሰሩት የሚገባ የወል ግዴታ ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች በሚገባ ከፈፀሙት አጅር ያገኛሉ፤ ሌላው የማህበረሰቡም ክፍል በዚህ ኃላፊነት ከመጠየቅ ይድናል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ሁሉም የማኅበረሰብ ክፍል ይህን ኃላፊነት ባለመወጣቱ ይከሰሳል፡፡
- ማንኛውም ሰው ነሲሐውን ለሚቀበሉና ትእዛዙን ለሚፈጽሙ ብሎም ለደህንነቱ የማይሰጋ ከሆ የችሎታውን ያህል ነሲሐ ማድረግ ይገባዋል፡፡ ነገር ግን ነፍሱን ጥፋት ላይ እንዲጥል እንደማይገደድ የሐዲሱ ጭብጥ ያስረዳል፡፡

የመመዘኛ ጥያቄዎች

1. ለአላህ ነሲሐ ማድረግን እንዴት ትተገብራለህ? በተግባር ያዋልከው አንድ ምሳሌ ካለህ ጥቀስ?
2. ለአላህ መጽሐፍትና ለመልእክተኛው ነሲሐ ማድረግን እንዴት ትተገብራለህ?
3. ለሙስሊም መሪዎችና ለተራው ህዝብ ነሲሐ ማድረግን እንዴት ትተገብራለህ?
4. ታላቁ የነሲሐ አይነት ምንድን እንደሆነ ጥቀሱ፡፡
5. ከነሲሐ ሥርዓቶች የተወሰኑትን ጥቀሱ፡፡ነሲሐ ስታደርግ ስምን ያህል እነዚህን ሥርዓቶች ጠብቀሃል?

6. በግል ሕይወትህ ውስጥ ይህን ሐዲስ እንዴት በተግባር ልታውለው እንደምትችል ግለጽ፡፡

ስምንተኛው ሐዲስ

የሙስሊም ደም ጥብቅነት

عَنْ ابْنِ عُمَرَ رَضِيَ اللَّهُ عَنْهُمَا، أَنَّ رَسُولَ اللَّهِ صلى الله عليه وسلم قَالَ: "أُمِرْت أَنْ أُقَاتِلَ النَّاسَ حَتَّى يَشْهَدُوا أَنْ لَا إِلَهَ إِلَّا اللَّهُ وَأَنَّ مُحَمَّدًا رَسُولُ اللَّهِ، وَيُقِيمُوا الصَّلَاةَ، وَيُؤْتُوا الزَّكَاةَ؛ فَإِذَا فَعَلُوا ذَلِكَ عَصَمُوا مِنِّي دِمَاءَهُمْ وَأَمْوَالَهُمْ إِلَّا بِحَقِّ الْإِسْلَامِ، وَحِسَابُهُمْ عَلَى اللَّهِ تَعَالَى".رَوَاهُ الْبُخَارِيُّ وَمُسْلِمٌ.

ከኢብኑ ዑመር (ረ.ዐ) እንደተወራው የአላህ ሞልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡ – ‹‹ሰዎችን ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ እንደሌለና ሙሐመድም የአላህ ሞልዕክተኛ መሆናቸውን እስኪመሰክሩ፣ ሰላትንም እስከሚሰግዱና ዘካንም እስኪያወጡ ድረስ እንድጋደላቸው ታዝዣለሁ፡፡ ይህን ካደረጉ ከእስልምና አግባብ ወጪ ካልሆነ ደማቸውንና ገንዘባቸውን ከእኔ ጠበቁ፡፡ ሒሳባቸውም በአላህ ላይ ነው፡፡ ›› (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)

የትምህርቱ አላማዎች

1. የሐዲሱን አሳሳቢነት እንዲገልጽ ማስቻል፡፡
2. የሙስሊምን ደምና የሀብቱን ክብር እንዲያብራራ ማስቻል፡፡
3. የሙስሊም ደም ማፍሰስ የሚፈቅድባቸውን ሁኔታዎች እንዲያብራራ ማስቻል፡፡

የሐዲሱ አስፈላጊነት

ይህ ሐዲስ ታላላቅ የእስልምና ሃይማኖት መሰረቶችን ያዘለ ፍፁም ታላቅ ሐዲስ ነው፡፡ እነርሱም፡- ከአላህ በቀር በእውነት የሚመለክ ሌላ አምላክ እንደሌለና ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የአላህ መልእክተኛ መሆናቸውን ከልብ መመስከር፣ ሶላትን እንደታዘዘው አድርጎ መፈፀምና ዘካን ለሚገባቸው ሰዎች መስጠት ናቸው፡፡

የቃላቶችና ሐረጎች ፍቺዎች

- ‹‹ታዝዣለሁ››፡- አላህ አዞኛል
- ‹‹ሰዎችን››፡- ጣኦትን የሚያመልኩትና በአላህ ላይ የሚያጋሩትን
- ‹‹ሰላትን እስኪሰግዱ››፡- በታዘዙት መሰረት ግዴታዋንና ሱናዎቿን ጠብቀው እስኪፈጽሙና በርሷ ላይ ዘውታሪ እስኪሆኑ
- ‹‹ዘካንም እስኪያወጡ››፡- ከገንዘባቸው ግዴታ የሆነውን አውጥተው ለሚገባቸው ሰዎች እስኪሰጡ ድረስ
- ‹‹ጠበቁ››፡- (የታዘዙትን በመፈጸማቸው) ከችግር ራሳቸውን ተከለከሉ፡፡
- ‹‹ሂሳባቸው በአላህ ላይ ነው››፡- የውስጣቸውን መተሳሰብ የልባቸውን እውነት መገምገም የአላህ ብቻ ነው፡፡ ምክንያቱም ልብን የሚመለከት እርሱ ብቻ ነው፡፡

አጠቃላይ ትርጓሜ

ሁለቱን ሸሃደተይን (ምስክርነቶች) በምላስ ብቻ መናገር ገንዘብን ለመጠበቅ በቂ ነውን? ከብዙ መረጃዎች እንደተረጋገጠው የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ወደርሳቸው እስልምናን ፈልገው ከሚመጡት ሁሉ ሁለቱን ሸሃዳዎች ብቻ ይቀበላሉ፡፡ ደማቸውንም ጠብቀው እንደ ሙስሊም ይቆጥሯቸዋል፡፡

ቡኻሪና ሙስሊምን ዋቢ በማድረግ ከአቢ ሁረይራ (ረ.ዐ) እንደተዘገበው ደግሞ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት ሌላ አምላክ የለም ብለው እስከሚመሰክሩ ድረስ ሰዎችን እንድጋደላቸው ታዝዣለሁ፡፡ ይህን ያደረገ ሰው ሃብቱንና ነፍሱን ከኔ ጠበቀ ሒሳቡም በአላህ ላይ ነው፡፡»

የሙስሊም ዘገባ ደግሞ እንዲህ ይላል «ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት ሌላ አምላክ እንደሌለ እስኪመሰክሩና እኔ ይዣው በመጣሁት መልእክትም እስኪያምኑ ድረስ» ይላል፡፡

ሁለቱን ሽሃዳዎች መናገር ብቻውን የሰውን ደምና ገንዘብ ይጠብቃል፡፡ ሙስሊምም ያደርጋል፡፡ አንድ ሰው ሰላቱን ከሰገደ ዘካን ከሰጠ ደግሞ ለሙስሊሞች የሚገባው መብት ሁሉ ለርሱም ይኖረዋል፡፡ የሙስሊሞች ግዴታም በርሱ ላይ ይኖራል፡፡

ተፈላጊው ኢማን

ተፈላጊው ኢማን ቁርጥ ያለ እምነትና የኢስላም መርሆችን ያለ ጥርጥር መቀበል እንደሆነ በርካታ ሐዲሶች በግልፅ ያመለክታሉ፡፡ ለኢማን ትክክለኝነት የሚቀርቡ የምሁራንን መረጃዎች በመጥቀስ ወደ ኢማን መድረስ ግዴታ አይደለም፡፡ ለኢማን ተቀባይነትም መስፈርት አይደለም፡፡ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) በዚህና በሌሎችም ሐዲሶቻቸው እርሳቸው ይዘውት የመጡትን ማመን በቂ እንደሆነ አስተምረዋል፡፡ መረጃዎች ማወቅን መስፈርት አላደረጉም፡፡

በተገቢው ሁኔታ እንጂ

አግባብ ከሚሆኑ ሁኔታዎች መሀል ሶላትን መስገድና ዘካን መስጠት ይጠቀሳሉ፡፡ አንዳንድ ዑለማዎች ፆምንም እዚህ ውስጥ ያካትታሉ፡፡ እንዲሁም አንድ ሙስሊም ግድያን የሚያስፈርድ ወንጀል መፈጸሙ ከነዚህ አግባቦች ውስጥ ይጠቀሳል፡፡ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ)፡- «ከአላህ በቀር በእውነት የሚገዙት ሌላ አምላክ እንደሌለና እኔም የአላህ መልእክተኛ መሆኔን የሚመሰክር ሰው ከሶስት ምክንያቶች በአንዱ እንጂ ደሙ ፈጽሞ አይፈቀድም፡፡ አግብቶ የሚያውቅ ሆኖ ሳለ ዝሙት የሚፈጽም፤ ነፍስን ያጠፋ ሰው (ለማካካስ) እና ዲኑን የተወና ከጀመዓ ጋር የተቋረጠ» ብለዋል፡፡

ሂሳባቸው በአላህ ላይ ነው

ምስጢርን የሚያውቅና ልቦናን የሚመረምር አላህ (ሱ.ወ) ብቻ ነው፡፡ እውነተኛ ሙእሚን ከሆነ ጀነት ያስገባዋል፡፡ ውሸታምና ለይዩልኝ ኢስላምን የተቀላቀለ (የተቀበለ) የሰለመ ከሆነ ደግሞ ከእሳት ዝቅተኛው ወለል ውስጥ የሚቀጣ ሙናፊቅ ይሆናል፡፡ በዱኒያ ውስጥ የመልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ኃላፊነት

መግለፅና ማስታወስ ብቻ ነው፡፡ ቡኻሪና ሙስሊም ውስጥ እንደተዘገበው የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ለኻሊድ እንዲህ ሲሉ ነግረውታል«እኔ የሰዎችን ልብ እንድመራመርና ሆዳቸውን እንድሰነጥቅ አልታዘዝኩም፡፡»

ከሐዲሱ የምንቀስመው ትምህርት

የሙስሊሞች ደምና ሃብታቸው እርም መሆኑን

የመመዘኛ ጥያቄዎች

1. የሙስሊሞች ገንዘብና ደም ላይ ድንበር ማለፍ አይፈቅድም ይህን አብራራ
2. ሁለቱን ሸሃዳዎች መናገር ብቻውን ገንዘብና ነፍስን ለመጠበቅ በቂ ነውን?
3. «ይህን ካደረጉ ከእስልምና አግባብ በስተቀር ደማቸውንና ገንዘቦቻቸውን ከኔ ጠበቁ፡፡»
4. የእስልምና አግባብ ሲቀር ማለት ምንን ማለት ነው?
5. «ሂሳባቸውም በአላህ ላይ ነው፡፡» የሚለው ንግግር ምንን ለመጠቆም ታስቦ ነው፡፡
6. ከዚህ ከተከበረው ሐዲስ ምንን ተማርክ

ዘጠነኛው ሐዲስ

ማግፉትና አለማክፈር

عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ عَبْدِ الرَّحْمَنِ بْنِ صَخْرٍ رَضِيَ اللهُقَالَ: سَمِعْت رَسُولَ اللَّهِ صلى الله عليه وسلم يَقُولُ: "مَا نَهَيْتُكُمْ عَنْهُ فَاجْتَنِبُوهُ، وَمَا أَمَرْتُكُمْ بِهِ فَأْتُوا مِنْهُ مَا اسْتَطَعْتُمْ، فَإِنَّمَا أَهْلَكَ الَّذِينَ مِنْ قَبْلِكُمْ كَثْرَةُ مَسَائِلِهِمْ وَاخْتِلَافُهُمْ عَلَى أَنْبِيَائِهِمْ ".رَوَاهُ الْبُخَارِيُّ وَمُسْلِمٌ.

ከአበሀረይራ (ረ.ዐ) ዐብዱረሕማኝ አብን ሰኽር (ረ.ዐ)፡- ‹‹የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ)፡- ‹ከርሱ የከለከልኳቸሁን ነገር ተጠንቀቁ፤ በርሱም ያዘዝኳቸሁን የቻላችሁትን ያህል ፈፅሙ፡ በርግጥ ከናንተ በፊት የነበሩ ሰዎችን ያጠፉቸው ጥያቄ ማበዛቸውና ከነቢያቶቻቸው ጋር ማለያየታቸው ነው፡ ›› (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)

የትምህርቱ አላማ

1. የሐዲሱን አንገብጋቢነት እንዲገልፅ ማስቻል።
2. ሐዲሱ የተነገረበትን ምክንያት እንዲጠቅስ ማስቻል።
3. ክልክል ነገሮችን በመራቅ ዙሪያ ማጥበቅ አስፈላጊ የሆነበትን ምክንያት እንዲያብራራ ማስቻል።
4. ቀደምት ህዝቦች የጠፉበትን ምክንያት እንዲያብራራ ማስቻል።
5. በዚህ ሐዲስ ከመስራት መሰናክል የሚሆኑበትን ነገሮች እንዲያብራራ ማስቻል።
6. ይህን ሐዲስ በሕይወቱ ውስጥ እንዴት መተግበር እንደሚችል እንዲያብራራ ማስቻል።

የሐዲሱ አንገብጋቢነት

ይህ ሐዲስ አንገብጋቢ የሆኑ በርካታ ትምህርቶችን የሚሰጥ ሐዲስ ነው። ልትጠብቀውና ብዙ ጥናትም ልታደርግበት ይገባል። ከታላላቅ የእስልምና

መሠረቶች አንዱ ነው፡፡ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ከተሰጣቸው ሃሳብን ጠቅለል አድርጎ በአጭሩ የማስተላለፍ ተአምር ውስጥም አንዱ ነው፡፡ በውስጡ ተዘርዝረው የማያልቁ ብዙ ህግጋት ይጠቃለላሉ፡፡ ሐዲሱ ከታላላቅ የዲን መሰረቶች እና የኢስላም መርሆች አንጻር እጅግ ትልቅ ነው፡፡ ይህን መሸምደድ እና ትኩረት መስጠቱ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

ሐዲሱ የተነገረበት ምክንያት

ይህ ሐዲስ የተነገረበትን ሰበብ ኢማም ሙስሊም ከአቡ ሁረይራ (ረ.ዐ) ይዘው እንዲህ ዘግበውታል፡፡ «የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ዲስኩር (ኹጥባ) ለማድረግ ከመሀላችን ቆሙ፡፡ እንዲህም አሉ «ሰዎች ሆይ! አላህ በናንተ ላይ ሐጅን ግድ አድርጓል ሐጅ አድርጉ፡፡» አንድ ሰው ከመሃል ተነሳና እንዲህ አለ «በየዓመቱ ነውን?» መልእክተኛውም (ሰ.ዐ.ወ) ዝም አሉ፡፡ ሰውየውም ሦስት ጊዜ ጥያቄውን ደጋገመው፡፡ የአላህ መልእክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ አሉ፡- «አዎን ብል ኖሮ ግዴታ ይሆን ነበር፤ እናንተም መፈጸሙን አትችሉም ነበር፡፡» ከዚያም እንዲህ አሉ «የተውኳችሁን ተዉኝ ከናንተ በፊት የነበሩ ሰዎች የጠፉት ጥያቄ በማብዛታቸውና ነቢያቶቻቸውን በመንቀፋቸው ነው፡፡ አንዳች ነገር ባዘዝኳችሁ ጊዜ የቻላችሁትን ያህል ፈጽሙ፤ ከከለከልኳችሁም ሙሉ በሙሉ ራቁ፡፡» በአንዳንድ ዘገባዎች ላይም እንደተነገረው ጠያቂው አቅረዕ ኢብኑ ሃሲብ (ረ.ዐ) ነበር ተብሏል፡፡

የቃላትና ሐረጎች ፍቺዎች

- ‹‹የከለከልኳችሁን››፡- እንድትተውት ያዘዝኳችሁን ተግባር፤ **‹ነህይ›**፡- ክልክል
- ‹‹ራቁ››፡ – ተዉት
- ‹‹የቻላችሁትን››፡ – ችግር ውስጥ ሳትወድቁ መተግበር የቻላችሁትን
- ‹‹ያጠፉቸው›› ፡ – የጥፋታቸው ሰበብ የሆነው
- ‹‹ጥያቄዎችን ማበዛታቸው›› ፡ – ከጉዳያቸው የማይገናኝ፤ አንገብጋቢነት የሌለው ብዙ ጥያቄ

አጠቃላይ ትርጓሜ

‹‹የከለከልኳቸሁን ተከልከሉ››፡ – ክልክልነት በአላህ መጽሐፍ እና በአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ሐዲስ ላይ ለተለያዩ ጥቅሞች ሲውል እንመለከታለን፡፡ እዚህ ሐዲስ ላይ ክልክል በማለት ለመግለጽ የተፈለገው በእስልምና እርም የሆነውንና የተጠላውን ተግባር ነው፡፡

‹‹እርም የሆነ እግድ(ክልከላ)››፡ – የዚህ የክልከላ ዓይነት ምሳሌዎች ዝሙት፤ አልኮል መጠጣት፤ ወለድ መብላት፤ ስርቆትና ነፍስን ከአግባብ ውጪ ማጥፋትን መከልከል ናቸው፡፡ እነዚህን የመሳሰሉ መከልከሎችን በአንድ ጊዜ ማቆም ግዴታ ነው፡፡ ለጥያቄ የደረሰ፤ አእምሮው ጤናማ የሆነና ህፃን ያልሆነ ሰው ይህን ተግባር መፈፀም አይፈቀድለትም በወንጀልነትም ያስቀጣዋል፡፡ እነዚህን ተግባሮች ለመፈፀም ከባድ ችግር ያስገደደው እንደሆነ ግን ፍጹም ቀጥ ያለው የአላህ መለኮታዊ ሕግ (ሸሪዓህ) ባስቀመጣቸው ቅድመ-ሁኔታዎችና አጥሮች መሰረት ብቻ ቢፈጽማቸው ወንጀል አይሆንበትም፡፡ (ምክንያቱም ተገዶና ከአቅሙ በላይ ሆኖበት ስለሆነ፡፡)

‹‹የሞላት እገዳ (ክልከላ)››፡ – የዚህ እገዳ ምሳሌዎች ከሚሆኑት ጉዳዬች ውስጥ የጀመሳ ሰላት ለሚመጣ ሰው ሽንኩርት መብላት መከለከሉ ይጠቀሳል፡፡ችግር ቢኖርም ባይኖርም እነኚህን እግዶች መስራት ይፈቀዳል፡፡ ነገር ግን ትኩረት የሚሰጠው አንድን ሙስሊም የሚያስከብረውና የሚያልቀው ነገር ከነዚህ ነገሮች መራቁና መጠንቀቁ ነው፡፡

ክልክል ነገሮች መራቅና የርከሠትን ስር በማስወገድ (በመንቀል) ላይ ማከረር፡- የአላህ ሸሪአ ሁሌም ምድራዊው ሥርዓት ላይ ርከሠት እንዳይኖር ለማገድ ይተጋል፡፡ የርከሠት ዘር እንዲሠክንም ይታገላል፡፡ ስለዚህም ነው ክልክል ነገሮች ላይ የሚያደርገው ትኩረት ትእዛዛት ላይ ከሚያደረገው ትኩረት የጠነከረ ሆኖ የምንመለከተው፡፡ ይህ ማለት ትእዛዝ ላይ ቸልተኝነት አለ ማለት ግን አይደለም፡፡ ክልክል ነገሮች ላይ መራቅ እንደሚገባ የሚያደርገው ቅስቀሳ ትአዛዛት ላይ ከሚደረገው ይለያል፡፡ በተለይም እርም የሆኑ ነገሮች ላይ ፍጹም ክልከላን ያበጃል፡፡ ምክንያቱም የሚከለከለው ነገር ላይ ግልጽ የሆነ ብክለት መኖሩ

የተረጋገጡ በመሆናቸው የተከለከሉ ናቸው፡፡ ስለዚህ ማንም ሰው ክልክልን እንዲፈፅም ምንም ምክንያት አይሠጠውም፡፡

ከላይ በተጠቀሰው ማብራሪያ ዙሪያ የብዙ ሙስሊሞች የአካሄድ ችግር ይገለፃል፡፡ በተለይም በዚህ ዘመን በአብዛኛው የሕይወት ተግባሮቻቸው ላይ መጋጨትን ትመለከታለህ፡፡ የአላህን ትእዛዝ ለመፈፀምና ግዴታቸውን ለማድረስ ሲተጉ ይስተዋላል፤ አንዳንዴም ግዴታ ባልሆኑና ተወዳጅ ስራዎች ላይ የሙጥኝ ብለው ታገኛቸዋለህ፡፡ ይህ የተወደደ ቢሆንም በዛው ልክ ግን ክልክል በሆኑ ጉዳዮች ላይ ሲዘናጉ መመልከት አዲስ አይደለም፡፡ ከዚህም ብሶ ከባድ ወንጀሎች ውስጥም ይዘፈቃሉ፡፡ ጾመኛን በወለድ ሲገበያይ፤ ሀጅና ዘካ ላይ የበረታችው ሴት ያለ ሂጃብ ስትጓዝ መመልከት ዘመነኝነት እስኪመስል በርክቷል፡፡

ይህ ግን የአላህ ሸሪዓ ካስቀመጠው ውጭ ነው፡፡ የኢስላም የአምልኮት መሰረቱ አላህ ፍፁም ክልክል ያደረገውን መራቅ ነው፡፡ የመዳን መንገድም ነፍስንና መጥፎ ዝንባሌን መታገል ነው፡፡ የዚህ ደሞዝ ደግሞ አብዛኛውን ግዴታን በመፈጸም ከሚገኘው ምንዳ በላይ ነው፡፡ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላሉ፡- *«እርምን ተጠንቀቅ ከሰዎች መሀል ይበልጥ አላህን የምታመልክ ትሆናለህ፡፡»* ቲርሚዝይ ዘግበውታል፡፡

ዓሊሻም(ረ.ዐ) እንዲህ ይላሉ፡- «ታጋይን (በደረጃ) መቅደም የሚፈልግ ካለ ከወንጀል ይራቅ፡፡»

ዑመርም (ረ.ዐ)ኃጢያትን የሚሹ ግን ስለማይሠሯት ሰዎች ተጠይቀው እንዲህ ብለዋል፡- «እነዚህ አላህ ልባቸውን ለተቅዋ ያዘጋጃቸው ናቸው፡፡ ምህረትና ታላቅ ምንዳ አለላቸው፡፡» በማለት መልሰዋል፡፡

ዑመር ኢብኑ ዐብዱልዐዚዝ (ረ.ዐ) እንዲህ አሉ፡፡«ተቅዋ ማለት ሌሊቱን መቆም፣ ቀኑን በጾም መዋል ከዚያም በመሀል ወንጀልን መቀላቀል አይደለም፡፡ ነገር ግን ተቅዋ አላህ ያዘዘውን መፈጸም የከለከለውን መከልከል ነው፡፡ ከዚህ በኋላ ሌሎች ትርፍ ሥራዎች ካሉ መልካም ላይ መልካም ላይ እንደመጨመር ነው፡፡»

ቀደምት ህዝቦች የጠፉባቸው ምክንያቶች፡- የተከበሩት መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ቀደምት ህዝቦች ከጠፉባቸው፤ ኃይላቸውን ካደከሙባቸው፤ አንዳንዴም ሁሉን የሚያጠቃልል ቅጣት ከተቀጡባቸው ምክንያቶች የሚከተሉት ሁለቱ ነገሮች እንደሆኑ ገልፀዋል፡፡ አንደኛው አላስፈጊና ፋይዳ ቢስ ጥያቄዎችን ማብዛት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ትእዛዛትን መንቀፍ እና የአላህን ድንጋጌዎች አለመፈጸም ናቸው፡፡

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ሰሐቦቻቸውን በሙሉ ጥያቄ ማብዛትን ከልክለዋል፡፡ የከለከሉበትም ምክንያት ግዴታዎች እንዳይበዙባቸው በመስጋት ነው፡፡ በከንቱ ነገር ከመጠመድና በማይረቡ ነገሮች ከመዋከብ ለማቀብም ነው፡፡ ጥቅም የሌለውን ነገር መጠየቅ ባይጐዳም እንኳ የተጠላ ነገር ነው፡፡ ቡኻሪ ከሙጊራ ኢብኑ ሹዕባ እንደዘገቡት «የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) አሉባልታን፤ ጥያቄ ማብዛትንና ገንዘብ ማባከንን ከልክለዋል፡፡»

የመጠየቂያ ጥያቄዎች

1. የሐዲሱን አንገብጋቢነት አብራራ፡፡
2. ሐዲሱ የተነገረበትን ምክንያት ጥቀስ፡፡
3. የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ክልከልን በመራቅ በኩል ስለማከረራቸው አብራራ፡፡
4. ሐዲሱ ላይ የተገለጹትን ቀደምት ህዝቦች የጠፉባቸውን ምክንያቶች ግለጽ፡፡
5. አሉባልታ እና ጥያቄ ማብዛትን የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ይጠላሉ፡፡ ከዚህ ሐዲስ ጀርባ የተረዳኸው ጥበብ ምንድን ነው?
6. በዚህ ሐዲስ በመስራት በኩል ያንተን ተጨባጭ ሁኔታ ግለጽ፡፡
7. ይህን ሐዲስ በሕይወትህ ውስጥ እንዴት መተግበር ትችላለህ?

ስድሲኛው ሐዲስ

መልካም የሆነ ሐላል የተቀባይነት መስፈርት ነው

عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رَضِيَ اللهُقَالَ: قَالَ رَسُولُ اللَّهِ صلى الله عليه وسلم "إِنَّ اللَّهَ طَيِّبٌ لَا يَقْبَلُ إِلَّا طَيِّبًا، وَإِنَّ اللَّهَ أَمَرَ الْمُؤْمِنِينَ بِمَا أَمَرَ بِهِ الْمُرْسَلِينَ فَقَالَ تَعَالَى: "يَا أَيُّهَا الرُّسُلُ كُلُوا مِنْ الطَّيِّبَاتِ وَاعْمَلُوا صَالِحًا"، وَقَالَ تَعَالَى: "يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا كُلُوا مِنْ طَيِّبَاتِ مَا رَزَقْنَاكُمْ" ثُمَّ ذَكَرَ الرَّجُلَ يُطِيلُ السَّفَرَ أَشْعَثَ أَغْبَرَ يَمُدُّ يَدَيْهِ إِلَى السَّمَاءِ: يَا رَبِّ! يَا رَبِّ! وَمَطْعَمُهُ حَرَامٌ، وَمَشْرَبُهُ حَرَامٌ، وَمَلْبَسُهُ حَرَامٌ، وَغُذِّيَ بِالْحَرَامِ، فَأَنَّى يُسْتَجَابُ لَهُ؟". رَوَاهُ مُسْلِمٌ.

አቢ ሁረይራ እንዲህ አሉ፤ የአላህ ሰላትና ሰላምታ (ሰ.ዐ.ወ) የሚከተለውን ብለዋል፡ – ‹‹አላህ መልካም ነው፣ መልካምን እንጂ አይቀበልም፡ አላህ መልእክተኞቹን ባዘዘበት ጉዳይ ምእመናንም አዟል፡፡ አላህ እንዲህ አለ፡ –

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلرُّسُلُ كُلُواْ مِنَ ٱلطَّيِّبَٰتِ وَٱعۡمَلُواْ صَٰلِحًا ﴾ المؤمنون: ٥١

“እናንተ መልክተኞች ሆይ! ከተፈቀዱት ምግቦች ብሉ፤ በጎ ሥራንም ሥሩ፤” (አል-ሙእሚኑን፡ 51)

አላህም እንዲህ አለ፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ كُلُواْ مِن طَيِّبَٰتِ مَا رَزَقۡنَٰكُمۡ ﴾ البقرة: ١٧٢

“እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ከነዚያ ከሰጠናችሁ ጣፋጮች ብሉ፥ ”

(አል-በቀራህ፡ 172)

ከዚያም ስለ አንድ ሰው ሁኔታ አነሱ፡፡ (ሃይማኖታዊ) መንገድ ያረዝማል (ያበዛል)፡፡ ፀጉሩ የተንጨባረረ፣ አቧራ የለበሰም ነው፡፡ እጆቹን ወደ ሰማይ ዘርግቶ ጌታዬ ሆይ! ጌታዬ ሆይ! እያለ ይጣራል፡፡ (ይህ ሰው) የሚበላው ሐራም፤ የሚጠጣው ሐራም፤ የተገነባው በሐራም ነው፡፡ እንዴት ተቀባይነት ያገኛልን?›› ሙስሊም ዘግበውታል፡፡

የትምህርቱ አላማ

1. የሐዲሱን አሳሳቢነት (አስፈላጊነት) እንዲያብራራ ማስቻል፡፡
2. ተቀባይነት ያለው መልካም ስራ ሲባል ምን ለመግለጽ እንደሆነ እንዲያብራራ ማስቻል፡፡
3. ዱዓው ተቀባይነት የሚያገኝባቸውን ምክንያቶች እንዲገልጽ ማስቻል፡፡
4. ዱዓው ተቀባይነት የሚያገኝባቸውን ምክንያቶች ለማግኘት ሊጓጓ ይገባዋል፡፡
5. ይህን ሐዲስ ምን ያህል እንደሚተገብረው ሊያብራራ ይገባል፡፡

የሐዲሱ አንገብጋቢነት

ይህ ሐዲስ የኢስላም መሠረቶች የሆኑት ህግጋት ከተመሠረቱባቸው ሐዲሶች መካከል የሚቆጠር ነው፡፡ ሐላልን ለመያዝና ሐራምን ለመራቅ ፍቱን መንገድ ያስተምራል፡፡ ለራሱ የሚወደውን ለወንድሙ የሚወድ እንዲሁም ለራሱ የሚጠላውን ለወንድሙ የሚጠላ ግለሰብ ያለበትን ማህበረሰብ ለማስገኘት ታላላቅ ፋይዳዎችና ሰፊ ጥቅሞችን ያካተተ ሐዲስ ነው፡፡ የሸሪአ ድንበር ላይ በረከት ባለው ሐላል ተብቃቅተው የሚቆሙ በደስታና በእርጋታ የሚኖሩ ሰዎች የሚፈጥሩበትን መንገድም ይጠቁማል፡፡

የቃላትና ሐረጎች ፍቺዎች

‹‹አላህ መልካም ነው›› – ከጉድለት የጠራ ቅዱስ ነው፡፡

‹‹መልካምን አንጂ አይቀበልም›› – ከገንዘብም ሆነ ከስራ ከብክለት የጠራና ሐላል የሆነ እንጂ አይቀበልም፡፡ «መልእክተኞችን ባዘዘበት ጉዳይ» ሐላልን መብላት እንዳለባቸው ሁለቱንም ጭፍራዎች በተመሳሳይ ሁኔታ አዟል፡፡

‹‹የተንጨረረ›› – ባለመበጠሩ ምክንያት ፀጉሩ የተበታተነ፡፡

‹‹አቧራም›› – ጂሃድና ሐጅን ለመሰሉ አምልኮዎች በሚያደርገው ጉዞ ምክንያት የፀጉሩን ቀለም አቧራ ለውሶታል፡፡

‹‹እጆቹን ወደ ሰማይ ዘርግቶ››፡ - ዱዓ ለማድረግና ለመማጸን እጆቹን ከፍ ያደርጋል፡፡

‹‹እንዴት ተቀባይነት ያገኛል››፡ – ባህሪው እንደተጠቀሰው ሆኖ ሳለ ጥያቄው እንዴት ተቀባይነት ያገኛል፡፡ አያገኝም!

አጠቃላይ ትርጓሜው

1. ተቀባይነት ያለው መልካም ነገር

ይህ በአካል የሚፈፀሙ ተግባራትን፣ በገንዘብ የሚተገበሩ ሥራዎችን፣ ንግግሮችንና እምነትን ይጨምራል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) መልካምና ንጹሕ የሆነን፤ ከእይታ እና ከይስሙልኝ የጸዳን ሥራ እንጂ አይቀበልም፡፡ ሐላል የሆነና ከሐራም የጠራን ገንዘብን እንጂ በፍፁም አይቀበልም፡፡ ከንግግር መልካም የሆነው እንጂ ወደርሱ አይወጣም፡፡ አላህ እንዲህ ብሏል፡-

"መልካም ንግግር ወደርሱ ይወጣል፤ በጎ ሥራም ከፍ ያደርገዋል፤" (ፋጢር፡ 10)

ሙእሚን ሁለመናው መልካም ነው፡፡ ልቡ ላይ ያለው ኢማን የጸዳ ነው፡፡ ምላሱ ላይ በሰፈረው ዚክርና አካሉ ላይ በሚነበበው መልካም ሥራም የተዋበ ነው፡፡ ይህም የኢማን ፍሬ ነው፡፡

2. ሥራ እንዴት መልካምና ተቀባይነት ያለው ሊሆን ይችላል?

ሙእሚንን ሥራውን መልካም ከሚያደርጉትና ተቀባይነት ከሚያስገኙለት ተግባሮች ውስጥ የሚመገባቸው ምግቦች መልካምና ሐላል መሆናቸው ነው፡፡ በዚህ ሐዲስ ውስጥም ሐላልን በመብላት እንጂ ስራ ተቀባይነት እንደማይኖረው መረጃ አለ፡፡ ሐራም ሥራን ያከስማል፤ ተቀባይነትም ያሳጣል፡፡ አላህ መልእክተኞችን ባዘዘበት ጉዳይ ሙእሚኖችንም አዟል፡፡ አላህ እንዲህ ብሏል፡-

وقال الله تعالى: ﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلرُّسُلُ كُلُواْ مِنَ ٱلطَّيِّبَٰتِ وَٱعۡمَلُواْ صَٰلِحًا ﴾
﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ كُلُواْ مِن طَيِّبَٰتِ مَا رَزَقۡنَٰكُمۡ ﴾

የዚህ ትርጓሜ መልእክተኞችና ሕዝቦቻቸውን ከመልካም በመመገብ ወይም ሐላልን በመጠቀም እና መልካምን በመሰራት ታዘዋል። «መልካምን እንጂ አይቀበልም» የሚለው ንግግር ትርጓሜው፤ ስራዎች ደሞዝና መልካም ምንዳ ለማስገኘት የሚበቁት የተጠቀሰው መስፈርት ሲሟላ ብቻ ነው። ግዴታን ለመወጣት እና ፈርድን ለመስራት ያህል ብቻ ከሆነ ግን ተቀባይነቱም ምናልባት ይገኝ ይሆናል።

3. የዱዓን ተቀባይነት የሚያስገኙ ምክንያቶች

<u>መንገድን ማስረዘም</u>፡- ሃይማኖታዊ ጉዞ የዱዓን ተቀባይነት ያስገኛል። አቡዳዉድ ኢብኑ ማጃህ እና ቲርሚዚይ እንደዘገቡት የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ያለ ምንም ጥርጥር ሶስት ዱዓዎች (ጥሪዎች) ተቀባይነት አላቸው። የተበዳይ ዱዓ፣ የመንገደኛ ዱዓና የወላጅ ዱዓ ለልጅ።» መንገድ መቆረጥና መላን ማጣት ዱዓን ተቀባይነት ከሚያስስጡ ምክንያቶች ዋነኛዎቹ ናቸው።

<u>እጆችን ወደ ሰማይ መዘርጋት</u>፡- ይህ ከዱዓ ሥነ-ሥርዓቶች አንዱ ነው። ኢማም አህመድ እንደዘገቡት የአላህመልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «አላህ እጅግ ለጋስና ሐያእ የሚያደርግ አምላክ ነው፤ አንድ ሰው እጆቹን ወደ እርሱ በዘረጋ ጊዜ ባዶ፣ ፍሬ አልባ ሆነው ሊመልሳቸው ያፍራል።»

<u>በልመናህ አላህ ላይ ሙጥኝ ማለት</u>፡- ይህ የአላህን (ሱ.ወ) ጌትነትና ለጋስነት ደጋግሞ በማውሳት ይፈጸማል።

<u>የዱዓን ተቀባይነት ከሚከለክሉ ጉዳዮች መራቅ</u>፡- የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) በሐዲሱ ላይ እንዳመላከቱን በምግብ፣ መጠጥና ልብስ እንዲሁም ራስን በመገንባት ላይ በሐራም መጠቀም ዱዓን ተቀባይነት ያሳጣሉ።

ከሐዲሱ የምንቀስማቸው ትምህርቶች

- ሐዲሱ በሐላል ብቻ መጠቀምንና ከእርሱ ውጪ ያሉ መንገዶችን መከልከልን አበክሮ ያስረዳል።

- ዱዓው ተቀባይነት እንዲያገኝ የፈለገ ሰው ምግቡን፣ መጠጡንና የመሳሉትን ከሐላል ብቻ ሊያደርግ ይገባል።
- አላህ (ሱ.ወ) ከሙእሚኖች መልካም ልግስናን ሁሉ ይቀበላል፤ ያሳድጋታል፤ ይባርካታልም።

የመጨረሻ ጥያቄዎች

1. የሐዲሱን አንገብጋቢነት አብራራ።
2. መልካምና ተቀባይነት ያላት ተግባር ማለት ምን እንደሆነ አብራራ።
3. ዱዓን ተቀባይነት የሚያሰጡ ምክንያቶችን አስታውስ።
4. አንድ ተግባር እንዴት መልካምና ተቀባይነት ያለው ሊሆን ይችላል?
5. ይህን ሐዲስ ምን ያህል በተግባር ላይ እንደምታውለው አብራራ።

ምዕራፍ ሦስት

ዐቂዳ

ሁለተኛው የእምነት መሠረት

በመላእክት ማመን

የትምህርቱ ዓላማ

1. በመላእክት ማመን ምን ማለት እንደሆነ ግልፅ ማድረግ፡፡
2. የመላእክትን ማንነትና አካላዊ ምንነት ግልፅ ማድረግ፡፡
3. በመላእክት አለማመን(ከሸሪዓው አንፃር) ምን እንደሚያስወስን መረዳት፡፡

1. በመላእክት ማመን ምን ማለት እንደሆነ ግልፅ ማድረግ

በመላእክት ማመን ማለት ለአላህ (ሱ.ወ) ክብርሃን የተፈጠሩ መላእክት የሚባሉ ፍጥረታት እንዳሉት፣ እነርሱም እርሱ ያዘዛቸውን ትእዛዝ የማይጥሱና አላህ ባዘዛቸው የሥራ ድርሻቸው ላይ ቀጥ ያሉ መሆኑን በቁርጠኝነት ማመን ነው፡፡

መላእክት አሸናፊና ገናና የሆነው አላህ (ሱ.ወ) ከፈጠራቸው ፍጥረታት ዓይነት ናቸው፡፡ አንድ አማኝ የነርሱን መኖር እንዲሁም ከባህሪና ከሥራ በኩልም በአላህ ኪታብ (ቁርአን) እና በአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ሐዲስ ስለ እነርሱ የተነገረውን ምንም ሳይጨምር፣ ሳይቀንስና ሳይለውጥ እስካላመነ ድረስ እምነቱ ሙሉ ሊሆን ወይም ሊስተካከል አይችልም፡፡

በመላእክት ማመን ከሸሪዓ አንፃር በማንኛውም ለኃላፊነት (አቅመ አዳም) የደረሰ ግለሰብ ላይ ግዴታ ነው፡፡ ይህም ማለት መላእክት (እንደፍጡር) እየኖሩ ያሉ፣ የተከበሩ፣ አላህ ያዘዛቸውን የማይጥሱ፣ የታዘዙትን የሚተገብሩ፣ በተለያዩ ጥሩ በሆኑ (የፍጥረታት) ገፅታዎች መመሰል የሚችሉ፣ በወንድና በሴት ፆታ የማይገለፁ፣ የማይጋቡ፣ የማይበሉ፣ የማይጠጡና እንዲሁም የማይተኙ መሆናቸውን ማመንን ያጠቃልላል፡፡ መላእክት ብዙ አይነት ሲሆኑ ከነርሱ መካከል ከፊሎቹ ዐርሽን የተሸከሙ፣ ከፊሎቹ የአላህን መልእክት (ወሕይ) የሚያደርሱ፣ ከፊሎቹ (ሰው የሚሠራውንና የሚናገረውን) የሚጽፉ፣ ከፊሎቹ ተጠባባቂዎች ናቸው፡፡

ከፊሎቹ ደግሞ ሩሕን (ነፍስን) ለማውጣት የተመደቡ ሲሆን የነዚህ መላእክት አለቃቸው"መለከል-መውት"ነው። ሲሳይን በማከፋፈል ለተመደቡት ደግሞ አለቃቸው ሚካኤል ነው። ጀነትን በመጠበቅ ለተመደቡት አለቃቸው ሪድዋን ነው። ገሀነምን ለመጠበቅ ለተመደቡት ደግሞ አለቃቸው ማሊክ ነው። ቀብር ውስጥ ጠያቂዎች ተደርገው የተመደቡም አሉ።

ከመላእክት መካከል ስማቸው በአላህ መጽሐፍ (ቁርአን ውስጥ) የተጠቀሱ አሉ። እነርሱም ጂብሪል፣ ሚካኤል እና ማሊክ ናቸው። በሥራ ድርሻቸው ለተጠቀሱት መላእክት በተወሱበት የተግባር ዓይነት እውነት ብለን መቀበል ግድ ሲለን በስም ለተጠቀሱት እንደ ጂብሪል፣ ሚካኢልና ማሊክ ላሉት ደግሞ በስማቸው የተወሳውን ሁሉ እውነት ብለን መቀበል ይኖርብናል። እንደዚሁም በትክክለኛ ሐዲስ ስለተወሱትም መላእክት ማመን ግደታችን ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

﴿ ءَامَنَ ٱلرَّسُولُ بِمَآ أُنزِلَ إِلَيۡهِ مِن رَّبِّهِۦ وَٱلۡمُؤۡمِنُونَۚ كُلٌّ ءَامَنَ بِٱللَّهِ وَمَلَٰٓئِكَتِهِۦ وَكُتُبِهِۦ وَرُسُلِهِۦ لَا نُفَرِّقُ بَيۡنَ أَحَدٖ مِّن رُّسُلِهِۦۚ وَقَالُواْ سَمِعۡنَا وَأَطَعۡنَاۖ غُفۡرَانَكَ رَبَّنَا وَإِلَيۡكَ ٱلۡمَصِيرُ ٢٨٥ ﴾ البقرة: ٢٨٥

"መልእክተኛውም በእርሱ ላይ ከጌታው በተወረደው ነገር አመነ፤ ምእመናንም አመኑ፤ ሁሉም በአላህ፣ በመላእክቱ፣ በመጻሕፍቱና በመልእክተኞቹ አመኑ፡፡" (አል-በቀራህ፡ 285)

2. ከምን እንደተፈጠሩና አካላዊ ማንነታቸውን በተመለከተ

በትክክለኛ የሐዲስ ማስረጃ እንደተነገረው መላእክት የተፈጠሩት ከብርሃን ነው። እመት ዓኢሻ (ረ.ዐ) እንደተናገሩት ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል "መላእክት ከብርሃን ተፈጥረዋል፣ አጋንንት ደግሞ ከነበልባል እሳት ተፈጥረዋል፣ አደም ደግሞ ለናንተ ከተወሳው ነገር (ከጭቃ ማለታቸው ነው) ተፈጥሯል" (ሙስሊም ዘግበውታል)

አካላዊ ማንነታቸውን አስመልክቶ በቁርአንና በሱና የተጠቀሰ ነገር ባለመኖሩ እውቀቱን ለአላህ እንተዋለን። ስለነርሱ የተወሳው ነገር ቢኖር ሁለትም፣ ሶስትም፣

አራትም ክንፍ ያላቸው እንዳሉ ነው፡፡ ጅብሪል (ዐ.ሰ) ስድስት መቶ ክንፍ እንዳለው ተነግሯል፡፡ በትክክለኛ ማስረጃ እንደተረጋገጠው በጣም ኃይለኛ እንደሆኑ ይታወቃል፡፡ የነቢዩላህ ሉጥ (ዐ.ሰ) ህዝቦችን ከተማ ተሸክመው የገለበጧት አሉ፡፡ አርሽንም ተሸካሚዎች አሉ፡፡ በአንድ መላኢካ ጩኸት የሷልህ ህዝቦች ጠፍተዋል፡፡ ከአንድ መላኢካ በቀንድ በሚነፋ ጩኸት አላህ የፈለገው ሲቀር በሰማይና በምድር ውስጥ ያለ ሁሉ ይጠፋሉ፡፡ በሌላ ተመሳሳይ ጩኸት ፍጥረታት በሙሉ ይቀሰቀሳሉ፡፡

3. በመላእክት አለማመን (ከሸፈጓው አንጻር) ምን ያስመስናል

በመጽሐፍ (ቁርአን)፣ በሐዲስና በኢጅማዕ (ዑለማዎች ስምምነት) ማስረጃ የመላእክት መኖር ተረጋግጧል፡፡ የመላእክትን መኖር የነቀፈ ሰው ከሓዲ (ካፊር) ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

﴿وَمَن يَكۡفُرۡ بِٱللَّهِ وَمَلَٰٓئِكَتِهِۦ وَكُتُبِهِۦ وَرُسُلِهِۦ وَٱلۡيَوۡمِ ٱلۡأٓخِرِ فَقَدۡ ضَلَّ ضَلَٰلَۢا بَعِيدًا ١٣٦﴾ النساء: ١٣٦

"በአላህ፣ በመላእክቶቹ፣ በመጻሕፍቱና በመልእክተኞቹ የካደ በእርግጥ በጣም እሩቅ (የከፋ) የሆነ ጥመትን ጠፍቷል" (አል-ኒሳእ፡ 136)

ተግባራዊ እርምጃዎች

1. አላህን በመታዘዝ ላይ ዘወትር ተቻኮል፣ የሚከተለውን የአላህ ቃል ሁልጊዜም አስታውስ፡-

﴿وَإِنَّ عَلَيۡكُمۡ لَحَٰفِظِينَ ١٠ كِرَامٗا كَٰتِبِينَ ١١ يَعۡلَمُونَ مَا تَفۡعَلُونَ ١٢﴾ الانفطار: ١٠ - ١٢

"በእርግጥ በእናንተ ላይ ተጠባባቂዎች አሉ፣ የተከበሩ ጸሐፊዎች፣ የምትሠሩትን ሁሉ የሚያውቁ" (አል-ኢንፊጣር: 10-12)

2. የምትናገራትን አያንዳንዷን ቃል አስተንትን፣ እርሷ ላንተ ወይም ባንተ ላይ መስካሪ ናትና፤ የሚከተለውን የአላህ (ሱ.ወ) ቃል አስታውስ፡-

﴿ مَّا يَلْفِظُ مِن قَوْلٍ إِلَّا لَدَيْهِ رَقِيبٌ عَتِيدٌ ﴾ ق: ١٨

"ከቃል ምንም አይናገርም በአጠገቡ ተጠባቂና ዝግጁ የሆኑ (መላእክት) ያለበት ቢሆን እንጅ" (ቃፍ: 18)

3. የአላህ ስም የሚወሳበት ስብስብ ላይ መገኘት አዘውትር፣ መላእክት የአላህ ስም የሚወሳበት ቦታ ላይ ይጣዳሉና።

4. መላእክትን በተግባር ትመሳሰል ዘንድ አላህን በማስታወስና በማጥራት ላይ ተቻኮል፣ መላእክት አላህን መታዘዝና እርሱን ማጥራት የዘወትር ተግባራቸው ነውና።

5. የግዴታ ሶላቶችን በተለይም የዐስርና የፈጅር ሶላቶች በጀማዓህ ለመስገድ ተቻኮል መላእክት በነዚህ ሶላቶች ላይ ይገኛሉና። ሸይኻኒ አቡ ሁረይራን (ረ.ዐ) ጠቅሰው እንዳወሩት ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- "መላእክት በቀንና በሌሊት ይፈራረቃሉ። በዐስርና በፈጅር ሶላት ላይ ይሰበሰባሉ። ከዚያም እናንተ ጋር ያደሩት መላእክት ወደ ሰማይ ይወጣሉ። ጌታቸውም እርሱ አዋቂ ሆኖ ሳለ 'ባሮቼ በምን ሁኔታ ላይ ሳሉ ትታችኋቸው መጣችሁ?" በማለት ይጠይቃቸዋል። እነርሱም "እየሰገዱ አገኘናቸው እየሰገዱም ትተናቸው መጣን" በማለት መልስ ይሰጣሉ።

6. እውቀትን ፍለጋ ተጣደፍ፣ አቡ ዳውድ ከአቡ ደርዳእ (ረ.ዐ) እንደዘገቡት የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- "በርግጥ መላእክት በእውቀት ፈላጊ ላይ ክንፋቸውን ይዘረጉለታል።"

7. ለሰዎች ጥሩ ነገርን በማስተማር ላይ ተቻኮል። ሰዎችን ጥሩ ነገር ለሚያስተምር አላህ፣ መላእክትና፣ በሰማይና በምድር ያሉ በሙሉ ዱዓ ያደርጉለታል።

የመጠዘኛ ጥያቄዎች

1. በመላእክት ማመን ምን ማለት እንደሆነ አብራራ
2. መላእክት ምን እንደሆኑና አካላዊ ምንነታቸውን አብራራ
3. በመላእክት አለማመን (ከሸሪዓው አንፃር) ምን ያስወስናል?

ሦስተኛው የእምነት መሠረት

በአላህ መጻሕፍት ማመን

የትምህርቱ ዓላማዎች

1. በመጻሕፍት ማመን ምን ማለት እንደሆነ ግልፅ ማድረግ።
2. ከፊሎቹን የቁርአን ልዩ ባህሪያት መጥቀስ።
3. ከፊሎቹን የቁርአን ተአምራዊ ገፅታዎች መግለፅ።

1. በአላህ መጻሕፍት ማመን ምን ማለት እንደሆነ ግልፅ ማድረግ

በመጻሕፍት ማመን ማለት አላህ (ሱ.ወ) ትእዛዙንና ክልከላውን፣ ቃል-ኪዳኑንና ማስፈራሪያውን፣ እንዲሁም ከንግግር የፈለገውን በውስጣቸው የያዙ መጻሕፍትን በመልእክተኞቹ ላይ ማውረዱን በቁርጠኝነት ማመን ነው። ከነዚህ መጻሕፍት ሁሉ በላጩ በሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ የወረደው የተከበረው ቁርአን መሆኑንም ልናምን ይገባል። አላህ (ሱ.ወ) ያወረዳቸውና በቁርአን ውስጥ የተጠቀሱት ሌሎች መጻሕፍት ለሙሳ (ዐ.ሰ) የወረደው ተውራት፣ ለዒሳ (ዐ.ሰ) የወረደው ኢንጂልና ለዳውድ (ዐ.ሰ) የወረደው ዘቡር ናቸው። በተጨማሪም አላህ ሌሎች መጽሐፍትን እንዳወረደ ልናምን ይገባል። ከነዚህ መካከልም በቁርአን ውስጥ የተጠቀሱት ለኢብራሂም እና ለሙሳ (ዐ.ሰ) ያወረዳቸው ጽሑፎች ተጠቅሰዋል። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ ءَامِنُواْ بِٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦ وَٱلۡكِتَٰبِ ٱلَّذِي نَزَّلَ عَلَىٰ رَسُولِهِۦ وَٱلَّذِيٓ أَنزَلَ مِن قَبۡلُۚ وَمَن يَكۡفُرۡ بِٱللَّهِ وَمَلَٰٓئِكَتِهِۦ وَكُتُبِهِۦ وَرُسُلِهِۦ وَٱلۡيَوۡمِ ٱلۡأٓخِرِ فَقَدۡ ضَلَّ ضَلَٰلَۢا بَعِيدًا ﴾ ١٣٦ النساء:

"እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በአላህና በመልክተኛው በዚያም በመልክተኛው ላይ ባወረደው መጽሐፍ በዚያም ከበፊቱ ባወረደው መጽሐፍ እመኑ። በአላህና በመላእክቱም በመጽሐፎቹም በመልክተኞቹም በሚጨረሻውም ቀን የካደ ሰው (ከእውነት) የራቀን መሳሳት በርግጥ ተሳሳተ።" (አን-ኒሳእ: 136)

ቀደምት የወረዱት መጻሕፍት የመበረዝ፣ የመቀየርና የመለወጥ አደጋ የደረሰባቸው መሆኑን ማመን ግደታ ነው፡፡ የተከበረው ቁርአንን በተመለከተ ግን የተጠበቀ መጽሐፍ መሆኑንና አንዲትም ፊደል ሊቀየርበት እንደማይችል ልናምን ይገባል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ቀደምት የወረዱት መጻሕፍት ጥበቃ የተሰጠው ለወረዱበት ህዝብ (ህብረተሰብ) ስለነበርና ህዝቦቹ የመጠበቅ ኃላፊነታቸውን ባግባቡ ባለመወጣታቸው ነው፡፡ የተከበረው ቁርአንን ግን የመጠበቅ ኃላፊነቱን አሸናፊና የበላይ የሆነው አላህ ራሱ ስለወሰደው እንደተጠበቀ ይኖራል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

﴿ إِنَّا نَحۡنُ نَزَّلۡنَا ٱلذِّكۡرَ وَإِنَّا لَهُۥ لَحَٰفِظُونَ ٩ ﴾ الحجر: ٩

“እ— l`œ”” እ—¨< ›¨[É¨<&እ—U K`c< Övm-‡ ”“:” (አል-ሒጅር: 9)

2. ከቁርኣን ልዩ ባህሪያት

የተከበረው ቁርአን ቀድመውት ከወረዱት ሰማያዊ መጻሕፍት የሚለይበት ልዩ ባህሪያት አሉት፡-

- ከዚህ በፊት የወረዱት መጻሕፍት ይዘውት የነበረውን መለኮታዊ የመልእክት ጭብጥ አጠቃሎ የያዘ መሆኑ፣ በነዚህ የተለያዩ መጻሕፍት ተበታትነው የሚገኙ መልካምና የላቁ አስተምህሮቶችን ሰብስቦ መያዙ፣ ሁሉንም ያካበበና በነርሱ ላይ ተጠባባቂ መሆኑ፣ በሌሎች መጻሕፍት ውስጥ ያሉ እውነታዎችን የሚያረጋግጥና በነርሱም ውስጥ የተደረጉ ብረዛዎችንና ቅየራዎችን የሚያጋልጥ መሆኑ፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

﴿ وَأَنزَلۡنَآ إِلَيۡكَ ٱلۡكِتَٰبَ بِٱلۡحَقِّ مُصَدِّقٗا لِّمَا بَيۡنَ يَدَيۡهِ مِنَ ٱلۡكِتَٰبِ وَمُهَيۡمِنًا عَلَيۡهِ ٤٨ ﴾ المائدة: ٤٨

“ወደ አንተም ሚዛፉን ከበፊቱ ያለውን ሚዛፍ አረጋጋጭና በእርሱ ላይ ተጠባባቂ ሲኾን በእወነ ት አወረድን፡ ፡ ” (አል-ማኢዳህ፡ 48)

አላህ (ሱ.ወ) ለሁሉም የሰው ልጆች፣ ለሁሉም ዘመንና ቦታ እንደሚስማማ አድርጎ ያወረደው መሆኑና ለአንድ ለተለየ ሕዝብ ብቻ ያልወረደ መሆኑ፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

﴿ تَبَارَكَ ٱلَّذِى نَزَّلَ ٱلْفُرْقَانَ عَلَىٰ عَبْدِهِۦ لِيَكُونَ لِلْعَٰلَمِينَ نَذِيرًا ﴾ الفرقان: ١

"ያ በባሪያው ላይ ፉርቃንን (ቁርአንን) ለዓለማት አስፈራሪ ይሆን ዘንድ ያወረደ (አምላክ) ክብርና ጥራት ተገባው፡፡" (አል-ፉርቃን፡ 1)

- ቁርአን አላህ እንደሚጠብቀው ቃል የገባለት ብቸኛ መለኮታዊ መጽሐፍ መሆኑ፡፡ የተናጋሪዎች ሁሉ አሸናፊ (አላህ) እንዲህ ብሏል፡-

﴿ إِنَّا نَحْنُ نَزَّلْنَا ٱلذِّكْرَ وَإِنَّا لَهُۥ لَحَٰفِظُونَ ﴾ الحجر: ٩

"ቁርአንን እኛው አወረድነው፤ እኛም ለርሱ ጠቂዎቹ ነን፡፡" (አል-ሂጅር፡ 9)

ይህም የሆነበት ምክንያት የሰው ልጆች ይመሩበት ዘንድ የወረደውና የአላህ የመጨረሻ ቃል የሆነው የቁርአን አስተምህሮ ዘመን ሳይሽረው ለሁልጊዜም እንዲቆይ አላህ (ሱ.ወ) በመፈለጉ ይህንን መልእክት የመበረዝ፣ የመቀየርም ሆነ የመለወጥ አደጋ እንዳይደርስበት አላህ ራሱ ስለጠበቀው ነው፡፡

﴿ فَإِن يَصْبِرُوا۟ فَٱلنَّارُ مَثْوًى لَّهُمْ ۖ وَإِن يَسْتَعْتِبُوا۟ فَمَا هُم مِّنَ ٱلْمُعْتَبِينَ ﴾ فصلت: ٢٤

"እርሱ (ቁርአን) አሸናፊ የሆነ መጽሀፍ ነው፤ ከበስተፊቱም ከበስተኋላውም ስህተት የሚመጣበት ከጥበበኛውና ከምስጉኑ (አላህ) የተወረደ ነው፡፡" (ፉሲለት፡ 24)

- አላህ (ሱ.ወ) ንግግሩ ወደ ሰው ልጅ አእምሮና ጆሮ ውስጥ እንዲሰርፅና መልእክቱ እንዲደርስ ከዚያም ወደ ተጨባጭ ተግባር እንዲቀየር ይፈልጋል፡፡ ይህ ደግሞ ቁርአን በራሱ ገር ካልሆነ በስተቀር በቀላሉ ለማስታወስና ለመረዳት ስለማይቻል አላህ ገር አድርጎታል፡-

﴿ وَلَقَدۡ يَسَّرۡنَا ٱلۡقُرۡءَانَ لِلذِّكۡرِ فَهَلۡ مِن مُّدَّكِرٖ ﴾القمر: ١٧

"ቁርአንን ለማንዘብ በእርግጥ አገራነው፣ ተገንዛቢም አለን?''

(አል-ቀመር፡ 17)

3. የቁርአን ተአምሬት

በቁርአን ውስጥ ከሚገኙ የተአምራት መገለጫዎች፡-

መጀመሪያ መገለጫ፡- የቁርአን ያማረ ቅንብሩ፣ የቃላት አሰካኩ፣ የተሳካና ልብ የሚማርክ መልእክቱ፣ የማብራራት ምጥቀቱና የዐረቦችን የቋንቋ ክህሎት ሰንጥቆ ያለፈ ያገላለፅ ኃይሉ፣ ከጥበበኛውና ከምስጉኑ (አምላክ) የወረደ፣ አንቀጾቹ በጥበብ የተቀመሩ፣ ቃላቶቹ በሚገባ የተብራሩ፣ ያገላለጽ ምጥቀቱ አእምሮን የዘለለ፣ የቋንቋ ፍሰቱ ንግግርን ሁሉ ያስናቀ መሆኑ።

ሁለተኛው መገለጫ፡- አስገራሚ ሥርዓታዊ ቅንብሩ፣ እንግዳ የሆነና ከዐረቦች የንግግር ዘይቤ እንዲሁም የቋንቋ ህግጋትና ሥርዓት የተለየ መሆኑ፣ ቁርአን የመጣበት የአነጋገር ስልት፣ የአንቀጾቹ አከፋፈልና የመቆሚያ ቦታ ስኬት፣ የቃላቱ መጣጣምና የመለያ ክፍፍላቸው ጥምረት፣ ከርሱ በፊትም ሆነ ከርሱ በኋላ ተወዳዳሪ የማይገኝለት መሆኑ፣ አንድም ሰው በከፊል እንኳን የርሱን ተመሳሳይ ማምጣት አለመቻሉ።

ለዚህ ነው (ቁርአንን) በጥላቻው ቁንጮ ደርሶ የነበረው ዑትባ ኢቢኑ ረቢዓ ቁርአንን በሰማ ጊዜ እንዲህ ያለው፡- "ሰዎች ሆይ! እኔ አንድን ነገር በእርግጥ ሳላውቀው፣ሳላነበውና ሳልናገረው እንደማልተወው ታውቃላቸሁ። በአላህ እምላለሁ እርሱን የሚመስል ሰምቶ የማላውቀውን ንግግር በእርግጥ ሰማሁ። እርሱ ግጥምም አይደለም፣ ድግምትም አይደለም፣ጥንቆላም አይደለም።"

ሦስተኛው መገለጫ፡- ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ማንበብና መጻፍ የማይችሉ ሆነው ሳለ ቁርአን ከሕይወት መፈጠር ጀምሮ በርሳቸው ላይ እስከወረደበት ጊዜ ድረስ ቀድመው የተከሰቱ ነገሮችን መዘገቡ አንዱ ተአምር ነው። ቁርአን የነቢያትና የህዝቦቻቸውን ታሪክና በዘመኑ የጠፉ ህዝቦችን ሁኔታ ዘግቧል። ከመጽሐፉ

ባለቤቶች ለቀረቡ ዋሻ ውስጥ (ሦስት መቶ ዘጠኝ ዓመት) ሲኖሩ ስለነበሩ ህዝቦች፣ ስለ ሙሳና ኺድር (ሰላም በእነርሱ ላይ ይውረድና)፣ ስለ ዙል-ቀርነይን ሁኔታና ስለ ሌሎችም ፈታኝ ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥቷል።

አራተኛው መገለጫ፡- በወሕይ (በጂብሪል አማካኝነት ከአላህ በቀጥታ ለነቢዩ ሙሐመድ የሚወርድ መልእክት) ካልሆነ በስተቀር በወቅቱ ሊታወቁ የማይችሉ ወደፊት የሚከሰቱ ክስተቶችን መዘገቡ ሌላው ተአምር ነው። ቁርአን እንደሚፈፀሙ የተናገራቸው እነዚህ ክስተቶች ከንግግሩ አንድም ነገር ሳይቀር የተፈፀሙ አሉ። ከነዚህ መካከል በሱረቱል ፈትህ ቁጥር 27 ላይ "አላህ ለመልእክተኛው ሕልሙን እውነተኛ ሲሆን አላህ የሻ እንደሆነ ጸጥተኞች ሆናችሁ ራሶቻችሁን ላጭታችሁ አሳጥራችሁም የማትፈሩ ስትሆኑ የተከበረውን መስጊድ በእርግጥ ትገባላችሁ..." ያለውንና በሱረቱ አር-ሩም ቁጥር 2-3 "ሮም ተሸነፈች፤ በጣም ቅርብ በሆነችው ምድር። እነርሱም ከመሸነፋቸው በኋላ በእርግጥ ያሸንፋሉ፤ በጥቂት ዓመታት ውስጥ (ያሸንፋሉ)..."ያለውን መጥቀስ ይቻላል።

አምስተኛው መገለጫ፡- እርሱነቱ ዘውታሪ፣ ተአምሩ ዘላለማዊ፣ የዓመታት መቀያየር ምንም የማይበግረው፣ እስከ ዕለተ-ቂያማ ድረስ የዘመን መለዋወጥ ክብሩን የማይቀንሰው መሆኑ ሌላ ተአምር ነው። ቁርአን ዘውታሪና ዘላለማዊ ከመሆኑ ጋር አላህ (ሱ.ወ) ሊጠብቀው ቃል ገብቶለታል፡-

﴿ إِنَّا نَحۡنُ نَزَّلۡنَا ٱلذِّكۡرَ وَإِنَّا لَهُۥ لَحَٰفِظُونَ ﴾الحجر: ٩

"ቁርአንን እኛው አወረድነው፣ እኛም ለርሱ ጠበቂዎቹ ነን።" (አል-ሒጅር: 9)

﴿ لَّا يَأۡتِيهِ ٱلۡبَٰطِلُ مِنۢ بَيۡنِ يَدَيۡهِ وَلَا مِنۡ خَلۡفِهِۦۖ تَنزِيلٞ مِّنۡ حَكِيمٍ حَمِيدٖ ﴾فصلت: ٤٢

"ከኋላውም ከፊቱም ወሸት አይመጣበትም ጥበበኛ ምስጉን ከሆነው ጌታ የተወረደ ነው።" (አል-ፉሲለት፡ 42)

ስድስተኛው መገለጫ፡- ባጠቃላይ አረቦችም ሆነ በተለይም ደግሞ ነቢዩ ሙሐመድ ከነቢይነታቸው በስተፊት በዘመኑ የማያውቁት፣ በዚያን ጊዜ አሉ የሚባሉ ሊቃውንቶች ያልደረሱበት፣በወቅቱ ከነበሩት ጽሁፎቻቸው ያልተጻፈ

ትምህርትና ዕውቀትን ቁርአን ሰብስቦ የያዘ መሆኑ ሌላኛው ተአምር ነው፡፡ አላህ እንዲህ በማለት እውነትን ተናገረ፡-

﴿ وَلَقَدۡ ضَرَبۡنَا لِلنَّاسِ فِي هَٰذَا ٱلۡقُرۡءَانِ مِن كُلِّ مَثَلٖ لَّعَلَّهُمۡ يَتَذَكَّرُونَ ﴾الزمر: ٢٧

"በዚህም ቁርአን ወስጥ ለሰዎች ይገሠጹ ዘንድ ከየምሳሌው ሁሉ በእርግጥ አብራራን፡፡'' (አዝ-ዙመር፡ 27)

ሰባተኛው መገለጫ፡- የቁርአን ሳይንሳዊ ተአምራት፡- ቁርአንን ለሚያነብና በሰው ልጅና በዩኒቨርስ እንዲሁም በሌሎች የሳይንስ ጥናት ዘርፎች ግንዛቤ ያለው ሰው የሚረዳው ነገር ቢኖር በሰው ልጅ አእምሮ ለተገኙ ማንኛውም አይነት ሳይንሳዊ እውነታዎች በሙሉ በምልከታ ወይም በቀጥተኛ መልኩ በቁርአን ውስጥ የተጠቀሰ መነሻ እንዳላቸው ነው፡፡ *(ሳይንሳዊ ተአምሮች በተከበረው ቁርአን ውስጥ፤ ሸህ ዘንዳኒና ዶክተር ዘግሉል አል-ነጃር የተወሰደ)*

ይህ የቁርአን ባህሪ መቆሚያ የሌለው ነው፡፡ የሰው ልጅ የሳይንሳዊ ዕውቀቱ እየሰፋ በሄደ ቁጥር የቁርአን ተአምራዊነት፣ አስደናቂነትና ታላቅነቱ ለሳይንቲስቶች የበለጠ ግልፅ እየሆነ ይመጣል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ በማለት እውነትን ተናግሯል፡-

﴿ سَنُرِيهِمۡ ءَايَٰتِنَا فِي ٱلۡأٓفَاقِ وَفِيٓ أَنفُسِهِمۡ حَتَّىٰ يَتَبَيَّنَ لَهُمۡ أَنَّهُ ٱلۡحَقُّۗ أَوَلَمۡ يَكۡفِ بِرَبِّكَ أَنَّهُۥ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ شَهِيدٌ ﴾ فصلت: ٥٣

"እርሱም (ቁርአን) እውነት መሆኑን ለነርሱ እስከሚለጽላቸው ድረስ በአፅናፎቹ ወስጥና በነፍሶቻቸውም ወስጥ ያሉትን ተአምራቶቻችንን በእርግጥ እናሳያቸዋለን፡፡ ጌታህም እርሱ በነገሩ ሁሉ ላይ ዐዋቂ መሾኑ አይበቃህምን?'' (ፉሲለት፡ 53)

ስምንተኛው መገለጫ፡- ቁርአን እርሱን የሚያዳምጡ ሰዎችን ልብ በአስገራሚ ሁኔታ የመማረክ ኃይሉና በሚያነቡት ሰዎች ላይ የሚፈጥረው ከባድና ብርቱ ተፅእኖ ሌላኛው የተአምር መገለጫ ነው፡፡ ቁርአን በአስተባባዮች ላይ የሚያሳድረው ጫና በጣም ከባድና አደገኛ ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ (አስተባባዮች) ለራሳቸው፣ ለሴቶቻቸውና ለልጆቻቸውም ጭምር ቁርአንን ማዳመጥ ከሚፈጥርባቸው ተፅዕኖ በመፍራት እንዲህ ይሉ እንደነበር በሱረቱ ፉሲለት ቁጥር 26 ተገልጿል፡-

"ይህንን ቁርአን አትስሙ ታሸንፉም ዘንድበርሱ ወስጥ (ሲነ በብ) ተንጫጩ፡ "

የአማኞችን ሁኔታ ስንመለከት የቁርአን ድንቅ ማራኪነት፣ በነፍሶቻቸው ላይ የሚያሳድረው ብርቱ ተፅኖና እንዲሁም በልቦቻቸው ላይ የሚፈጥረው ልዩ የክብር ስሜት ይህንን መለኮታዊ መጽሐፍ እንዲናፍቁት፣ ሌሎች ሥነ-ጽሑፎችንም ሆነ ንግግሮች እንዲርቁና ከምንጭ አጠገብ እንደበቀለ ቡቃያ ልባቸውን የሚያረጥቡበት የሕይወታቸው አካል አድርገውት እንዲኖሩ አስችሏቸዋል። ለመሆኑ ለዚህ ሁሉ ምስጢሩ ምንዲን ነው? በሙእሚኖች ደም ውስጥ የተሰራጨው ይህ አዲስ ሩሕ ምን ይሆን? የሙስሊሞችን ነፍስ በበላይነት የማረከው ይህ ተአምር ምን ይሆን? እርሱ በርግጥ አላህ (ሱ.ወ) ይህንን የሚድረግ ኃይል የቸረው የራሱ የአላህ (ሱ.ወ) መጽሐፍ (ቁርአን) ነው። አላህ (ሱ.ወ) ስለ ቁርአን በሱራ አዝ-ዙመር አንቀጽ 23 እንዲህ ብሏል፡-

﴿ ٱللَّهُ نَزَّلَ أَحۡسَنَ ٱلۡحَدِيثِ كِتَٰبٗا مُّتَشَٰبِهٗا مَّثَانِيَ تَقۡشَعِرُّ مِنۡهُ جُلُودُ ٱلَّذِينَ يَخۡشَوۡنَ رَبَّهُمۡ ثُمَّ تَلِينُ جُلُودُهُمۡ وَقُلُوبُهُمۡ إِلَىٰ ذِكۡرِ ٱللَّهِۚ ﴾ الزمر: ٢٣

"አላህ ከዜና ሁሉ ሚልካምን ተመሳሳይ ተደጋጋሚ የኾነን መጽሐፍ አወረደ፤ ከርሱ (ግሣጼ) የነዚያ ጌታቸውን የሚፈሩት ሰዎች ቆዳዎች ይኮማተራሉ፤ ከዚያም ቆዳዎቻቸውና ልቦቻቸው ወደ አላህ (ተስፋ) ሚዘታዎስ ይለዝባሉ..." (አዝ-ዙመር፡ 23

በሱራ-አል-ሐሽር አንቀጽ 21 ደግሞ እንዲህ ይላል፡-

﴿ لَوۡ أَنزَلۡنَا هَٰذَا ٱلۡقُرۡءَانَ عَلَىٰ جَبَلٖ لَّرَأَيۡتَهُۥ خَٰشِعٗا مُّتَصَدِّعٗا مِّنۡ خَشۡيَةِ ٱللَّهِۚ ﴾ الحشر: ٢١

"ይህንን ቁርአን በተራራ ላይ ባወረድነው ኖሮ ከአላህ ፍራቻ (የተነሳ) ተዋራጅ፣ ተሰንጣቂ ኾኖ ባየኸው ነበር..." (አል-ሐሽር፡ 21)

የመጨረሻ ጥያቄዎች

1. በመጻሕፍት ማመን ምን ማለት እንደሆነ አብራራ።
2. ከፊሎቹን የቁርአን ልዩ ባህሪያት ጥቀስ።
3. ከፊሎቹን የቁርአን ተአምራዊ ገፅታዎች አብራራ።

ምዕራፍ አራት

ቆይታ
ከአላህ መልዕክተኛ
(ሰ.ዐ.ወ) ታሪክ ጋር

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) በሒራእ ዋሻ ውስጥ መገለል

የትምህርቱ አላማ

1. የአላህ መልዕክተኛ(ሰ.ዐ.ወ) በሒራእ ዋሻ የነበራቸውን መገለል እንዲያብራራ ማስቻል።
2. እጅግ ከላቀውና ከተከበረው አላህ ጋር የሚደረግ መገለል ከሚሰጣቸው ጥቅሞች መካከል የተወሰኑትን እንዲገልፅ ማስቻል።
3. እጅግ ከላቀውና ከተከበረው አላህ ጋር የሚደረግ መገለልን ሊያጎናፅፉ የሚያስችሉ አንዳንድ ዕውቀታዊ ስልቶችን እንዲፈፅም ማስቻል።
4. እጅግ ከላቀውና ከተከበረው አላህ ጋር በብቸኝነት ሲገለል የተሰማውን ስሜትና ያገኛቸውን አንድ አንድ ጥቅሞች እንዲዘረዝር ማስቻል።

ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ) እድሜያቸው ወደ 40 እየተቃረበ ሲመጣ፥ ከወትሮው በተለየ ከሰው መነጠልን በተለያዩ ጊዜያት እየወደዱት መጥተዋል። አላህም ለመገለያው ቦታ የሒራእ ዋሻን እንዲወዱት አድርጓቸዋል። ሒራእ ማለት ከመካ በሰሜን ምዕራብ በኩል የሚገኝ ተራራ ሲሆን ነቢያችንም (ሰ.ዐ.ወ) ዋሻው ውስጥ ለብዙ ሌሊቶች፣ አንዳንዴም አስር፣ ሌላ ጊዜም ከዚያም በላይ እስከ ወር ለሚዘልቁ ቀናት አላህን በመገዛት ያሳልፉ ነበር።

ከዚያ ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ። ብዙም ሳይቆዩ ለሚቀጥለው ኸልዋ በአዲስ ስንቅ ይቋጥሩ ነበር። በእነዚህ ኸልዋዎች (መገለሎች) በአንደኛው ላይ ወሕይ እስከመጣላቸው ድረስ በዚህ ሁኔታ አሳልፈዋል።

ኸልዋ /አላህን ለመገዛት መገለል/

የነቢያችንን (ሰ.ዐ.ወ) ልቦና እንዲህ በፍቅር የገዛው ኸልዋ፥ ለአጠቃላይ ሙስሊሞች በተለይ ደግሞ ወደ ኢስላም ለሚጣሩ ዳዒዎች እጅግ የላቁ ጠቀሜታዎች አሉት። ከዚህም መካከል፦

1. በልቦና ሙስጥ እጅግ የተላቀሙና የተከበረሙ አላህ ፍቅር እንዲገለብት ማስቻል

አላህን (ሱ.ወ) እንደሚወድ አእምሯዊ መረጋጋት ብቻውን በቂ አይደለም። ይህ ቢሆን ኖሮ ኦሬንታሊስቶች[1] አላህንና ነቢያቸንን /ሰ.ዐ.ወ./ ወዳጅ ከሆኑት ተርታ ይሰለፉ ነበር። ለመሆኑ ለአንድ ሂሳባዊ የስሌት ህግ አለያም አል-ጀብራ ጥያቄ ከምሁራን ራሱን አሳልፎ መስዋእት ስላደረገ አንድ ምሁር ሰምታችኋልን; ታውቃላችሁን?... በእርግጥ በአላህ ከማመን በኋላ ወደ እሱ ውዴታ መዳረሻ መንገዶች በዋነኝነት የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ. የታላቅነቱ ማረጋገጫ የሆኑ ምልክቶችን፤ ውለታውና ፀጋዎቹን በብዛት ማስተንተን፣

ለ. በአንደበትና በልቦና እሱን (አላህን) ማውሳት ማብዛት፣

ሐ. ግዴታ የሆኑ ተግባራትን በጥንቃቄ ተጠባብቆ መሥራት ሱንና /ነዋፊል/ የሆኑትንም ማብዛት።

ይህ ሁሉ ሊገራ የሚችለው በተደጋጋሚ ከአላህ ጋር መገለልን /ኸልዋ/ በማዘውተር ነው።

2. የነፍስን ዝለምታዎች ማከምና በስንክ-ሳሮቿ ላይ እሷን መተሳሰብ

የሰው ልጅ ነፍስ ከሰዎች ተነጥሎ በመተሳሰብና ያለፈቻቸውን ድንበሮች እያስታወሱ ጉድለቶቿን ማስተዋል እንጂ የማይታከሙ የብዙ በሽታዎች መናኸሪያ ናት።

አንዳንዴ የሰው ልጅ በውጫዊ ገጽታው በበርካታ መልካምና አምልኮታዊ ተግባራት የታጀበ፣ ሌሎች ሰዎች ወደ መልካም ነገር በመጥራት ላይ የተሰማራ በሆነበት ሁኔታ እነኳን በልቦና ውስጥ ስር ሰደው ልቦናን የሚቆጣጠሩና

[1] ሙስሊም ያልሆኑ ኢስላምንና ሌሎች ሃይማኖትን የሚያጠኑ ሃይማኖተ-አልባ፣ የሩቅ ምስራቅን አስተሳሰብ የሚያራምዱ ምሁራን

ብርሃኑንም የሚያከስሙ በሆኑት ራስን መኮፈስ፣ ጉራ፣ ታይታ፣ ምቀኝነትና ዓለማዊ ፍቅር ችግሮች ሊጠቃ ይችላል።

ብቻውን ሆኖ ሲያስተነትን ግን የሰው ልጅ የነፍስያ እውነታ ይገለጽለታል። ምን ያህል ነፍስ አላህን ፈላጊና ደሀ እንደሆነች፣ በያንዳንዷ ቅጽበት የሱን (የአላህን) እርዳታ ፈላጊ መሆኗ፤ ሰዎች እሱን ለመጥቀምም ሆነ ለመጉዳት የማይችሉ ደካሞች መሆናቸውን ይደርስበታል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሙገሳቸውም ሆነ ወቀሳቸው ውጤት አልባ እንደሆነ ይገለጥለታል፤ ይህና ሌሎችም መሠል እውነታዎች ፍንትው ብለው ሲታዩት ሥራውን ለአላህ ብቻ አጥርቶ ይሰራል፤ ይተናነሳል... ወዘተ.። በተደጋጋሚ መገልልን /ኸልዋን/ በማብዛቱ የተነሳ ባገኘው ብርሃን የነፍሱ በሽታዎች ፍንትው ብለው ይገለጣሉ።

ተግባራዊ እሳቤዎች

ይህ ሁሉ እውን የሚሆነው ራስን ከዓለማዊ ጭንቀቶችና ሁከቶች፣ ከከንቱ ብለጭልጭ በቀን፣ በለሊት፤ በወራትና፤ በዓመታት ለተወሰኑ ግን ተደጋጋሚ ለሆኑ ወቅቶች ገለል ብሎ ራስን መመልከት ሲቻል ነው። ለምሳሌ

1. በረመዷን የመጨረሻው አስር ቀናት ወይም በየወሩ አንዲት ምሽት በመስጂድ ውስጥ ኢዕቲካፍ ማድረግ፣
2. በየሌሊቱ የመጨረሻው 1/3ኛ ክፍል የኢስቲግፋር ወቅት፣
3. በጠዋት እና በማታ ውዳሴ /አዝካር/ ወቅት አዝካሮችን ማድረግ፣
4. ከመኝታ በፊት ነፍስን መተሳሰቢያ አጋጣሚ መኖርና የመኝታ ዚክር ማድረግ፣
5. መስጂድ ለመስገድ በጊዜ መሄድ፣ ለሰላት ቁጭ ብለውም ሲጠባበቁ፣
6. ከሰላት በኋላ ቁጭ ብሎ ዱዓ በማድረግ ወቅት ላይ፣
7. ሌላው ቢቀር አዛን እየሰማ ከሙአዚኑ ተከትሎ ካለ በኋላም ሊሆን ይችላል፣ ከላይ የተጠቀሱት ጊዜያት ሁሉም ቀልብ ከዱንያ ጋ ያለውን መገናኛ

በመቁረጥ ትኩረቱን ትልቅና አሸናፊ ወደ ሆነው አላህ በአዲስ መልክ የሚያቆራኝበት ወቅቶች ናቸው።

የመጨረሻ ጥያቄዎች

1. የነቢያችንን (ሰ.ዐ.ወ) በብቸኝነት መገለል (ኽልዋ) አብራራ።
2. ከኽልዋ ጥቅሞች ከፊሉን አብራራ።
3. ወደ አላህ ጋ በብቸኝነት መገለልን ከሚያጎናጽፉ መንገዶች ከፊሎቹን ጥቀስ።
4. ለራስህ የተገበርከው ለሌሎችም የምትመክረው ከአላህ (ሱ.ወ) ጋር ለመገለል (ኽልዋ) የምትጠቀምባቸው መንገዶች እንዲሁም ያገኘኸውን ውጤትና ያሳደረብህን አዎንታዊ ተፅዕኖ ጥቀስ።

የወሕዩ መጀመር

የትምህርቱ ዓላማ

1. ከወሕይ መውረድ በፊት የተከሰቱ መንደርደሪያ ትእይንቶችን እንዲገልጽ ማስቻል።
2. ወሕይ በወረደበት ወቅት እናታችን ኸዲጃ (ረ.ዐ) የነበራቸውን አቋም እንዲገልጽ ማስቻል።
3. የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) የተከሰተባቸውን ክስተት ለወረቀት ኢብኑ-ነውፈል በነገሩት ጊዜ ምላሹ ምን እንደነበረ እንዲጠቅስ ማስቻል።
4. ከዚህ የታሪክ አጋጣሚ የሚገኙትን ትምህርቶች እና ምክሮች ነቅሶ እንዲያወጣ ማስቻል ናቸው።

ኢማም አል-ቡኻሪ ከእመት ዓኢሻ (ረ.ዐ) የወሕይ አጀማመር እንዴት እንደነበር የገለጹበትን ዘገባ ዘግበዋል። ዓኢሻ (ረ.ዐ) እንዲህ ብለዋል፦

«የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) (ከወሕይ) የጀመራቸው መልካም ሕልሞችን በእንቅልፋቸው መመልከት ነው። ልክ እንደ ንጋት ጎህ ሆና የምትከሰት ብትሆን እንጂ ሕልም አያዩም ነበር። መገለልን ወደዱ። በሒራእ ዋሻ ውስጥ ብቻቸውን ለዚህ የሚሆን ስንቅን ለመሰነቅ ወደ ቤተሰቦቻቸው ሳይመለሱ ብዙ ሌሊቶችን ያሳልፉ ነበር። ከዚያም ወደ ኸዲጃ (ረ.ዐ) ይመለሱና ስንቅ ይሰንቃሉ። በሒራእ

ዋሻ ውስጥ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ከጌታቸው የሆነው እውነት እስከመጣላቸው ድረስ ቀጥለው ነበር።።

መልአክ መጥቶ “አንብብ” አላቸው።። ‹እኔ አንባቢ አይደለሁም› በማለት መለሱ።።በጣም እስክደክም ድረስ ጭምቅ አደረገኝና ለቀቀኝ። እንደገና ‹አንብብ› አለኝ። ‹እኔ አንባቢ አይደለሁም› ስል መለስኩኝ። ይዞኝ በድጋሚ በጣም እስክደክም ድረስ ጭምቅ አድርጎኝ ለቀቀኝና ‹አንብብ አለኝ› እኔም ‹አንባቢ አይደለሁም› አልኩት። ለሶስተኛ ጊዜ በጣም እስክደክም ድረስ ጨምቆ ለቀቀኝና እንዲህ በማለት ተናገረኝ፡-

﴿ٱقۡرَأۡ بِٱسۡمِ رَبِّكَ ٱلَّذِي خَلَقَ ١ خَلَقَ ٱلۡإِنسَٰنَ مِنۡ عَلَقٍ ٢ ٱقۡرَأۡ وَرَبُّكَ ٱلۡأَكۡرَمُ ٣ ٱلَّذِي عَلَّمَ بِٱلۡقَلَمِ ٤ عَلَّمَ ٱلۡإِنسَٰنَ مَا لَمۡ يَعۡلَمۡ ٥﴾ العلق: ١ - ٥

“አንብቡ በዚያ (ሁሉን) በፈጠረው ጌታህ ስም። ሰውን ከረጋ ደም በፈጠረው (ጌታህ ስም)። አንብቡ ጌታህ በጣም ቸር ሲሆን፤ ያ በብዕሪ ያስተማረ፤ ሰውን ያላወቀውን ሁሉ ያሳወቀ ሲሆን።።” (አል-ዐለቅ፡ 1-5)

አላህ በፍፁም የማያዋርዳቸው ሰዎች ባሕሪያት

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ልባቸው በጣም እየመታና እየተርገፈገፉ ወደ ባለቤታቸው ኸዲጃ ቢንት ኹወይሊድ (ረ.ዐ) ዘንድ ተመለሱ።። ‹አከናንቡኝ፤ አከናንቡኝ› አሉ።። የያዛቸው ፍርሃት እስኪለቃቸው ድረስ አከናነቧቸው።። ለኸዲጃ (ረ.ዐ) ክስተቱን ሁሉ እንዲህ በማለት ነገሯቸው።። “በእርግጥ እኔ ለነፍሴ ፈራሁ!” ኸድጃም (ረ.ዐ) “በፍፁም! በአላህ እምላለሁ! አላህ በጭራሽ አያዋርድህም አንተኮ ዝምድናን የምትቀጥል፤ የተቸገረን የምትረዳ፤ እንግዳን የምታከብር፤ ለሌላቸው ሰጪና ሐቅ ላይ የምትተባበር ነህ።።” አለቻቸው።።

የሰዋቂ ምስክርነትና ቀደሞች ፈለግ

ኸዲጃ (ረ.ዐ) ነቢያችንን ወደ ወረቀት-ኢብኑ ነውፈል ዘንድ ወሰደቻቸው።። ወረቀት ኢብኑ ነውፈል የኸድጃ አጎት ልጅ ሲሆን በጃሂሊያው ዘመን ክርስትናን

የተቀበለ ሰው ነው፡፡ ከወንጌልም አላህ የፈለገለትን በኢብራይስጥ ቋንቋ ይፅፍ ነበር፡፡ከእርጅናም ብዛት ዓይኑ ታውሮ ነበር፡፡ ኸዲጃም(ረ.ዐ) “የወንድሜ ልጅ ሆይ! እስቲ የወንድምህ ልጅ የሚልህን ስማ፡፡” አለችው፡፡ ወረቀትም ለአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) የወንድሜ ልጅ ሆይ ምንድነው የሚታይህ በማለት ጠየቃቸው፡፡

የአላህ መልዕክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) የታያቸውን ነገር ነገሩት፡፡ ወረቀትም፣ ‹‹ይህማ በሙሳ (ዐ.ሰ) ላይ የወረደው ሕግ ነው (ጂብሪል ወይም ወሕይ)፡፡

ዋ! ጠንካራ ወጣት ሆኜ በነበር! ዋ! ያኔ ወገኖችህ ከሀገርህ ሲያስወጡህ በሕይወት ኖሬ በነበር!» አለ፡፡ የአላህ መልዕክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) ‹‹እውን ያስወጡኛልን? በማለት ጠየቁት፡፡›› “እሱም፣ አዎ አንድም ሰው አንተ በመጣህበት ተመሳሳይ የመጣ በጭራሽ የለም ጠላት የሚያፈራ ቢሆን እንጂ፣ ቀኑን ካደረሰኝ ሁነኛ እገዛን ባገዝኩህ ነበር››፡፡ ወረቀት ግን ብዙም ሣይቆይ ሞተ፡፡ ወህይም ተወሰኑ ጊዜያት ተቋረጠ፡፡

ቡኻሪ ከጃቢር ኢብኑ ዐብደላህ (ረ.ዐ) እንደዘገቡት ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ) ስለ ወሕይ መቋረጥ ሲናገሩ ‹‹በመሄድ ላይ ሳለሁ ከሰማይ አንዳች ድምጽ ሰማሁ፡፡ ዓይኔን ወደዚያው ቀና አደረግኩ፡፡ ያ ሒራእ ዋሻ ውስጥ የመጣብኝ መልአክ በምድርና ሰማይ መካከል በሆነ ዙፋን ላይ ተቀምጧል፡፡ በጣም ደነገጥኩኝ፡፡ በፍጥነትም ተመልሼ ‹አከናንቡኝ! አከናንቡኝ!› አልኩ፡፡ አላህም

‹‹አንተ (ልብስህን) ደራቢው ሆይ፡፡ ተነስ አስጠንቅቅም፡፡ ጌታህንም አተልቅ፡፡ ልብስህንም አፅዳ፡፡ ጭቃትንም ራቅ፡፡ ማዘዝትንም የምትፈልግ ኾነህ (በረከትን) አትለግስ፡፡ ለጌታህም ታገስ፡፡ ›› የሚለውን አንቀድ አወረደ፡፡

ቀጥሎም ወሕይ ተቋረጠ”

ወህይ የተቋረጠበትን የጊዜ ቆይታ በተመለከተ የተለያዩ ንግግሮች የተሠነዘሩ ሲሆን ትክክለኛው ለተወሰኑ ቀናት ነበር የሚለው ነው፡፡ ኢብኑ ሰዕድ ከኢብኑ

ዐባስ ያወሩት ይህን የሚደግፍ ነው (አር-ረሒቁል- መኽቱም፣ ሰፊዩ አር-ረህማን አል-ሙባረኽፉሪ)

የመመዘኛ ጥያቄዎች

1. አንድ ሙእሚን የግድ ከነፍሡ የሚሆንበትና የሚተሳሰብበት ጊዜ የግድ ሊኖረው ይገባል? ይህን በሚገባ አብራራ፡፡ ራስህን አጉድለህ ስታገኘው የሚሰማህ ስሜት ምንድን ነው?
2. ለአንድ ሙእሚን አላህ እንዳያዋርደው ቢኖሩት የሚገቡና የግድ የሆኑ ባህሪያት አሉ፡

   - እነዚህን ባህሪያት አብራራ
   - አንተን በጣም የጎደለህና ማሟላት የሚያስፈልግህ?የትኛው ባህሪነው

3. ወረቀት ኢብኑ ነውፈል የአላህ መልዕክተኛ(ሰ.ዐ.ወ)የተናገረውን አስተንትን፡፡ ይህን ስታነብ ምን ተሰማህ?
4. የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ ወሕይ ከጀመረበት ክስተት ያገኘኸውን ትምህርትና ተሞክሮ ነቅሰህ አቅርብ፡፡

ምስጢራዊ የዳዕዋ ሂደት

የትምህርቱ አላማ

1. ምስጢራዊ ደዕዋን ሲባል ምን ለማለት እንደተፈለገ እንዲያብራራ ማስቻል
2. በዳሩ-ል አርቀም ውስጥ የነበረው የትምህርታዊ ግንኙነቶችን አስፈላጊነት እንዲያብራራ ማስቻል
3. በቅድሚያ ወደ ኢስላም የገቡ ሰዎችን ስም እንዲዘረዝር ማስቻል
4. ከዚህ የሲራ ክፍል የሚገኘውን ጠቃሚ ትምህርትና ፋይዳ ነቅሶ ማውጣት እንዲችል ማስቻል፡፡

ከወሕይ መውረድ በኋላ ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ) ለአላህ ትእዛዝ አዎንታዊ ምላሽ መስጠት ጀመሩ፤ አላህን በብቸኝነት ማምለክና ጣኦታትን ወደ መተው መጣራትን ተያያዙት፡፡ ነገር ግን ቁረይሾች ለጣኦቶቻቸው እና ለሽርክ አምልኮዎቻቸው ካላቸው ጭፍን ታማኝነትና ወገንተኝነት አንጻር ጥሪው ድንገተኛ እንዳይሆንባቸው በመስጋት ደዕዋውን በምስጥር ያካሂዱ ነበር፡፡ በቁረይሾች አደባባዮች በግልፅ ደዕዋ አያደርጉምም ነበር፡፡ በጣም የሚቀርባቸው ዘመድ ወይም ከዚህ በፊት ለሚያውቁት ሰው ካልሆነ በስተቀር ጥሪያቸውን አያደርጉለትም ነበር፡፡

ቅን ግንባር ቀደሞች

ኸዲጃ፣ ዐሊይ ኢብኑ አቢ ጧሊብ፣ የነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ) ያሳደጉትና አገልጋያቸው የነበረው ዘይድ ኢብኑ ሐሪሳ፣ አቡበክር ኢብኑ አቢቁሐፋ፣ ዑስማን ኢብኑ ዐፋን፣ ዙበይር ኢብኑል ዐዋም፣ ዐብዱረሕማን ኢብኑ ዐውፍ፣ ሰዕድ ኢብኑ አቢወቃስ... (ረ.ዐ) እና አቡበክር (ረ.ዐ) ጥሪ ያደረጉላቸው በግንባር ቀደምትነት ይሰለፋሉ፡፡

ትምህርታዊ የስነላ ግንኙነቶች በአርቀም ቤት

እነዚህ ሰሐቦች ከነቢያችን ጋ በምስጢር ይገናኙ ነበር፡፡ አንደኛቸው መስገድ አልያም ዒባዳ ማድረግ ሲፈልግ ከቁረይሾች እይታ ለመደበቅ መካ ውስጥ ከሚገኙ ጥጎች ወደ አንዱ ጥግ ይሄድ ነበር፡፡ ወደ ኢስላም የሚገቡት ወንድና ሴቶች ቁጥር ከሰላሳ ሲበልጥ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ከነርሱ መካከል የአንዳቸውን ቤት መረጡላቸው፡፡ ይህ ቤት የአርቀም ኢብኑ አቢ አርቀም ቤት ነበር፡፡ ለመማር፣ ለእነዛ (ተርቢያ)ና የጥሪውን ጉዳይ እየተገናኙ ለማስተማር ይመች ዘንድ ነበር ይህን ቤት የመረጡት፡፡ በዚህ ወቅት ዳዕዋው ደርሷቸው ወደ ኢስላም የገቡ ሰዎች ቁጥር አርባ አካባቢ ይደርስ ነበር፡፡ ታዲያ አብዛኞቹ ድሆች፣ ባሪያዎችና በቁረይሽም ዘንድ ቦታ የማይሰጣቸው ግልሰቦች ነበሩ፡፡

የዳዕዋው ድብቅነት ለዳዕዋው ችግርን ከመስጋት እንጂ ለነፍስ ከመፍራት የመነጨ አልነበረም፡፡ ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ) በመጀመሪያዎቹ ሶስት ዓመታት የድብቅ ዳዕዋን የመረጡበት ምክንያት ለራሳቸው ከመስጋት የመነጨ አልነበረም፡፡ በርግጥ ዳዕዋውን ከጅምሩ ለሁሉም አይነት ሰዎች ግልጽ እንዲያደርጉት ጌታቸው

ቢያዛቸው ኖሮ ከፊታቸው ሞት ቢጠብቃቸው እንኳን ለመፈጸም ምንም ሰዓት አያባክኑም ነበር።

ነገር ግን የመጀመሪዎቹን የዳዕዋ ጊዜያት ዳዕዋውን በድብቅና በምስጢር ያምኑልኛል፣ ይቀበሉኛል እንዲሁም ዳዕዋው ያሸንፋቸዋል ብለው ላሰቧቸው ሰዎች ብቻ እንዲያደርጉ አላህ አሳውቋቸዋል። ይህም የሆነው በአላህ ላይ የሚኖረን መሰረታዊ ኢማን እንዳይበረዝና ቀጥሎ የሚመጡ ዳዒዎች በአላህ ላይ ብቻ በመተማመን እና በመታገዝ ላይ እንዲያተኩሩ ትምህርት እንዲሆን ነው።

ከዚህ በመነሳት በየትኛውም ዘመን የሚኖሩ የኢስላማዊ ዳዕዋ ባለቤቶች ዳዕዋቸውን የሚያደርጉበትን ስልት (በምስጢር ወይስ በግልፅ የሚለውን) ካሉበት ዘመን ሁኔታና ተጨባጭ አንፃር መወሰን ይችላሉ ማለት ነው። ይህ የኢስላም ሸሪዓ ገር ከመሆኑ አንፃር የተቀመጠ ሲሆን ስልቱ የነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ) ሲራ ላይ የተመረኮዘ እንዲሁም ከላይ የተጠቀሱትን አራት ሂደቶችን መሰረት ያደረገ በዋነኝነት የሙስሊሞችና የዳዕዋውን (ጥቅም) ከግምት ያስገባ መሆኑ ነው።

ለዚህም ነው አብዛኞቹ ሙስሊም ሊቃውንት፤ ሙስሊሞች በቁጥር ሲያንሱ ወይም በዝግጅት ደካማ ሲሆኑ፣ ጠላቶቻቸው ላይ ምንም አይነት ተፅእኖ መፍጠር ሳይችሉ እንሸነፋለን ወይም ጠላቶቻችን ይጎዱናል ብለው ከጠረጠሩ ነፍስን የመጠበቅ ጉዳይ ቅድሚያ ሊሰጠው እንደሚገባ የተስማሙት። ምክንያቱም ዲንን ጠብቆ ለማቆየት በየትኛውም መልኩ ሕይወትን ጠብቆ ማቆየት የግድ ይለናል።

እውነታው ላይ ላዩን ስንመለከተው ለነፍስ ቅድሚያ መስጠት ይመስላል። ነገር ግን ጉዳዩን በጥልቀት ከተመለከትነው በተጨባጭ ዲንን ጠብቆ ማቆየት ሆኖ እናገኘዋለን። በዚህ እይነት የሙስሊሞችን ነፍስ በሰላም ጠብቆ ማቆየት፤ ወደፊት እንዲጓዙና ሌሎች ክፍት የሆኑ ሜዳዎች (የዳዕዋ ዘርፍና ስልቶች) በተገኙ ጊዜ ትግል እንዲያደርጉ እድል ስለሚሰጣቸው ለዲኑ ቅድሚያ ተሰጥቷል እንላለን። ይህ ሳይሆን ቢቀርና ሙስሊሞች ቢጠፉ በዲኑ ላይ የመጣ ጉዳት ተደርጎ ይወሰዳል።

ደካሞችና ድኾች ቀድመው ለጥፊው ምላሽ ይሰጡ የነበረው ለምንድን ነው?

የአላህ መልዕክተኛን (ሰ.ዐ.ወ) የሕይወት ታሪክ የዘገቡ ድርሳናት እንደሚገልፁልን በምስጢራዊው ዳዕዋ ወቅት ወደ ኢስላም የገቡት ሰዎች በአብዛኛው ድኾች፣ ደካሞችና ባሪያዎች የተቀላቀሉበት ነበር። ታዲያ ከዚህ ጀርባ ያለው ጥበብ ምንድን ነው? ኢስላማዊ መንግስቱስ ሲመሰረት በነዚህ ሰዎች መሰረት ላይ የመገንባቱ ምስጢርስ ምንድን ነው?

መልሱ፡- ይህ የነቢያት ዳዕዋ የመጀመሪያው ሂደት የሚያስተናግደው ተፈጥሮአዊ ክስተት ነው። ምስጢሩም፤ አላህ ሁሉንም መልእክተኞች ሲልካቸው ከሰው ልጅ አገዛዝና የስልጣን ተፅእኖ ወደ አላህ ብቸኛ አስተዳደርና ስልጣን ነፃ ያወጡ ዘንድ ነው። ራሳቸውን አማልክትና ፈላጭ ቆራጭ አድርገው የበላይ ነን የሚሉትን አምባገነኖች ምንነት የሚያዋርድና የሚያንኮታኩት ጥሪ ነው። ይህም ከደካሞች፣ ከተዋረዱ እና ከባሪያዎች ሁኔታ ጋር ስለሚገጣጠም ለጥሪው አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ በአፀፋው እነዚያ አምላክ ነን፣ አስተዳዳሪዎችም ነን ባዮች ከመኩራራትና ከጥላቻ በዘለለ ለኢስላማዊው ጥሪ መሰናክል ሆነው ይቆማሉ። ይህ እውነታ የበለጠ ግልፅ እንዲሆንልህ በፋርሱ ጦር መሪ ሩስቱም እና በሰዕድ ኢብኑ አቢ ወቃስ ጦር ተራ ወታደር ረቢዕ ኢብን ዓምር መካከል በቃዲሲያ ጦርነት ወቅት የተካሄደውን ንግግር ተመልከት። ሩስቱም እንዲህ አለው *«ምንድን ነው እኛን እንድትዋጉን እና ሀገራችንን ዘልቃችሁ እንደትመጡ ያደረጋችሁ?"* ረቢዕ ኢብኑ ዓሚርም *«እኛ የመጣነው በፍላጎት ሰዎችን ከሰዎች ባርነት ወደ አላህን ብቻ ወደ ማምለክ ነፃነት ለማምጣት ነው»* አለው፤ ከዚያም ከቀኝ እና ከግራ ለሩስቱም ሩኩዕ ያደረጉ ሰዎችን ሰልፍ ተመለከተና በመገረም *«በእርግጥ ከዚህ በፊት ስለናንተ ህልሞች ይደርሱን ነበር። አሁን በተጨባጭ ሳያቸሁ ግን ከናንተ በታች ቂል የሆነን ህዝብ አልተመለከትኩም። እኛ ሙስሊሞች እኮ ከፊላችን ከፊሉን ባሪያ አደርጎ እኮ አይገዛውም! እናንተም እንደኛ በመካከላችሁ በመልካም እንደምትውሉ ነበር የማስበው ምናልባትም በጣም ጥሩ ከሰራችሁት ነገር አንዳችሁ የአንዳችሁ ጌታ (አምላክ) እንደሆናችሁ እየነገራችሁኝ መሆኑ ሊሆን ይችላል ...»*

ይህኔ ደካሞቹ እርስ በርሳቸው መጠቃቀስና ማጉረምረም ጀመሩ *«በአላህ እንምላለን! ይህ አረብ እውነት ተናገረ»* ነገር ግን መሪዎቹ እና አስተዳዳሪዎቹ የረቢዕን ንግግር ውስጣዊ ማንነታቸውን ያፈራረሰ መብረቅ ሆነባቸው። እርስ

በርስም *«በርግጥ ረቢዕ የወረወረው ንግግር ባሮቻችንን ወደ እርሱ ሳይጎትታቸው (ሳያዘናብላቸው) የሚቀር አይደለም አሉ።»*

የመመዘኛ ጥያቄዎች

1. የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) በዳሩ-ል-አር-ቀም ኢብኑ አቢ አርቀም ቤት ውስጥ በርሳቸው ያመኑትን ሰዎች በከፍተኛ ጉጉት ሲሰበስቡ ነበር፤ ባንተ አመለካከት የነዚህ ግንኙነቶች አስፈላጊነት ምንድን ነው? ከእርሱስ እንዴት ልትጠቀም ትችላለህ?
2. *«እኛ ሰዎች ሰዎችን ከማምለክ ባርነት ፍላጎቱ ያለውን ሰው አላህን ብቻ ወደ ማምለክ ነፃነት ለማውጣት አላህ የላከን ህዝቦች ነን»* ይህን የተናገረው ማን ነው ስታነበው ምን ይሰማሀል? ንግግሩስ ምንን ያመለክታል?
3. የመጀመሪያዎቹ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ያመኑትን ሰዎች ስም ጥቀስ? አብዛኛዎቹስ ወጣት መሆናቸውን አስተውልሀልን? ታዲያ ከዚህ ምን ትማራለህ?
4. የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ዳዕዋውን ከቅርብ ዘመዶቻቸው ነው የጀመሩት። ይህ ምንን ያመለክታል? አንተስ ከዘመዶችህ አንፃር ምን እያደረግክ ነው?
5. ይህንን የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) የሕይወት ታሪክ ክፍል በመማርህ በግልህ ያገኘኸውን ጥቅም ጥቀስ።

ደቂቂ ጥቂ

የትምህርቱ አላማ

1. የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ዳዕዋን በይፋ ማድረግ እንዴት እንደጀመሩ እንዲያብራራ ማስቻል።
2. የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ)በይፋ መጥራት እንደጀመሩ መቼ እንዲገልፅ ማስቻል።
3. ቁረይሾች ዳዕዋው ይፋ ሲሆን የነበራቸውን አቋም እንዲያብራራ ማስቻል።
4. ከዚህ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ታሪክ ክፍል ያገኘውን ጠቃሚ ትምህርትና ተሞክሮ ነቅሶ እንዲያወጣ ማስቻል።

5. ከነዚህ ተሞክሮዎችና ትምህርቶች በሕይወቱ ምን ያህል እንደተጠቀመ እንዲያብራራ።

ኢብኑ ሂሻም እንደዘገቡት «ከሴትም ከወንድም ወሬው በመካ ውስጥ እስኪሰራጭ ድረስ ሰዎች በብዛት ወደ ኢስላም ገቡ። ይህ ወቅት የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ዳዕዋውን በድብቅ ማድረግ ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ በአላህ ትዕዛዝ ግልጽ እስከወጣበት ጊዜ የነበሩት ሶስት ዓመታት ናቸው።

﴿ فَٱصۡدَعۡ بِمَا تُؤۡمَرُ وَأَعۡرِضۡ عَنِ ٱلۡمُشۡرِكِينَ ﴿٩٤﴾ ﴾ الحجر: ٩٤

ይህን ጊዜ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) "¾ታ²¡uƒ"U 'Ñ` uÃó ÓKê& ›Ò]-‹"U }ª†¨<።" (አል-ሒጅር፡ 94)

ለሚለው የአላህ ትዕዛዝ ምላሽ መስጠት እና መተግበር ጀመሩ። ሶፋ ተራራም ላይ ወጡና «የፈህር ጎሳዎች፤ የዐዲይ ጎሳ ልጆች... እያሉ ሰዎች እስኪሰባሰቡ ድረስ መጣራቱን ተያያዙት። በዙሪያቸው ሰዎች ይሰባሰቡ ጀመር። ራሳቸው መምጣት ያልቻሉትም ምን እንደሆነ ለማወቅ መልክተኛ ላኩ።

ነቢዩም (ሰ.ዐ.ወ) «በሸለቆው አቅጣጫ ወራሪ ሊወጋችሁ እየመጣ ነው ብላችሁ ታምኑኛላችሁን?» ብለው ጠየቁ። «ውሸት ከአንተ አይተን አናውቅም» ብለው መለሱላቸው። ነቢዩም (ሰ.ዐ.ወ) «እንግዲያውስ ብርቱ ቅጣት እንዳያገኛችሁ አስጠንቃቂያችሁ ነኝ» በማለት ሲናገሩ አቡ ለሀብ በቁጣ ‹ቀኑን ሙሉ የከሰርክ ሆነህ ዋል! የሰበሰብከን ለዚሁ ነውን?› አለ። የሚለው የአላህ ቃል አወረደ

﴿ تَبَّتۡ يَدَآ أَبِي لَهَبٖ وَتَبَّ ﴿١﴾ ﴾ المسد: ١

"የአቡ ለሀብ ሁለት እጆች ከሰሩ (ጠፉ፤ እርሱ) ከሰረም ። " (አል-ለሀብ፡ ነ)

ከዚያም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወረዱ።

﴿ وَأَنذِرۡ عَشِيرَتَكَ ٱلۡأَقۡرَبِينَ ﴿٢١٤﴾ ﴾ الشعراء: ٢١٤

"ቅርብ ዘመዶችህንም አስጠንቅቅ። " (አሽ-ሹዐራእ፡ 214)

ለሚለው የአላህ ቃልም እንዲሁ ምላሽ ሰጡ፡፡ በዙሪያቸው ያሉትን ዘመዶችና የቅርብ ቤተሰቦች ሰበሰቡና «እናንተ የከዕብ ኢብኑ ሉአይ ልጆች ሆይ! ራሳችሁን ከእሳት አድኑ፡፡ የሙረት ኢብኑ ከዕብ ልጆች ሆይ ራሳችሁን ከእሳት አድኑ፤ የዐብድ ሸምስ ልጆች ሆይ ! ራሳችሁን ከእሳት አድኑ፡፡ የዐብድ መናፍ ልጆች ሆይ! ራሳችሁን ከእሳት አድኑ፡፡ የዐብዱል ሙጦሊብ ልጆች ሆይ! ራሳችሁን ከእሳት አድኑ፡፡ ፋጢማ ሆይ! ራስሽን ከእሳት አድኚ፡፡ እኔ ከአላህ ዘንድ ምንም አልጠቅምሽም፡፡ ግና ዘመዶቼ ናችሁና ዝምድናችንን እንከባከባለሁ፡፡»

ዳዕዋው በግልፅ መደረግ ሲጀምር የቁረይሽ ምላሽ ጀርባ መስጠትና ማውገዝ ሲሆን ለዚህም ከአባቶቻቸው የወረሱትን እምነት ፈጽሞ መተው እንደማይችሉ ምክንያት በማቅረብ ነበር፡፡ አላህ ይህን እውነታ ሲናገር ለእነርሱም

﴿ وَإِذَا قِيلَ لَهُمُ ٱتَّبِعُواْ مَآ أَنزَلَ ٱللَّهُ قَالُواْ بَلۡ نَتَّبِعُ مَآ أَلۡفَيۡنَا عَلَيۡهِ ءَابَآءَنَآۚ أَوَلَوۡ كَانَ ءَابَآؤُهُمۡ لَا يَعۡقِلُونَ شَيۡـٔٗا وَلَا يَهۡتَدُونَ ١٧٠ ﴾ البقرة: ١٧٠

«አላህ ያወረደውን ተከተሉ» በተባሉ ጊዜ «አይደለም አባቶቻችንን በርሱ ላይ ያገኘንበትን ነገር እንከተላለን»ይላሉ፤ አባቶቻቸው ምንም የሚውቁና (ወደ እውነት) የሚመሩም ቢሆኑ (ይከተሏቸዋልን?)" (አል-በቀራህ፡ 170)

የአማልክቶቻቸውን ዋጋ-ቢስነት ሲያሳውቋቸው፤ ህልሞቻቸውን ውድቅ ሲያደርጉባቸውና ጣኦት አምልኮት ሙጥኝ ለማለታቸው ያቀረቡትን ምክንያት ውድቅ በማድረግ የአያቶቻቸውና አባቶቻቸው ፈለግ ስለሆነ ብቻ መሆኑን ሲያጋልጧቸው፤ አባቶቻቸው አቅል ሁሉ አእምሮ እንደሌላቸው ሲናገሩ፤ ከነርሱ ውስጥ አላህ በኢስላም ካዳናቸው እንዲሁም ከጎናቸው ቆመው ሲከላከሉላቸው ከነበሩት ከአጎታቸው አቡ ጧሊብ ውጭ ሁሉም ነገሩን ትልቅ ቦታ ሰጥተውት አወገዙትም፤ ፍፁም በጠላትነት ፈርጀው ለመቃወም አደሙ፡፡

ቅድሚያ ለዘመድና ቤተሰብ

ጥያቄ፡- አላህ ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ለምን ዳዕዋውን ለቤተሰቦቻቸውና ዘመዶቻቸው እንዲያደርሱ በተለይ አዘዛቸው?

መልስ፦ እዚህ ውስጥ ባጠቃላይ በሁሉም ሙስሊም በተለይ ደግሞ እንደ ዳዕዋ ሰው የተለያዩ የተጠያቂነት ደረጃዎች እንዳሉ ማመላከቻ ነው።

ትንሹ የተጠያቂነት ደረጃ፦ ይህ አንድ ሰው ስለራሱ ተጠያቂ የሚሆንበት ደረጃ ነው። ለዚህ እርከን ተገቢው የሆነውን ሐቅ ለመስጠት ሲባል ነበር። የወሕይ ጅማሮ የተመለከትነውን ያህል በተለይ ደግሞ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ከአላህ ዘንድ የተላኩ ነቢይና የሚወርድላቸውም ወህይ ከአላህ (ሱ.ወ) መሆኑን በራሳቸው አምነው እስኪረጋጉ በዚህም ሁኔታም ራሳቸው በቀዳሚነት አማኝ እንዲሆኑ ከዚያ በኋላ ለሚመጣላቸው ትእዛዝ መርህና ድንጋጌዎች ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ ነበር።

ቀጥሎ የሚመጣው የተጠያቂነት ደረጃ፦ አንድ ሙስሊም ስለቤተሰቦቹ እና ስለዘመዶቹ የሚኖረው ተጠያቂነት ነው። ይህን ሓላፊነት በአግባቡ መወጣትን ስንቃኝ አላህ ቤተሰብንና ዘመዶችን ማስጠንቀቅና ዳዕዋን ለነርሱ በይፋ ለሁሉም የማድረስ ሃላፊነትን ካዘዘ በኋላ ሆኖ እናገኘዋለን፤ ይህም የተሰጠውን ስፍራ በሚገባ ያመላክታል። ይህን የኃላፊነት ደረጃ የመሸከሙ ሂደት ማንኛውም ቤተሰብና ቅርብ ዘመዶች ያሉትን በሙሉ የሚያካትት ሲሆን የጥሪውም ይዘት የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ለህዝቦቻቸው በሚያደርጉት ጥሪ ለቤተሰቦቹና ለዘመዶቹ በሚያደርገው ጥሪ መካከል እምብዛም ምናልባት የመጀመሪያው በአላህ ወህይ እየተመራ ወደ አዲስ እምነትና የሕይወት ጎዳና ሲጣራ ሌላኛው ይህንን ጥሪ አድራሽና የሱ ቃል አቀባይ ከመሆኑ በስተቀር።

ሶስተኛው ደረጃ፦ አንድ ዓሊምና ዳዒ ስለ መንደሩ ወይም ስለሀገሩ እንዲሁም አንድ አስተዳደሪ ስለሀገሩና ህዝቦቹ የሚኖርበት ኃላፊነት ነው።

የመጨረሻ ጥያቄዎች

1. ዳዕዋን በይፋ የማድረግ አስፈላጊነት አብራራ
2. አርአያነትና ፅናት በይፋ ዳዕዋን ለማድረግ ከምንጠቀምባቸው ድንቅ መንገዶች ውስጥ ዋነኞቹ ናቸው። ይህንን አብራራ
3. «የቅርብ ዘመዶችህን አስጠንቅቅ» ከዚህ ጥሪ (ትዕዛዝ) ምን ትጠቀማለህ? ይህንን ካለፍክባቸው ተግባራዊ ገጠመኞችህ ጋር አብራራ።

4. ከዚህ የትምህርት ክፍል የሚገኙ ጠቃሚ ትምህርቶችን ለይተህ አውጣ፡፡
5. ከዚህ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) የሕይወት ታሪክ ትምህርት ምን ያህል እንደተጠቀምክ ግለጽ

ጥፊውን ለማኮላሸት ጥቅም ላይ የዋሉ ልዩ ልዩ ስልቶች

የትምህርቱ አላማ

1. ቁረይሾች ዳዕዋን ለማኮላሸት የተጠቀሟቸውን ዘዴዎች እንዲዘረዝር ማስቻል
2. የቁረይሾች ዳዕዋን ለማኮላሻ የተጠቀሙባቸውን ስልቶች እንዲያብራራ ማስቻል
3. በዚያን ጊዜ የነበረውን ዳዕዋን የማኮላሻ ስልት በአሁን ጊዜ ካለው ጋር እንዲያስተሳስር ማስቻል
4. ከዚህ የታሪክ ክፍል ጠቃሚ ምክርና ተግሳፅ ነቅሶ እንዲያወጣ ማስቻል
5. በነዚህ ምክርና ተግሳፅ ምን ያህል እንደተጠቀመ እንዲያብራራ ማስቻል

ቁረይሾች ማስዋሸታቸውና ማስተባበላቸው ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) ከዳዕዋቸው እንደማያግዳቸው ሲያዩ በድጋሚ ቆም ብለው ማሰብ ጀምሩ፤ ይህንን ዳዕዋ ለማኮላሸት የሚረዱ ዘዴዎችንም መረጡ፡፡ ይህም እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

1. ማፌዝ፣ ማናናቅ፣ ማሳገጥና ማስተባበል

የዚህ ስልት ጠቀሜታ ሙስሊሞችን ማዋረድና ውስጣዊ ጥንካሬያቸውን ማዳከም ነበር፡፡ ነቢያችንንም (ሰ.ዐ.ወ) የዘቀጡ ቅጥፈቶችን እና የቂል ስድቦችን ሰደቧቸው፡፡ እብድ ብለውም ይጠሯቸው ነበር፡፡

﴿ وَقَالُواْ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِى نُزِّلَ عَلَيۡهِ ٱلذِّكۡرُ إِنَّكَ لَمَجۡنُونٞ ٦ ﴾الحجر: ٦

“›”} Á u`c< LÃ l`œ” ¾}¨[ÅKƒ JÃ! ›”} uÀ`ÓØ °wÉ ’l$ ›K<U::” (አል-ሒጅር፡ 6)

ደጋሚና ቀጣፊ ይሏቸው ጀመር፡-

﴿ وَعَجِبُوٓاْ أَن جَآءَهُم مُّنذِرٞ مِّنۡهُمۡۖ وَقَالَ ٱلۡكَٰفِرُونَ هَٰذَا سَٰحِرٞ كَذَّابٌ ٤ ﴾ص: ٤

"ከነሱ የኾነ አስፈራሪም ስለመጣቸው ተደነቁ፤ ከሓዲዎቹም፦ «ይህ ደግሞ ጭንቅ (ጠንቋይ) ውሸታም ነው» አሉ፡፡" (ሷድ፡ 4)

በጥላቻ እይታና ስሜት ይሸኟቸዋል፤ ይቀበሏቸዋል፡፡

﴿وَإِن يَكَادُ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ لَيُزْلِقُونَكَ بِأَبْصَٰرِهِمْ لَمَّا سَمِعُواْ ٱلذِّكْرَ وَيَقُولُونَ إِنَّهُۥ لَمَجْنُونٌ ۝٥١﴾ القلم: ٥١

"እነሆ፥ እነዚያም የካዱት ሰዎች ቁርኣኑን በሰሙ ጊዜ፥ በዓይኖቻቸው ሊጥሉህ (ሊያጠፉህ) ይቃረባሉ፤ «እርሱም በእርግጥ ዕብድ ነው» ይላሉ፡፡"

(አል-ቀለም፡ 51)

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በደካማ ባልንጀሮቻቸው ተከበው በሚቀመጡ ጊዜ "አቀማማጮቹ እነዚህ ናቸው" እያሉ ያፌዙባቸው እንደነበር፡፡

﴿أَهَٰٓؤُلَآءِ مَنَّ ٱللَّهُ عَلَيْهِم مِّنۢ بَيْنِنَآ ۗ ۝٥٣﴾ الأنعام: ٥٣

"ከመሃከላችን አላህ የለገሰላቸው እነኚህ ናቸውን" ይሉም ነበር፡፡

(አል-አንዓም፡ 53)

አላህ እንዲህ በማለት ይመልሳል፡-

﴿أَلَيْسَ ٱللَّهُ بِأَعْلَمَ بِٱلشَّٰكِرِينَ ۝٥٣﴾ الأنعام: ٥٣

"አላህ አመስጋኞችን አዋቂ አይደለምን" (አል-አንዓም፡ 53)

ሁኔታቸውን አላህ እንዲህ ሲል ተርኮልናል

﴿إِنَّ ٱلَّذِينَ أَجْرَمُواْ كَانُواْ مِنَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ يَضْحَكُونَ ۝٢٩ وَإِذَا مَرُّواْ بِهِمْ يَتَغَامَزُونَ ۝٣٠ وَإِذَا ٱنقَلَبُوٓاْ إِلَىٰٓ أَهْلِهِمُ ٱنقَلَبُواْ فَكِهِينَ ۝٣١ وَإِذَا رَأَوْهُمْ قَالُوٓاْ إِنَّ هَٰٓؤُلَآءِ لَضَآلُّونَ ۝٣٢ وَمَآ أُرْسِلُواْ عَلَيْهِمْ حَٰفِظِينَ ۝٣٣﴾ المطففين: ٢٩ - ٣٣

"እነዚያ ያመጹት በነዚያ ባመኑት በእርግጥ ይስቁ ነበሩ፡፡ በነሱም ላይ ባለፉ ጊዜ ይጠቃቀሱ ነበር፡፡ ወደ ቤተሰቦቻቸውም በተመለሱ ጊዜ (በመላለቃቸው) ተደሳቾች ኾነው ይመለሱ ነበር፡፡ ባዩዋቸውም ጊዜ፥ «እነዚህ

በእርግጥ ተሳሳቾች ናቸው» ይሉ ነበር፡፡ በነሱ ላይ ተጠበቂዎች ተደርገው ያልተላኩ ሲኾኑ፡፡" (አል-ሙጠፊፊን፡ 29-33)

2. አስተምህሮቻቸውን ማጠልሸት፣ በእሱ ላይም ብዥታዎችን መፍጠር

በመልእክተኛውና በስብእናቸው ዙሪያ የሀሰት ወሬዎችን መንዛት፣ ጥርጣሬን ማንገስ ተራው ሰው ቆም ብሎ ለማሰብና ለማስተንተን ፋታ በማያገኝበት አኳኋን የሀሰት ዘመቻውን በስፋትና በብዛት ማሰራጨት፡፡ ቁርአንን አስመልክተው እንዲህ ብለዋል፡-

﴿ وَقَالُوٓاْ أَسَٰطِيرُ ٱلۡأَوَّلِينَ ٱكۡتَتَبَهَا فَهِيَ تُمۡلَىٰ عَلَيۡهِ بُكۡرَةٗ وَأَصِيلٗا ٥ ﴾

"አሉም «የ መጅመሪያዎቹ ሰዎች ተረቶች ናት፡፡ አስጻፋት፡፡ እርሷም በእርሱ ላይ ጧትና ሜዳ ትነ በብለታለች፡፡» (አል-ፉርቃን፡ 5)

﴿ وَقَالَ ٱلَّذِينَ كَفَرُوٓاْ إِنۡ هَٰذَآ إِلَّآ إِفۡكٌ ٱفۡتَرَىٰهُ وَأَعَانَهُۥ عَلَيۡهِ قَوۡمٌ ءَاخَرُونَۖ فَقَدۡ جَآءُو ظُلۡمٗا وَزُورٗا ٤ ﴾ الفرقان: ٤

"እነዚያም የካዱት ይህ (ቁርአን ማዛመድ) የቀጠፈው በርሱም ላይ ሌሎች ሕዝቦች ያገዙት የኾነ ወሸት እንጂ ሌለ አይደለም አሉ፡፡ በርግጥም በደልንና እብለትን ሠሩ፡፡" (አል-ፉርቃን፡ 4)

﴿ إِنَّمَا يُعَلِّمُهُۥ بَشَرٞۗ ١٠٣ ﴾ النحل: ١٠٣

"እ"c<U #እ`c<" (ነ`œ"") ¾T>Áe}U[¨<ǂ c¨< w‰o ¨"<::"

(አን-ነሕል፡ 103) ይሉ ነበር፡፡

መልእክተኛውን (ሰ.ዐ.ወ) አስመልክቶ

﴿ وَقَالُواْ مَالِ هَٰذَا ٱلرَّسُولِ يَأۡكُلُ ٱلطَّعَامَ وَيَمۡشِي فِي ٱلۡأَسۡوَاقِۙ لَوۡلَآ أُنزِلَ إِلَيۡهِ مَلَكٞ فَيَكُونَ مَعَهُۥ نَذِيرًا ٧ ﴾ الفرقان: ٧

"ለዚህም ሚልክተኛ ምጣብን የሚላ፣ በገበያዎችም የሚሹድ ሲኾን ምን (ሚልክተኛነት) አለው ከርሱ ጋር አስፈራሪ ይኾን ዘንድ ወደርሱ ሚልአክ (ገሃድ) አይወረድም ኖሯልን አሉ፡ ፡ " (አል-ፉርቃን፡ 7)

ለነዚህና መሰል እብለቶቻቸው የተሰጡ ምላሾችን ቁርአን ውስጥ በብዛት እናገኛለን፡፡

3. ቁርአንን የጥንት ስፈታሪክ ነዉ በማለት ማጣጣል

ይህን ስልት ሰዎች ቁርአንን እንዳይሰሙና ትኩረታቸው ወደ እሱ እንዳያደርጉ የሰዎችን ህሊና ለማጥመድ የተጠቀሙበት መንገድ ነበር፡፡ ነድር ቢን አልሐሪስ በአንድ ወቅት ለቁረይሾች እንዲህ አላቸው *«እናንት የቁረይሽ ህዝቦች ሆይ! በአላህ እምላለሁ ዘዴው ያልተሰጣችሁ የሆነ ነገር ነው እናንተ ላይ የወረደው፡፡ ሙሀመድ እኮ እናንተ ውስጥ የነበረ ያደገ የምትወዱት ወጣት ነበር፡፡ ከሁላችሁም በላይ በንግግሩ እውነተኛና በአደራ ታማኝ ነበር፡፡ ባመጣላችሁም ነገር ሲመጣላችሁ ግን ድግምተኛ አላችሁት በርግጥ የድግምተኞችን ንፍስታ እና ትብታብ አይተናል በአላህ እምላለሁ፤ በፍጹም ድግምተኛ አይደለም፡፡ ጠንቋይ አላችሁት በእርግጥ የጠንቋዮችን ማስፈራሪያ አይተናል ማጓራታቸውንም ሰምተናል በአላህ እምላለሁ! በፍጹም ጠንቋይ አይደለም፡፡ ገጣሚ አላችሁት በአላህ ይሁንብኝ! ገጣሚም አይደለም፡፡ እብድ አላችሁት በርግጥ እብዶችን አይተናል ከመተናነቁም ሆነ ንግግሩም ከማምታታትና ነገር ከማደበላለቅ የጸዳ ነው እናንተ ቁረይሽ ነሳዎች ሆይ! በሚገባ ወደ ራሳችሁ ተመልከቱ በእውነቱ ትልቅ ዱብዳ ነው የወረደባችሁ፡፡፡»*

ቀጥሎም ነድር ጉዞውን ወደ ሒይራህ (ኢራቅ) በማድረግ የፋርስን የጥንት ንጉሳን ወሬዎች፣ የሩስቱምንና የአስፈንድሪያን ታሪክ ተማረ፡፡ እናም የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ስለ አላህ ሊያስታውሱና ቅጣቱን ሊያስጠነቅቁ ከሰዎች ጋር ቆይታ አድርገው ሲያጠናቅቁ ነድር ቢን አል-ሐሪስ እርሳቸውን በመተካት እንዲህ ይላል፡- *«በአላህ እምላለሁ መሐመድ ከኔ ይበልጥ ያማረ ወግ የለውም፡፡»* ከዚያም ስለ ፋርስ ንጉሳን፣ ስለ ሩስቱምና አስፈንደሪያስ ያወጋቸዋል፡፡ እንዲህም ሲል ይጠይቃቸዋል *«ታዲያ እንዴት ሆኖ ነው መሐመድ በወግ ከኔ የሚበልጠው?»*

የኢብኑ አባስ ዘገባ እንደሚያመለክተው ነድር ዘማሪ እንስቶችን ገዝቶ ነበር። አንድ ሰው ወደ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ያዘነበለ መሆኑን ፈጽሞ አይሰማም ከዘማሪ እንስቶቹ አንዷ ወደዚህ ሰው ዘንድ ሄዳ እንድታጠጣው፣ እንድትመግበውና እንድትዘፍንለትና ካዘነበለበት የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ጥሪ እስኪመለስ ድረስ የሚያደርግ ቢሆን እንጂ። እርሱን በማስመልከት የሚከተለው የቁርአን አንቀጽ ወርዷል፡-

﴿ وَمِنَ ٱلنَّاسِ مَن يَشۡتَرِي لَهۡوَ ٱلۡحَدِيثِ لِيُضِلَّ عَن سَبِيلِ ٱللَّهِ بِغَيۡرِ عِلۡمٖ وَيَتَّخِذَهَا هُزُوًاۚ أُوْلَٰٓئِكَ لَهُمۡ عَذَابٞ مُّهِينٞ ٦ ﴾لقمان: ٦

"ከሰዎችም ያለ ዕውቀት ኾኖ ከአላህ መንገድ ሊያሳስትና ሚዛን አድርጎ ሊይዛት፣ አታላይ ወሬን የሚዛ አልለ፤ እነዚያ ለነሱ አዋራጅ ቅጣት አላቸው፡ ፡" (ሉቅማን፡ 6)

4. የድቢድቤ ስልት

በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሕይወት ታሪክ ዘጋቢ ምሁራን ዘንድ እንደተዘገበው ዑትባ ኢብኑ ረቢዐህ በህዝቦቹ ዘንድ የተከበረ ጥበብና ብልሀት ያለው ሰው ነበር። በቁረይሾች ስብሰባ ላይ *«እናንተ ቁረይሾች ሆይ! ሙሐመድ ጋር ሄጄ ባናግረውስ? አንዳንድ ነገሮችንም በድርድር አቅርቤለት ከፊሉን ቢቀበለኝና ብቻ የፈለገውን ሰጥተነው ቢተወን?»* አላቸው። እነሱም *"እንዴታ አንተ የወሊድ አባት ሆይ ! ተነስ ሂድና አናግረው"* አሉት። ዑትባም ወደ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ)ዘንድ መጥቶ ተቀመጠና፡-

«የወንድሜ ልጅ ሆይ! እስከማውቀው ድረስ አንተ እኛ ውስጥ በዝምድናም ሆነ በነሳ ትልቅ ቦታና ክብር ያለህ ሰው ነህ፤ በርግጥ ወደ ህዝቦችህ ከባድ የሆነን ነገር ይዘህ መጥተሃል፤ በርሱም ህብረታቸውን በትነሃል፣ አስተሳሰባቸውን ቂላቂል አድርገህል... እስኪ አንዳንድ ነገሮችን ለድርድር አቀርብልሀለሁ ሰማኝና አስበህበት ምናልባት ከፊሉን ትቀበለኝ ይሆናል» አላቸው። የአላህ መልዕክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) *«የወሊድ አባት ሆይ! ተናገር ተናገር እሰማህለሁ»* አሉት። *«የወንድሜ ልጅ ሆይ! በዚህ ይዘኸው በመጣኸው ጉዳይ ገንዘብ ከሆነ የፈለግከው ከኛ የበለጠ ሀብታም እስክትሆን ገንዘብ እንሰበስብልሀለን፣ ክብር ከሆነ የምትፈልገው በማንኛውም ጉዳይ*

ከአንተ ላንወጣ ከኛ በላይ እንሾምሀለን፣ ንግስናም ከሆነ የምትፈልገው ከላያችን እናነግስሃለን፣ይህ የሚመጣብህን ራዕይ ስትመለከተው መከላከል የማትችለው ከሆነ ገንዘባችንን አውጥተን ሀኪም እንፈልግልህና ከርሱ ነጻ እስክትሆን ድረስ ሁሉን እናድርግልሀለን፡፡» አለ፡፡ የአላህ መልዕክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) *«የወሊድ አባት ሆይ! ጨረስክ»* አሉት «አዎ» አላቸው፡፡*«እንግዲያውስ ስማኝ»*አሉትና የሚከተሉትን የቁርአን አንቀጾች አነበቡለት፡-

﴿ حمٓ ۝١ تَنزِيلٌ مِّنَ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ ۝٢ كِتَٰبٞ فُصِّلَتۡ ءَايَٰتُهُۥ قُرۡءَانًا عَرَبِيّٗا لِّقَوۡمٖ يَعۡلَمُونَ ۝٣ بَشِيرٗا وَنَذِيرٗا فَأَعۡرَضَ أَكۡثَرُهُمۡ فَهُمۡ لَا يَسۡمَعُونَ ۝٤ وَقَالُواْ قُلُوبُنَا فِيٓ أَكِنَّةٖ مِّمَّا تَدۡعُونَآ إِلَيۡهِ وَفِيٓ ءَاذَانِنَا وَقۡرٞ وَمِنۢ بَيۡنِنَا وَبَيۡنِكَ حِجَابٞ فَٱعۡمَلۡ إِنَّنَا عَٰمِلُونَ ۝٥ قُلۡ إِنَّمَآ أَنَا۠ بَشَرٞ مِّثۡلُكُمۡ يُوحَىٰٓ إِلَيَّ أَنَّمَآ إِلَٰهُكُمۡ إِلَٰهٞ وَٰحِدٞ فَٱسۡتَقِيمُوٓاْ إِلَيۡهِ وَٱسۡتَغۡفِرُوهُۗ وَوَيۡلٞ لِّلۡمُشۡرِكِينَ ۝٦ ﴾فصلت: ١ - ٦

"ሐ.መ. (ሓሚም)፡፡ (ይህ ቁርኣን) እጅግ በጣም ርኅሩኅ፥ በጣም አዛኝ ከሆነው (አላህ) የተወረደ ነው፡፡ አንቀጾቹ የተብራሩ የኾነ መጽሐፍ ነው፤ ዐረብኛ ቁርኣን ሲኾን፥ ለሚገነዘቡ ሕዝቦች (የተበራራ) ነው፡፡ አብሳሪና አስፈራሪ ሲኾን (ተወረደ)፤ አብዛኛዎቻቸውም ተዉት፡፡ እነሱም አይሰሙም፡፡ አሉም፡ – «ልቦቻችን ከዚያ ወደርሱ ከምትጠሩን እምነት በማሸፈኛዎች ወለጥ ናቸው፤ በጆሮዎቻችንም ላይ ደንቁርና አልለ፤ በኛና ባንተም መካከል፥ ግርዶሽ አልለ፤ (በሃይማኖትህ) ሥራዎች እኛ ሠሪዎች ነንና፡፡» (እንዲህ) በላቸው፡ – «እኔ ማለላችሁ ሰው ብቻ ነኝ፤ አምላካችሁ አንድ አምላክ ብቻ ነው፤ ወደ ርሱም ቀጥ በሉ፤ ምሕረትንም ለምኑት ሚስት፥ ወደኔ ይወረድልኛል፡፡ ለአጋሪዎቹም ወዮላቸው፡፡" (አል-ፉሲለት፡ 1-6)

ከዚያም የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ሲያነቡ ዑትባም እያዳመጠ

﴿ فَإِنۡ أَعۡرَضُواْ فَقُلۡ أَنذَرۡتُكُمۡ صَٰعِقَةٗ مِّثۡلَ صَٰعِقَةِ عَادٖ وَثَمُودَ ۝١٣ ﴾فصلت: ١٣

"(ከእምነት) እንቢ «በሉም እንደ ዓድና ሠሙድ መቅሰፍት ብጤ የኾነ መቅሰፍት አስጠነቅቃችኋለሁ፥» በላቸው፡፡" (ፉሲለት፡ 13)

ሲደርሱ አፋቸውን ያዛቸውና ማንበብ እንዲያቆሙ ተማጸናቸው፡፡ ይህም የሆነው ከአንቀጹ አስፈራሪነት የተነሳ ነው፡፡ ከዚያም ዑትባ ወደ ጓደኞቹ ተመልሶ

በተቀመጠ ጊዜ ‹የወሊድ አባት ሆይ ከምን ደረስክ፣ ምን ነካህ? አሉት፡፡ ዐትባም ‹የነካኝማ.. ሰምቼ የማላውቀውን ንግግር መስማቴ ነው፤ በአላህ እምላለሁ ግጥም አይደለም፤ ድግምትም ጥንቆላም አይደለም፤ በአላህ እምላለሁ ጥፍጥና አለው ሰርጾም ይገባል፤ የሰው ልጅ ንግግርም አይደለም፡፡ የበላይ ይሆናል እንጂ የበላይ አይኮንበትም፡፡ እናንት ቁረይሾች ሆይ! እሽ በሉኝና ይህን ሰዉ ከነ ጉዳዩ ተዉት፤ ልቀቁት፡፡ በአላህ እምላለሁ የሰማሁት ነገር ትልቅ ይሆናል፤ አረቦች ጉዳት ካደረሱበት (ከገደደሉት) ተገላገላችሁት፡፡ ከአረቦች የበላይ ከሆነ ንግስናው ንግስናችሁ ነው ክብሩም ክብራችሁ ነው›› አላቸው፡፡ «በአላህ እንምላለን! የወሊድ አባት ሆይ! በምላሱ ደግሞብሀል›› አሉት ዐትባም ‹ይህ የኔ ሀሳብ ነው የፈለጋችሁትን አድርጉ› አላቸው፡፡

ጦበሪይ፣ ኢብኑ ከሢር እና ሌሎችም እንደዘገቡት ወሊድ ኢብኑል ሙጊራ፣ ዓስ ኢብኑ ዋኢል እና ጥቂት ሙሽሪኮች ለአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) የሚከተለውን የድርድር ሀሳብ አቀረቡ፡፡ ከነርሱ በላይ ሀብታም እስኪሆኑ ድረስ ብር ሊሰጧቸው እና ቆንጆ ድንግል ሴት ሊያጋቧቸው በምላሹ አማልክቶቻቸውን መስደብና ባህሎቻቸውን ማቄል እንዲተዉ ጠየቁ፡፡ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) የተላኩበትን ወደ ሀቅ ዳዕዋ ማድረግ እንጂ አሻፈረኝ አሉ፡፡ በዚህን ጊዜ ‹‹*እኛ ለምላክህን ለንድ ቀን እንገዛውና ሌላ ቀን የኛን ለማልክት ተገዛ ለሏቸው*›› ይህንንም አሻፈረኝ አሉ፡፡ አላህም የሚከተለውን ቃል አወረደ

﴿ قُلْ يَٰٓأَيُّهَا ٱلْكَٰفِرُونَ ﴿١﴾ لَآ أَعْبُدُ مَا تَعْبُدُونَ ﴿٢﴾ وَلَآ أَنتُمْ عَٰبِدُونَ مَآ أَعْبُدُ ﴿٣﴾ وَلَآ أَنَا۠ عَابِدٌ مَّا عَبَدتُّمْ ﴿٤﴾ وَلَآ أَنتُمْ عَٰبِدُونَ مَآ أَعْبُدُ ﴿٥﴾ لَكُمْ دِينُكُمْ وَلِيَ دِينِ ﴿٦﴾ ﴾

"በላቸው «እናንተ ከሓዲዎች ሆይ ! ያንን የምትግዘትን (ጣዖት አሁን) አልግዛም ፡ እናንተም እኔ የምገዛዉን (አምላክም አሁን) ተገዢዎች አይደላችሁም ፡ እኔም ያንን የተገዛችሁትን (ወደፊት) ተገዢ አይደለሁም ፡ እናንተም እኔ የምገዛዉን (ወደፊት) ተገዢዎች አይደላችሁም ፡ ለእናንተ ሃይማኖታችሁ አልላችሁ፡ ፡ ለእኔም ሃይማኖቴ አለኝ፡ ፡ " (አል-ካፊሩን፡ 1-6)

ከቁረይሾች ውስጥ የተከበሩት ሹማምንቶች ካወጡና ካወረዱ በኋላ ዐትባ አብኑ ወሊድ ያደረገውን ሙከራ ደግመው ለመሞከር ተስማምተው ወደ አላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ ተሰባስበው በመሄድ ሹመት እና ገንዘብን በድርድር

አቀረቡላቸው፡፡ እንዲሁም የሚመጣባቸው ነገር አጋንንት ራዕይ ከሆነ ሀኪም ሊያመጡ ቃል ገቡላቸው፡፡ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) *«የምትሉት ሁሉ እኔ ዘንድ የለም፤ ወደናንተ የመጣሁበት ነገር ይዤ ሰመጣ ገንዘብ፣ ክብርና ጉማስና ፈልጌ አይደለም፡፡ ግና አላህ ወደናንተ መልክተኛ አድርጎ ላከኝ፡፡ መጽሐፉንም በኔ ላይ አወረደ፡፡ አብሳሪና አስጠንቃቂ እንድሆን ሰላዘዘኝ የጌታዬን መልክት አደረስኩላችሁ፤ መከርኳችሁም፡፡ ያመጣሁትን ከተቀበላችሁኝ በዚህም በመጪው ዓለምም ድርሻችሁ ነው፡፡ እምቢ ካላችሁም አላህ በመካከላችን እስኪፈርድ በእርሱ ትዕዛዝ ሰር እታገሳለሁ፡፡»* አሉ፡፡ «ካቀረብንልህ ነገሮች ምንም የማትቀበለን ከሆነ ይህን ብቻ አድርግልን፤ ከህዝቦች ሁሉ ከኛ በላይ ጠባብ በሆነ ሀገር፣ ባነሰ ግብዓት እና በተጣበበ ኑሮ የሚኖር ማንም እንደሌለ ታውቃለህ፤ በላከህ (መልእክት) የላከህን ጌታ ጠይቅልን፤ ይሄን ያጣበበንን ተራራ ያንቀሳቅስልን፤ ልክ እንደ ሻም እና ዒራቅ ወንዞች ወንዝ ያፍልቅልን ወይም ደግሞ ያለፉት አባቶቻችንን ከሞት ይቀስቅስልን፡፡ ታዲያ ከሚቀሰቀሱት ውስጥ አንዱ ቁሰይ ኢብኑ ኪላብ ይሁን እና እውነተኛ ሽማግሌ ስለነበር የምትለው ነገር እውነት ይሁን ውሸት እንጠይቀዋለን፡፡ ላንተም የአትክልት ስፍራ፤ ያሸበረቀና ያማረ ቤት፣ ከምናይህ ሁኔታህ የሚያብቃቃህ በወርቅና በብር የተሞላ ካዝና ይስጥህና ሀብታም ያድርግህ፡፡ የጠየቅንህን ካስደረግክ እናምንልሀለን፡፡ አላህ ዘንድም ያለህን ቦታ እንረዳለን እንደምትለውም መልክተኛ አድርጎ ልኮሃልም ማለት ነው፡፡»

የአላህ መልዕክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) *«ይህን አላደርገውም ጌታውንም በእንዲህ አይነት ጥያቄ የሚጠይቅ ሰውም አይደለሁም አሏቸው፡፡»* ከብዙ ንግግር እና ክርክር በኋላ ቁረይሾችም «ይህን የሚያስተምርህ የማማ አካባቢ የሚገኝ ረሕማን የሚባል ሰው እንደሆነ ደርሰንበታል፡፡ በአላህ እምላለሁ በረሕማን በፍጹም አናምንም፡፡ ሙሐመድ (ሆይ!) አማራጮችን ሁሉ ሰጥተንሃል፤ በአላህ እምላለሁ ሳናጠፋህ ወይም ሳታጠፋን አንላቀቅም» ብለው ተነስተው ሄዱ፡፡

5. ማሰቃየት

ቁረይረሾች ከዚህ በፊት የኢስላምን ዳዕዋ ለማቆም የተጠቀሟቸው ስልቶች ምንም ጥቅም እንዳላስገኙላቸው ሲረዱ ነቢያችንን (ሰ.ዐ.ወ) እና ሶሐቦችን ማሰቃየትና መቅጣት ጀመሩ፡፡ ቡኻሪ ከአብደላህ ኢብኑ መስዑድ (ረ.ዐ)

እንደዘገቡት ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ) ካዕባ ጋር እየሰገዱ ሳለ አቡ ጀህልና ጓደኞቹ ተቀምጠው ባሉበት «ሙሐመድ ሱጁድ ሲወርዱ ፈርስ አምጥቶ ጀርባው ላይ የሚጥል ማን ነው» ብለው ተጠያየቁ፡፡ ከውስጣቸው እጅጉን የጠመመው ሰው (ዑቅባ ኢብኑ ሙዓይጥ ይባላል) አምጥቶ ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ) ሱጁድ እስኪያደርጉ ጠብቆ በትከሻቸው መሀል ከጀርባቸው ላይ አስቀመጠው፡፡ ይህ ሁሉ ሲሆን ከመመልከት ውጭ ምንም ማድረግ አልችልም ነበር፡፡ ምን አለ አቅም ቢኖረኝ!! በኩራት በመምቦጣረር አንዳቸው አንዱ ላይ እየተዘናበለ ሲሳሳቁ ፋጢማ (ረ.ዐ) መጥታ ከጀርባቸው ላይ እስክታነሳላቸው ድረስ በሱጁድ ላይ ቆይተው ነበር፡፡ ከዚያም ራሳቸውን ቀና አደረጉና ሦስት ጊዜ ‹አላህ ሆይ! ቁረይሾችን አንድ በላቸው› ብለው ዱዓ ሲያደርጉ በዚያ ሀገር የተደረገ ዱዓ ተቀባይነት እንደሚኖረው ስለሚያውቁ በጣም ደነገጡ፡፡

ከዚህም አልፈው የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) በመካከላቸው፣ ባጠገባቸው አሊያም በመንገድ ሲያልፉ እንዲሁም በስብሰባዎቻቸው ላይ ያፌዙ ይቀልዱ እና ያላግጡባቸው ነበር፡፡

ጦበሪ እና ኢብኑ ኢስሐቅ እንደዘገቡት ከቁረይሾች አንዱ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ከመካ መንገዶች በአንዱ ላይ ሲያልፉ አፈር ዘግኖ ጭንቅላታቸው ላይ በተነባቸው፡፡ በዚሁ ሁኔታ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ ከልጆቻቸው አንዷ እያለቀሰች አፈሩን ስታጥብላቸው «ልጄ አታልቅሽ፤ አላህ አባትሽን ይከላከልለታል» ይሏት ነበር፡፡ በአብዛኛው ህዝብም ሆነ በግለሰቦች ዘንድ ካላቸው ትልቅ ተምሳሌትነት እና ክብር እንዲሁም በአቡ ጧሊብ ከሚደረግላቸው ከለላ አልፎ ወራዳ የሆኑ በደሎች ይደርሱባቸው ነበር፡፡

ሶሐቦቻቸውማ (ረ.ዐ) ታጋሽ እንኳን ሊያወሳው የሚዘገንን የሆኑ የስቃይ አይነቶች ተፈራርቀውባቸዋል፡፡ ከቅጣቱ ብዛት የሞተው ሞቶ የታወረው ታውሯል… ይህ ሁሉ ግን ከአላህ ዲን (ኢስላም) ቅንጣትን ታክል ንቅንቅ አላደረጋቸውም፡፡ በያንዳንዳቸው ዙሪያ የተዘገበውን ብናነሳ ስለሚረዝም ከገጠማቸው ቅጣቶች የተወሰኑ ምሳሌዎችን እንጥቀስ፡-

1. ዑስማን ኢብኑ ዐፋንን (ረ.ዐ) አጎታቸው ከዘምባባ ቅጠል በተሰራ ሰሌን ይጠቀልሏቸውና ከስር ጭስ በማጨስ ይቀጧቸው ነበር።

2. ሙስዐብ ኢብኑ ዑመይር (ረ.ዐ) እናታቸው መስለማቸውን ባወቀች ጊዜ ከሰዎች ሁሉ የተሻለ ፀጋ የሞላበት ኑሮ ከሚኖሩበት ቤታቸው አስወጥታቸው ቆዳቸው ልክ እንደ እባብ ቆዳ እየተቀረፈፈ እስኪላጥ ድረስ ለረሀብ ዳርጋቸዋለች።

3. ቢላል (ረ.ዐ) የኡመያ ኢብኑ ኸለፍ አልጁመህይ ባሪያ ነበር። ኡመያ የፀሐይቷ ንዳድ ከፍ ሲል በጋለው የመካ አሸዋ ላይ ቢላልን አስተኝቶ ትልቅ ቋጥኝ ደረቱ ላይ በማስቀመጥ «በአላህ እምላለሁ በሙሐመድ ክደህ ዑዛንና ላትን እስካላመለክህ ድረስ ትሞታለህ እንጂ አለቅህም» ይለው ነበር። ከዚህ ሁሉ ስቃይ ጋር የቢላል መልስ ግን ‹አሐዱን አሐድ› ነበር።

4. ዐማር ኢብኑ ያሲር (ረ.ዐ) የበኒ መኽዙም አገልጋይ (ባሪያ) ነበር። ከነወላጆቹ ሰለመ። ጣኦታዊያን -በዋናኝነት አቡጀህል ፀሐይ ስትበረታ ወደ ሜዳ ያወጧቸውና በግለቱ ይቀጣቸው ነበር። በመቀጣት ላይ ሳሉ ነቢያቸን (ሰ.ዐ.ወ) ባጠገባቸው አለፉ። «የያሲር ቤተሰብ ሆይ! ታገሱ፤ ጀነት ቃል ተገብቶላችኋል» አሏቸው። ያሲር ከቅጣቱ ብዛት ሲሞት ሱመያን (የዐማርን እናት) አቡ ጀህል ብልቷ ላይ በስለት ወግቶ ገደላት። በዚህም በኢስላም ታሪክ የመጀመሪያዋ እንስት ሸሂድ (መስዋእት) ለመሆን ታደለች። ዐማር ላይ ስቃዩን አበረቱበት። አንድ ጊዜ በጸሐይ ግለት፣ ሌላ ግዜ ደረቱ ላይ ቋጥኝ በማስቀመጥ፣ ቀጥሎም ውሃ ውስጥ በመድፈቅ ቅጣቶችን እያፈራረቁ አሰቃዩት። «ሙሐመድን ሳትሰድብ ወይም ስለላትና ዑዛ በጎ ነገር ካልተናገርክ አንተውህም» አሉት። ያሉትንም ለመፈፀም ተስማማ። ተገዶም ፍቃዳቸውን ፈፀመ። ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድም እያለቀሰ በመምጣት ይቅርታ ጠየቃቸው። አላህም ተከታዩን ቁርአናዊ መልእክት አስተላለፈ

﴿ مَن كَفَرَ بِٱللَّهِ مِنۢ بَعۡدِ إِيمَٰنِهِۦٓ إِلَّا مَنۡ أُكۡرِهَ وَقَلۡبُهُۥ مُطۡمَئِنُّۢ بِٱلۡإِيمَٰنِ ﴾ ﴿١٠٦﴾

"ከእምነቱ በኋላ በአላህ የካደ ሰው (ብርቱ ቅጣት አለው)። ልቡ በእምነት የረጋ ኾኖ (በክህደት ቃል በመናገር) የተገደደ ሰው ብቻ

ሲቀር፡ ፡ ግን ልባቸወን በክሕደት የከፈቱ ሰዎች በነሱ ላይ ከአላህ ቁጣ አለባቸው፡ ፡ ለእነሱም ታላቅ ቅጣት አልላቸው፡ ፡ " (አን-ነሕል፡ 106)

5. ስሙ አፍለሕ(ረ.ዐ) የሚባል የበኒ ዐብደዳር ባሪያን እግሩን በገመድ አጥብቀው አስረው መሬት ለመሬት ይጎትቱት ነበር፡፡

6. ኸባብ ኢብኑል ዐረት (ረ.ዐ) ጣኦታዊያን የበረታ ስቃይ ያደርሱበት ነበር፡፡ ብዙ ጊዜ በጠራራይቷ ነዲድ ጸሐይ በጋለ አለት ራቁቱን አስተኙት፡፡ መንቀሳቀስ እንዳይችልም ትልቅ አለት ደረቱ ላይ አስቀመጡበት፡፡ አለቱ ጀርባውን ሰርስሮ በመግባቱ ቀዝቅዞ ከላዩ ላይ ሲወድቅለት ሰውነቱ ላይ ትልቅ ሽንቁርን ትቶ ነበር፡፡

7. ለአላህ ሲሉ መከራን የተሸከሙ የነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ) ባልደረቦች (ሰሀቦች) ስም ዝርዝር ብዙ ነው፡፡ ጣኦታዊያን አንድ ሰው መስለሙን በሰሙ ቁጥር እጅግ የሚያሳቅቅ ቅጣት ይቀጡት ነበር፡፡ እዚህ ጋር ኢማሙ አል-ቡኻሪ የዘገቡትን አንድ ታሪክን እናውሳ፡፡ ኸባብ ኢብኑል ዐረት ሲናገር «አንድ ቀን ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በከዕባ ጥላ ስር ፎጣቸውን ተንተርሰው ሳሉ ወደርሳቸው መጣሁ፡፡ በወቅቱ ከጣኦታዊያን ይደርስብን የነበረው መከራ ከባድ ስለነበር ነቢዩንም «አንቱ የአላህ መልእክተኛ ሆይ! አላህን አይለምኑልንምን?» ስላቸው ፊታቸው በንዴት ቀላ፡፡ ከተጋደሙበት ቀና ብለው ተቀመጠው *«ከናንተ በፊት የነበሩ ህዝቦች በብረት ሙሸጥ(መላጊያ) አጥንታቸው እስኪቀር ሰጋቸው ሲቧጠጥ ከዲናቸው ንቅንቅ አይሉም ነበር፡፡ አላህም ይህንን ጉዳይ (ኢስላምን) ሙሉዕ ያደርገዋል(እተፈለገበት ያደርሰዋል)፡፡ አንድ ተጓዥ ከሰንዓ ተነስቶ ሐድረሞት እስኪደርስ አላህን ከዚያም ፍየሎቹን ተኩላ እንዳይበላበት እንጂ ማንንም ሳይፈራ ይጓዛል፡፡ እናንተ ግን ትቸኩላላችሁ»* አሉኝ፤ ብሏል፡፡

የመጨረሻ ጥያቄዎች

1. የኢስላምን ጥሪ ለማኮላሸት ቁረይሾች የተጠቀሙባቸውን ስልቶች ዘርዝር፡፡

2. የቁረይሾች ጥሪውን የማኮላሻ ስልቶችን አብራራ፡፡

3. እጅጉን የላቀውና የተከበረው አላህ በቁርአን *«(ነገሩ) እንደዚሁ ነው፡፡ እነዚያን ከነርሱ በፊት የነበሩትን ከመልዕክተኛ ማንም አልመጣላቸውም፡፡ (እርሱ)*

ድግምተኛ ወይም እብድ ነው ያሉ ቢሆን እንጂ::» (አዝ-ዛሪያት፡ 52) ይላል:: ከዚህች አንቀጽ በመነሳት በአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ዘመን ደእዋን ለማስቆም ቁረይሾች የተጠቀሙበትን ስልትና በአሁኑ ዘመን የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ፈለግ ተከትሎ በይፋ የወጣ ሰው መካከል ያለውን መመሳሰል እና ትስስር ግለጽ::

4. ከዚህ የታሪክ ክፍል የቀሰምከውን ተግሳፅና ምክር ግለፅ::
5. ከዚህ የሲራ ክፍል ያገነኘውን ምክርና ትምህርት በግልህ ምን ያህል እንደተጠቀምክበት በነቂስ አቅርብ::

ምዕራፍ አምስት

የሶሐቦች ቅንጭብ ታሪክ

- ዑመር ኢብኑ አል-ኸጣብ (ረ.ዐ)
- አቡ ዑበይዳህ ዓምር ኢብኑ አል-ጀራሕ (ረ.ዐ)
- ሰልማን አል-ፋሪሲይ (ረ.ዐ)

ዑመር ኢብኑ አል-ኸጣብ(ረ.ዐ)

የትምህርቱ ዓላማ

1. የዑመር ኢብን አል-ኸጣብን (ረ.ዐ) አጭር የሕይወት ታሪክ በተወሰኑ መስመሮች እንዲያሰፍር ማስቻል።
2. የዑመር ኢብን አል-ኸጣብን (ረ.ዐ) ስም መጠሪያና መገለጫ እንዲዘረዝር ማስቻል።
3. የዑመርን (ረ.ዐ) ትሩፋቶች እንዲያብራራ ማስቻል።
4. ከዑመር (ረ.ዐ) ሕይወት ታሪክ የቀሰማቸውን እውቀቶችንና ፋናዎችን እንዲያስቀምጥ ማስቻል።
5. ከዑመር (ረ.ዐ) ታሪክ ይበልጥ የተመሰጠባቸውን የዑመር (ረ.ዐ) ትሩፋቶችንና ፋናዎችን እንዲጠቅስ ማስቻል።
6. ይበልጥ የተመሰጠባቸውን የዑመር ኢብን አል-ኸጣብ (ረ.ዐ) ንግግሮች እንዲያብራራ ማስቻል።

ታሪኩ በአጭሩ

1. የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ከመላካቸው ከ30 ዓመት በፊት ተወለዱ።
2. እርሳቸው በሰለሙበት ወቅት የሙስሊሞች ቁጥር 39 ደርሶ ነበር።
3. የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) አማች ሲሆኑ የምእመናን እናት የሆኑት የእመት ሐፍሷ (ረ.ዐ) አባት ናቸው።
4. ለኸሊፋነት በተመረጡበት ወቅት እድሜአቸው 55 ዓመት ነበር።
5. በኸሊፋነት የቆዩት አሥር ዓመት ከስድስት ወር እና አራት ቀን ነበር።
6. ሻም (የዛሬው ሶሪያ፣ ፍልስጤምና ዮርዳኖስ አካባቢ) ሚራቅ እና ኢራን፣ ግብፅ፣ በርቀህ፣ ምዕራባዊ ትሪፖሊ፣ አዘርበጃን እና ነሃውንድ በርሳቸው የኸሊፋነት ዘመን ነበር የተከፈቱት።

7. የበስራና ኩፋ ከተሞችም የተገነቡት በኸሊፋነታቸው ዘመን ነበር።።

8. የሂጅራን አቆጣጠር ቀመር ያስቀመጡትና የመዝገብ አያያዝን ለመጀመሪያ ጊዜ ያስተዋወቁት እርሳቸው ነበሩ።።

9. ከወዳጆቻቸው ከአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እና ከአቡበክር አስ-ስዲቅ (ረ.ዐ) ጋር በእመት ዓኢሻ (ረ.ዐ) ቤት ውስጥ ተቀበሩ።።

10. በዘመነ ጃሂሊያ/ቅድመ እስልምና/ ቀሪበት ኡምሙ ኩልሡም ቢንት ጀርወልን በእስልምና ውስጥ ደግሞ ዘይነብ ቢን መዝዑንን፣ ኡምሙ ኩልሡም ቢንት ዐሊን፣ ጀሚላ ቢንት ሣቢትን፣ ኡምሙ ሐኪም ቢንት አልሃሪስን እና ዓቲካ ቢንት ዘይድን ያገቡ ሲሆን ከፊሎቹ እርሳቸው በሕይወት እያሉ ነበር የሞቱት።።

11. አሥራ ሁለት ልጆች የነበሯቸው ሲሆን ስድስቱ ወንዶች ዐብዱላህ፣ ዐብዱረህማን፣ ዘይድ፣ ዑበይዱላህ፣ ዓሲም እና ዒያድ የሚባሉ ሲሆን ስድስቱ ሴቶች ደግሞ ሐፍሷ፣ ሩቀያ፣ ፋጢማ፣ ሰፊያ፣ ዘይነብ እና ኡምሙ አልወሊድ ይባላሉ።።

ሥማቸው፣ መጠሪያቸው እና ባህሪያቸው

ሙሉ ሥማቸው ዑመር ኢብን አልኸጧብ ኢብን ኑፈይል ኢብኑ ዐብዱልዑዛ ይባላል።። የዘር ግንዳቸው ከዕብ ኢብኑ ሉአይ ላይ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘር ጋር የሚገናኝ ሲሆን ከዐዲይ ልጆች የሆኑ የቁረይሽ ጎሣ አባል ናቸው።።

መጠሪያቸው ‹አቡ ሐፍስ› ሲሆን ሐፍስ ማለት ትርጉሙ የአንበሣ ግልገል ማለት ነው።። ስያሜውንም ያወጡላቸው በታላቁ የበድር ጦርነት እለት ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ናቸው።። ከዚህም በተጨማሪ ዑመር የሠለሙ ዕለት የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ‹አል-ፋሩቅ› በማለትም ጠርተዋቸዋል።። ትርጉሙም ‹መለያ› ማለት ሲሆን በዑመር አማካኝነት አላህ እስልምናን ስላጠናከረና በሱም ሀቅ እና ውሸትን የለየ በመሆኑ ነው።።

ዑመር(ረ.ዐ) ያደጉት የዐረቦች ሃይማኖታዊዋ ከተማ በሆነችው መካ ውስጥ ነው።። የተገኙት በጥንካሬ እና በሀይለኛነቱ ከሚታወቅ ቤተሰብ ነው።። በጃሂሊያ (ከእስልምና በፊት) በነበረው ጊዜ በቁረይሾች እና በሌላ ጎሣ መካከል የከረረ

ግጭት አሊያም ጦርነት የተከሠተ እንደሆነ ቤታቸው የሽምግልና መናኸሪያ ሆኖ ያገለግል ነበር። በመሆኑም ቁረይሾች በወቅቱ ዑመርን በስማቸው የሚናገር ቃል አቀባይ አድርገው ይልኳቸው ነበር። ማኅበረሰቡን ለጦርነት ለመቀስቀስ ካስፈለገም ቀስቃሽ ነበሩ። ፉከራና መሸለል ካስፈለገም እንዲሁ። ጠላት ከነሱ እንዲሸሽ እና ለማስፈራራትም ይጠቀሟቸዋል።

ዑመር (ረ.ዐ) በቁመታቸው ረዘም ያሉ ሲሆን ርዝመታቸውም ጎልቶ የሚታይ ነበር። ከሰዎች ጋር ሲሄዱ የፈረሠኛ ያህል ይቀድማሉ። በመልክ የቀይ ዳማ ናቸው። ቆንጆ ፊት ደንደን ወፈር ያሉ እግሮች እና እጆች፣ ራሰ-በራ ቀለል ያለ ትከሻ፣ ብርቱ እና ጠንከር ያለ አፈጣጠር፣ ገዘፍ ያለ ሰውነት እና ጎርነን ያለ ድምፅ ያላቸው ሰው ነበሩ። ሺፋእ ቢንት ዐብዱረህማን ስለርሣቸው አፈጣጠርና ቁመና ስትናገር እንዲህ ብላለች። ‹ዑመር ከተናገሩ የሚሰሙ፣ ሲሄዱ ፈጣን የሆኑ፣ ሲማቱም የሚያሣምሙ ዓይነት ሰው ናቸው። እርሳቸው እውነትም አብነት መሆን የሚችሉ ሰው ናቸው።›

ዑመር እጅግ ቀልጣፋና ንቁ ከሚባሉ የቁረይሽ ወጣቶች መካከል አንዱ ሲሆኑ በጥንካሬም የሚያህላቸው አልነበረም። ጨዋታዎችም ይሁን ከባዕድ አምልኮ የጃሂሊያ ወጣቶች በተሣተፉባቸው ነገሮች ውስጥ ሁሉ ተሣትፈዋል። አስካሪ መጠጥ ጠጥተዋል፣ ጣኦታትን አምልከዋል። በመጀመሪያዎቹ የእስልምና የጥሪ ዓመታት ወቅትም ዑመር በሙስሊሞች ላይ ከፍተኛ ችግሮችን አድርሰዋል። ዑመር መፃፍና ማንበብ ከሚችሉ ውስን የመካ ሰዎች መካከልም የሚጠቀሱ ናቸው። የዕቁብ ኢብኑ ሱፍያን በታሪኩ ውስጥ ከዘር ኢብኑ ሁበይሽ እንደዘገበው እንዲህ ብሏል፡- ዑመርን እጅግ የተከፋ ፊት ይዘው በሚሣፈር እንሠሣ ላይ እንዳለ ሰው ከሰው ተነጥሎ አገኘሁት። ይህንንም ታሪክ ለአንድ የዑመር ልጅ ነገርኩት። እሱም እንዲህ አለ ‹ከአንዳንድ ትላልቅ ሰዎች እንደ ሰማነው ከሆነ ዑመር ነጭ ፊት የነበረው ሲሆን በረማዳ ዓመት ድርቅና ረሃቡ ሰዎች ላይ በበረታ ጊዜ ሥጋና ቅቤ ነገር መብላትን በመተዉና ዘይት በማዘውተሩ ምክንያት መልኩ ወደ ዳለቻነት ሊቀየር እንደቻለ ነው።› ብሏል።

ኢስላምን መቀበላቸው

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በተላኩ ጊዜ የዑመር እድሜ ሠላሳ ዓመት ነበር። የሰለሙትም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በተላኩ በስድስተኛው ዓመት ነው። ኢስላምን የመቀበላቸው ታሪክም በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሕይወት ታሪክ ውስጥ ከተጠቀሱ እውቅ ታሪኮች ውስጥ አንዱ ሆኖ ዘወትር ይጠቀሣል። ዑመር ከሰለሙበት ቅፅበት ጀምሮ ያ ሙስሊሞች ላይ ያሣዩ የነበረው ኃይለኛነታቸው ሙሉ በሙሉ ወደ ከሃዲያን አዞሩት። እነሱንም ዋና ጠላቱ አደረጉ። በዚህም አቋማቸው የተነሣ በእስልምና መንገድ ለስቃይና ለድብደባ ተዳርገዋል።

ወደ እስልምና በመግባት ዑመርን ሠላሣ ዘጠኝ ሰሐቦች የቀደሟቸው ሲሆን እሳቸው አርባኛው ሰው ናቸው። ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እስልምና እንዲጠናከር ካላቸው ጉጉት የተነሣ ‹አምላኬ ሆይ! ወዳንተ ተወዳጅ በሆኑ ከሁለቱ ሰዎች በአንዱ እስልምናን አጠናክር። በአቢ ጀህል ኢብኑ ሂሻም አሊያም በዑመር ኢብኑ አልኸጧብ።› በማለት ዱዓእ አድርገው ነበር። አላህም (ሱ.ወ) ለመልእክተኛው ዱዓእ ምላሽ ሠጠ። አቢ ጀህል ለቅናቻ አልታደለም። ዑመር (ረ.ዐ) ግን የአላህ ፈቃድ ሆኖ ወደ እስልምና ተመሩ። ይህ ክስተት ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) አላህ (ሱ.ወ) ዘንድ ተወዳጅና ተሠሚ ነቢይ መሆናቸውንና የክብር ቦታ ያላቸው ስለመሆኑም አመላካች ነው።

በሌላ ዘገባም ኡምሙ ዑመር ቢንት ሀሣን አሥ-ሠቀፊይየህ ባለቤቷን ሰዕድ ኢብን ጠቅሣ እንደዘገበችው የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ‹አምላኬ ሆይ! ሃይማኖትህን በዑመር አጠናክር፤ አላህ ሆይ! ሃይማኖትህን በዑመር አጠናክር።› በማለት ዱዓ ያደርጉ እንደነበር ነው።

አህመድ በሰፍዋን ኢብኑ ዐምር ዘገባ ከሹረይህ ኢብኑ ዑበይድ እንደዘገቡት ደግሞ ዑመር (ረ.ዐ) እንዲህ ብለዋል። ‹አንድ ቀን የአላህን መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ለማግኘት ብዬ ከቤት ወጣሁኝ። ወደ መስጊድ ቀድመውኝ ሄደው አገኘኋቸው። ሄጄ ከኋላቸው ቆምኩኝ። ‹አል-ሐቀህ› ምዕራፍን ማንበብ ያዙ። በቁርአን ድርሠት እጅግ መደመም ያዝኩኝ። በእጅጉ መሠጠኝ። ‹ቁረይሾች እንዳሉት ሁሉ በአላህ እምላለሁ! ይህ ሰው ገጣሚ ነው› አልኩኝ። እርሣቸውም፦

﴿إِنَّهُۥ لَقَوۡلُ رَسُولٖ كَرِيمٖ وَمَا هُوَ بِقَوۡلِ شَاعِرٖۚ قَلِيلٗا مَّا تُؤۡمِنُونَ﴾

"እርሱ፥ (ቁርአን) የተከበረ መልክተኛ ቃል ነው፡ እርሰም የባለቅኔ ቃል (ግጥም) አይደለም፡ ጥቂትን ብቻ ታምኖላችሁ፡"" የሚለውን የቁርአን አንቀጽ አነበቡ።

‹ጠንቋይ ነው› አልኩኝ። እርሳቸውም፡-

﴿وَلَا بِقَوۡلِ كَاهِنٖۚ قَلِيلٗا مَّا تَذَكَّرُونَ﴾

"የጠንቋይም ቃል አይደለም፤ ጥቂትን ብቻ ታስታውሳላችሁ፡"

በማለት አነበቡና ከዚያም ምዕራፏን ጨረሱ። በዚህም መነሻነት እስልምና በልቤ ውስጥ ሰረፀ። ቦታም አገኘ። ተደላደለ።

እርሳቸውን ረዥሙን አሰላለማቸውን ታሪክ ተረኩላቸው። ከዚያ ውስጥም፡-

ሙሐመድ ኢብኑ ዑስማን ኢብኑ አቢ ሸይባህ በታሪኩ ውስጥ ኢብኑ ዐባስ፣ ዑመርን ስለ አሰላለማቸው ጠየቋቸው የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) በእሳቸው (በዑመር)፣ በሀምዛ እና በዳር አል-አርቀም ውስጥ ተደብቀው ከሰሐቦቻቸው መካከል ከነበሩበት ኾነው ወደ መካ መጡ። ቁረይሾች ዑመር እንደቀድሞው ሊከለክሏቸው እንደማይችሉ አወቁ። የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) በዚህ ጊዜ "አልፋሩቅ"/እውነትን ከውሸት የሚለይ/ብለው ጠሩኝ።› አሉ።

ከአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ተምሳሌት ጋር የነበራቸው ወዳጅነት

ዑመር ከአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር የነበረባቸው ጓደኝነትና ወዳጅነት በጌታው ላይ ፍፁም በሆነ መልኩ እርግጠኛ እንደሆነ አማኝ ነው። ለነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እጅግ ሲበዛ ታዛዥ ናቸው። ዑመር በእስልምና ጠላቶች ላይ እጅግ ብርቱ፣ በሀቅ ላይ እጅግ ጠንካራ እንዲሁም አላህ (ሱ.ወ) ለደነገጋቸው ህግጋቶች በፅኑ እጅ የሠጡ ሰው ናቸው። ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር በሁሉም ጦርነቶች ላይ ተሳትፈዋል። የአላህ መልእክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) እርሳቸው ዘንድ ያለውን ክብር በሚያሣይና ለኢስላም የከፈለውን መስዋእትነት በሚያሣይ መልኩ አወድሰዋቸዋል፡- ‹አላህ እውነትን በዑመር ምላስና ቀልብ ላይ አድርጓል።›

በማለት፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ዑመር የትክክለኛ ሀሣባቸው እና የታላቅ አዕምሮ ባለቤትም ናቸው፡፡ በዚያ ነገር ላይ ወሕይ/መለኮታዊ ራእይ/ ከመውረዱ በፊት ሀሣቡ በሦስት ሥራዎች ላይ ከቁርአን ሀሣብ ጋር ገጥሟል፡፡ አስካሪ መጠጥ ሐራም እርም ይደረግ ዘንድ ሀሳብ ያቀርቡ ነበር፡፡ አላህም መጠጥን እርም የሚያደርግ አንቀፅ አወረደ፡-

"እላንተ ያመናችሁ ሆይ! የሚያሰክር መጠጥ፥ ቁማርም ጣዖታትም አዝላምም ከሰይጣን ሥራ የኾኑ እርኩስ ብቻ ናቸው፤ (እርኩስን) ራቁትም፤ ልትድኑ ይከጀላልና፡ ፡ "

ከበድር ምርኮኞችም መቤዣ መቀበልን ይቃወሙ ነበር፡፡ በዚህም ቁርአን ወርዷል፡፡ የምእመናን እናቶች ማለትም የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሚስቶችም ሂጃብ እንዲለብሱ ሀሣብ ይሠጡ ነበር፡፡ ይህንንም አስመልክቶ ቁርአን ወረደ፡፡

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) በሞቱ ጊዜ ዑመር ክፉኛ ደነገጡ፡፡ ሁኔታውን ባለማመን፡የአላህ መልክተኛ በፍፁም አልሞቱም፡ በማለትም ያስተባበሉ ሲሆን ፡አላህን ለማግኘት ሄደዋልና እንደገና ወደኛ ይመለሳሉ፡፡ የሚል አቋምም እስከመያዝ ደረሰው ነበር፡፡ ፡የአላህ መልእክተኛ ሞተዋል፡ የሚል ካለም አንገቱን እንደሚቀላ በይፋ ተናገሩ፡፡ ይህ ሁሉ የሆነው ለአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ካለው ፍቅር የተነሣ ስሜታቸውን መቆጣጠር ባለመቻላቸው ነበር፡፡

ለአላህ ጠላቶች በተለይም ለከሃዲያንና ለመናፍቃን ከዑመር የበለጠ ብርቱ ጠላት አልነበረም፡፡ በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ መጥፎ የሚያወራ አሊያም የሚናገር ሰው ያዩ አሊያም የሰሙ እንደሆነ ፡የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ይተውኝ የዚህን ሙናፊቅ አንገት ልቀንጥስ፡ በማለት ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ፈቃድ ይጠይቁ ነበር፡፡ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) በጀነት መስክረውላቸዋል፡፡ በመሆኑም ዑመር (ረ.ዐ) በምድር ላይ በሕይወት እያሉ በጀነት ከተበሰሩ አሥር ሰሐቦች መካከል አንዱ ናቸው ማለት ነው፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እሳቸውን (ዑመርን) ወደው ይህችን ምድር መሰናበታቸው ብቻ በእጅጉ ለዑመር ክብር ሊያሰጣቸው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡

ዑመር በአቡ በክር የኸሊፋነት ዘመን

ዑመር (ረ.ዐ) በአቡበክር (ረ.ዐ) የኸሊፋነት ዘመን እውነተኛ ጓደኞቸውና የበጎ ነገር ሁሉ ተባባሪያቸው ነበሩ። ሰሐቦች በበኒ ሳኢዳ ተሰብስበው በሀሣብ በተለያዩ ጊዜ አላህ (ሱ.ወ) በሱ አማካይነት የሙስሊሞችን ቀልብ አንድ አደረገና ሁሉም ሰው ለአቡበክር ኸሊፋነት ቃል ገባ። በወቅቱ ፈጠን በማለት አስቀድመው ለአቡበክር ቃል ኪዳን የገቡት ዑመር ነበሩ። ኋላ ላይ አንሷሮችም ሙሃጅሮችም /የመዲናና የመካ ሰዎች/ ተከተሏቸው።

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ትተው የሄዱትን ክፍተት ለመሙላት እጅግ ተገቢው ሰው አቡበክር እንደሆኑ ዑመር ጠንቅቀው ያውቁ ነበር። የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) በታመሙ ጊዜ አቡበክር ለሰሃቦች ኢማም እንዲሆኑ ማድረጋቸው ለኸሊፋነት በእጩነት እያዘጋጇቸው ስለመሆኑ ሁሉም ሰሃቦች ተረድተውታል። ዑመርም ለቃልኪዳኑ የፈጠኑበት ዋናው ምክንያት የሙስሊሙ አንድነት እንዲጠበቅና በመጎልበትና በመስፋፋት ላይ ለሚገኘው የሙስሊም መንግስት በዚህ ወሣኝ በሆነው ጉዳይ ቶሎ መቋጫ ለማበጀት ነው።

በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሕይወት ዘመን የነበረው የዑመር ጥንካሬ በአቡበክር (ረ.ዐ) ዘመንም ቀጥሎ ነበር። አቡበክር እጅግ ታጋሽና እዝነት የተሞሉ ለስላሣ ሰው ነበሩ። ይቅርታና እርጋታ ሁሌም ባህሪያቸው ላይ ጎልቶ ይታያል። በመሆኑም ይህን ፀባይ ሚዛናዊ የሚያደርግ ታጋሽነትን ከጥንካሬ ጋር የያዘ ለስልጣን እና ባለሥልጣንም አስፈሪ ሞገስ የሚያላብስ የዑመር ዓይነት ጠንከር ያለ ሰው ያስፈልግ ነበር። ስለሆነም ዑመር ይህን ቦታ ሞሉት። አቡበክርም በየወቅቱ የዑመርን ሀሳብ ይቀበሉ አስተያየታቸውንም ተግባር ላይ ያውሉ ነበር።

አንድ ቀን አቡበክር (ረ.ዐ) አንዳች ነገር አዘዙና ዑመር (ረ.ዐ) ሳይፈጽሙት ቀሩ። ሰዎችም ለአቡበክር ‹በአላህ እምላለሁ! ኸሊፋው ዑመር ይሁን አንቱ አናውቅም› አሏቸው። አቡበክርም ‹በአላህ እምላለሁ! ከፈቀደ እሱ ነው› በማለት መለሱላቸው።

ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሞት በኋላ ታላላቅ ሰሃቦች ኸሊፋቸውን ለመምረጥ ሰቂፋ ላይ በተሰበሰቡበት ወቅት ዑመር ለአቡበክር ‹አንተ ከኔ በላጭ ነህ።› አሏቸው። አቡበክር በበኩላቸው ‹አንተ ግን ከኔ በላይ ጠንካራ ነህ።› በማለት መለሱለት።

ዑመርም ‹ጥንካሬዬ ከብልጫህ ጋር ነው› አሉ፡፡ በዚህም መልኩ እነኚህ ሁለት ትላልቅ ሀይሎች ተዋሀዱ፡፡ የአቡበክር በላጭነት፣ ታጋሽነታቸው፣ ብስለታቸውና ቁርጠኝነታቸው፣ ከዑመር ጥንካሬ፣ ኃይልና የአስፈሪነት ሞገስ ጋር ተዳምሮ እጅግ ጠንካራ የሆነውን ኢስላማዊ መንግስት ለመመስረት ያበረከተው አስተዋፅኦ ቀላል አልነበረም፡፡

ዑመር በኸሊፋነት ዘመን ውስጥ

ዑመር (ረ.ዐ) በኸሊፋነት የተመረጡበት ጊዜ ሙስሊሙ ማኅበረሰብ የርሳቸው ዓይነት ኸሊፋ በሚፈልግበት ወቅት ነበር፡፡ ሙስሊሞች በጊዜው ከሮማውያን ፋርሶች ጋር ከፍተኛ ጦርነት ውስጥ ነበሩ፡፡ በመሆኑም የሙስሊም ሀገራት አላህን ፈሪ፣ ቆራጥ እና በሣል መሪ ያስፈልጋቸው ነበር፡፡ በዑመር የአስተዳደር ብቃት በመመሪያዎቹና በአመራር፣ በቁርጠኝነቱ፣ በቁጥብነቱ፣ መጠቀም ግድ ይላቸው ነበርና ዑመር ኃላፊነት ላይ በወጡ ማግስት ድል በድል የሆኑት ዐረቦች ዱኒያ በግራም በቀኝም የነሱ ሆነች፡፡ ሀብት እንደ ጉድ ተለቀቀባቸው፡፡ በርግጥም ለበርካታ አመታት የአላህን ዲን በመከላከሉ ረገድ በጅሃድ ተዳክመው ኖረዋልና ወደርሷ ቀልባቸው ማዘንበሉና መሣቡ አልቀረም፡፡ ከብልጭልጩ ዓለም ጥፍጥና ለመቋደስ በእጅጉ ቋመጡ፡፡ በመሆኑም ይህ ከባድ ፈተና ነበርና ትልቅ አደጋ ተደቀነባቸው፡፡

ዑመር የሙስሊሞች ኸሊፋ ከሆኑበት ጊዜ ጀምሮ በእስልምና ታሪክ ውስጥ ድንቅ እና ህያው የሆኑ በርካታ ሥራዎችን ሠርተዋል፡፡ ከነኚህም መካከል፡-

- አቡበክር ጀምረውት የነበሩውን ፋርሶችንና ሮማዊያንን የመዋጋቱን እንቅስቃሴ ከጫፍ አድርሰዋል፡፡ በዚህም ሙስሊሞች ግብፅን፣ ሶሪያና አካባቢውን፣ ዒራቅንና ኢራንን ለመቆጣጠር በቅተዋል፡፡
- የመንግስትን የአስተዳደር ሥርዓት ያስተካከሉ ሲሆን ሰነዶችንና መዛግብቶችን አዘጋጅተዋል፣ የግብር ሥርዓትን ሥራ ላይ አውለዋል፣ከመሬት የሚገኘውን ማንኛውንም ምርትና ማአድን በእኩልና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ በተስተካከለ የፖለቲካ ሁኔታ ከፋፍለዋል፡፡ እጅግ ድንቅ በሆነ እሳቤያቸው ለሙስሊሙ መንግስት ያስፈልጋል ያሉትን ስርዓት እና መመሪያዎችንም አውጥተዋል፡፡

ይህም ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ህልፈት በኋላ በታሪክ ታይቶ የማይታወቅ የተደራጀ የመንግሥት የአሠራር ሥርዓት ነበር።

- በሙስሊሞች የተከፈቱ አዳዲስ ሀገራትን በሀይል እና በማስፈራራት፣ በልስላሴና በቁርጠኝነት ፍትህ እና ይቅርታን በቀላቀለ ሚዛናዊ አካሄድ አስተዳደሩ። ለዚህም የዑመር አመራር ለብዙዎች ህዝቦችና ሀገራት ትልቅ ምሣሌ መሆን የቻለ ነበር። ህዝቦችን በፍትህ እና በእዝነት በማስተዳደሩ ደረጃ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ የዑመር ዓይነት መሪ እንዳልታየ ይነገራል።

ታላቅነታቸውን ከሚያሣዩ ነገሮች መካከል ጥቂቶቹ

1ኛ) እምነትን ከአደጋ መከላከል

ዑመር ከመስለማቸው በፊት በሙስሊሞች ላይ የነበራቸው የጠላትነትና የጥላቻ አቋም እጅግ የከፋ ነበር። የኢስላም የእምነት አመለካከት/ዐቂዳ/ ዋጋ እንደሌለው ያስቡ፣ ሙስሊሞችም በዐቂዳቸው ከመላው ዐረብ ዐቂዳ ያፈነገጡ እንደሆኑ አድርገው ያስቡ ነበር። የጣኦት አምልኮ እምነታቸውን ለመከላከልና ሙስሊሞችን በሃይማኖታቸው የተነሣ ለማሠቃየት ያላደረጉት ነገር አልነበረም።

እስልምናን ከተቀበሉ በኋላ ግን ነገሮች ሁሉ በቅፅበት ተገለባበጡ። ከእናት አባቱ ወርሶት ለነበረው እምነት ይከላከል ከነበረው በላይ ለአዲሱ እምነቱ መቆርቆር ጀመረ። ከሰለሙ በኋላ አንዳች ነገር ሳይፈሩ የቁረይሽ መሪዎች ወደ ተሰበሰቡበት የከዕባ አካባቢ በመሄድ እስልምናን መቀበላቸውን በይፋ ተናገሩ። ‹እሱ ከቀድሞ ሃይማኖቱ በመመለስ ወደ እስልምና ገብቷል።›

ሙስሊሞች በወቅቱ እምነታቸውን ይደብቁም ነበር። በመሆኑም ሰዎች ተነስተው በመረባረብ ደበደቧቸው። እሳቸውም ይከላከሉ ጀመር። ነገርግን አጎታቸው አቡ ጀህል ተነሣና ከለላን ቸራቸው(ከድብደባውም አስጣሏቸው)። ሰዎችም በዚህን ጊዜ ተውዋቸው። ነገር ግን ዑመር የሌሎች ሙስሊሞችን መደብደብ ባዩ ጊዜ አላስቻላቸውም። እነሱን ያጋጠመ ችግር ሁሉ እኔንም ሊያጋጥመኝ ይገባል አሉና አጎታቸው ከለላውን እንዲያነሳላቸው ነገሩት። ሰዎችም

እንደገና ይደበድቡት እሳቸውም ይከላከሉ ጀመር፡፡ ኋላ ላይ ግን እስልምና በዑመር አማካይነት መጠናከሩ አልቀረም፡፡

2ኛ) በሐቅ ላይ የነበራቸው ጥንካሬ

ዑመር በሐቅ መንገድ ላይ ማስመሠልንና መለሣለስን አያውቁም ነበር፡፡ በሐቅ መንገድ ለወዳጅም ይሁን ለዘመድ አይቅለሰለሱም፡፡ የበድር ምርኮኞች አንገታቸው እንዲቀላ አስተያየት ሰጥተው ነበር፡፡ ሰዎቹ የተከበሩ የቁረይሽ ታላላቅ ሰዎች ነበሩ፡፡ ይህንንም ያሉት የሸርክ ሰዎች ሰላም እንደማይገባቸውና መሸበር እንዳለባቸው በማሰብ እንዲሁም ለአላህና ለመልእክተኛው ጠላቶች ተመጣጣኝ ቅጣት ይሆን ዘንድ ነው፡፡

ዑመር (ረ.ዐ) በሁደይቢያ ስምምነት ወቅት ቁረይሾች ያቀረቡትንና የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) የተስማሙበትን መስፈርት አልወደዱትም ነበር፡፡ ሁኔታውን የሙስሊሞች ድክመትና የመለሣለስ ውጤት አድርገው ያስቡም ነበር፡፡ ወደ አላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ በመምጣት ‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ! እኛ በሀቅ እነሱ በውሸት ላይ አይደለንም!› አሏቸው፡፡ እርሣቸውም ‹በርግጥ ነው፡፡› አሉ፡፡ ‹ሚኾቻችን የጀነት ሚኾቻቸው ደግሞ የጀሀነም አይደሉምን!› አላቸው፡፡ እርሣቸውም ‹በርግጥ አዎ› አሉት፡፡ ‹እንግዲያውስ ለዱኒያ ብለን ዲናችንን እንዴት (አሳልፈን) እንሠጣለን!› አሏቸው፡፡ የአላህ መልእክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) ‹የኸጧብ ልጅ ሆይ! እኔ የአላህ መልእክተኛ ነኝ፡፡ እሱ በፍፁም ጥሎ አይጥለኝም፡፡› በማለት ሊያረጋጓቸው ሞከሩ፡፡ ዑመር ወደ አቡበክር በመሄድም ለአላህ መልእክተኛ ያሏቸውን ነገር ጠየቁ፡፡ አቡበክርም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንደመለሱት መለሱለት፡፡

3ኛ) ለመፈዎች ፍፁም ታዛዥ መሆናቸው

ዑመር እውነት ነው ብለው ባሰቡበት ነገር ላይ እጅግ ፅኑ ከመሆናቸው በተጨማሪ አንድ ውሣኔ ከተላለፈ ግን ለበላይ አመራሮቹ በቅድሚያ እጅ በመስጠትና በመታዘዝ የሚታወቁ ሰው ነበሩ፡፡ በሁደይቢያ ስምምነት ወቅት የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ከሙሽሪኮች ጋር ያደረጉት ውል ምንም እንኳ ከዑመር ሀሣብ ጋር በእጅጉ የተቃረነና ያስቆጣቸው ቢሆንም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ)

‹የኸጧብ ልጅ ሆይ! እኔ የአላህ መልእክተኛ ነኝ፡፡ በአላህ እምላለሁ! አላህ ፈፅሞ አይጥለኝም፡፡› ባሏቸው ጊዜ ግን ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የወደዱትን ነገር ከመውደድና ለትእዛዛቸው ከማንብደድ ውጭ አማራጭ አልነበራቸውም፡፡

ሙርተዶችን/ከእስልምና በኋላ ወደ ክህደት ያፈነገጡ ሰዎችን/ በሚዋጉበት ወቅት ከአቡበክር ጋር ክርክር ውስጥ ገብተው የነበረ ሲሆን እነሱን አለመዋጋት የእሳቸው የዑመር ሀሣብ ነበር፡፡ አቡበክር ግን ‹እነርሱን መፋለሙ ግዴታ ነው፡፡› የሚል የፀና አቋም ነበራቸው፡፡ ዑመር ኸሊፋው በሀሣባቸው መፅናታቸውን ባስተዋሉ ጊዜ በሀሣባቸው የመስማማት ልቦና ተከፈተላቸው፡፡ አላህም እውነትን በአቡበክር ምላስ እንዳመጣ ተረዱ፡፡ ግዳጃቸውን ለመወጣት ከሁሉም ቀደም ብሎ አቡበክርን የታዘዟቸውም እርሳቸው ነበሩ፡፡

4ኛ) ስህዝባቸው ያላቸው ትዝነት

ዑመር ከሐቅ አንፃር እጅግ የጠነከረ አቋም ያላቸው ከመሆኑ ጋር ከህዝባቸው በተለይም ደካማና ድሃ ለሆኑት ወገኖች እጅግ ያዝኑ ነበር፡፡ ለሚያገለግሉትና ለሚያስተዳድሩት ህዝብም በታሪክ አቻ ያልተገኘላቸው የርህራሄ ስሜት ነበራቸው፡፡ ዑመር በኸሊፋነት በተሾሙበት ወቅት ሙስሊሞች ሀይለኝነታቸውን ያውቁ ነበርና ሁኔታውን በፈሩ ጊዜ ዑመር እንዲህ በማለት ንግግር አድርገው ነበር፡፡

‹ያ ሀይለኝነት አሁን ከበፊቱ የጨመረ ስለመሆኑ አትዘንጉ፡፡ ነገርግን በበደለኞችና በሙስሊሞች ላይ ድንበርን በሚያልፉት ወገኖች ላይ ነው፡፡ የሠላም፣ የእምነትና የመካከለኛ አካሄድ ባለቤት ለሆኑ ሰዎች ግን እጅግ ለስላሣ ነኝ፡፡ አንድ ሰው ሲበደል አሊያም ድንበር ሲታለፍበት አይቼ የምተው አይደለሁም፡፡ ጉንጩን ከመሬት አጣብቄ እግሬን በሌላኛው ጉንጩ ላይ በማሣረፍ ሀቅን እንዲቀበል አደርገዋለሁ፡፡ በሌላ በኩል ግን ቁጥብና ጨዋ ለሆኑ ሰዎች በተቃራኒው ጉንጩን መሬት ላይ አሣርፍላቸዋለሁ፡፡›

የዑመር እዝነት ይህን ይመስል ነበር፡፡ ይህም እጅግ ጠንካራና ፍትሃዊ የሆነ አዛኝና ለሃይማኖቱ አሣቢ የሆነ መሪ የሚያደርገው ተግባር ነው፡፡ በዚህ ወደር የለሽ ባህሪያቸውም የተነሣ ዑመር ሰዎች ለሊቱን ተኝተው ሲያድሩ እርሣቸው

የህዝባቸውን ሁኔታ ለማየትና ችግረኞችን፤ ድሆችን ፍለጋ ይዘዋወሩ ነበር፡፡ ይህንን ታሪካቸውንና ገጠመኛቸውን ብዙዎቻችን የምናውቅ ይመስለኛል፡፡ በአንድ ወቅት አንዲት የመዲና ሴት ለልጆቿዋ የምታበላቸው በማጣቷ እያበሰለችላቸው በማስመሰል ባዶ ድስት ጥዳ ታታልላቸው ነበር፡፡ ይህን የምታደርገው ልጆችዋ ማልቀስ አቁመው ደክመው እንዲተኙላት በማሰብ ነው፡፡ ዑመር የዚህችን ሴትዮ ሁኔታ ባስተዋሉ ጊዜ ፈጥነው ከግምጃ ቤት ዱቄትና ዘይት ተሸክመው በማምጣት በእጃቸውም ምግቡን በማብሰል ልጆቹ ጠግበው እስኪበሉና ደስ ብሏቸውም እስኪጫወቱ ድረስ ነበር ያደረጉት፡፡

ከዚህ በላይ እጅግ የሚገርመው ደግሞ በረማዳ ዓመት የሆነው ነው፡፡ ይህ የሆነው በ18ኛው አመተ ሂጅራ ሲሆን በወቅቱ በሂጃዝ /መካከለኛው የዐረቢያ ምድር አካባቢ/ የሚኖሩ ሰዎችን ለዘጠኝ ወራት ያህል የዘለቀ ከፍተኛ የሆነ ድርቅ አግኝቷቸው ነበር፡፡ ከሁኔታው ከባድነት የተነሣ የዱር አውሬዎች ወደ ሰዎች በመሸሽ መጠጊያና ምግብ እስከመፈለግ ደርሠዋል፡፡ ሰዎችም የሚበላ ነገር ፍለጋ የአውሬና የነፍሣት ጉድጓዶችን ጭምር ይቆፍሩ ነበር፡፡ በመጨረሻም ዑመር የሚቀመስ ነገር ያፈላልጉላቸው ዘንድ ወደ ከተማ ሰዎች የእርዳታ ጥሪ አቀረቡ፡፡ ሰዎችም ለጥሪው ምላሽ ሠጡ፡፡ ዑመር በዚያ ዘመን በሀዘንና በሀሳብ በእጅጉ ነበር የተጎዱት፡፡ ይህም ከባድ ሀዘን በሰውነታቸው ላይ ትልቅ ክሣትን አመጣባቸው፡፡ ነጭ የነበረው መልካቸውም ጠቆረ፡፡ ሰዎች በወቅቱ እንዲህ እስከማለት ደርሰዋል፡፡ ‹አላህ (ሱ.ወ) በረማዳ ዘመን ያንን ችግር ከህዝቡ ላይ ባያነሣ ኖሮ ዑመር የሙስሊሞች ሁኔታ አሣስቦት በሀዘን ብዛት ይሞት ነበር፡፡›

በወቅቱ ከከተሞች አካባቢ ዱቄት፣ ቅቤና ሥጋ ይመጣላቸው የነበረ ሲሆን ዑመር ግን አንዳችም ሣይነኩ ለተጎዱ ሙስሊሞች ያከፋፍሉታል፡፡ ምግባቸውም ጥቁር ቂጣ እና ማጣቀሻ ዘይት ነበር፡፡ በወቅቱ ‹ሙስሊሞች ሁሉ እስኪጠግቡ ድረስ ሥጋና ቅቤ ላልበላ ለነፍሴ ምዬላታለሁ፡፡› በማለት ነፍሣቸውን አስታግሰዋታል፡፡

5ኛ) ዘገር የመምሬት ብቃታቸው

ዑመር (ረ.ዐ) ሠራተኞቻቸውን በደንብ ይቆጣጠራሉ፣ የግዛት አስተዳዳሪዎችንም በጥንቃቄ ይመርጣሉ። ከሚባዳና ዙህድ/ለዱኒያ ግዴለሽነት/ በላቀ መልኩ አንድን ሰው ለመሾም መስፈርት የሚያደርጉት የሥራ ብቃቱን ነው። ለመሾም የሚፈልጉትን ሰው በሰዎች መካከል ሲሆን አሚራቸው ሣይሆን እንደ አሚራቸው የሚሆን። አሚራቸው በሆነ ጊዜ ደግሞ ከነሱ ውስጥ እንደ አንዱ የሚሆን።› ‹የዚህ ዓይነት ሰው እፈልጋለሁ... እያሉ ያፈላልጉ ነበር

ለዚህም ይመስላል በአመራር ብቃታቸው የሚታወቁትን እንደ ዐምር ኢብኑ አልዓስ፣ ሙዓዊያ ኢብኑ አቢ ሱፍያን፣ ሙጊራ ኢብኑ ሹዕባንና የመሣሰሉትን ሰሃቦች በሚባዳና በዙህድ ከነሱ በላጭ ከሆኑት ከነዑስማን ኢብኑ ዐፋን፣ዐሊ፣ ጦልሐ፣ ዙበይርና ከመሣሰሉት በማስቀደም የሾሙት። ምክንያታቸውም የሾሟቸው ሰዎች ሥራውን አሣምረው እንደሚሠሩላቸው፣ በነገሮች እንደማይለሣለሱና ሰዎችም በፍራቻ እንደሚታዘዟቸው ያውቁ ስለነበር ነው።

ዑመር አንድ ሰው የሾሙ እንደሆነ ደብዳቤ ይጽፉለታል። ከሙሃጅሮችና ከአንሷር ሰዎችም የተወሰኑ ሰዎችን ምስክር ያደርጉበታል። ተሿሚዎቻቸውን ወደ ከተሞች ሲልኩ እንዲህ ይሏቸው ነበር፡-

‹እኔ አምባገገን አድርጌ አይደለም የሾምኳችሁ። ነገር ግን መሪዎች አድርጌ ነው የላክኋችሁ። ሙስሊሞችን አትቅጡ፣ አታዋርዷቸው፣ ግፍ አትስሩባቸው፣ አትፈትኗቸውም› (ይህን ማለታቸው በዘመቻ ላይ የቆይታ ጊዜያቸውን ከሁለት በዓላት በላይ ከቤተሰቦቻቸውና ሴቶቻቸው አታርዝሙባቸው ለማለት ነው።) የተባለ ሲሆን በመከልከልም አትበድሏቸው።› ይሏቸው ነበር።

በአንድ ወቅትም እንዲህ ብለው ነበር ‹እኔ አንድ ሰው ለመሾም አስብና ከሱ የተሻለ ሣገኝ ግን እተዋለሁ።› ዑመር በየአመቱ በሀጅ ወቅት ገዢዎቻቸው ስለሚመጡ ስለየመጡበት አካባቢ ሁኔታና እንዲሁም ስለ አስተዳደር ጉዳይ የሚጠይቁበት ዓመታዊ ኮንፈረንስ ነበራቸው።

ዑመር ርቀዋቸው ስለሚገኙ አስተዳዳሪዎቻቸው የነበራቸው መረጃና ዕውቀት በቅርብ እንዳሉ ያስመስላል። ሠራተኞች፣ አስተዳዳሪዎችና ዳኞች ዑመር

አጠገባቸው ሆኖ እያያቸው እስኪመስላቸው ድረስ ስለነሱ ትንሽ ትልቁን ሁሉ ያውቁ ነበር።

አስተዳዳሪዎች ሣያውቁ እነርሱ ወደ ሚያስተዳድሩት ግዛት የሚሄዱና በመረጃ የሚያግዟቸው ኢንስፔክተሮችም ነበሯቸው። ከነሱም አንደበት ስለ መሪዎቻቸው ሁኔታ አንዳንድ ነገሮችን ይጠይቃሉ። በአፅንኦትም ያዳምጣሉ። እነሱም በዐይናቸው የማየት ያህል ነገሮችን ይገልፁላቸዋል። ለዚህም ነው በዑመር የአስተዳዳሪነት ዘመን በሱ ፍትሃዊነትና መንግስቱ በጥንካሬ ሊዘልቅ የቻለው።

6ኛ) መመፈያዎችንና ድንጋጌዎችን የማጡጣት ብልሃት

ዑመር (ረ.ዐ) የአላህን ዲን (ሃይማኖት) ጠንቅቀው የሚያውቁ ሰው ናቸው። ስለ ሸሪዓ ህግጋት ምስጢርም ጥልቅ እውቀት ነበራቸው። የወረዱ የቁርኣን አንቀፆች ጥሩ ተንታኝም ነበሩ። በኸሊፋነት ዘመናቸው አዲስ ወደ እስልምና ለገቡ ሰዎች የሚደረገውን ጥቅማጥቅም ከልክለው ነበር። ለተደጓሚዎችም ኮስተር ባለ መልኩ በግልጽ እንዲህ አሏቸው ‹ያኔ ይሠጣችሁ የነበረው (ጥቅማ ጥቅም) የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ኢስላም በደከመ ሁኔታ ላይ ስለነበሩ ነው። አሁን ግን አላህ ዲኑን አጠናክሮታል። የፈለገ ማመን ይችላል የፈለገ ደግሞ መካድ መብቱ ነው።›

በዚያ በረማዳ የረሃብ ዘመን ደግሞ ከረሃቡ የተነሣ በሰዎች ላይ የደረሠውን የከፋ ችግር በማስተዋላቸው ይመስላል የሠረቀ ሰው ላይ የሚፈፀም ቅጣት እንዳይተገበር አግደው የነበረበት ሁኔታም ነበር። ባሮች ጌቶቻቸው ከፍተኛ ግፍ ፈፅመውባቸው አቤቱታ ያቀረቡ እንደሆነም ነፃ ያወጧቸው ነበር።

የሰሃቦች፣ የታቢዒዮችና እነሱንም ተከትለው የመጡ መልካም ሰዎች ትልቅ አብነት ሊሆን የሚችሉት ዑመር (ረ.ዐ) በከፊል ይህን ይመስላሉ። የርሳቸው አካሄድና የእስልምና አረዳድ ለእስልምና እውቀትም ሆነ እሱን በማግራቱ በኩል ያበረከተው አስተዋፅኦ ቀላል አልነበረም።

አላህ (ሱ.ወ) ለዑመር (ረ.ዐ) ይዘንላቸው። ለኢስላም ከበጎ እሣቤ፣ ከፍትህና ከሥልጣኔ፣ መሰረታዊ እና ፅኑ ነገሮችን በማበርከት ላደረጉት ጥረትና መልካም ነገር ሁሉ አላህ በመልካም ይመንዳቸው።

ከምርጥ ንግግሮቻቸው

ዑመር (ረ.ዐ) የኸሊፋነት ኃላፊነት በተሰጣቸው ጊዜ እንዲህ በማለት ተናግረው ነበር፡-

- ‹አላህ እናንተን በኔ ፈትኗችኋል፡፡ እኔንም በናንተ ፈትኖኛል፤ ከወዳጇ በኋላም እኔን በናንተ ውስጥ አስቀርቷል፡፡ በአላህ እምላለሁ! ከናንተ ጉዳይ ወደኔ የሚመጣውን ማንኛውንም ነገር ለሌላ ለማንም አሣልፌ አልሠጥም፡፡ የእውነት እና የእምነት ባለቤት ከሆኑትም መብታቸውን የማስቀርበት ምክንያት የለም፡፡ መልካም ካደረጉ መልካም አደርግላቸዋለሁ መጥፎ ከሠሩ ደግሞ እቀጣቸዋለሁ፡፡›

- ለጥፋት ፈፅሞ አልተዋችሁም፣ ለችግርም አልዳርጋችሁም፣ ወደ አንድ ቦታ ልኬያችሁ ከሆነ እስክትመለሱ ድረስ የዚያ ቤተሰብ ኃላፊ እኔ ነኝ፡፡

- በተደጋጋሚ ጠላትን ድል በማድረግ የሚታወቀውን ጀግናውን ኻሊድ ኢብኑ አልወሊድን ባልተጠበቀ ሁኔታ ከኃላፊነት ካነሱ በኋላም ለከተማ ሰዎች እንዲህ በማለት ጽፈዋል፡- ‹ኻሊድን ጠልቼ አሊያም ተንኮል አስቤ አይደለም ከኃላፊነት ያነሳሁት፡፡ ነገርግን ሰዎች በርሱ ፍፁም በመተማመን ችግር ውስጥ እንዳይገቡ ፈራሁ፡፡ ለፈተና እንዳይጋለጡም ሰጋሁ፡፡ ሁሉንም ነገር የሚሠራው አላህ መሆኑን እንዲያውቁ ለማሣየት ፈልጌ ነው፡፡›

- የሚራቅ ጦርነትን እንዲመራ ለሰዕድ ኃላፊነትን በሠጡት ጊዜ ለሰዕድ እንዲህ በማለት ጽፈው ነበር፡፡ ‹ሰዎች የአላህ መልእክተኛ አጎት እና ወዳጅ ነው የሚሉህ ነገር አደራህን እንዳያዘናጋህ፡፡ አላህ መጥፎን በመጥፎ አያብስም፣ ነገርግን መጥፎን በመልካም ነገር ያብሣል፡፡ እርሱን በመታዘዝ እንጂ በአላህና በሰው መካከል ዝምድና የለም፡፡ የሰው ልጅ ትልቁም ሆነ ተራ የሚባለው በአላህ ዘንድ እኩል ናቸው፡፡ አላህ ጌታቸው ሲሆን እነርሱ ደግሞ ባሮቹ ናቸው፡፡ በደህንነት ይበላለጣሉ፡፡ እርሱን በመታዘዝም ከሱ ዘንድ ያለውን ይቋደሣሉ፡፡›

የመጀመሪያ ዲስኩራቸው

- ‹ቁርኣንን አንብቡ ከርሱ ጋርም ተዋወቁ፤ በርሱ ሥሩ ከህዝቦቹ ትሆናላችሁ፡፡ ከመመዘናችሁ በፊት ራሣችሁን መዝኑ፤ ለትልቁ የመቅረቢያ ቀንም ተውባችሁ ተዘጋጁ፡፡ ለዚያ አንዲትም ነገር ሳትደበቅ አላህ ዘንድ ለምትቀርቡበት ቀን፡፡ አላህን በማመፅ ላይ ቢያዝ አንድም ሰው ሊታዘዙት መብት የለውም፡፡ ንቁ! እኔ ነፍሴን ከአላህ ሀብት አንፃር የቲምን እንደሚንከባከብ ሰው ነኝ፡፡ ካለኝ በራሴ እብቃቃለሁ ካጣሁ ደግሞ መልካም በሆነ መልኩ እወስዳለሁ፡፡›

- ከድስኩራቸው እንዲሁ፡- ‹ሰዎች ሆይ! አንዳንድ ከጃሎት ድህነት ነው፡፡ አንዳንድ ተስፋ መቁረጥም ሀብት ነው፡፡ እናንተ የማትበሉትን ትሰበስባላችሁ፤ በአታላዩዋ ዓለምም ውስጥ ሆናችሁ የማትደርሱበትን ነገር ተስፋ ታደርጋላችሁ፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በነበሩበት ዘመን ይወርድ የነበረው ወህይ/መለኮታዊ ራእይ/ ትወስዱ ነበር፡፡ አንድን ነገር በውስጡ የደበቀ ሰው በደበቀው ነገር ይያዛል፤ይፋ ያደረገውም እንዲሁ፡፡እባካችሁ መልካም ሥነ-ምግባራችሁን አሣዩን፡፡ የውስጣችሁን ግን አላህ ይወቅ፡፡ የሆነ (መጥፎ) ነገር አሣይቶን ውስጡ መልካም እንደሆን የሚነግረንን ሰው አናምነውም፡፡ መልካም ነገር ያሣየንን ግን በመልካምነቱ እንጠረጥረዋለን፡፡ ስግብግብነት ከንፍቅና መሆኑን እወቁ፡፡ ስለዚህ መልካም የሆነውን ነገር ሁሉ ለነፍሶቻችሁ አስቀድሙ፡፡

﴿وَمَن يُوقَ شُحَّ نَفۡسِهِۦ فَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡمُفۡلِحُونَ ١٦﴾ التغابن: ١٦

"አላህንም የቻላችሁትን ያክል ፍሩት፤ ትዕዛዙን ስሙ፤ ታዘዙም፤ ለግሱም፤ ለነፍሶቻችሁ መልካምን፥ (ይሰጣቹኋልና)፤ የነፍሱንም ንፍገት የሚከለክ ሰው፥ እነዚያ እነሱ ፍላጎታቸውን የሚገኙ ናቸው፡፡" (አት-ተጋቡን፡ 16)

እናንተ ሰዎች ሆይ! መመለሻችሁን አሳምሩ፡፡ ሁኔታዎቻችሁን አስተካክሉ፡፡ ጌታችሁ የሆነውን አላህን ፍሩ፡፡›

ድብቅ እና ደፋ

ሰዕድን ለጦርነት በላኩት ጊዜ እንዲህ መክረውት ነበር፡- ‹ራስህንና ካንተ ጋር ያሉትን መልካም ነገር አስለምድ፡፡ በበጎ ነገርም በሱም መልካም ነገራትን ሁሉ ጀምር፡፡ ለሁሉም መልካም ልማድ ዝግጅት እንደሚያስፈልገው እወቅ፡፡ የመልካም ነገር

ዝግጅቱ ከትእግስት ይጀምራል፡፡ ባገኘህ አሊያም በደረሰብህ ችግር ላይ ሁሉ አደራህን ትእግስት ይኑርህ፡፡ የአላህ ፍራቻ ይሰበሰብልሃልና፡፡ የአላህ ፍራቻ በሁለት ነገሮች ውስጥ እንደሚጠቃለል እወቅ፡፡ ይኸውም እርሱን በመታዘዝ እና እርሱ ከከለከለው ነገር በመራቅ ነው፡፡ እርሱን የሚታዘዝ ሰው እርሱን ሊታዘዝ የቻለው ይህችን ዓለም በመጥላቱና አኺራን በመውደዱ ነው፡፡ እርሱን አልታዘዝ ያለውም እርሱን ያልታዘዘው ይህችን ዓለም በመውደዱና አኺራን በመጥላቱ ነው፡፡ ቀልብ አላህ እሷን የፈጠረበት እውነታ አላት፡፡ ከነኚህም መካከል ግልፅ እና ድብቅ የሆኑ ነገራት አሉ፡፡ ግልፁ ነገር እሱን የሚወድ ሰውም ሆነ የሚያጥላላ ሰው በርሷ ዘንድ እኩል መሆኑ ነው፡፡ ድብቁ ነገር ደግሞ ከምላሱ በሚወጣው የጥበብ ቃልና ለሰው ባለው ውዴታ ይታወቃል፡፡ በሰው ዘንድ ለመወደድ አትሰስት፡፡ ነቢያት አላህ ለሰዎች እንዲያስወድዳቸው ለምነውታል፡፡ አላህ አንድን ሰው የወደደ እንደሆነ ያስወድደዋል፡፡ የጠላው እንደሆነም ሌሎች እንዲጠሉት ያደርጋል፡፡ በአላህ ዘንድ ያለህን ደረጃ በሰው ዘንድ በጉዳይህ በሚወስነው ጋር አነፃፅር፡፡›

ጠንቋሎች ስለንድ ጦር ከጠላትም በላይ እጅግ አስፈሪ ነው

ለሰዕድ እና ከርሱ ጋር ለነበሩ ወታደሮች እንዲህ በማለት ፅፈዋል፡- ‹አንተንና ካንተ ጋር ያሉትን ወታደሮች ሁሉ በሁሉም ሁኔታችሁ ውስጥ አላህን እንድትፈሩ አዝዛችኋለሁ፡፡ በጠላት ላይ ትልቁ ትጥቅ የአላህ ፍራቻ ነው፡፡ በጦርነትም ላይ ትልቁ የማሸነፊያ ስንቅ እሱ ነው፡፡ አንተና ካንተ ጋር ያሉ ሁሉ ሃጢአትን በእጅጉ እንድትጠነቀቁ እመክራችኋለሁ፡፡ የአንድ ጦር ወንጀልና ሀጢአት ከጠላት ጦር በላይ ለጦሩ አስፈሪ ነው፡፡ ሙስሊሞች እኮ ከአላህ ድልን የሚያገኙት ጠላቶቻቸው በአላህ ያመፁ በመሆናቸው ነው፡፡ ይህ ባይሆን ኖሮ በነሱ ላይ የበላይነትን አናገኝም ነበር፡፡ ቁጥራችን ከቁጥራቸው አንፃር ትንሽ ነውና፡፡ ዝግጅታችንም እንደ ዝግጅታቸው አይደለምና፡፡ በአላህ በማመፅ በኩል ከነሱ ጋር ተመሣሣይ/እኩል/ የሆንን እንደሆነ በሀይልና ጥንካሬ እነርሱ በኛ ላይ ብልጫ ይኖራቸዋል፡፡ በደረጃ የማንበልጣቸው ከሆነ በሀይላችን አናሸንፋቸውም፡፡ደግሞ የምትሠሩትን የሚያውቁ ጠባቂ መላኢኮች በናንተ ላይ ተመድበው እንዳሉ እወቁ፡፡ እነርሱንም እፈሩ፡፡ በአላህ መንገድ ላይ ሆናችሁም ሀጢአት አትሥሩ፡፡ ጠላታችን ከኛ በላይ የመጥፎ ሥራዎች ባለቤት ነውና አላህ እነሱን በኛ አይለቅብንም

ብላችሁ አትዘናጉ፡፡ አላህ በበኒ ኢስራኢሎች ላይ መጀሶችን /እሣት አምላኪዎችን/ እንደለቀቀባቸው ሁሉ በህዝቦች ላይ ከነሱ የከፉትን ሊለቅባቸው ይችላል፡፡

﴿فَجَاسُواْ خِلَٰلَ ٱلدِّيَارِۚ وَكَانَ وَعۡدٗا مَّفۡعُولٗا ٥﴾ الإسراء: ٥

"uu?„‹U S"ŸM ÃSLKdK<& (Ãu[w\ታM&) ÃI }ðéT> kÖaU 'u`::" (አል-ኢስራእ፡ 5)

በጠላቶቻችሁ ላይ ድልን እንዲሠጣችሁ እንደምትለምኑት ሁሉ በነፍሶቻችሁም ላይ እንዲያግዛችሁ አላህን ለምኑት፡፡ ይህን ለኔም ለናንተም እለምንላችኋለሁ፡፡›

የመመዘኛ ጥያቄዎች

1. የዑመርን (ረ.ዐ) ታሪክ በተወሰኑ መስመሮች ነቅሰህ በማውጣት አስቀምጥ
2. የዑመርን (ረ.ዐ) ስም፣ መጠሪያና መገለጫ ጥቀስ
3. የዑመርን (ረ.ዐ) ትሩፋትና አሻራዎች አብራራ
4. ዑመርን (ረ.ዐ) የሕይወት ታሪክ ሊጠቅሙ የሚችሉትን ትምህርቶችና ምክሮች ነቅሰህ በማውጣት አስፍር፡፡
5. ከዑመር (ረ.ዐ) ትሩፋትና አሻራዎች የተመሰጥክባቸውን አብይ ትሩፋትና አሻራዎች ነቅሰህ በማውጣት በአጭሩ አስቀምጥ፡፡
6. ከዑመር (ረ.ዐ) ንግግሮች ይበልጥ የመሰጡህን ንግግሮች ነቅሰህ በማውጣት አብራራ፡፡ ተመስጦው በአንተ ላይ እንዴት ነበር፡፡

አቡ ዑበይዳህ ዑምር ኢብኑ አል-ጀራሕ

(40 ከሂጅራ በፊት እስከ 18 ከሂጅራ በኋላ)

(584-630 ዓ.ል)

የትምህርቱ ዓላማ

1. የዚህ ሕዝብ ቀሳትና የሆነው ማን እንደሆነ እንዲያስተዋውቅ ማስቻል፡፡
2. የዑበይዱላህ ኢብን አል-ጀራሕን አበይት አሻራዎች እንዲዘረዝር ማስቻል፡፡
3. በአቢ ዑበይዱላህ ኢብን አል-ጀራሕ ለአንዱ ወታደሩ ከመሞታቸው በፊት የሰጡትን ምክር እንዲጠቅስ ማስቻል፡፡
4. ከአቢ ዑበይዱላህ ኢብን አልጀራሕ (ረ.ዐ) የቀሰሙትን እንዲጠቅስ ማስቻል፡፡

ሙሉ ሥማቸው ዐምር ኢብኑ ዐብዱላህ ኢብኑ አል-ጀራሕ ኢብኑ ሂላል ኢብኑ ኡሀይብ ኢብኑ ደባህ ኢብኑ አል-ሐሪስ ኢብኑ ፈህር ኢብኑ ማሊክ ሲሆን ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር በቅድመ አያታቸው ፈህር ኢብኑ ማሊክ ላይ ይገናኛሉ፡፡

እናታቸው ደግሞ ኡመይማ ቢንት ጃቢር ኢብኑ ዐብዱልዐዚዝ ኢብኑ ዓሚራህ ትባላለች፡፡ በብዛት የሚታወቁበት መጠሪያ ሥማቸው አቡ ዑበይዳህ ሲሆን የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ‹አሚን /ታማኙ/› በማለት ጠርተዋቸዋል፡፡ አቡ ዑበይዳ ቢሰልሙም አባታቸው ግን በሽርክ፣ በክህደት እና ጥመት መንገዱ ፀና፡፡ አባታቸውን ወደ እስልምና ለማስገባት ያደረጉት ጥረትም አልተሣካላቸውም፡፡ ሙስሊሞች እና የመካ ከሃዲያን በተገናኙበት በታላቁ የበድር ጦርነት ቀን አቡ ዑበይዳ ከአባታቸው ጋር በተለያየ ጎራ በመሆን ፊት ለፊት ተገናኙ፡፡ እምነት እና የሥጋ ዝምድና አንድ ላይ የመጡባቸው አቡ ዑበይዳህ እምነታቸውን መረጡ፡፡ የአላህን እና የዲኑን ጠላት አባታቸውን ከመጋደል ውጭ ምርጫ አልነበራቸውምና አባታቸውን ገደሉ፡፡ በዚህ ዙሪያም አላህ (ሱ.ወ) የቁርአን አንቀጽ አወረደ፡፡

﴿لَّا تَجِدُ قَوۡمٗا يُؤۡمِنُونَ بِٱللَّهِ وَٱلۡيَوۡمِ ٱلۡأٓخِرِ يُوَآدُّونَ مَنۡ حَآدَّ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥ وَلَوۡ كَانُوٓاْ ءَابَآءَهُمۡ أَوۡ أَبۡنَآءَهُمۡ أَوۡ إِخۡوَٰنَهُمۡ أَوۡ عَشِيرَتَهُمۡۚ أُوْلَٰٓئِكَ كَتَبَ فِي قُلُوبِهِمُ ٱلۡإِيمَٰنَ ٢٢﴾ المجادلة: ٢٢

"በአላህና በሚጨርሻው ቀን የሚያምኑትን ሕዝቦች፥ አላህንና መልክተኛውን የሚቃወሩትን ሰዎች፤ አባቶቻቸው ወይም ልጆቻቸው፤ ወይም ወንደሞቻቸው ወይም ዘመዶቻቸው ቢኾኑም እንኳ የሚወዳጁ ኾነ ው አታገኛቸውም፤ እነዚያ በልቦቻቸው ወስጥ እምነትን ጽፏል፤" (አል-ሙጀደላህ፡ 22)

አቡ ዑበይዳ ረጅም፣ ቀጭን እና ብዙም ፂም ያልነበራቸው ሰው ናቸው። እውቅ ፈረሠኛና ታላቅ ጀግና ሲሆኑ ጠንካራ አፈጣጠርና ሰውነት የነበራቸው ሰው ነበሩ። ስለዚህች ዓለም በነበራቸው የግድ የለሽነት አመለካከታቸው ይታወቃሉ። አላህን በጣም የሚፈሩና እውነተኛ ፍራቻ ያደረባቸው፣ በጦርነት ወቅት ጀግንነታቸው ጎልቶ የሚታይ፣ ፈጣሪያቸው ፊት በሚቀርቡበት ጊዜ ግን ከፍራቻው የተነሳ እጅግ የሚርበተበቱ ሰው ነበሩ።

አቡ ዑበይዳ በአቡበክር እጅ ነበር ኢስላምን የተቀበሉት። ወደ እስልምና ይገባ ዘንድ ጥሪ ባደረጉላቸው ጊዜ ወደ እምነቱ የገቡት እጅግ ፈጥነው ነው። የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ፊት በመቆምም እስልምናቸውን በይፋ አወጁ። ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የሌለ ስለመሆኑ እና ሙሀመድም (ሰ.ዐ.ወ) እውነተኛ የአላህ መልእክተኛ መሆናቸውን መሠከሩ።

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ስለሳቸው እንዲህ ብለዋል ‹ለሁሉም ህዝብ ታማኝ አለው። የዚህ ኡመት ታማኙ ሰው አቡ ዑበይዳህ ዓምር ኢብኑ አልጀራህ ነው።›

ሙስሊሞች በመካ ይደርስባቸው የነበረውን ግፍ በመሸሽ ወደ ሃበሻ እንዲሠደዱ ነቢዩ በፈቀዱላቸው ጊዜ ከተሠደዱ ሰዎች መካከል ነበሩ። ከቆይታ በኋላም ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጎን በመቆም እስልምናን ለመከላከል ወደ መዲና ተመልሰዋል። ከርሣቸው ጋርም በሁሉም ዘመቻዎች እና ጦርነቶች ላይ ተሣትፈዋል። ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከሞቱ በኋላም ቢሆን የእምነት ጉዟቸውን አላቋረጡም። ለእስልምናም አቅማቸው የፈቀደውን ሁሉ አበርክተዋል። የቻሉትን

ሁሉ ሠርተዋል፡፡ ስለዚህች ዓለም ግድ ያልነበራቸው /ዛሂድ/ ነበሩ፡፡ ትልቁ ሀሣባቸውንም አኺራ ላይ በማድረግ ኖረዋል፡፡ ለማይቀረው እወነተኛ ሀገራቸውም በወጉ ሰንቀዋል፡፡ ሲበዛ አላህን ፈሪ፣ ቃል ኪዳን ጠባቂና ታማኝ ሰው ነበሩ፡፡

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) አቡ ዑበይዳህን ወደዋቸዋል፡፡ አቡ ዑበይዳም እርሣቸውን አብዝተው ወደዋል፡፡ በኡሁድ ጦርነት በሙስሊሞች ላይ ከፍተኛ ጉዳት በደረሠበት ወቅት አቡ ዑበይዳ ለነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በፅናት እና ቆራጥነት የተከላከሉ ትልቅ ምሽጋቸው ሆነው ነበር የዋሉት፡፡

የነጅራን ልዑካኖች እስልምናን ፈልገው ከየመን ወደ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ በመጡ ጊዜ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ አሏቸው፡- ‹ታማኝ የሆነ ሰው ከናንተ ጋር እልካለሁ፡፡ እውነት ታማኝ... እውነት ታማኝ ... እውነት ታማኝ፡፡› አሏቸው፡፡ ከነርሱ ጋርም ቁርአንን ያስተምሯቸው ዘንድ አቡ ዑበይዳህን ላኩ፡፡

አቡ ዑበይዳ ስለዚህች ዓለም የነበራቸው ግድ የለሽነት

ኢማም ጦበራኒ ከማሊክ (ረ.ዐ) እንደዘገቡት ዑመር ኢብኑ አልኸጧብ (ረ.ዐ) አራት መቶ ዲናር ወስደው ከአንድ ቋጠሮ ውስጥ በማድረግ ለአንድ አገልጋያቸው በመስጠት ‹ውሰድና ለአቡ ዑበይዳ ስጥ ጥቂት እዚያው ቆይና ምን እንደሚያደርግም ተመልከት፡፡› አሉት፡፡ አገልጋያቸውም ወደርሱ በመሄድ ‹የምእመናን መሪ ይህን አንዳንድ ጉዳይህን ፈፅምበት ይሉሃል፡፡› አለው፡፡ አቡ ዑበይዳም ‹አላህ ዑመርን ያስጠጋው፣ ይዘንለትም፡፡› አለ፡፡ ከዚያም ሴት አገልጋዩን በመጥራት ‹አንቺ ልጅ ሆይ! እነኚህን ሰባት ነገሮች ውሰጂና እስክትጨርሺ ድረስ ለእገሌ፣ አምስቱን ለእገሌ፣ አምስቱን ደግሞ ለእገሌ ስጭ..፡፡› አላት፡፡ አገልጋዩም ወደ ዑመር (ረ.ዐ) በመመለስ ያየውን ሁሉ ነገራቸው፡፡

ኢማም ቡኻሪም በታሪኩ ውስጥ ከዘይድ ኢብኑ አስለም ከአባቱ እንደዘገቡት ዑመር ኢብኑ አልኸጧብ ለሰሃቦቻቸውም ‹እስቲ ተመኙ!› አሏቸው፡፡ አንደኛው ‹ይህን ቤት የሚሞላ ወርቅ ቢኖረኝና በአላህ መንገድ ላይ ብመፀውት ብዬ ተመኘሁ፡፡› አለ፡፡ ሌላኛውም እንዲሁ ተመኘ፡፡ ዑመር እንዲህ አሉ፡- ‹እኔ ግን ይህን ቤት የሚሞላ የአቡ ዑበይዳ ኢብኑ አል ጀራህ፣ የሙዓዝ ኢብኑ ጀበል እና

የሁዘይፋ ኢብኑ አል የማን ዓይነት ሰዎች በኖሩኝና በአላህ መንገድ ላይ ባሠማራቸው ተመኘሁ::›

ከዚያም ለአቡ ዑበይዳ ኢብኑ አልጀራህ ገንዘብ ላኩ እሳቸውም አከፋፍለው ጨረሱ፤ ለሙዓዝ ኢብኑ ጀበልም እንዲሁ ላኩ እሳቸውም አከፋፈሉ፤ ለሁዘይፋ ኢብኑ አል የማንም ላኩ እሳቸውም አከፋፈሉ:: ዑመርም ለሰዎች ‹ብያችሁ ነበር::› አሏቸው::

በይሀቂ ከአስለም እንደዘገቡት በረማዳ ዓመት መሬት በደረቀች ጊዜ ዑመር ኢብኑ አልኻጧብ አቡ ዑበይዳህ ኢብኑ አልጀራህን ጠሩና እንዲወጡ አዘዟቸው:: እሳቸውም ወጡ:: ሲመለሱ አንድ ሺህ ዲናር ላኩላቸው:: አቡ ዑበይዳም ‹የኸጧብ ልጅ ሆይ! እኔ ላንተ አልሠራሁም:: የሠራሁት ለአላህ ነው:: ለአላህ ብዬ በሠራሁት ነገር ደግሞ አንዳችም ነገር አልወስድም::› አሉ:: ዑመርም እንዲህ አሏቸው ‹የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ለሆነ ነገር ልከውን ስንመለስ የሆነ ነገር ሲሠጡን ደስ አላለንም ነበር:: የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ግን እንቢ አሉን:: አንተ ሰው እባክህን ይህን ነገር ተቀበል:: በዲንህም ሆነ በዱኒያ ጉዳይህ ላይ ታገዝበት::› አሉ:: አቡ ዑበይዳም ተቀበሉ:: ኢብኑ ኹዘይማና ሃኪምም ዘግበውታል::

ሙዐመር እንደዘገቡት ደግሞ ዑመር ወደ ሻም ሀገር በመጡ ጊዜ በርካታ ሕዝብና በምድር ላይ ታላላቅ የሚባሉ ሰዎች አቀባበል አደረጉላቸው:: ዑመርም እንደ ደረሱ ‹ወንድሜ የታለ?› በማለት ጠየቁ:: ‹ማነው እሱ?› አሏቸው:: ‹አቡ ዑበይዳህ::› አሏቸው:: ‹አሁን ይመጣል::› አሏቸው:: በመጡ ጊዜ ወረዱና ጨበጧቸው:: ወደ አቡ ዑበይዳ ቤትም ገቡ:: ዑመር በቤቱ ውስጥ ያዩት ነገር ሰይፋቸውን፣ ጥሩራቸውን እና ኮርቻቸውን ብቻ ነበር:: ዑመርም ‹ሌሎች ጓደኞችህ ያላቸውን ነገር ምናለ አንተም ቢኖርህ::› አሉ:: ‹የምእመናን መሪ ሆይ! ይህ ከመድረሻዬ ያደርሠኛል::› አሏቸው::

ችሮታቸው፣ ጠተናነሳቸው

በመተናነስና ለሌሎች ዝቅ በማለት ሰናይ ባህሪያት በኩል አቡ ዑበይዳ ትልቅ አስገራሚ ምሳሌ መሆን የሚችሉ ሰው ናቸው።

ዑመር ኢብኑ አልኸጣብ (ረ.ዐ) በኸሊፋነት እንደተሾሙ ለአቡ ዑበይዳህ ከኻሊድ ኢብኑ አልወሊድ ኃላፊነትን ተረክቦ የሙስሊሙን ጦር ይመሩ ዘንድ ላኩባቸው። በወቅቱ ኻሊድ ከጠላት ጋር ጦርነት ውስጥ ሊገባ እጅግ ተቃርቦ ነበር። የዑመር መልእክተኛ አቡ ዑበይዳ ዘንድ ደርሰው መልእክቱን ለኻሊድ ሰጧቸው። አቡ ዑበይዳ በጊዜው ሁኔታውንና ሊያስከትል የሚችለውን መዘዝ በደንብ አጤኑ። በመሆኑም ወሣኙ ፍልሚያ እስከሚያበቃበት ጊዜ ድረስ ነገሩን ከኻሊድ ደበቁ።

ከጦርነቱ በኋላም ወደ ጦሩ መሪ ኻሊድ ዘንድ እጅግ በመተናነስ ሄደው ‹ይህ የምእመናን መሪ የላኩት መልእክት ነው።› በማለት ሰጧቸው። ኻሊድም ‹አቡ ዑበይዳ ሆይ! አላህ ይዘንልህ። መልእክቱ እንደደረሠህ ለምን አልነገርከኝም ነበር።› አሏቸው።አቡ ዑበይዳም ‹ጦርነቱን እንዳላስተጓጉልብህ ፈራሁ። የዚህችን ዓለም ሥልጣን የምንፈልግ ለሷም የምንሠራ አይደለንም። ሁላችንም በአላህ መንገድ ወንድማማቾች ነን› አሏቸው።

አቡ ዑበይዳ የጊዜው አስፈሪዎቹ ፋርሶች የተንበረከኩላቸው፣ ጠንካሮቹ ሮሞች እጅ የሠጡላቸው ጀግና ናቸው። በአመራሩ ጊዜም ግዛቱ በሻም አካባቢ እየሠፋ ሄደ። በሳቸው መሪነት በተደረጉ ዘመቻዎች ሙስሊሞች ታላላቅ ድሎችን ተጎናፀፉ። ነገርግን ይህ ሁሉ ግዛትና ሀብት ለዲናቸውና ለኢኺራቸው ከመሥራት አላዘናጋቸውም። የዚህችን ዓለም ብልጭልጭ ጥቅም ከምንም ባለመቁጠራቸው የተነሣ ወደ ዱኒያ አልተሳቡም። አልተስገበገቡላትም፣ አልጓጉላትምም። የሙስሊሞች አሚር ቢሆኑም ከተራው ሰው የሚለዩበት ሁኔታ አልነበረም። ከነርሱ ጋር ተቀላቅሎ ባሉበት ሁኔታ እርሳቸውን ከሌሎች ባልደረቦቻቸው መለየት ያስቸግራል።

ዑመር ወደ ሻም ሀገር በመጡበት ወቅት አቡ ዑበይዳ አቀባበል አደረጉላቸው፤ ጨበጧቸውም፤ እጃቸውንም ሣሙት። ከዚያም ሁለቱ ሰዎች

ተነጥለው ማልቀስ ያዙ፡፡ ኢብኑ ተሚምም ከዚህ በመነሣት ‹እጅን መሣም ሱና ነው፡፡› ይሉ ነበር፡፡

በሞት አፋፍ ላይ ሆነው ለወታደሮቻቸው ያስተላለፉት ኑዛዜ

አቡ ዑበይዳ በዑመር ኢብኑ አልኸጧብ የኸሊፋነት ዘመን በዮርዳኖስ ምድር ሳሉ በወረርሽኝ በሽታ ተጠቁ። ሞት አፋፍ ላይ በደረሱም ጊዜ ለወታደሮቻቸው የሚከተለውን የኑዛዜ መልእክት አስተላልፈው ነበር።

‹እኔ በአንድ ነገር እመክራችኋለሁ ከሰማችሁኝ ዘወትርም መልካም ነገር ላይ ትሆናላችሁ...ሰላትን ስገዱ፣ ዘካን ስጡ፣ የረመዷንን ወር ጹሙ፣ መፅውቱ፣ ሀጅና ዑምራ አድርጉ፣ ተመካከሩ፣ ለአሚሮቻችሁ አስቡ/መልካም ምክር ስጡ/ አታታሏቸው፣ ይህች ዱኒያ እንዳታጠፋችሁ ተጠንቀቁ። የሰው ልጅ ሺህ ዓመት ቢኖር እንኳ አሁን እኔን የምታዩበት ዓይነት አወዳደቅ መውደቁ አይቀርም... አላህ በሰው ልጅ ላይ ሞትን ጽፏል፤ ብልሁም ሆነ ለጌታው ታዛዥ የሆነው ለማይቀረው ቀን የሚዘጋጀውም ይሞታሉ...። የአላህ ሰላምታና እዝነት በናንተ ላይ ይሁን።

ከዚያም ወደ ሙዓዝ ዘወር በማለት ‹ሙዓዝ ሆይ! ሰዎችን አሰግድ።› አሏቸው። ወዲያውኑ ነፍሳቸው ከሰውነታቸው ተለየች። ሙዓዝም ‹ሰዎች ሆይ! የዚህ ሰው ሞት አስደንጋጭና አሣማሚ ነው። በአላህ እምላለሁ! እኔ ከዚህ ሰው የበለጠ ልበ ሰፊ፣ ለፍፃሜው የሚጨነቅ፣ ለህዝቡ አሳቢ የሆነ ሰው አላየሁም። አላህ ይዘንለት በሉ አላህ ይዘንላችሁ።› አሏቸው።

አቡ ዑበይዳ ከከሃዲያን ጋር በተዋጉባትና ትልቅ ፈተና ባዩበት ምድር ላይ የመጨረሻውን የእስትንፋስ ቃል ተናገሩ። እርኩስ ከሆነው ባእድ አምልኮ ካፀዷት በኋላ ፍትህና ጥበብን ካሠፈኑ በኋላም እዚያው ተቀበሩ።

ዑመር ኢብኑ አልኸጧብ ሞት አፋፍ ላይ ሆነው እንዲህ ብለው ነበር ‹አቡ ዑበይዳን ባገኘው ኖሮ አንድም ሰው ሳላማክር በኸሊፋነት እንዲተካኝ አደርገው ነበር። ስለጉዳዬ የተጠየቅኩ እንደሆነም የአላህን ታማኝ እና የአላህን መልእክተኛ ታማኝ የሆነ ሰው ነው የተካሁት እላለሁ።

አቡ ዑበይዳ በርግጥም ከአላህ፣ ከአላህ መልእክተኛም ሆነ ከራሳቸው ጋር እውነተኛና ለእምነታቸውም ማድረግ ያለባቸውን ሁሉ ያደረጉ ታማኝ ሰው ነበሩ።

አላህ (ሱ.ወ) ለአቡ ዑበይዳ ይዘንለት፡፡ ከጀነት ሰልሰቢል የተሰኘ መጠጥ ያጠጣቸው፡፡

የመመዘኛ ጥያቄዎች

1. የዚህ ሕዝብ (ኡምማህ) ታማኝ ማነው?
2. የአቡ-ዑበይዳህን (ረ.ዐ) አሻራዎች ከእሱስ ምን እንደተማርክ ጥቀስ፡፡
3. አቡ-ዑበይዳህ ለወታደራቸው ያስተላለፉትን ትዕዛዝ ከሚሰጠው ምክርና ትምህርት ጋር በማያያዝ ጥቀስ፡፡
4. ከአቡ-ዑበይዳህ ኢብን አል-ጀራህ (ረ.ዐ) የሕይወት ታሪክ የቀሰምካቸውን ትምህርቶች ጥቀስ፡፡

ሰልማን አል-ፋሪሲ
(እውነትን ፈላጊው)

የዚህን እውነትንና አምላኩን ፈላጊ ሰሃባ ታሪክ እስቲ ከራሱ አንደበት እንስማ፡፡ እሱ ስለራሱ ስሜት በስሜቱ ውስጥ ሆኖ ያወራንና ዝርዝር ሁኔታዎችንም ይነግረን ዘንድ እድል እንስጠው፡፡

እንዲህ ይላል አስበሃን (ኢራን ውስጥ የምትገኝ ከተማ ናት) አካባቢ ጂያን ከምትባል መንደር የተገኘሁ ፈረሠኛ ነኝ፡፡ አባቴ የመንደሯ አስተዳዳሪ አለቃ ነበር፡፡ የመንደሯም ዋና ሀብታምና እጅግ የተከበረ ሰው ነው፡፡ ከተወለድኩበት ጊዜ ጀምሮ ከአላህ ፍጡራን ሁሉ ወደርሱ ዘንድ ይበልጥ የተወደድኩ ነኝ ለማለት እደፍራለሁ፡፡ ለኔ የነበረው ውዴታ በየቀኑ ሲጨምር እንጂ ሲቀንስ አይታይም፡፡ በመሆኑም ክፉ ነገር እንዳይደርስብኝ በመስጋት ይመስላል ሴት ልጅ ቤት እንድትውል እንደሚደረገው ሁሉ እሱም ቤት ውስጥ እንድውልና ከቤት እንዳልወጣ ያደርገኝ ነበር፡፡ በመጀሪያ /የእሣት አምላኪዎች እምነት/ ላይ ጠንካራ ተከታይ ነበርኩ፡፡ የምናመልከው እሳት ዋና አቀጣጣይ እስከመሆንም ደርሼ ነበር፡፡ በቀንም ሆነ በለሊት ለአፍታ እንኳ ነበልባሏ እንዳይጠፋ ዘወትር በመከታተል አቀጣጥላት ነበር፡፡

አባቴ ብዙ ነገር የምትሸፍንልንና ትልቅ ምርት የምናገኝበት የእርሻ መተዳደሪያ ማሣ ነበረው፡፡ እዚያ በመዋልም ዘወትር የማሣውን ምርት ያመጣልን ነበር፡፡ አንድ ቀን ግን በሆነ ሥራ በመጠመዱ ምክንያት ወደ መንደሩ መሄድ አልቻለም፡፡ ‹ልጄ ሆይ! በምታየው መልኩ ወደ እርሻ ማሣው መድረስ አልቻልኩም፡፡ ዛሬ ወደዚያ ሂድና አንተ ኃላፊነቱን ተወጣ፡፡› አለኝ፡፡ እኔም ወደዚያው በማሰብ ከቤት ተንቀሣቀስኩኝ፡፡ በመንገድ ላይ ሳለሁ ግን አንድ የክርስቲያኖች ቤተመቅደስ አጋጠመኝ፡፡ ሰዎች እሷ ውስጥ ሆነው ሲፀልዩ ድምፃቸውን ሰማሁ፡፡ ይህ ነገርም ትኩረቴን ሣበው፡፡

አባቴ ለረጅም ጊዜ በቤት ውስጥ አስሮ አኑሮኝ ስለነበር ከዚያ ቀደም ብሎ ስለ ክርስቲያኖችም ሆነ ስለ ሌሎች እምነቶች ምንም የማውቀው ነገር

አልነበረኝም። ድምፃቸውን በሰማሁ ጊዜም የሚሠሩትን ለማየት ብዬ ወደ ቤተክርስቲያኑ ውስጥ ገባሁ።

ባየኋቸውም ጊዜ ፀሎታቸው ማረከኝ። ወደ እምነታቸው ለመግባትም ከጀልኩኝ። በውስጤም ‹በአላህ እምላለሁ! ይሄ እኛ ካለንበት ነገር ይሻላል› አልኩኝ። በአላህ እምላለሁ! ፀሐይ እስክትጠልቅ ድረስ ከዚያ ቦታ አልተለየሁም። ወደ አባቴ መልእክትም አልሄድኩም። ሰዎቹንም ‹የዚህ እምነት መሠረቱ ምንድ ነው?› ብዬ ጠየቅኋቸው እነርሱም ‹ከሻም /ሶሪያና አካባቢው/ ሀገር ነው› አሉኝ።

ወደ ቤትም በተመለስኩ ጊዜ አባቴ አገኘኝና ምን ስሠራ እንደዋልኩ ጠየቀኝ። ‹አባቴ ሆይ! በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ የሚፀልዩ ሰዎች አጋጠሙኝና ስለእምነታቸው የያሁት ነገር ማርኮኝ ፀሃይ እስከምትጠልቅበት ጊዜ ድረስ እዚያው ነበር የዋልኩት› አልኩት።

በሠራሁት ነገር አባቴ በጣም ተቆጣና ፊቱ ጠቆረ። ‹ልጄ ሆይ! ያ እምነት ምንም መልካም ነገር የለውም። የእናት አባቶችህ ሃይማኖት ከሱ የተሻለ ነው።› አለኝ። ‹አይደለም በአላህ እምላለሁ! አይሆንም! ሃይማኖታቸው ከሃይማኖታችን ይበልጣል› አልኩት። አባቴ የተናገርኩት ነገር አስፈራው። ከቀደምት እምነቴም እንዳልመለስ ሠጋ። ስለሆነም ቤት ውስጥ አገተኝ። በእግሬም ሠንሠለት አደረገብኝ።

አጋጣሚው በተመቻቸልኝ ጊዜ ወደ ሻም ሀገር የሚሄድ ቅፍለት ካለ ያሳውቁኝ ዘንድ ወደ ክርስቲያኖቹ መልእክት ላክሁኝ። ብዙም ሣይቆይ ወደ ሻም የሚሄድ ቅፍለት እነርሱ ዘንድ መጣ። እነርሱም መልእክት ላኩብኝ። ሰንሰለቴን ፈታሁና በድብቅ ከነርሱ ጋር ሆኜ ወደ ሻም ሀገር ስደት ወጣሁ።

ሻም ሀገር ደርሰን ባረፍን ጊዜ ‹ከዚህ እምነት ሰዎች ውስጥ በላጩ ሰው ማነው?› ብዬ ጠየቅኩኝ። እነርሱም ‹የቤተክርስቲያኒቱ የበላይ ጠባቂ አል-አስቀፍ /ጳጳስ/ ነው።› አሉኝ። ወደርሱም ሄድኩና ‹እኔ ወደ ክርስትና መግባት እፈልጋለሁ፤ ካንተ ላለመለየትና ላገለግልህም እሻለሁ፤ ካንተ ለመማርና ካንተ ጋር ለመፀለይም ፈቅጃለሁ› አልኩት። እርሱም ፈቃደኛ ሆነ። እርሱ ዘንድ ገባሁና እሱን ማገልገል ያዝኩኝ።

ነገር ግን ሰውየው መጥፎ ሰው ስለመሆኑ ለማወቅ ብዙ ጊዜ አልጀብኝም። ተከታዮቹ እንዲመፀውቱ ያነሳሣቸዋል። የምንዳዋንም ታላቅነት ይነግራቸው ነበር። ነገርግን በአላህ መንገድ ላይ እንዲያውል አስበው ሲሠጡት ለድሆችና ለችግረኞች ምንም ሣይሠጥ የሚሠጠውን ሁሉ ለራሱ ያስቀምጥ ነበር። በዚህ መልኩም ሰባት /ትልልቅ ስልቻዎችን/ጆኒያዎችን/ አከማችቷል።

በዚህ ምክንያት እጅግ ጠላሁት። ሆኖም ግን በሕይወት ብዙም ባለመቆየቱ ክርስቲያኖች ሊቀብሩት ተሰበሰቡ። ‹ይህ የናንተ ሰውዬ መጥፎ ሰው ነው። እናንተን ትመፀውቱ ዘንድ ያነሣሣችኋል፤ ምንዳዋንም ይነግራችኋል። ስታመጡ ግን ለራሱ ያኖራል ያከማቻል። ለድሆች አንዳችም ነገር አይሠጥም› አልኳቸው። እነርሱም ‹ይህን ነገር እንዴት ልታውቅ ቻልክ?› አሉኝ። እኔም ‹ያስቀመጠበትን ቦታ አሣያችኋለሁ› አልኳቸው። ‹አሣየን› አሉኝ። ቦታውን አሣየኋቸውና ወርቅና ብር የተሞላ ሰባት ትላልቅ ስልቻዎችን አወጡ። ይህን ባዩ ጊዜ ‹በአላህ እንምላለን! አንቀብረውም!› አሉ። ከዚያም በድኑን ሠቀሉና በድንጋይ ወገሩት።

ወዲውኑ ሌላ ጳጳስ በቦታው ላይ ሾሙ። ይህኛው ከዚህች ዓለም ጥቅማ ጥቅም እጅግ ቁጥብ የሆነና ለአኺራው በእጅጉ የሚሰንቅ ትጉ ሰው ነበር። በቀንም ሆነ በለሊት በአምልኮው ላይ ይበረታል። ስለሆነም በጣም ወደድኩት። ከሱ ጋርም የተወሠነ ጊዜ ተቀመጥኩኝ። በሞት አፋፍ ላይ በደረሠ ጊዜም ‹እባከህን ለማን አደራ ትሠጠኛለህ? ካንተ በኋላስ ከማን ጋር እሆን ዘንድ ትመክረኛለህ?› አልኩት።

እርሱም ‹ልጄ ሆይ! አንድ በመውሱል የሚገኝ ሰው ካልሆነ በስተቀር እኔ ባለሁበት ነገር ላይ ያለ ሰው አንድም አላውቅም። እርሱም እገሌ ይባላል። እውነት ከርሱ ዘንድ ነው ያለው። አላጣመመም፤ አልቀየረም።› አለኝ።

በሞተም ጊዜ መውሱል ወደሚገኘው ሰውዬ ዘንድ ሄድኩኝ። እዚያም ደርሼ ታሪኬን አጫወትኩት። ‹እገሌ በሞት አፋፍ ላይ ሆኖ ወዳንተ እንድሄድ መክሮኝ አንተም የእውነት መንገድ የያዝክ ስለመሆኑም ነግሮኝ ነበር።› አልኩት። እሱም ‹ጥሩ እኔ ዘንድ ሁን።› አለኝ። እሱ ዘንድም አረፍኩኝ። ሰውዬውንም በመልካም ሁኔታ ላይ አገኘሁት። ብዙም ሣይቆይ ግን እሱም ሊሞት ሆነ። ሞት አፋፍ ላይ በደረሠም ጊዜ

‹እንግዲውስ የአላህ ነገር ሆኖ በዚህ ሁኔታ ላይ ደርሠሃል፡፡ ስለኔም ጉዳይ አንተም የምታውቀው ነው፡፡ ለማን አደራ ትሠጠኛለህ ማን ዘንድ እንድሄድስ ትመክረኛለህ?› አልኩት፡፡

እሱም ‹በአላህ እምላለሁ! ልጄ እኔ ባለሁበት ነገር ላይ ያለ አንድ በነሲቢን ያለ ሰው ቢሆን እንጂ ሌላ አላውቅም፡፡ እርሱም እገሌ ይባላል፡፡ እርሱ ዘንድ ሂድ› አለኝ፡፡ ቀብሩ በተፈፀመም ጊዜ ነሲቢን ከሚገኘው ሰውዬ ዘንድ ሄድኩኝ፡፡ ሁኔታዬንና የተመከርኩትንም ነገርኩት፡፡

እሱም ‹ችግር የለም እኛ ዘንድ ትሆናለህ› አለኝ፡፡ ከርሱ ዘንድም አረፍኩኝ፡፡ ከበፊቶቹ ሰዎች የተሻለ ሆኖ አገኘሁት፡፡ ነገር ግን በአላህ እምላለሁ! እሱም ሰውዬ ብዙ ሳይቆይ ሞት አፋፍ ላይ ደረሠ፡፡ እናም ጠጋ ብዬ ‹ስለኔ ጉዳይ የምታውቅ ይመስለኛል፡፡ ለማን አደራ ትሠጠኛለህ?› አልኩት፡፡

እርሱም ‹ልጄ ሆይ! እኛ በያዝነው ጉዳይ ላይ ያለ አንድ በዐሙሪያ የሚገኝ ሰው ካልሆነ በስተቀር ማንም ያለ አይመስለኝም፡፡ እገሌ ይባላል፡፡ እርሱ ዘንድ ሂድ፡፡› አለኝ፡፡ እኔም እርሱ ዘንድ ሄድኩኝ፡፡ ጉዳዬንም ነገርኩት፡፡ እሱም እኔ ዘንድ ሁን ችግር የለም አለኝ፡፡ እሱም በጓደኞቹ የቀጥተኛ መንገድ ሁኔታ ላይ ነበር፡፡ እርሱ ዘንድም ሆኜ ላሞችንና ጥቂት ፍየሎችን አረባሁ፡፡

ሆኖም ግን እሱም ቢሆን በወዳጆቹ ላይ የደረሰው የሞት ዱላ ሲደርስበት ብዙ አልቆየም፡፡ በሞት አፋፍ ላይ በደረሠም ጊዜ ‹ስለኔ ጉዳይ ካንተ የተደበቀ አይደለም፡፡ ለማን አደራ ትለኛለህ ምን እንዳረግስ ትመክረኛለህ?› አልኩት፡፡

እሱም ‹እኛ የያዝነውን ነገር የያዘ በምድር ላይ የቀረ አንድም ሰው ያለ አይመስለኝም፡፡ ነገር ግን በዐረቢያ ምድር በኢብራሂም ሃይማኖት ላይ ነብይ የሚላክበት ዘመን ደርሷል፡፡ ከዚያም ከሀገሩ ወጥቶ በሁለት ኮረብታዎች መካከል ወደምትገኝ የተምር ዛፍ ሀገር ይሠደዳል፡፡ ድብቅ ያልሆኑ ምልክቶችም አሉት፡፡ ስጦታ/ሀዲያ/ ይቀበላል ነገርግን ምፅዋት አይቀበልም፡፡ በትከሻው መካከል የነቢይነት ማህተም አለው፡፡ እዚያች ሀገር መድረስ የምትችል ከሆነ ሂድ፡፡› አለኝ፡፡

ጳጳሱ ከሞተ በኋላ በዐሙሪያ ለተወሠነ ጊዜ ቆየሁ፡፡ ከኩለብ ጎሣ የሆኑ የዐረብ ነጋዴዎች ወደ አካባቢው በመጡ ጊዜ ጠጋ ብዬ ‹ወደ ዐረብ ምድር የምትወስዱኝ ከሆነ እነኚህን ላሞቼንና ፍየሎቼን እሰጣችኋለሁ፡፡› አልኳቸው፡፡ እነሱም ‹እንወስድሃለን፡፡› በማለት ተስማመሙ፡፡ እነሱን ሰጠኋቸውና አብሬያቸው ጉዞ ጀመርኩኝ፡፡ ‹ዋዲ አልቁራ› ከምትባል ቦታ ስንደርስ ግን ካዱኝና ለአንድ ይሁዲ ሸጡኝ፡፡ እኔም እርሱን ማገልገል ያዝኩኝ፡፡

ብዙም ሣይቆይ ከበኒ ቁረይዟ /የመዲና አይሁድ ጎሣ/ የሆነ አጎቱ ሊጎበኘው መጣና እንዳገለግለው ብሎ ገዛኝ፡፡ ወደ የሥሪብም/መዲና/ ወሠደኝ፡፡ ሀገሩ ስደርስ የዐሙሪያው ወዳጄ ጠቅሦልኝ የነበረውን የተምር ዛፍ አየሁኝ፡፡ መዲናንም እሱ በጠቀሰው መልኩ ሆና አገኘኋት፡፡ ከአዲሱ አሣዳሪዬ ጋርም እዚያው መኖር ጀመርኩኝ፡፡

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በወቅቱ መካ ላይ ሆነው ህዝባቸውን ወደ እስልምና እየጠሩ ነበር፡፡ ባርነት ጊዜ የማይሠጥ እጅግ ከባድ ሥራ በመሆኑ ስለርሣቸው ምንም ሳልሰማ በርካታ ጊዜያት አለፉ፡፡ ነገርግን ብዙም ሳይቆይ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) በስደት ወደ መዲና መጡ፡፡

በአላህ እምላለሁ! በምሠራበት የተምር ዛፍ አናት ላይ ሆኜና አሣዳሪዬ ከሥሯ ሆኖ ሳለ የአጎቱ ልጅ የሆነው ሰው መጣና ‹አላህ በኒ ቁላ (አውስና ኸዝረጅ የመዲና ጎሣዎች ማለቱ ነው) ላይ ቁጣውን ያውርድ! በአላህ እምላለሁ! እነሱ አንድ ነቢይ ነኝ ብሎ በተነሣው ሰውዬ ምክንያት አሁን ቁባእ ላይ ተሰብስበው ይገኛሉ፡፡› ሲል ሰማሁት፡፡

ንግግሩን እንደሠማሁ እንደ ወባ አንዘፈዘፈኝ፡፡ ከመንቀጥቀጤ የተነሣም አሣዳሪዬ ላይ እንዳልወድቅ ፈራሁኝ፡፡ በመሆኑም ፈጠን ብዬ ከተምር ዛፉ ወረድኩኝ፡፡ ለሰውዬውም ‹ምንድን ነበር ያልከው? እስቲ ወሬውን ድገምልኝ?› አልኩት፡፡ አሣዳሪዬ በሁኔታዬ በመቆጣት በሀይለኛ ጥፊ መታኝ፡፡ እንዲህም አለኝ ‹ስለዚህ ጉዳይ ምን የሚያገባህ ነገር አለ? በል ወደ ነበርክበት ሥራህ ተመለስ፡፡›

መሸትሸት ሲል ከሰበሰብኩት ተምር የተወሠነውን ያዝኩና የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ወዳረፉበት ቦታ አመራሁ፡፡ ገባሁና እንዲህ አልኳቸው፡፡

‹መልካም ሰው እንደሆንክ ደርሶኛል፡፡ ካንተ ጋርም ችግረኞችና ባይተዋር ጓደኞች እንዳሉህ ሰምቻለሁ፡፡ ይህ ለናንተ ለመመፅወት ብዬ ያዘጋጀሁት ነው፡፡›በማለት ወደርሣቸው አቀረብኩኝ፡፡ እርሣቸውም ጓደኞቻቸውን ‹ብሉ› አሏቸው፡፡ ራሣቸው ግን አልበሉም፡፡ እኔም በውስጤ ‹ይህች አንዲ ምልክት ናት፡፡› አልኩኝ፡፡

ከዚያም ተመለስኩና የተወሠነ ተምር ሰበሰብኩ፡፡የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ከቁባእ ወደ መዲና በተመለሱ ጊዜ መጣሁና ‹ምፅዋት እንደማይበሉ አስተውያለሁ፡፡ ይህ ለርስዎ ያለኝን ክብር የገለፅኩበት ስጦታ ነውና ይቀበሉኝ፡፡› አልኳቸው፡፡ እርሣቸውም ተቀበሉኝና በሉ፡፡ ሰሃቦቻቸውም ከርሣቸው ጋር በሉ፡፡ እኔም በውስጤ ‹ይህች ሁለተኛ ናት፡፡› አልኩኝ፡፡

አንድ ቀን ደግሞ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) አንድ ሰሃባቸው ሞቶ በበቂዕ አል-ገርቀድ በመቅበር ላይ እያሉ መጣሁ፡፡ ሁለት ኩታዎችን ለብሰው ቁጭ ብለው አገኘኋቸው፡፡ ሰላምታ አቀረብኩላቸውና ያ የዐሙሪያው ወዳጄ የጠቀሠልኝን ማህተማቸውን ለማየት ብየ ወደ ኋላቸው ዞርኩኝ፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጀርባቸውን እየተመለከትኩ መሆኔን ባዩ ጊዜ ሀሳቤን አወቁ፡፡ ኩታቸውን ከጀርባቸው ላይ አወረዱ፡፡ እኔም የነቢይነት ማህተማቸውን ተመለከትኩ፡፡ በዚህም አወቅኳቸውና ወድቄባቸው እስማቸውና አለቅስ ያዝኩኝ፡፡ የአላህ መልእክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) ‹ምን ሆነህ ነው?› አሉኝ፡፡

እኔም ታሪኬን ሁሉ በዝርዝር ነገርኳቸው፡፡ እርሣቸውም ተገረሙ፡፡ ሰሃቦቻቸውም ታሪኬን ከኔው እንዲሰሙ ፈለጉ፡፡ እነሱንም አሠማኋቸው፡፡ እነርሱም በእጅጉ ተገረሙ፡፡ በጣምም ደስ አላቸው፡፡

ሰልማን በመዲና ሕይወቱ ለአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ከሚቀርቡ ሰዎች መካከል አንዱ ሆነ፡፡ መልእክተኛውም (ሰ.ዐ.ወ) ስለርሱ እንዲህ ብለዋል፡- ‹ሰልማን ከኛ ነው ቤተዘመድ፡፡›

ሃኪም ከአነስ ኢብኑ ማሊክ እንደዘገቡት ደግሞ ሰልማን አልፋሪሲ ዑመር (ረ.ዐ) ትራስ ተደግፈው ጋደም ባሉበት ሁኔታ ወደርሣቸው ዘንድ ገባ፡፡ ዑመርም ትራሱን ወረወሩለት፡፡ ሰልማንም ‹አላህ እና መልእክተኛው እውነት አሉ፡፡› አለ፡፡ ዑመርም ‹የዐብደላህ አባት ሆይ! ንገረን እስቲ ምንድነው እሱ?› አሉት፡፡ እሱም

‹አንድ ቀን የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ትራስ ተደግፈው ጋደም ባሉበት ሁኔታ ወደርሳቸው ዘንድ ገባሁ፡፡ እርሣቸውም ትራሱን ወረወሩልኝና እንዲህ አሉ፡፡ ‹ሰልማን ሆይ! አንድ ሙስሊም ወደ አንድ ሙስሊም ወንድሙ ቤት አይገባም፤ ለክብሩ ትራስ የወረወረለት እንደሆነ አላህ ምህረት ያደረገለት ቢሆን እንጂ፡፡›

ሰልማን (ረ.ዐ) ከመልካም አማካሪዎችና የጥሩ ሀሣብ አመንጭ ከሆኑ ሰዎች መካከል የሚጠቀስ ነው፡፡ አል-ሙባረክ ፉሪ ረሒቅ አልመኽቱም በተሠኘው ድንቅ መጽሐፋቸው ውስጥ በአህዛብ ጦርነት ወቅት የሆነውን ሲተርኩ እንዲህ ይላሉ “የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ወዲያውኑ ምክር ቤቱን ለአስቸኳይ ስብሰባ ጠሩ፡፡ አጀንዳቸውም ከመዲና መከላከል ስለሚችሉበት ሁኔታ ላይ ነበር፡፡ በአመራሮቸና በምክር ቤቱ አባላት መካከል ከፍተኛ ውይይት ከተደረገ በኋላ ብልሁ ሰሃባ ሰልማን አልፋሪሲ ባቀረበው ሀሣብ ላይ ከመግባባት ደረሱ፡፡

በወቅቱ ሰልማን እንዲህ በማለት ሀሳብ አቅርቦ ነበር ‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ! እኛ በፋርስ ምድር እያለን በጠላት ጦር የተከበብን እንደሆነ በዙሪያችን ጉድጓድ እንቆፍር ነበር› በርግጥም የዚህ ዓይነቱ ተግባር ዐረቦች ከዚህ ቀደም የማያውቁት ታክቲክ ነበር፡፡ የአላህ መልእክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) ይሽው ስልት በአፋጣኝ ተግባር ላይ ይውል ዘንድ እያንዳንዱ አሥር ሰው አርባ ክንድ ቦይ እንዲቆፍር ሰዎችን መደቡ፡፡

ሰልማን (ረ.ዐ) እውቀትን ከጠገቡ ሰሃቦች መካከልም ነበር፡፡ ቡኻሪ ከአቢ ጀሂፋህ በዘገቡት ሐዲስ እንዲህ ብሏል ‹ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰልማንና አቡ ደርዳእን ወንድማማች አደረጓቸው፡፡ ሰልማን ለጉብኝት ወንድሙ አቡ ደርዳእ ዘንድ ቤቱ ሄደ፡፡ ኡሙ ደርዳእ/የአቡ ደርዳእ ባለቤት/ ራሷን የጣለች ሆና ሲያገኛት ‹ምነው ምን ሆነሽ ነው?› በማለት ጠየቃት፡፡

እሷም ‹ይህ ወንድምህ አቡ ደርዳእ ስለዚህች ዓለም ግድ የሌለው ሰው ነው፡፡› አለችው፡፡ አቡደርዳእ ወደቤት መጣ፡፡ ሰልማንም ምግብ ሠራለትና ‹ብላ› አለው፡፡ አቡደርዳእ ግን ‹ፆመኛ ነኝ› አለ፡፡ ሰልማን ‹አንተ ካልበላህ እኔም አልበላም፡፡› በማለቱ በላ፡፡ ምሽት በሆነ ጊዜ አቡደርዳእ ለሶላት ሊነሣ ሲል ሰልማን ‹ተኛ› አለው፡፡ ትንሽ ቆይቶ አሁንም ሊነሣ ሲል አሁንም ‹ተኛ› አለው፡፡ ወደ ለሊቱ

መጨረሻ አካባቢ ግን ሰልማን ለአቡ ደርዳእ ‹በል አሁን ተነስ።› አለው። አብረውም ሰገዱ። ሰልማን ለአቡደርዳእ በመጨረሻም እንዲህ አለው።

‹ለጌታህ ባንተ ላይ ሀቅ አለብህ። ለነፍስህም ባንተ ላይ ሀቅ አለብህ። ለሚስትህም/ቤተሰብህ/ ባንተ ላይ ሀቅ አለብህ። ለሁሉም ሐቅ ሐቁን ስጥ።› ›ነቢዩም (ሰ.ዐ.ወ) በመጡ ጊዜ ይህንኑ ነገር አወሣላቸው። እርሣቸውም ‹ሰልማን እውነት ተናገረ።› አሉ። በሌላ ዘገባ ደግሞ ‹ሰልማን እውቀት ጠግቧል።› እንዳሉ ተላልፏል።

የሰልማን ዝህድና

አቡ ነዒም ከዐጢያ ኢብኑ ዓሚር እንደዘገቡት ዐጢያ እንዲህ ብሏል፡- ‹በአንድ ወቅት ሰልማን አልፋሪሲን ምግብ እንዲበላ ሲያስገድዱት አየሁ። እሱም ‹ይብቃኝ ይብቃኝ› የአላህ መልአክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ‹በዚህች ዓለም ላይ ብዙን ጊዜ የሚጠግቡ ሰዎች በአኺራ ለረጅም ጊዜ የሚራቡት እነሱ ናቸው።› ሲሉ ሰምቻለሁ። ሰልማን ሆይ! ይህች የቅርቢቱ ዓለም እኮ ለሙእሚኑ እስር ቤት ለካፊር/ከሐዲ/ ደግሞ ጀነት ናት› ሲል ሰምቻለሁ።› አለ።

አቡ ነዒም በሌላ ዘገባ ከሀሠን እንዳስተላለፉት ደግሞ ‹የሰልማን ክፍያ ሰላሣ ሺህ ሙስሊሞችን አሚር ሆኖ ያስተዳድር በነበረ ጊዜ ሠላሣ ሺህ ነበር። ለሰዎች ኹጥባ/ንግግር/ ያደርግ የነበረውም ከፊሉን ለመኝታው ያነጥፍ ከፊሉን ደግሞ ይለብስ በነበረው ካባው ነው። ክፍያውን ያወጣ እንደሆነ ለወደፊት ሀገሩ ያስቀድማል/ወዲውኑ ሰጥቶ ይጨርሣል።/ በእጁ ከሠራው ነገርም ይበላል።› ብሏል።

ኢብኑ ሰዕድ ደግሞ ከመዕን እና ከአነስ ኢብኑ ማሊክ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፈው ‹ሰልማን አል-ፋሪሲ ቤት ስላልነበረው በሄደበት ሁሉ የሚጠለለው በፈይእ ነበር። አንድ ሰውዬ ከሙቀት ሀሩር የምትጠለልበት ከብርድም የምትጠበቅበት ቤት ልስራልህ።› አለው። ሰልማንም ‹በጅ› አለው። ሰውየው ዘወር ብሎ በሄደ ጊዜም በሩቁ ተጣራና ‹ቤቱን እንዴት ነው የምትሠራው?› በማለት ጠየቀው። ሰውዬውም ‹ስትቆም እራስህን ስተትኛ ደግሞ እግርህን ሊነካ በሚችል መልኩ ነው የምሠራው።› አለው። ሰልማንም ‹ጥሩ› አለው።

ሰልማን አልፋሪሲ የዱኒያ በሰዎች ላይ መለቀቅ ያሰጋው ነበር

ጦበራኒ ከአንድ ከበኒ ዐበስ ከሆነ ሰውዬ እንደዘገቡት ሰውዬው እንዲህ ብሏል፡- ‹በደጅላህ ወንዝ ዳርቻ ላይ ከሰልማን ጋር ታስረን ነበር፡፡ እሱም ‹የበኒ ዐበስ ወንድሜ ሆይ! ውረድና ጠጣ፡፡› አለኝ፡፡ እኔም ጠጣሁኝ፡፡ ‹ይህ መጠጣትህ ከደጅለህ ወንዝ ምን ያህል ያነደለ ይመስልሃል?› በማለት ጠየቀኝ፡፡ እኔም ‹ምንም ሊያነድል አይችልም፡፡› አልኩት፡፡ ‹እንግዲያውስ እውቀትም እንዲሁ ነው፡፡ ይወሠዳል ይወሠዳል ነገር ግን ሁሌም አይነድልም፡፡› አለኝ፡፡ ከዚያም ‹በል ተሳፈር› አለኝና ጉዞ ጀመርን፡፡ ገብስና ስንዴ በተከመረበት አካባቢ አለፍን፡፡ እሱም ወደዚያው እያመለከተ ‹ይህ ነገር ለኛ እንዲህ መስፋቱና ለሙህመድ ባልደረቦች ግን መዘጋቱ / እነሱ ምንም ከዚህ ዓይነቱ ፀጋ አለማግኘታቸው/ ለኛ በጎ ለነሱ ደግሞ መጥፎ ነገር ይመስልሃልን!?› አለኝ፡፡ እኔም ‹እኔ አላውቅም እንጂ፡፡› አልኩት፡፡ ሰልማን ግን ‹እኔ ግን አውቃለሁ፡፡ ይህ መሆኑ ለኛ መጥፎ ለነሱ ደግሞ በጎ ነገር ነው፡፡› አለኝ፡፡ ቀጥሎም ‹የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እኮ አላህን እስከተገናኙበት ጊዜ ድረስ በተከታታይ ለሦስት ቀን ጠግበው አያውቁም ነበር፡› አለኝ፡፡

አንድ ቀን ሰዕድ ኢብኑ አቢ ወቃስ(ረ.ዐ) ሰልማን ታሞ በነበረበት ሁኔታ ሊጎበኘው እሱ ወዳለበት ገባ፡፡ ሰልማንም ሰዕድን ሲያይ አለቀሠ፡፡ ሰዕድም <ወዳጆችህን ትገናኛለህ የአላህን መልእክተኛ ሀውድ ላይ ታገኛለህ፤ የአላህ መልእክተኛ ካንተ ወደው ነው የሞቱት ምን ያስለቅስሃል?› አለው፡፡ ሰልማንም ‹ሞትን ፈርቼ አሊያም በዱኒያ ላይ ለመቆየት ጓጉቼ አይደለም የማለቅሰው፡፡ ነገርግን የአላህ መልክተኛ(ሰዐወ) ‹ከዱኒያ ላይ አንድ መንገደኛ ሰው የሚይዘውን ያህል ብቻ ያዙ፡፡› በማለት ቃል አስገብተውን ነበር፡፡ ‹እኔ ግን እነኚህ ሁሉ መጣቀሚያዎች በዙሪያዬ አሉ› አለ፡፡ (በዙሪያው የውዱእ ማድረጊያ እቃ፣ የልብስ ማጠቢያ ሳፋና የመሣሰሉት ቀላል እቃዎች ብቻ ነበሩ፡፡) ጦበራኒ እና ኢብኑ ሂባን በዘገባው እንዳከሉት ‹የሰልማን እቃ ሲሰበሰብ ዋጋው አሥራ አምስት አሊያም አሥራ ምናምን ድርሃም ብቻ ነበር፡፡› ሰዕድ ‹እስቲ አንተም ካንተ በኋላ እንድንይዘው አደራ የምትለን ነገር ካለ፡፡› አለው፡፡ ሰልማንም ‹በሀሣብህ ጊዜ

ስታስብ፣ በፍርድ ጊዜም ስትፈርድ፣ በእጅህ ላይ ያለውን ስታከፋፍል ጌታህን አስታውስ፡፡› አለው፡፡

ሰላም በሰልማን አልፋሪሲ ላይ ይሁን! ሀቅን ፍለጋ በብዙ አቅጣጫዎችና ሩቅ ቦታዎች ተጉዟል፡፡ ሰላም በሰልማን ላይ ይሁን! ሀቅን አውቆ አምኖበትም እምነቱንም ፀንቶ ይዟል፡፡ በሞተም እለት ዳግም ህያው ሆኖ በሚቀሰቀሰበት እለትም ሰላም በሱ ላይ ይሁን፡፡

ምዕራፍ ስድስት

ራስን ወደ ተሻለ ደረጃ መመለጥ

አጠቃላይ ዓላማ

ራሱን ወደ ተሻለ ደረጃ ለመለወጥ ፍላጎት እንዲኖረውና ለትግበራውም እንዲፈጥን ማስቻል

ዓላማዎች

1. የሰው ልጅ ነፍስ በተፈጥሮው ለጥሩም ሆነ ለመጥፎ ውስጣዊ ዝንባሌ እንዳለው እንዲረዳ ማስቻል።
2. ራስን ወደ ተሻለ ደረጃ የመለወጥ አሳሳቢነትና አስፈላጊነት እንዲያብራራ ማስቻል።
3. የሰውን ልጅ የነፍስ ባህሪያትና ክፍተቶቿን እንዲያብራራ ማስቻል።
4. ነፍስን የማነልበቻ መንገዶችን እንዲያብራራ ማስቻል።

የመጀመሪያው ዓላማ

የሰው ልጅ ነፍስ በተፈጥሮው ለጥሩም ሆነ ለመጥፎ ውስጣዊ ዝንባሌ እንዳለው እንዲረዳ ማስቻል

የትምህርቱ ዓላማ

1. የሰው ልጅ ነፍስ በተፈጥሮው ለጥሩም ሆነ ለመጥፎ ውስጣዊ ዝንባሌ እንዳለው እንዲያብራራ ማስቻል።
2. ሰዎች ከነፍሶቻቸው ጋር በሚያደርጉት መስተጋብር አመዳደባቸውን እንዲያብራራ ማስቻል።

1. የሰው ልጅ ነፍስ በተፈጥሮው ለጥሩም ሆነ ለመጥፎ ዝግጁ መሆኑ

እውነተኛ የሆነው አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

﴿وَنَفۡسٖ وَمَا سَوَّىٰهَا ٧ فَأَلۡهَمَهَا فُجُورَهَا وَتَقۡوَىٰهَا ٨ قَدۡ أَفۡلَحَ مَن زَكَّىٰهَا ٩ وَقَدۡ خَابَ مَن دَسَّىٰهَا ١٠﴾ الشمس: ٧ - ١٠

"በነ ፍስም ባስተካከላትም፤ አመጽዋንና ፍርሃትዋንም ባሳወቃት፥ (አምላክ እምላለሁ) ፤ (ከጎጠኔት) ያጠራት ሰው ፍላጎቱን በእርግጥ አገኘ፡ ፡ (በጎጠኔት) የሸፈናትም ሰው፡ በመና ት አፈረ፡ ፡ " (አሽ-ሸምስ፡ 7-10)

በሌላ የቁርአን አንቀፅ እንዲህ ይላል፡-

﴿ فَأَمَّا مَن طَغَىٰ ﴿٣٧﴾ وَءَاثَرَ ٱلْحَيَوٰةَ ٱلدُّنْيَا ﴿٣٨﴾ فَإِنَّ ٱلْجَحِيمَ هِىَ ٱلْمَأْوَىٰ ﴿٣٩﴾ وَأَمَّا مَنْ خَافَ مَقَامَ رَبِّهِۦ وَنَهَى ٱلنَّفْسَ عَنِ ٱلْهَوَىٰ ﴿٤٠﴾ فَإِنَّ ٱلْجَنَّةَ هِىَ ٱلْمَأْوَىٰ ﴿٤١﴾ ﴾ النازعات: ٣٧ - ٤١

"የካደ ሰውም ቅርቢቱንም ሕይወት የመረጠ፡ ገሀነ ም እርሷ በእርግጥ መኖሪያው ናት፡ ፡ በጌታው ፊት መቆምን የፈራ ሰውም ነ ፍሱንም ከዝንባሌዋ የከለከለ፥ ገነ ት እርሷ በእርግጥ መኖሪያው ናት፡ ፡ " (አን-ናዚአት: 37-41)

ከነዚህና ከሌሎችም ተመሳሳይ የቁርአን አንቀጾች እስልምና የሰውን ልጅ ከመሠረቱ በምን አይነት መልኩ እንደሚያየው እንገነዘባለን፡፡ ይህ ፍጡር ሁለት የተደባለቁ ባህሪያት ኑረውት ተፈጥሯል፡- የዝንባሌ ድብልቅና እና የአመለካከት ድብልቅ፡፡ ድብልቅ የሚለው ቃል የሰው ልጅ የተፈጠረበትን ውህድ ከመግለፅ አኳያ የተቀመጠ ነው፡፡ ይህም ሲባል የሰው ልጅ የምድር ጭቃ እና በአላህ ከተነፋበት ከርሱ ሩሕ የተገኘ ቅምር መሆኑን ለመግለፅ ነው፡፡ የሰው ልጅ ድብልቁ ለጥሩም ይሁን ለበጎ፣ ለቅንነትም ይሁን ለጥመት እኩል በኩል ዝንባሌ እንዲኖረው ተደርጎ ነው፡፡ ጥሩና መጥፎውን የመለየት አቅም አለው፡፡ እንደዚሁም ነፍሱን ወደ ጥሩ ወይም ወደ መጥፎ እኩል በኩል የማመላከት ብቃት ተቸሮታል፡፡ ይህንን በውስጡ ተደብቆ ያለ ተፈጥሯዊ ችሎታ ቁርአን አንዳንድ ጊዜ "ኢልሃም" (የማወቅ ችሎታ) በሚል ሲገልፀው (ለምሳሌ፡-

﴿ وَنَفْسٍ وَمَا سَوَّىٰهَا ﴿٧﴾ فَأَلْهَمَهَا فُجُورَهَا وَتَقْوَىٰهَا ﴿٨﴾ ﴾

"በነ ፍስም ባስተካከላትም፤ አመፅዋንና ፍርሃትዋንም ባሳወቃት [አምላክ] እምላለሁ") በሌላ ጊዜ ደግሞ "ሂዳያህ" ወይም መመራት በሚል አስቀምጦታል (-

ለምሳሌ "وَهَدَيْنَٰهُ ٱلنَّجْدَيْنِ" "ሁለትን መንገዶችን አልመራነ ውምን?")

ከዚህ መረዳት የምንችለው የሰው ልጅ ይህ ድብቅ የሆነ የዝንባሌ ኃይል መሠረታዊ ባህሪው እንደሆነ ነው፡፡ ከፈጣሪ የወረዱ መልእክቶች፣ የዳዕዋ

ጥሪዎችና ውጫዊ ግፊቶች በሙሉ ይህን በውስጥ ተደብቆ ያለ የዝንባሌ ችሎታ ለመቀስቀስና ወደዚህ ወይም ወደዚያ ሂድ ለማለት የታለሙ ነገሮች ናቸው።።

[ከዚህ ውስጣዊ ዝንባሌ ጎን ለጎን የሰው ልጅ ማንነቱ የሚገለፅበት አንድ ሌላ መሠረታዊ አቅም አለው።። ይህንን አቅም ነፍሱን ለማለምለምና ለማፅዳት፣ ለጥሩ ያለውን ዝንባሌ ለማጎልበትና ለመጥፎ ያለውን ዝንባሌ ለማሸነፍ የተጠቀመበት ሰው በእርግጥ ስኬታማ ይሆናል።። በተቃራኒው ይህንን የውስጥ አቅም ያጨለመ፣ የደበቀና ያዳከመ ደግም በእርግጥ ይከስራል።።

﴿ قَدۡ أَفۡلَحَ مَن زَكَّىٰهَا ٩ وَقَدۡ خَابَ مَن دَسَّىٰهَا ١٠ ﴾

"ከኃጢአት ያጠራት ሰው ፍላጎቱን በእርግጥ አገኘ፡ ። በኃጢአት የሸፈናትም ሰው በእርግጥ አፈረ"][2]

[ጥራት የተገባው አላህ ለሰው ልጅ ካደረገው ርህራሄ አንዱ በውስጥ ዝንባሌው ብቻ ሳይተወው መለኮታዊ መልእክቶችን በማውረድ ቋሚና ጥልቅ የሆኑ መለኪያዎችን ማስቀመጡ እና ሰው በውስጡ ያለውን ጥሩ ነገር ይፋ ማድረጉ ነው።። ይህም መንገዱን ግልጽ ያደርግለታል፣ መሠረታዊ የውስጥ አቅሙም በትክክል መንቀሳቀስና የሚጓዝበትን አቅጣጫ መምረጥ ይችላል።።][3]

[አላህ የሰውን ልጅ ነፍስ በፈጠራት ጊዜ ከእርሷ ጋር አብሮ ለጥሩውም ይሁን ለመጥፎው የዝንባሌ ኃይልን ፈጥሯል።። ከዚያም የሰው ልጅ ይህንን መሳሪያ በፈለገው መልኩ የመጠቀም ችሎታን አድርጎለታል።። መንገዱ እንደፈለገው የሚጎትተው ሳይሆን እርሱ መንገዱን የመምረጥ ሙሉ ነፃነት አለው፡- *"በነ ፍሰ ም ባ ሰ ተ ካ ከ ላ ት ም ፡ አ መ ቿ ዋ ን ና ፍ ር ሃ ት ዋ ን ም ባ ሳ ወ ቃ ት [አ ም ላ ክ] እ ም ላ ሰ ሥ"*።። በዚህ ነፃነት ላይ ተመሥርቶ የዚያች የሂሳብ ቀን የምንዳ ወይም የቅጣት ምርጫ ይካሄዳል ማለት ነው፡-"ከኃጢአት ያጠራት ሰው ፍላጎቱን በእርግጥ አገኘ።። በኃጢአት የሸፈናትም ሰው በእርግጥ አፈረ"][4]

---

[2] ፊዚላል-ተፍሲር -አሽ-ሸመስ: 9-10
[3] ፊ ዚላል
[4] መንሀጁ ታቢዒይን ፊ ተርበየቲ አን-ኑፉስ

[አላህ (ሱ.ወ) ለእያንዳንዱ ባሪያው በመጥፎ የምታዝ የሆነችን ነፍስ ፈጥሮለታል። ይህም ምን ያህል በእውነት እርሱን እንደሚገዛው ለማወቅ ነው። አላዋቂነትን፣ በዳይነትን እንዲሁም ስስታምነትን የዚህች ነፍስ ዋነኛ ባህሪያት አድርጓል። እርሷ ወደ ተንኮል ትዘነበላለች፣ ከጥሩ ነገር ትሸሻለች፣ መጨናነቅን አትወድም፣ ኃላፊነትን ትጠላለች። ባሪያው ለእርሱ ያለውን እውነተኛ ታዛዥነት ማረጋገጥ እንዲችል እርሷን ዋነኛዋ የፈተና ቁልፍና የተግባር ሜዳ ትሆን ዘንድ በዚህ አይነት ባህሪያት ፈጥሯታል። እርሷ ባትኖር ኖሮ ትእዛዙን የማንጥስ መላእክት በሆን ነበር። አላህ ነፍሳችንን እንድንታገላትና እርሷን ድል አድርገን ውዴታውንና ገነቱን እንዲንወርስ ይፈልጋል።

አላህ እንዲህ ይላል፡-

وَأَمَّا مَنْ خَافَ مَقَامَ رَبِّهِۦ وَنَهَى ٱلنَّفْسَ عَنِ ٱلْهَوَىٰ ﴿٤٠﴾ فَإِنَّ ٱلْجَنَّةَ هِىَ ٱلْمَأْوَىٰ ﴿٤١﴾

"በጌታው ፊት መቆምን የፈራ ሰውም ነፍሱንም ከዝንባሌዋ የከለከለ፥ ገነት እርሷ በእርግጥ መኖሪያው ናት፡ ፡" (አን-ናዚአት: 40-41)[5]

1. የሰዎች ስሜታዊ ከነፍሶቻቸው ጋር በሚያደርጉት መስተጋብር

ሰዎች ከነፍሶቻቸው ጋር በሚያደርጉት መስተጋብር በሦስት ይከፈላሉ፡-

ስንደኛ፡-ነፍሱን ስጥብቅ የሚታገል

ይህ ሰው በሚከተሉት ባህሪያትና ተግባራት ይገለፃል፡-

- ጌታውን በብቸኝነት እንዳይገዛ ከሚያደርጉት ማዕቀቦች ዋነኛዋ ያች ከጎኑ ያለችው ነፍሱ መሆኗን ያረጋገጠ ነው። እርሷ ከጠላት ሁሉ በላይ ጠላቱ በመሆኗ የትግልን ባንዲራ በእርሷ ላይ አውጇል፣ ለርሷም መቆጣጠሪያ አብጅቷል፣ በትንሹም ይሁን በትልቁ ሥራዋ ይተሳሰባታል።

- ስሜቱን ይቃወማል፣ ነፍሱን የተፈቀደላትን ነገር ድንበሩን ስታልፍ በመጠኑ ከመጠቀም ውጭ እንደፈለገች እንድትፈነጭ አይፈቅድላትም። በውጤቱ እንቢተኛ የሚያደርጋትን ነገርም ሆነ ሥራውንና ዒባዳውን የሚያበላሽ ነገር

[5] አል-ሂላሊይ ዚሂረቱ አድ-ደዕፍ አን-ነፍሲይ

እንድትሠራ እድል አይሰጣትም፡፡ በእርግጥ ይህ ሰው ነፍሱን በትልቅ ዋጋ ለአላህ በደስታ ሸጧታል፡-

﴿إِنَّ ٱللَّهَ ٱشۡتَرَىٰ مِنَ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ أَنفُسَهُمۡ وَأَمۡوَٰلَهُم بِأَنَّ لَهُمُ ٱلۡجَنَّةَۚ ١١١﴾

"›Ll ŸUÀS“”¥ ’õf‰†¨<”“ Ñ”²x‰†¨<”¥ Ñ’ƒ K’c< w‰ ÁL†¨< uS§” Ñ³†¨<¥ :” (አት-ተውባህ: ١١١)

- ነፍሱን ያብቃቃ ነው፡፡ ዱንያ ወደርሱ ብትዘነበል አይደሰትም፡፡ ከርሱ ዘወር ብትልም አይከፋም፡፡ ከበላዩ ያሉ የዱንያ ሰዎችን አይመለከትም፡፡
- በአላህ ይመካል፣ ውሳኔውን ወዶ ይቀበላል፣ ምንጊዜም ቢሆን ከዱንያ ጥቅም ይልቅ ለዲኑ የሚጠቅመውን ያስቀድማል፡፡ ሐላልን አሳዶ ይፈልጋል፡፡ ከአሻሚ ነገሮች ይርቃል፡፡ በመልካም ሥነ-ምግባር የታነፀ ነው፣ ክልክል ነገሮችን ይጠነቀቃል፡፡ አደራውን ይጠብቃል፡፡ ቃል ኪዳኑን ይሞላል፡፡
- የኔ ሀሳብ ይበልጣል በሚል ወሰን አያልፍም፤ ሁል ጊዜም "እኔ ያልኩት ነው ትክክል ሀሳብ ስህተት ሊኖረው ይችላል፤ ስህተት ነው ያልኩት የሌሎች ሀሳብ ትክክል ሊሆን ይችላል" የሚለውን የሻፊዒይ ንግግር ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
- በተግባሩም ሆነ በንግግሩ ሱናን ይጠብቃል፣ ወደ አላህ መጸጸትና ምህረት መጠየቅ የዘወትር ሥራዎቹ ናቸው፡፡

ሁለተኛ፡- ለነፍሱና ለስሜቱ የተገዛ

ይህ ሰው በሚከተሉት ባህሪያትና ተግባራት ይገለፃል፡-

- የዚህ ምድብ ባለቤቶች በእርግጥ ነፍሶቻቸውንና ስሜቷን ከኋላ ተከትለው የሚሮጡ ናቸው፡፡ ነፍስ የከጀለችውን ነገርም ሆነ በስሜት የወደደችውን በፍፁም አይቃወሙም፡፡
- ይህ ምድብ የጌታው እዝነት ካልታደገው በስተቀር ማምለጫ ከሌለው ጥፋት ውስጥ ተዘፍቋል -ለምንስ አይሆንም? በርግጥ የራሱን ነፍሱንና ስሜቱን በማስቀደም መመኪያና ፈጣሪው የሆነውን የጌታውን ሚባዳ ለውጦታል፡፡ ይህ ሰው አላህ(ሱ.ወ) ከተናገረው ጋር ይገጥማል፡-

"أرأيت من اتخذ إلهه هواه أفأنت تكون عليه وكيلا "

"ፍላጎቱን አምላኩ አድረጎ የያዘውን ሰው አየህን? አንተ በርሱ ላይ ጠባቂ ትሆናለህን?"::

ነፍሱ ለዱንያ ጌጣጌጥና ውበት አሳልፋ ሸጣዋለች፣ በስሜት ውስጥ ተዘፍቋል፣ ለአይኑና ለብልቱ ገደብ ለቆላቸዋል፣ ነፍሱ በፈለገችው ነገር ሁሉ ሆዱን ይሞላል፣ ሐላል ነው ወይስ ሐራም የሚለውን አያስተውልም::

- ነፍሱ ኃላፊነትና ጭንቅን አትችልም፣ ሶላትን አትጠብቅም፣ በፆም መዘውተር የለውም፣ ሌሎች ሒባዳዎችንም አይሠራም፣ የነፍሱ ባሪያና ምርኮኛ ሆኗል፣ በስሜቷም ተጠፍንጓል::

- ለራሱ ካልሆነ በስተቀር ጥሩ ነገርን አይወድም፣ ለርሱ ጥቅም ካልሆነ በስተቀር ምንም ሥራን አይሠራም፣ መፈክሩ "መድረሻ መዳረሻን ያጸድቃል!" የሚል ነው:: (የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጭው!)

- ሽይጧንን ተከትሏል፣ የሠራዊቱና የፓርቲው ጭፍራ ሆኗል:-

﴿ ٱسۡتَحۡوَذَ عَلَيۡهِمُ ٱلشَّيۡطَٰنُ فَأَنسَىٰهُمۡ ذِكۡرَ ٱللَّهِۚ أُوْلَٰٓئِكَ حِزۡبُ ٱلشَّيۡطَٰنِۚ أَلَآ إِنَّ حِزۡبَ ٱلشَّيۡطَٰنِ هُمُ ٱلۡخَٰسِرُونَ ١٩ ﴾ المجادلة: ١٩

"እነዚያ የሰይጣን ጭፍሮች ናቸው፤ ንቁ! የሰይጣን ጭፍሮች ከሳሪዎቹ እነርሱ ናቸው፡፡" (አል-ሙጃደላህ: 19)

ሦስተኛ:- አንድ ጊዜ ነፍሱን የሚቃወም በሌላ ጊዜ የነፍሱን ዝንባሌ የሚከተል

- የዚህ ምድብ ባለቤቶች በብዙ ሁኔታ ነፍሳቸውን ያሸነፉ ናቸው:: እርሷ ደግሞ በተራዋ በሌላ ወቅት ታሸንፋቸዋለች:: እነዚህ ሰዎች ከነፍሳቸው ፊት ለፊት ብዙ ጥንካሬንም ድከመትንም ያሳያሉ:: ይህ ድክመት በኛና በብዙዎቻችን መካከል-በአብዛኞችን ማለት ባይቻልም- የሚስተዋል ነው:: በዚህ ምድብ ውስጥ እንዳለመታደል ሆኖ በተወሰኑ አቋሞች ላይ በነፍሳቸው ፊት ለፊት

አቅማቸው የከዳቻቸው ከፊል ሰዎች ይገኙበታል። እነኝህ ሰዎች በነፍሳቸው ላይ ሙሉ በሙሉ ድል አድርገናል ብለው ያስባሉ። የማታለያ ዘዴዎቿ ምን እነደሆነ ገና አልባነኑም። ከላይ ከላይ ነፍሳቸውን ፍላጎቷን ገድበናል ብለው ያስባሉ ነገር ግን በድብቅ ፍላጎቷን ከበስተጀርባ ይከተላሉ። እውነታው ነፍሳቸው ድል አድርጋቸዋለች፣ ሳያውቁት ከፊት ለፊቷ እየነዳቻቸው ነው።

- ከነፍስ ጋር የሚደረግ ጦርነት ቀላልና ሜዳውም ውስን ነው ብሎ የሚያስብ ሰው ተሳስቷል። እንዲያውም ሞት ካልቋጨው በስተቀር የማያልቅ የሆነ ከባድ ጦርነት ነው። ስለሆነም ነፍሳችንን ሂሳብ በማድረግ ላይ ልንዘወትር፣ እንዲሁም ውስጧን ልንፈትሽ ግድ ይለናል።

- [ሙስሊም በሁለቱም ሕይወቱ -በመጀመሪያውም ሆነ በሁለተኛው- ደስታው ነፍሱን ሥርዓት ባስያዛት፣ ባስተካከላትና ባጸዳት መጠን እንደሆነ ያምናል። እንደዚሁም የነፍስ መጽዳትና መስተካከል የእምነትና የመልካም ሥራ ጥሩ ውጤት መሆኑንና የመቆሸሿና የመበላሸቷ ምክንያት ደግሞ የክህደትና የወንጀል መጥፎ ውጤት መሆኑን ያምናል። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ وَأَقِمِ ٱلصَّلَوٰةَ طَرَفَيِ ٱلنَّهَارِ وَزُلَفٗا مِّنَ ٱلَّيۡلِۚ إِنَّ ٱلۡحَسَنَٰتِ يُذۡهِبۡنَ ٱلسَّيِّـَٔاتِۚ ﴾ هود: ١١٤

"ሶላትንም በቀን ጫፎች ከሌሊትም ክፍሎች ፈጽም። መልካም ሥራዎች ጎጠኬቶችን ያስወግዳሉና። ይህ ለተገሳጮች ግሳጼ ነው።" (ሁድ: 114)

አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ كَلَّاۖ بَلۡۜ رَانَ عَلَىٰ قُلُوبِهِم مَّا كَانُواْ يَكۡسِبُونَ ١٤ ﴾ المطففين: ١٤

"በልቦቻቸው ላይ ይሠሩት የነበሩት (ጎጠኬት) ደገደባቸው።" (አል-ሙጦፊፊን: 14)

በዚህም ምክንያት ሙስሊም ነፍሱን በመግራት፣ በማስተካከልና በማጽዳት ላይ ይሠራል፤ እርሷ ሥርአት መያዝ ካለበት ሁሉ ቀዳሚዋ ናት።][6]

[6]መንሃጅ አል-ሙስሊም

የመመዘኛ ጥያቄዎች

1. የሰው ልጅ ነፍስ ለመልካምና ለመጥፎ ተግባር ዝግጁ መሆኗን አብራራ።
2. ሰዎች ከነፍሶቻቸው ጋር ባላቸው ግንኙነት አንጻር የሚኖራቸውን አመዳደብ አብራራ።
3. ላፍታ ከራስህ ነፍስ ጋር ቆም ብለህ አንተ ከየትኛው ምድብ እንደሆንክ አስተውል። ይህን የምታደርገው የራስህን ነፍስ ከየምድቡ ከተጠቀሱ ባህሪያት ጋር በማነጻጸር ነው። ከዚያ ምን ማድረግ እንዳለብህ ወስን።

ሁለተኛው ዓላማ

ፉስን ወደ ተሻለ ደረጃ የመለወጥ ስላላቢነትና ስስፈላጊነት እንዲያብራራ ማስቻል

የትምህርቱ ዓላማ

1. ነፍስን በማስተካከል ሂደት የተከበረው ቁርአንንና የተቀደሰው ሱንናን እገዛ እንዲያብራራ ማስቻል።
2. ኡምማው የተዝኪያ ባለቤቶችን ምን ያህል እንደሚፈልጋቸው ግልጽ እንዲያደርግ ማስልቻል።

1. ነፍስን በማስተካከል ሂደት የተከበረው ቁርአንና የተቀደሰው ሱንና ያላቸው ድጋፍ

በተከበረው ቁርአን፡-

ነፍስን በማጥራትና በማስተካከል ወደ ተሻለ ደረጃ የመለወጡን ተግባር ቁርአን ከፍተኛ አፅንኦት በመስጠት ይደግፈዋል። ለዚህም "ተዝኪያ" ወይም "ማበልጸግ፣ ማጥራት" የሚለውን ቃል ተጠቅሟል። በርግጥ ቁርአን አሳሳቢነቱንና አስፈላጊነቱን በብዙ ቦታዎች ላይ አበክሮ ገልጿል። ከፊሎቹን ለመጥቀስ ያህል የሚከተሉትን የአላህ (ሱ.ወ) ንግግሮች እንመለከታለን፡-

﴿وَنَفۡسٖ وَمَا سَوَّىٰهَا ٧ فَأَلۡهَمَهَا فُجُورَهَا وَتَقۡوَىٰهَا ٨ قَدۡ أَفۡلَحَ مَن زَكَّىٰهَا ٩ وَقَدۡ خَابَ مَن دَسَّىٰهَا ١٠﴾ الشمس: ٧ - ١٠

"በነፍስም ባስተካከላትም፤ አመጽዋንና ፍርሃትዋንም ባሳወቃት፥ (አምላክ እምላለሁ)፤ (ከጎጠኔት) ያጠራት ሰው ፍላጎቱን በእርግጥ አገኘ፡፡ (በጎጠኔት) የሸፈናትም ሰው፥ በውኑ አፈረ፡፡" (አሽ-ሸምስ: 7-8)

- አላህ (ሱ.ወ) ነፍሱን ለማጥራት የሚሮጥ ሰው ስኬታማ እንደሆነ ሲገልጽ እርሷን ችላ ያላትንና ያቆሸሻትን ደግሞ ከሳሪ መሆኑን አሳውቋል።

﴿ لَقَدۡ مَنَّ ٱللَّهُ عَلَى ٱلۡمُؤۡمِنِينَ إِذۡ بَعَثَ فِيهِمۡ رَسُولٗا مِّنۡ أَنفُسِهِمۡ يَتۡلُواْ عَلَيۡهِمۡ ءَايَٰتِهِۦ وَيُزَكِّيهِمۡ وَيُعَلِّمُهُمُ ٱلۡكِتَٰبَ وَٱلۡحِكۡمَةَ وَإِن كَانُواْ مِن قَبۡلُ لَفِي ضَلَٰلٖ مُّبِينٍ ١٦٤ ﴾ آل عمران: ١٦٤

"አላህ በምእምኖን ላይ ከነሳቸው የኾነ፤ በእነርሱ ላይ አንቀጾቹን የሚነብ፣ የሚጠራቸውም፣ መጽሐፍንና ጥበብን የሚስተምራቸውም የኾነ መልእክተኛ በወሳቹው በላከ ጊዜ፤ በርግጥ ለነሰላቸው፡፡ እነርሱም ከዚያ በፊት በግልጽ ስህተት ወስጥ ነበሩ፡፡" (አል-ዒምራን፡ 164)

- በርግጥ የልዕልና ባለቤት የሆነው አላህ ከራሳቸው የሆነን መልክተኛን በመካከላቸው በመላክ ከፍተኛ ችሮታ አበርክቶላቸዋል፡፡ የዚህን ችሮታ ታላቅነት የሚያነላው መልክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ከተላኩበት ዋነኛ ተግባር አንዱ እነርሱን ሊያጸዳቸው መሆኑ ነው፡፡ እዚህ አንቀጽ ላይ አላህ (ሱ.ወ) መጽሐፉንና ጥበብን ከማስተማር አስቀድሞ ተዝኪያን ማስቀመጡ የበለጠ በትኩረት እንድናስተውል ያስገድደናል፡፡

﴿ عَبَسَ وَتَوَلَّىٰٓ ١ أَن جَآءَهُ ٱلۡأَعۡمَىٰ ٢ وَمَا يُدۡرِيكَ لَعَلَّهُۥ يَزَّكَّىٰٓ ٣ أَوۡ يَذَّكَّرُ فَتَنفَعَهُ ٱلذِّكۡرَىٰٓ ٤ أَمَّا مَنِ ٱسۡتَغۡنَىٰ ٥ فَأَنتَ لَهُۥ تَصَدَّىٰ ٦ وَمَا عَلَيۡكَ أَلَّا يَزَّكَّىٰ ٧ وَأَمَّا مَن جَآءَكَ يَسۡعَىٰ ٨ وَهُوَ يَخۡشَىٰ ٩ فَأَنتَ عَنۡهُ تَلَهَّىٰ ١٠ كَلَآ إِنَّهَا تَذۡكِرَةٞ ١١ ﴾ عبس: ١ - ١١

"ፊቱን አጨፋገገ፤ ዞረም፤ ዕውሩ ስለመጣው፡፡ ምን ያሳወቅሃል? (ከኀጢአቶቹ) ሊጥራራ ይከጀላል፡፡ ወይም ሊገሠጽ፣ ግሣጼይቱም ልትጠቅመው (ይከጀላል)፡፡ የተብቃቃው ሰውዬ አንተ ለርሱ (ለእምነቱ በመጓጓት) በፈገግታ ትቀበለዋለህ፤ ባይጥራራ (ባያምን) ባንተ ላይ ምንም የሌለብህ ስትኾን፤ እየገሰገሰ የመጣ ሰውዬ እርሱ (አላህን) የሚፈራ ሲኾን፤ አንተ ከርሱ ትዘዘናጋለህ፡፡ ተከልክል፤ እርሷ ሚገንዘቢያ ናት፡፡" (ዐበስ: 1-11)

- አላህ (ሱ.ወ) በእርግጥ ውድ መልክተኛውን (ሰ.ዐ.ወ) ወቀሳቸው፤ ዕውቀትን ፈልጎ በጉጉት የመጣውን ዓይነ ስውር ችላ በማለታቸው -ሊጥራራ ከጅሎ የመጣውን-በእርግጥ መልክተኛው ከርሱ ዞር ያሉት ለእሰልምና ጥሪ የበለጠ ጠቃሚ ነው ብለው ባሰቡት ጉዳይ በመወጠራቸው ነው፤ ይህም እርሳቸው (ሰ.ዐ.ወ) የቁረይሽ ባላባቶች እንዲሰልሙ የሚያደርጉት ጥሪ ነበር፣ እነርሱ

ከሰለሙም ከጀርባቸው ያሉ የዐረብ ጎሳዎች ይሰልማሉ የሚል እምነትን ይዘው ነበር-ለመሆኑ አላህ (ሱ.ወ) ውድ መልክተኛውን የወቀሰበት ምንኛ የላቀ ጉዳይ ነው? ይህ ሁኔታ ነፍሱን ለማፅዳት የሚጣደፍ ሰው የሚሰጠውን ከፍ ያለ ደረጃና እንዲሁም ራስን የማጥራት ሥራ በራሱ በእውነተኛው አላህ ዘንድ የተሰጠውን የሚዛን ክብደት በግልፅ አመላካች ነው::

﴿ ٱذۡهَبۡ إِلَىٰ فِرۡعَوۡنَ إِنَّهُۥ طَغَىٰ ١٧ فَقُلۡ هَل لَّكَ إِلَىٰٓ أَن تَزَكَّىٰ ١٨ وَأَهۡدِيَكَ إِلَىٰ رَبِّكَ فَتَخۡشَىٰ ١٩ ﴾

"ወደ ፈርዖን ሺድ፤ እርሱ ወሰን አልፏልና:: በለውም፡ – «ወደ መጥራትህ ላንተ (መንገድ) አለህን?»«ወደ ጌታህም ልመራህ፥ ትፈራውም ዘንድ፤ (መንገድ አለህን?)» አለው፡ : " (አን-ናዚዓት፡ 17-19)

- አላህ (ሱ.ወ) ነቢዩላህ ሙሳን (ዐ.ሰ) ወደ ፈርዖን ይጥራራ ዘንድ እንዲጠሩት ላካቸው፤ (ከጥጋበኝነት ቆሻሻ ልትፀዳ ትፈልጋለህን? ከወንጀል ዝቅጠት? ወደ ሰላትና በረከት መንገድ መመራትን ትፈልጋለህን? የጌታህን መንገድ እንዳሳውቅህ ትሻለህን?) በማለት::

- ነቢዩላህ ሙሳ (ዐ.ሰ) ወደ ፈርዖን በዚህች ተዓምራዊ ንግግር የነበራቸው ተልእኮ ሲጠቃለል ተዝኪያ (መጥራራት) ያለውን ከፍተኛ ቦታ እንደሚያሳይና ወደ እርሱ መትጋትም የቱን ያህል አስፈላጊ መሆኑንን እንደሚያመላክት ከማንም የተደበቀ አይሆንም::

ከመልክተኛው ትክክለኛ ዘገባዎች:-

- መልክተኛው ያደርጉት ከነበረው ዱዓ መካከል "አላህ ሆይ! ነፍሴን ፍራቻዋን ስጣት፣ አጥራትም አንተ ከሁሉ በላይ የምታጠራት ነህና፣ አንተ መመኪያዋም ጌታዋም ነህና" (ከዘይድ ኢብኑ አርቀም ሙስሊም የዘገቡት)

- ረቢዓት አል-አስለሚይ በጀነት ጎረቤትዎ መሆን እፈልጋለሁ ብሎ በለመናቸው ጊዜ የጠየቁት ነገር *"በነፍስህ ላይ ሱጁድ በማብዛት አግዘኝ::"*

ከቀደምት ሰለፎች ሰሻፉ:-

- አቡበክር አስ-ሲዲቅ (ረ.ዐ) ዑመር ኢብኑል ኸጣብን (ረ.ዐ) ሲመክሯ "በመጀመሪያ የማስጠነቅቅህ ያችን በጎንና ጎንህ መካከል ያለችውን ነፍስህን ነው!"

- ዑመር ኢብኑል ኸጣብ (ረ.ዐ) እንዲህ ይሉ ነበር፡-"(ነገ አላህ ፊት) ከመመርመራችሁ በፊት ራሳችሁን (እዚሁ) መርምሩ፤ ሥራችሁ ከመመዘኑ በፊት (ራሳችሁን) መዝኑ..."

- ከፊሎቹ የእስልምና መሪዎች እንዲህ ይሉ ነበር፡- "እኔ ዘንድ ሰዎችን ሥርዓት ከሚያስይዝና ከሚያስተምር ሰው ይልቅ ነፍሱን ሥርዓት ያስያዛትና ያስተማራት የተከበረ ነው፡፡" ይህ አባባላቸው ሰዎችን ማስተማርና ዳዕዋ ማድረግን ለማሳነስ ሳይሆን ነፍስን ለማፅዳት ከሚሰጡት ክብር አኳያ ነው፡፡

- አንድ ጥፋተኛ ገጣሚ በርዘቃን ኢብኑ በድርን በአንድ የግጥም ቤት ተነኮሳቸው፡፡ እርሳቸውም በጣም ተቆጥተው ዑመር ኢብኑል ኸጣብ ዘንድ ከሰሱት፡፡ ምክንያቱም ሊታገሱት የማይችሉትን አስከፊ ንግግር ስለተናገራቸው ነው፡፡ ለመሆኑ ይህ አስከፊ ንግግር ምን ይሆን? እንዲህ ነበር ያላቸው፡- "መልካም ባህሪ አትበል ነፍስህ ከጥጋቧ ላትወገድ፥ አንተ ተመጋቢ ለባሽም ነህ ዝም ብለህ ቁጭ በል፤" ለማለት የፈለገው አንተ በመብላት፣ በመጠጣት፣ በመልበስ ላይ መዘውተርህ እስካልቀረ ድረስ ስለ ስነ-ምግባር መስተካከል ምንም ጉዳይ የለህም፣ ነፍስህንም ሆነ የሌላውን ነፍስ አፀዳለሁ ብለህ አትድከም ነው...ዑመር ኢብኑል ኸጣብ ይህንን ሰው ከዚህ ድርጊቱ ከለከሉት፣ ይቅርታ ካልጠየቀውም እንደሚቀጡት ነገሩት፡፡

- አላህ የሰውን ልጅ ከሌላው ፍጡር ያስበለጠበት ምክንያት አላህን በማወቅና የርሱን ውደታ ለማግኘት ነፍሱን በማጥራት ላይ ስለሚተጋ ነው፡፡ ከዚህች መለዮ ተግባሩ ከተወገደና በመብላት፣ በመጠጣትና ስሜቱን በማጣጣም ከተብቃቃ ግን ከእንሰሳትም በታች የተዋረደ ይሆናል፡፡

- አቡ ሃሚድ አል-ገዛሊ (አላህ ይዘንላቸውና) እንዲህ ብለዋል፡- "ፈረስ ከአህያ ጋር በጉልበትና በሸክም ቢመሳሰልም በሽቅድድሙና በጥሩ ቁመናው የተለየ ነው፡፡ በመሠረቱ ፈረስ የተፈጠረው ለዚህ ተግባሩ ነው፡፡ ነገር ግን ይህንን ተግባሩን ካቆመ ወደ አህያ ተራ ይወርዳል፡፡ እንደዚያውም የሰው ልጅ ከክብሩ ከወረደና በእንስሳዊ ባህሪው በተግባሩ ከተመሳሰለ እንደዚያው ይሆናል፡፡"[7]

[7]ኢሕያእ ቅጽ 3 ገፅ 9

2. ሱምማው የተዝኪያ ባለቤቶች ያስፈልጉታል

ነፍስን የማጥራት ተግባር አስፈላጊነትና በዲኑ የተሰጠውን ደረጃ አውቀናል። ነፍሳቸውን በማጥራት ላይ በእውቀታቸውና በተግባራቸው የጸኑ ሰዎች በአላህ ፈቃድ ህያው የሆኑ የዚህ ኡምማ የሕይወት እስትንፋስ ናቸው። የዚህን መልእክት ተመሳሳይ ሸሂድ ሐሰን አል-በና እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል፡- “የህብረተሰባችንን ነፍስ፣ ሕይወትና ስሜት በእውነት የሚያናግር እንደዚህ አይነት ራስን የማባነን ሥራ ሳንሠራ ወደ ለውጥ ለማሸጋገር ማሰብ ዘበት ይሆናል። ስለሆነም ይህን ማለት እችላለሁ፡- በዳዕዋችን ለህብረተሰባችን በቅድሚያ የምንጨነቅለት፣ በርሱ ላይ እድገቱን፣ መፋፋቱንና ስርጭቱን አጥብቀን የምንከታተለው ነገር ቢኖር፣ ይህን ሥር-ነቀል የሆነ ሕይወት የማባነን እንቅስቃሴ ነው። ከምንም በላይ በቅድሚያ የሕይወት መባነንን፣ የቀልብ ህያውነትንና የአካል መነቃቃትን እንፈልጋለን። በዚህ የዳዕዋ እንቅስቃሴያችን ለሌሎች የተለያዩ ቅርንጫፋዊ የማሻሻያ ተግባራት የምንሰጠው ትኩረት ነፍስን በማጥራት ሂደት ከምንሰጠው ትኩረት ጋር አይስተካከልም።”[8] ሙእተመር አል-ኻሚስ ላይ ደግሞ የህብረተሰባችን መድሃኒት ምን እንደሆነ በአንዲት ዐርፍተ ነገር አንዲህ ሲሉ በግልፅ አስቀምጠውታል፡- “ነፍስን ማከምና የህብረተሰቡን ሥነ-ምግባር መቆጣጠር!”

የአላህ (ሱ.ወ) ውሳኔ ነፍስህን የማጥራቱን ተግባር ካንተ የመለወጥ ፍላጎት ጋር በቀጥታ አቆራኝቶታል።የለውጡን የመጀመሪያ እርምጃም አንተ እንድትራመድ ያስገድዳል፡-

- በርግጥ አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿إِنَّ ٱللَّهَ لَا يُغَيِّرُ مَا بِقَوۡمٍ حَتَّىٰ يُغَيِّرُواْ مَا بِأَنفُسِهِمۡۗ ﴿١١﴾﴾ الرعد: ١١

“›Ll uQ′x‹ ²”É ÁK¨<” çÒ÷ u’õf‰†¨< ÁK¨<” (¤<’@ታ) እeŸT>K¨<Ö< É[e ›ÃK¨<ØU&” (አር-ረዕድ፡ ፲፩)

- በሌላ የቁርአን አንቀጽ

[8] ረሳኢል-ዳዕወቱና ፊ ጡሪን ጀዲድ

﴿وَٱلَّذِينَ ٱهۡتَدَوۡاْ زَادَهُمۡ هُدٗى وَءَاتَىٰهُمۡ تَقۡوَىٰهُمۡ ١٧﴾ محمد: ١٧

"እነዚያም የተመሩት፥ (አላህ) መሚትን ጨምሪላቸው፤ (ከእሳት) መጠበቂያቸውንም ሰጣቸው፡ ፡" (ሙሐመድ: 17)

- በአንቀጹ ውስጥ የቃላቶቹ ቅደም ተከተል ቆም ብለን እንድናስተውል ያስገድደናል... እነዚያ የተመሩት መመራትን ጀመሩት፤ ከዚያም አላህ መመራትን በመጨመር ካሳቸው፤ ከዚህም በላይ በጣም ጥልቅና ምሉዕ የሆነ ነገርን በመስጠት ዋለላቸው፡- "ተቅዋን (መጠበቂያቸውን) ሰጣቸው"። ተቅዋ (መጠበቂያ) በልብ ውስጥ ያለች ሁኔታ ስትሆን ባለቤቱን ሁልጊዜም ለአላህ ክብር እንዲያደገድግ ታደርገዋለች፣ የአላህ ተቆጣጣሪነት እንዲሰማውና ቁጣውንም እንዲፈራ፣ ውዴታውን እንዲፈልግ፣ እርሱ በማይወደው ተግባር ወይም ሁኔታ ላይ እንዳይገኝ ታስችለዋለች...ይህች ስነትና ሆደ ባሻነት ተቅዋ ትባላለች...አላህ ከባሮቹ ለፈለገው በእርሱ በተመሩ፣ እርሱን በፈለጉና ወደ እርሱ ውደታ ለመድረስ በጓጉ ጊዜ የሚሰጣት ሽልማት ናት።) (ፊዚላል)

- አላህ ስለ ሙሳ (ዐ.ሰ) ህዝቦች ሲናገር

﴿فَلَمَّا زَاغُوٓاْ أَزَاغَ ٱللَّهُ قُلُوبَهُمۡۚ وَٱللَّهُ لَا يَهۡدِي ٱلۡقَوۡمَ ٱلۡفَٰسِقِينَ ٥﴾ الصف: ٥

" (አስታወሳ፤ ከሓ ት) በተዘነበለም ጊዜ፥ አላህ ልቦቻቸውን አዘነበላቸው፤ አላህም አመጻኞቹን ሕዝቦች አያቀናም፡ ፡" (አስ-ሶፍ: 5)

ስለዚሁ ጉዳይ አላህ (ሱ.ወ) በድጋሜ እንዲህ ይላል፡-

﴿فَأَمَّا مَنۡ أَعۡطَىٰ وَٱتَّقَىٰ ٥ وَصَدَّقَ بِٱلۡحُسۡنَىٰ ٦ فَسَنُيَسِّرُهُۥ لِلۡيُسۡرَىٰ ٧ وَأَمَّا مَنۢ بَخِلَ وَٱسۡتَغۡنَىٰ ٨ وَكَذَّبَ بِٱلۡحُسۡنَىٰ ٩ فَسَنُيَسِّرُهُۥ لِلۡعُسۡرَىٰ ١٠﴾ الليل: ٥ - ١٠

"የሰጠ ሰውዬ ጌታውን የፈራም፤ በሚልካሚኑም (እምነ ት) ያረጋገጠ፤ ለገሪቱ ሥራ እናዘጋጀዋለን፡ ፡ የሰሰተ ሰውዬ የተቢቃቃም፤ (በራሱ የተሞላ) ፤ በሚልካሚኑ (እምነ ት) ያስተባበለም፤ ለከፉይቱ ሥራ እናዘጋጀዋለን፡ ፡"

(አል-ለይል: 5-10)

በእጅህ ላይ ሁለት ቁልፎች ተቀምጠዋል። ሁለት መንገዶች ከፊት ለፊትህ ይገኛሉ። ከአላህ (ሱ.ወ) ፍላጎት በኋላ ምርጫው ላንተና ላንተ ብቻ ተትቷል፡-

- በሐዲስ አል-ቁድስ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡ "ስንዝር ያህል ወደ እኔ የቀረበኝን በክንድ ያህል እቀርበዋለሁ፣ በክንድ ያህል የቀረበኝን የርሱን እጥፍ ያህል (ሁለት ክንድ ተዘርግቶ) እቀርበዋለሁ፣ በእርምጃ ወደ እኔ ቢመጣ እኔ በሶምሶማ እቀርበዋለሁ።"
- በመጀመሪያው እርምጃህ የአላህን ውዴታ ፈልገህ ነፍስህን በማጥራት ላይ በእውነት ስትራመድ የአምላክህን እገዛ ትደርስበታለህ። ከዚያም መንገዱ ያጥርልሃል። ካሰብከውም ትደርሳለህ። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

﴿فَأَمَّا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ بِٱللَّهِ وَٱعۡتَصَمُواْ بِهِۦ فَسَيُدۡخِلُهُمۡ فِي رَحۡمَةٖ مِّنۡهُ وَفَضۡلٖ وَيَهۡدِيهِمۡ إِلَيۡهِ صِرَٰطٗا مُّسۡتَقِيمًا ١٧٥﴾ النساء: ١٧٥

"እነዚያማ በአላህ ያመኑ በርሱም የተጠበቁ ከሱ በኾነው እዝነትና ችሮታ ወሳጥ በርግጥ ያስገባቸዋል፣ ወደ እርሱም ቀጥተኛ መንገድን ይመራቸዋል፣" (አን-ኒሳእ: 175)

﴿وَإِنَّ ٱللَّهَ لَهَادِ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ إِلَىٰ صِرَٰطٖ مُّسۡتَقِيمٖ ٥٤﴾ الحج: ٥٤

"አላህም እነዚያን ያመኑትን ወደ ቀጥተኛው መንገድ በርግጥ መሪ ነው፣" (አል-ሐጅ: 54)

ከዚያች ካለምካት ህዳሴ፤ የመጀመሪያዋ ደረጃ እስከምትደርስ ድረስ!! በል ፍጠን፣ በፅኑ ወስን፣ ነፍስህን ለመለወጥና ለማስተካከል በጌታህ በመታገዝ በቁርጠኝነት ጉዞህን ቀጥል...

- አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿وَلَوۡلَا فَضۡلُ ٱللَّهِ عَلَيۡكُمۡ وَرَحۡمَتُهُۥ مَا زَكَىٰ مِنكُم مِّنۡ أَحَدٍ أَبَدٗا وَلَٰكِنَّ ٱللَّهَ يُزَكِّي مَن يَشَآءُۚ وَٱللَّهُ سَمِيعٌ عَلِيمٌ ٢١﴾ النور: ٢١

“u“”}U LÃ ¾›LI ‹aታ“ እ”~ vM’u[*a÷ Ÿ“”} ›”ÉU ðêV vMÖ^ ’u`& Ó” ›LI ¾T>h¨<” c¨< ÁÖ^M& ›LlU cT> ®ªm ”¨<::” (አን-ኑር: 21)

ተግባራዊ ልምምድ

1. ሱጁድ ባደረግክ ቁጥር በሚከተለው ዱዓ አላህን ለምን፡-“አላህ ሆይ! ነፍሴን ፍራቻዋን ስጣት፣ አጥራትም አንተ ከሁሉ በላይ የምታጠራት ነህና፣ አንተ መመኪያዋም ጌታዋም ነህና::”
2. ነፍስህን በማጥራት ላይ የሚያግዙህን ማንኛውንም አይነት ተግባር ለመተግበር ተጣደፍ::
3. መልካም ሰዎችን በመጎዳኘት ላይ ዘውትር፤ ይህ ተግባር ነፍስን ያጸዳል::

የመጠዘኛ ጥያቄዎች

1. ቁርኣንና ሱንና ነፍስን ለማጥራት የሰጡት ትኩረት አብራራ::
2. የሰው ልጅ ነፍስን ለማጥራት ለጥራት ተገቢ የሆኑ ሰዎች እንደሚያስፈልጓቸው አብራራ::

ሦስተኛው ዓላማ

የነፍስን ባህሪያትና ጉድለቶቿን ሊገነዘብ

የትምህርቱ ዓላማ

1. የተከበረው ቁርአን የጠቀሳቸውን ዋና ዋና የነፍስ አይነቶች እንዲገነዘብ ማስቻል።
2. የሰው ልጅን ከፊል የነፍስ ባህሪያት እንዲያብራራ ማስቻል።

(ይህች አላህ በኛ ውስጥ ያስቀመጣት ነፍስ ብዙ ባህሪያት አሏት። በአንዲት ነፍስ ላይ የሚስተዋሉ ተቃራኒ ባህሪያት በቁጥር ብዙ ናቸው።)[9]

(አላህን በማውሳት፣ ቃሉን በመፈፀም፣ ትእዛዙን በመተግበርና የከለከለውን በመከልከል፣ ዲኑን በመጠበቅ፣ መልክተኛውን (ሰ.ዐ.ወ) በመከተል ላይ የተረጋጋች የሆነች ነፍስ አለች-"ነፍሱን ሙጥመኢናህ"። እንደዚሁም ባለቤቷ በዒባዳ ላይ ባለው ክፍተት የምትወቅስ የሆነች ወቃሽ ወይም "ነፍሱን ለዋማህ" የምትባል ነፍስ አለች። ነገር ግን "ነፍሱን ለዋማህ" አንዳንድ ጊዜ ትደክምና በመጥፎ የምታዝ ትሆናለች።)[10]

የነፍስን አይነቶች ማወቅ በጣም ወሳኝ ጉዳይ ነው፤ ይህ ሲሆን ጥሩዋን እንተገብራለን መጥፎዋን እንርቃለን። ከአይነቶቿ ዋና ዋናዎቹ አላህ (ሱ.ወ) በተከበረው መጽሐፉ የጠቀሳቸው ናቸው።[11]

1. ቅዱስ ቁርአን የጠቀሳቸው የነፍስ አይነቶች

አንደኛ፡ – በመጥፎ የምታዝ ነፍስ

[9] (መንሃጁ አት-ታቢዒን ፊ አት-ተርቢየቲ ኑፉስ)
[10] (ተዝኪያ ነቢል አል-ሙዓዝ)
[11] (መንሃጁ ታቢዒን ፊ ተረቢየቲ ኑፉስ)፡-

- (የተዝኪያ ባለቤቶች ስለ ነፍስ፣ እርሷን ስለመታገልና ስለመቃወም በሚያወሱበት ወቅት እነርሱ ነፍስ የሚሉት በጥቅል ትርጓሜው የቁጣና የስሜት ኃይልን ወይም በሌላ አነጋገር በሰው ውስጥ ያሉ መጥፎ ባህሪያትን ማለታቸው እንደሆነ መረዳት ይኖርብናል።)[12]

- (የነፍስን አደገኛነት ለመረዳት ከፈለግን አላህ (ሱ.ወ) ስለ ቃቤል የተናገረውን እናንብብ፡-

﴿ فَطَوَّعَتۡ لَهُۥ نَفۡسُهُۥ قَتۡلَ أَخِيهِ فَقَتَلَهُۥ فَأَصۡبَحَ مِنَ ٱلۡخَٰسِرِينَ ٣٠ ﴾ المائدة: ٣٠

"ነፍሱም ወንድማ መግደልን ለርሱ ሸለመችለት፤ (አነሳሳችዉ፤)፡፡ ገደለዉም፡ ከከሳሪዎቹም ኾነ፡፡" (አል-ማኢዳህ፡ 30)

- አላህ በየዕቁብ አንደበት ለልጆቹ እንዲህ ብሏቸዋል፡-

﴿ بَلۡ سَوَّلَتۡ لَكُمۡ أَنفُسُكُمۡ أَمۡرٗاۖ ١٨ ﴾ يوسف: ١٨

"«አይደለምኝ ነፍሶቻችሁ (ወሸት) ነገርን ለእናንተ ሸለሟችሁ፡፡"

(ዩሱፍ: 18)

- ሳሚሪይ ለእስራኤል ልጆች ጥጃ ለአምልኮ በሠራላቸው ጊዜ በራሱ አንደበት አላህ እንዲህ አናግሮታል፡-

﴿ وَكَذَٰلِكَ سَوَّلَتۡ لِي نَفۡسِي ٩٦ ﴾ طه: ٩٦

"እንደዚሀም ነፍሴ ሸለመችልኝ" (ጦሃ፡ 96)

- የንጉሱ ሚስት ስለ ነቢዩላህ ዩሱፍ (ዐ.ሰ) የተናገረችው፡-

﴿ وَمَآ أُبَرِّئُ نَفۡسِيٓۚ إِنَّ ٱلنَّفۡسَ لَأَمَّارَةُۢ بِٱلسُّوٓءِ إِلَّا مَا رَحِمَ رَبِّيٓۚ إِنَّ رَبِّي غَفُورٞ رَّحِيمٞ ﴾ يوسف: ٥٣

"ነፍሴንም (ከስሕተት) አላጠራም፡ ነፍስ ሁሉ ጌታዬ የጠበቃት ካልሆነች በስተቀር በመጥፎ ነገር በርግጥ አዛዥ ናትና፡፡ ጌታዬ በጣም መሓሪ አዛኝ ነው» (አለ)፡፡" (ዩሱፍ: 53)

[12](አል-ተዝኪያ)

(ይህም ማለት ነፍሴ ፍጹም ናት አልልም፣ ከጉድለትም አትጸዳም፤ የሰው ልጅ ነፍስ ወደ ስሜት የተዘነበለች ናት)[13]

- በቁርጡቢይ ተፍሲር ላይ እንደተጠቀሰው ነፍስ ለመጥፎ የጓጓች ናት፡፡ (በአንድ ባሪያ ላይ በአደገኛ ሁኔታ የበላይ የመሆኗ ማስረጃ እርሱ ለስሜቷ አብዝቶ እጅ መስጠቱ ነው፡፡ ለዚህም ኢብኑል ቀይም (አላህ ይዘንላቸውና) እንዲህ ብለዋል፡- “የቀልብ በሽታዎች በሙሉ ምንጫቸው ከነፍስ ነው፡፡ ሁሉም የተበላሹ ቁሳዊ ፍላጎቶች መነሻቸው ነፍስ ናት፡፡ ከዚያም ወደ ሌሎቹ የሰውነት ክፍሎች ይሸጋገራል፡፡ መጀመሪያ የሚጠቃው ቀልብ ነው፡፡”

- ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከነፍስ ተንኮል ባጠቃላይ እንዲሁም ከርሷ ከሚወለዱ የተግባር ተንኮሎች በሙሉ እንዲጠብቃቸው ጌታቸውን ለምነዋል፡፡

- ደጋግ የአላህ ባሮች ሁሉ የሚስማሙበት ነፍስ በቀልብና ወደ አላህ ለመድረስ በሚደረግ ጉዞ መካከል ቆራጭ መሆኗን ነው፡፡ ነፍሱን ያላሸነፈና ያልተቃወመ ሰው አላህ (ሱ.ወ) ዘንድ መግባትም ሆነ መድረስ አይችልም፡፡ የተወሰኑ አዋቂዎች እንደሚሉት፡-“አላህን ፈላጊዎች ጉዟቸው ልክ ነፍሳቸውን ሲያሸንፉ ይጠናቀቃል፡፡ በነፍሱ ላይ የበላይ የሆነ በርግጥ ስኬታማ ይሆናል፣ ይድናልም፤ ነፍሱ የበላይ የሆነችበት ደግሞ በርግጥ ከሰረ፣ ጠፋ፡፡”

- አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

﴿فَأَمَّا مَن طَغَىٰ ﴿٣٧﴾ وَءَاثَرَ ٱلۡحَيَوٰةَ ٱلدُّنۡيَا ﴿٣٨﴾ فَإِنَّ ٱلۡجَحِيمَ هِيَ ٱلۡمَأۡوَىٰ ﴿٣٩﴾ وَأَمَّا مَنۡ خَافَ مَقَامَ رَبِّهِۦ وَنَهَى ٱلنَّفۡسَ عَنِ ٱلۡهَوَىٰ ﴿٤٠﴾ فَإِنَّ ٱلۡجَنَّةَ هِيَ ٱلۡمَأۡوَىٰ ﴿٤١﴾﴾ النازعات: ٣٧ - ٤١

“የካደ ሰውዬ ቅርቢቱንም ሕይወት የሚጠቅመውን ሁሉ እርሷ በእርግጥ መኖሪያው ናት፡ ፡ በጌታው ፊት መቆምን የፈራ ሰውዬ ነፍሱንም ከዝንባሌዋ የከለከለ፥ ገነት እርሷ በእርግጥ መኖሪያው ናት፡ ፡ ” (አን-ናዚዓት፡ 37-41)

[13](ሰፍወቱ ተፋሲር 2/53)

(ነፍስ በመሠረቷ መጥፎውን መምረጥ ይቀናታል፤ ከዚህ ለየት ያሉ መኖራቸው እንዳለ ሆኖ፡፡ ነፍስ ባጠቃላይ የፍዳና የጠንቅ ምንጭ፤ የተንኮልና የጥፋት ጎተራ፤ እንዲሁም የበደልና የጥጋብ መነሻ ናት፡፡ ስለሆነም እርሷ እንድትጸዳና ስሜቷም የአላህን ህግ እንዲከተል ጠንካራ የኢማን ኃይል ያስፈልጋታል፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለሶሃቦቻቸው ይህንን ሁኔታ እንዲህ አረጋግጠውልናል፡- “ስለዚህ ጓደኞችሁ ምን ትላላችሁ? ስታከብሩት፣ ስትታዘዙትና ስታለብሱት ለተንኮል ያጋልጣችኋል፤ ስታዋርዱት፣ ስታርዙትና ስታስርቡትም አሁንም ለተንኮል ያጋልጣችኋል… ሶሐቦቹም አንቱ የአላህ መልክተኛ ሆይ ይህ መጥፎ ጓደኛ በምድር ላይ አለን? ብለው ጠየቋቸው… ነፍሴ በእጁ በሆነው እምላለሁ እርሷ በጎንና ጎናችሁ መካከል ያለችው ነፍሳችሁ ናት፡፡” (ሙስሊም ዘግበውታል) (ሙሐሰበቱ ነፍስ ዶ/ር ሁሰይን ሸሃተሁ)

- ነፍስ በባህሪዋ ወደ ስሜት ትዘነበላለች፤እርሷን በማስተካከል ላይ የለፋ ሲቀር፡፡ በዚህም በመጥፎ ከማዘዝ በጥሩ ወደ ማዘዝ ትሸጋገራለች፤ ከሚደረግላት የተርቢያ ኩትኮታ ብዛት መጥፎን የመምረጥ ባህሪዋ ወደ ሌላ ባህሪ ይቀየራል፤ ይህም ከአላህ ውደታ የሚያርቅን ማንኛውንም ሥራዋን በራስ የመውቀስ ባህሪ ነው፡፡

ሀለተኛ፡ – ራሷን ወቃሽ ነፍስ

- አላህ (ሱ.ወ) አል-ቂያማ ምዕራፍ መግቢያ ላይ

﴿وَلَآ أُقۡسِمُ بِٱلنَّفۡسِ ٱللَّوَّامَةِ ۝٢﴾ القيامة: ٢

“(ራሷን) ወቃሽ በኾነች ነፍስም እምላለሁ፤” (አል-ቂያማህ፡ 2) ይላል፡፡

(ቁራህ ኢብኑ ኻሊድ ከሐሰን አል-በስሪ ይህንን አንቀጽ አስመልክቶ እንደተናገሩት፡- በአላህ እምላለሁ! ሙስሊም ነፍሱን ሲወቅስ እንጅ አናየውም- በንግግሬ ምን ፈልጌ ነው? በአመጋገቤስ ምን ፈልጌ ነው? ነፍሴን ሳናግራት ምን ፈልጌ

ነው? በማለት!! ጠማማ ሰው ደግሞ ዝም ብሎ ከፊት ለፊቱ ይነጉዳል፣ ነፍሱን አይወቅሳትም።)[14]

- ሙእሚን ዘወትር ነፍሱን ጀነት ከመግባት ከሚያቅባት ንግግርም ይሁን ተግባር ያፀዳታል። ኢማም ሙጃሂድ ይህችን አይነት ነፍስ ሲገልጿት፡- "እርሷ ያቺ ያሳለፈችውን የምትወቅስና የምትጸጸት ናት፣ የሠራችውን ተንኮል ለምን ሠራሁት፣ ለሠራችው ጥሩ ነገር ደግሞ ለምን በብዙ አልሠራሁትም ብላ ራሷን ትኮንናለች" በቅርብም ይሁን በሩቅ ያሳለፈችውን ከወንጀልም የፈፀመቸውን ታስታውሳለች፣ በዚህ አይነት ላሳለፈችው ጥቁር ተግባር ልቦናዋን ተጠያቂ ታደርጋለች፤ ከአላህ ትእዛዝ ውጭ ላባከነችው ጊዜ ብርቱ ጸጸት ትጸጸታለች፤ ውደታውን ባለመታደሏ ታዝናለች፤ ለሸይጣን ጌጥ እጅ በመስጠቷ ትቆጫለች። የዚህች ነፍስ ባለቤት ከወቃሽ ነፍሱ ጋር ዘወትር በፍርድ ላይ ነው። ስለሆነም ይህች ነፍስ ጥሩና መጥፎን የምትለይ ህያውና ንቁ ነፍስ ናት።

- ሰይድ ቁጥብ (አላህ ይዘንለትና) እንደሚለው "ይህች ወቃሽ፣ ንቁ፣ አላህን ፈሪና እርብትብት ነፍስ ራሷን ምርመራ የምታደርግ ናት። ዙሪያዋን ትመለከታለች፣ የስሜቷ እውነታ ተገልፆላታል፣ በራሷ እንዳትታለል ትጠነቀቃለች፣ እርሷ በአላህ ዘንድ የተከበረች ነፍስ ናት፣ ለዚህም ቂያማን ያስታውሳታል። ይህች ነፍስ መጥመምን የፈለገችና በጥመቷ ለመቀጠል ከወሰነች የሰው ልጅ ነፍስ ተቃራኒ ገፅታ አላት። የጠማማዋ ነፍስ ባለቤት ያ የሚያስተባብል፣ ከእውነት የሚዞር፣ ነፍሱን ሂሳብ ሳያደርግ በመንቦጥረር ወደ ቤተሰቦቹ የሚሄድና ለፈጸመው መጥፎ ነገር ወቀሳም ጭንቀትም የሌለለው ደንታ ቢስ ነው።"

- የወቃሽ ነፍስ ባለቤት የነፍሱ ተንኮል ሁልጊዜ ይሰማዋል። በሆነች ቅፅበት እንዳታታልለው ነቅቶ ይጠባበቃል። በጧትና በማታ እንዲሁም ወደ መኝታ ፍራሹ ከመሄዱ በፊት ነፍሱን እንዲህ በማለት ያስታውሳታል፡- "በል አላህ ! ሆይ! የሩቁንም ሆነ የቅርቡን ዓዋቂ የሆንክ፣ የሰማይና የምድር ፈጣሪ፣ የሁሉም ነገር ተንከባካቢ ጌታና ባለቤት፣ ካንተ በስተቀር ሊገዙት የሚገባ አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፣ ከነፍሴ ተንኮል ባንተ እጠበቃለሁ፣ ከሸይጧንና

[14] አል-ቃማህ

ከአጋሮቹም”። ነፍሱን ለመቋቋም የጌታውን እገዛ ይጠይቃል። ይህም ወደ አላህ የሚማጸንበት የመጀመሪያ ጉዳዩ ነው። በዚህ አይነት ሂደት አዘውትሮ ከቀጠለ ወደ ሌላ ደረጃ እንዲሸጋገር ይረዳዋል። ይህ ነፍሱን በመውቀስ ሂደት የመዘውተሩ ውጤት ነፍሱ የተረጋጋች ነፍስ እንድትሆን ያስችለዋል።

ሦስተኛ፡ – የተረጋጋች ነፍስ

አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ يَٰٓأَيَّتُهَا ٱلنَّفْسُ ٱلْمُطْمَئِنَّةُ ﴿٢٧﴾ ٱرْجِعِىٓ إِلَىٰ رَبِّكِ رَاضِيَةً مَّرْضِيَّةً ﴿٢٨﴾ فَٱدْخُلِى فِى عِبَٰدِى ﴿٢٩﴾ وَٱدْخُلِى جَنَّتِى ﴿٣٠﴾ ﴾ الفجر: ٢٧ - ٣٠

“አንቺ የረካሸው ነፍስ ሆይ! «ወዳጅ፥ ተወዳጅ፥ ኾነሽ ወደ ጌታሽ ተመለሺ፡ ፡ «በባሮቼም ውስጥ ግቢ፥ ገነቴንም ግቢ” (አል-ፈጅር: 27-30)

ኢማም አል-ቁርጡቢ እንደሚሉት፡- “የተረጋጋች ነፍስ፣ የሰከነችና እውነት ያለች፣ አላህ ጌታዋ መሆኑን ያረጋገጠችና ለዚህም የተመረጠች ናት።”

ኢብን አባስ “የተረጋጋች ነፍስ ማለት ከአላህ ምንዳን እንደምታገኝ እርግጠኛ የሆነች ነፍስ ናት” ብለዋል። ሙጃሂድ ደግሞ “የአላህን ውሳኔ የወደደች፣ ያች እርሱ ያልወሰነባት ነገር የማይነካት መሆኑንና እርሱ የወሰነባት ነገር ደግሞ የማያልፋት መሆኑን ያወቀች” ናት ብለዋል። ሀሰን አልበስሪ እንደሚሉት “አላህ (ሱ.ወ) የአንድ ሙእሚን ባሪያውን ነፍስ መያዝ ሲፈልግ ያች ነፍስ ወደ አላህ ትረጋጋለች፣ አላህም ወደ እርሷ ይረጋጋል።”

ይህች ነፍስ ለእያንዳንዱ ንግግር፣ ክስተት፣ ቅፅበት፣ እንዲሁም እርምጃ የዘወትር ምርመራ ባይደረግባት ኖሮ እንዲህ አይነት ባህሪ ባልተላበሰች ነበር። ይህ አይነቱ ዘውታሪ ወቀሳ ቀጥተኛውን መስመር እስከምትደርስበት ድረስ መንገዷን ያስተካክልላታል፤ የፈተና ንፋስም ሆነ የዱንያ ጌጥ፣ የመከራ ብርታትም ይሁን የሽይጧን ማታለያ ተፅእኖ አያሳድሩባትም። እንዲያውም በእምነቷ ባላት መረጋጋት፣ በአላህ ውሳኔ ላይ ባላት እርግጠኝነትና ለፍላጎቱ ባላት ተገዥነት የተነሳ እነኝህን ሁሉ ፈተናዎች ታላግጥባቸዋለች።

ሰይድ ቁጥብ (የአላህ እዝነት ይውረድበትና) ስለዚህች ነፍስ እንዲህ ብሏል፡- “በደስታም ይሁን በመከራ፣ ስታገኝም ይሁን ስታጣ፣ ስትከለከልም ይሁን ስትሰጥ የተረጋጋች ነች... የተረጋጋች ነፍስ አትጠራጠርም፣ አታፈነግጥም፣ በመንገድ ላይ አትዋልልም፣ የጭንቅና የፍርሀት ቀን አትርበተበትም”። ሰዎች በፍርሀት ሲርዱ፣ ጭንቀት ሲውጣቸው፣ ውድቀት ሲያከናንባቸው፣አቅም ሲያጡ፣ በአቋማቸው ሲዋልሉ የዚህች ነፍስ ባለቤት ግን ሁልጊዜም እንደ ትልቅ ተራራ የፀናና ምንም ነገር የማይበግረው ይሆናል፤ ይህም ነፍሱ ከተጥለቀለቀችበት መረጋጋት የተነሳ ነው።

2. ከሰው ልጅ የነፍስ ባህሪያት

(ይህች አላህ በእኛ ውስጥ ያስቀመጣት ነፍስ ብዙ አይነት ባህሪያት አሏት። በአንዲት ነፍስ ውስጥ እንኳን ብዙ አይነት እርስ በርስ ተቃራኒ ባህሪያት ይስተዋላሉ።)[15]

በሸሪዓ የሚፈለገው አንድ ሙስሊም ነፍሱን ምስጉን በሆኑ ባህሪያት ላይ እንዲገራትና መጥፎ ከሆኑት በህሪያት ደግሞ እንዲያርቃት ነው። ከነዚህ የነፍስ ባህሪያት መካከል፡-

አንደኛ፡ – በሰው ልጅ ነፍስ ውስጥ ያለ ቅልቅል ባህሪ

- አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

﴿وَنَفۡسٖ وَمَا سَوَّىٰهَا ٧ فَأَلۡهَمَهَا فُجُورَهَا وَتَقۡوَىٰهَا ٨ قَدۡ أَفۡلَحَ مَن زَكَّىٰهَا ٩ وَقَدۡ خَابَ مَن دَسَّىٰهَا ١٠﴾ الشمس: ٧ - ١٠

“በነፍስም ባስተካከላትም፤ አመጽዋንና ፍርሃትዋንም ባሳወቃት፥ (አምላክ እምላለሁ)፤ (ከጎጠኔት) ያጠራት ሰው ፍላጎቱን በእርግጥ አገኘ፥ (በጎጠኔት) የሸፈናትም ሰው፥ በመጎት አፈረ።” (አሽ-ሸምስ: 7-10)

[15](መንሃጁ ታቢዒን ፊ ተርቢየቲ ኑፉስ)

ይህ አላህ በሰው ልጅ ውስጥ ያስቀመጠው የመምረጫ መሳሪያ ጥሩ ወይም መጥፎን መርጦ እንዲሠራ አስችሎታል። በእለተ ቂያማም ምርመራ የሚደረገው በዚህ ምርጫው ላይ ተመስርቶ ነው። ስለሆነም ይህች ነፍስ ወደ ጥሩ አቅጣጫ ወይም ደግሞ ወደ መጥፎ አቅጣጫ ለመለወጥ ዝግጁ ነች። ይህም የሰው ልጅ እርሷን ለመለወጥ በሚያደርገው የልፋት መጠን ይወሰናል። ወደ ጥሩ የመለወጥ ሂደት "ተዝኪያ" ሲሰኝ ወደ መጥፎ የመለወጡ ሂደት ደግም "ተድሲያ (በፅልመት መሸፈን)" ይባላል። ለዚህም አላህ (ሱ.ወ) (ከመጥፎ የሚደርስብህ ነገር ከነፍስህ ነው) ይላል። ምክንያቱም እውነትን ባለመምረጡ የደረሰበት መጥፎ ነገር በመሆኑ ነው። እኔ ጥሩ ነገርን የመተግበርና ከመጥፎ የመራቅ ብቃት አልተሰጠኝም በማለት የሚሞግት ሰው ካለ ውሸታም ነው። ምክንያቱም አላህ (ሱ.ወ) ይህንን ዝግጁነት በእርሱ ውስጥ ፈጥሯልና፤ የመጨረሻ ውሳኔው ግን በሰውየው የጥሩ ወይም የመጥፎ ምርጫ ላይ የተተወ ነው። ስለዚህም ይህ በሰው ልጅ ውስጥ እንዲህ አይነቱ ቅልቅል ባህሪ ከመሰረቱ አብሮት የተፈጠረ እንጅ እራሱን የቻለ ብቸኛ ባህሪ አይደለም።

ሀለተኛ፡ – ኃላፊነትን የማከም ችሎታ

- አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

﴿لَا يُكَلِّفُ ٱللَّهُ نَفۡسًا إِلَّا وُسۡعَهَاۚ ٢٨٦﴾ البقرة: ٢٨٦

"አላህ ነፍስን ከችሎታዋ በላይ አያስገድዳትም።" (አል-በቀራህ፡ 286)

አላህ (ሱ.ወ) በሰው ልጅ ነፍስ ውስጥ ለበጎ ወይም ለመጥፎ ተግባር ዝግጁነትን ሲፈጥር የሰው ልጅ እንዲተገብር የታዘዘውን ነገር ይገራለት ዘንድ የመሥራት ችሎታም አብሮ ተፈጥሮለታል። ኢብን ከሲር አላህ ሥራቸውን ይውደድላቸውና እንዲህ ብለዋል፡- "ይህ ማለት አንድ ሰው ከችሎታው በላይ የሆነ ኃላፊነት አይሰጠውም፤ ይህ ደግሞ አላህ (ሱ.ወ) ለፍጡራኑ ካለው እዝነት፣ ርህራሄና ለነርሱ ካለው ደግነት የመነጨ ነው። ለዚህም ነው

﴿وَإِن تُبۡدُواْ مَا فِيٓ أَنفُسِكُمۡ أَوۡ تُخۡفُوهُ يُحَاسِبۡكُم بِهِ ٱللَّهُۖ ٢٨٤﴾ البقرة: ٢٨٤

"በነፍሶቻችሁ ውስጥ ያለውን ብትገልጹ ወይም ብትደብቁት አላህ በርሱ ይቆጣጠራችኋል።" (አል-በቀራህ፡ 284)

የሚለው አንቀጽ ሲወርድ ሰሐቦች በነፍሳችን ውስጥ ያለን ሹክሹክታ ሂሳብ ከተደረግን እንዴት እንችላለን በሚል በፍርሃት ሲዋጡ አላህ ነፍስን ከችሎታዋ በላይ አያስገድዳትም በማለት ነስህ ያደረገላቸው። ይህም ማለት ምርመራ መደረጉና መጠየቁ የማይቀር ቢሆንም ግለሰቡ ሊከላከለው ከሚችለው በላይ በሆነው አይቀጣም፤ ሊከላከለው በማይችለው የነፍስ ጉትጎታ የሰው ልጅ አይገደድም።"

ሦስተኛ፡ – ሜቃለል

- ከነፍስ ባህሪያት መካከል አንዱ ሰውን ማታለሏና መጥፎ መሥራትን አቅልላ ማሳየቷ ነው። በዚያች ቅፅበት በሚሠራው መጥፎ ተግባር የሚመጣበትን መጥፎ ውጤት ታስረሳዋለች። እርሱም ቀላል አድርጎ ያየውና ወደ መጥፎ ተግባር ይራመዳል። አላህ (ሱ.ወ) ስለ አደም ልጆች (ቃቢልና ሐቢል) ሲተርክልን እንዲህ ይላል፡-

ቃቢል ወንድሙን ለመግደል ሲነሳ፡-

﴿ فَطَوَّعَتۡ لَهُۥ نَفۡسُهُۥ قَتۡلَ أَخِيهِ فَقَتَلَهُۥ فَأَصۡبَحَ مِنَ ٱلۡخَٰسِرِينَ ٣٠ ﴾ المائدة: ٣٠

"ነፍሱም ወንድሟን መግደልን ለርሱ ሸለመችለት፤ (አነሳሳችው፤)። ገደለውም። ከከሳሪዎቹም ኾነ።" (አል-ማኢዳህ: 30)

ኢማም አል-ቁርጡቢይ ይህን አንቀጽ ሲተረጉሙት "ሸለመችለት፣ ነፍሱ ነገሩን ቀላል አደረገችለት፣ አጃነነችው፣ ወንድሙን መግደልን ለርሱ አላመደችው፣ ገር አድረጋ አሳየችው" ብለዋል።[16]

አራተኛ፡ – አስጊጦ ማሳየት (ሜሽለም)

- ነፍስ ለባለቤቷ ወንጀል መሥራትን አስጊጣ ታሳየዋለች። ማጊያጊያጥ ማለት በአንድ ነገር ላይ እውነተኛ ገፅታውን ተቀይሮ ነፍስ እንድትቀበለው ማድረግ ማለት ነው። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

[16](ተፍሲር አል-ቁርጡቢ 6/138)

﴿قَالَ فَمَا خَطْبُكَ يَٰسَٰمِرِيُّ ﴿٩٥﴾ قَالَ بَصُرْتُ بِمَا لَمْ يَبْصُرُوا۟ بِهِۦ فَقَبَضْتُ قَبْضَةً مِّنْ أَثَرِ ٱلرَّسُولِ فَنَبَذْتُهَا وَكَذَٰلِكَ سَوَّلَتْ لِى نَفْسِى ﴿٩٦﴾﴾ طه: ٩٥ - ٩٦

"(መሳ) «ሳምሪዊው ሆይ! ነገርህም ምንድን ነው» አለ፡፡ ያላዩትን ነገር አየሁ፡፡ ከመልክተኛው (ከፈረሱ ኮቴ) ዱካም ጭበጥ አፈርን ዘገንኩ፡፡ (በቅርጹ ላይ) ጣልኳትም፡፡ እንደዚህም ነፍሴ ሸለመችልኝ» አለ፡፡" (ጣሃ፡ 95-96)

- ኢማም አል-ቁርጡቢይ እንደሚሉት (ነገርህ፤ ጉዳይህ ምንድን ነው? የሠራኸውን ነገር እንዲትሠራ ምን ገፋፋህ? እርሱም አለ፡- ያላዩትን አየሁ፤ ጅብሪል በፈረስ ላይ ሆኖ አየሁት፤ ነፍሴም ከኮቴው አፈርን እንድዘግን ገፋፋችኝ፣ ጭብጥ ዘገንኩኝ፤ የሆነ ነገር ላይ ስጥለው ሩሕ፣ስጋና ደም ያለው ሆነ፤ አንተን አምላክ አድርግልን ብለው ሲጠይቁህ ይህን ማድረግን ነፍሴ ሸለመችልኝ)[17]

- መሸለም የሚለው ቃል በዩሱፍ (ዐ.ሰ) ምዕራፍም ተጠቅሷል፤ በየዕቁብ (ዐ.ሰ) ንግግር

﴿بَلْ سَوَّلَتْ لَكُمْ أَنفُسُكُمْ أَمْرًا ۖ فَصَبْرٌ جَمِيلٌ ﴿١٨﴾﴾ يوسف: ١٨

"አይደለም፤ ነፍሶቻችሁ (ወሸት) ነገርን ለእናንተ ሸለመችሁ፡፡" (ዩሱፍ፡ 18)

አንደዚሁም ያችን መሰል ንግግር ዩሱፍ ታናሽ ወንድሙን እርሱ ጋር ባስቀረ ጊዜ ተናግሯቸዋል፡፡

አምስተኛ፡ -ጉትጎታ

- ጉትጎታ ሌሎች የማይሰሙት ድብቅ ድምፅ ነው፡፡ ስለሆነም ይህ ባህሪ ከነፍስ ባህሪ አንዱ ሆኗል፡፡ ይህም ለባለቤቷ በውስጥ የምታናግረው ነው፡፡ ይህ የውስጥ ወሬዋ ጥሩ ወይም መጥፎ ሊሆን ይችላል፡፡ ባለቤቷ እርሷን በመኮትኮት ላይ የሚደክም ከሆነ እርሷ በጥሩ ነገር ታዘዋለች፤ ካልሆነ ግን እርሷ ወደ መጥፎ ትጎተጉተዋለች፣ ታታልለዋለች፡፡

[17](ተፍሲር አል-ቁርጡቢይ ፲፩/239)

የመጠየቂያ ጥያቄዎች

1. የተከበረው ቁርአን የጠቀሳቸውን ዋና ዋና የነፍስ አይነቶች አብራራ።
2. ከየትኛው የነፍስ አይነት ነፍስህ እንደምትመደብ አስቀምጥ.. ከዚያም ምን መሥራት እንዳሰብክ አብራራ።
3. ከሰው ልጅ የነፍስ ባህሪያት ከፊሎቹን ዘርዝር።

ስድተኛው ዓላማ

ነፍስን የማጎልበቻ ዘዴዎችን እንዲያብራ ማስቻል

ነፍስን የማፅዳት፣ የማጎልበት፣ የማሳደግና የማስተካከል ተግባር የበጎ ነገሮች ሁሉ መግቢያ ነው። የስኬታማነት ሁሉ መንገድ ነው። እንዲሁም ይህ በራሱ ትልቅ አላማና ሊደረስበት የሚችል ነገር ነው። ዋጋው ውድ ነው። ቁርጠኛ የሆነ ውሳኔን፣ ብርቱ ትጥቅንና ከፍተኛ ትግልን ይጠይቃል። በተጨማሪም የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀምንና ረጅም ልፋትን ይፈልጋል። ትግሉ የአላህን ውደታ ለማግኘትና ወደ ተረጋጋች ነፍስ ደረጃ ለመድረስ በመመኘት ብቻ አይቋጭም። ከዚህ ቀጥሎ ከፊል ወሳኝ የነፍስ ማጎልበቻ ዘዴዎችን በዝርዝር እናያለን።

1- ስላህን መፍራትና ነፍስን ከስሜቷ መከልከል

የትምህርቱ ዓላማ

1. አላህን መፍራት ሲባል ምን ለማለት እንደተፈለገ እንዲያብራራ ማስቻል።
2. አላህን መፍራት ወሳኝነቱን እንዲያብራራ መስቻል።
3. ነፍሳቸውን እንደት ይቆጣጠሩ አንደነበር ከሰሃቦችና ከደጋግ ባሮች ምሳሌ እንዲጠቅስ ማስቻል።
4. አላህን ከመፍራትና ነፍሱን ከመቆጣጠር አኳያ እራሱን እንዲገመግም ማስቻል።

1. ስላህን መፍራት

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَأَمَّا مَنْ خَافَ مَقَامَ رَبِّهِۦ وَنَهَى ٱلنَّفْسَ عَنِ ٱلْهَوَىٰ ﴿٤٠﴾ فَإِنَّ ٱلْجَنَّةَ هِىَ ٱلْمَأْوَىٰ ﴿٤١﴾ ﴾

"በጌታው ፊት መቆምን የፈራ ሰውማ ነፍሱንም ከዝንባሌዋ የከለከለ፥ ገነት እርሷ በእርግጥ መኖሪያው ናት፡ ፡ " (አን-ናዚአት: 40-41)

ይህችን አንቀጽ አስመልክቶ የሙጃሂድን አስተያየት ቁርጡቢይ እንዲህ ዘግበውታል፡- "እርሱ በዱንያ ከአላህ (ሱ.ወ) ያለው ፍራቻ ነው፤ ወንጀል ላይ ከወደቀም ወዲያውኑ ይታቀባል፡፡ ነፍሱን ከዝንባሌዋ ይከለክላል ማለት ከወንጀልና ክልክል ከሆነው ነገር ይገስፃታል ማለት ነው፡፡"[18]

ኢብን መስዑድ ከርሳቸው በኋላ ለሚመጣው ዘመን አላህ እንዲጠብቃቸው ይለምኑ ነበር፤ ስሜት ሀገርን ከሚቆጣጠርበትና የበላይ ከሚሆንበት ዘመን (እናንተ እውነት ስሜትን በበላይነት የሚመራበት ዘመን ላይ ናችሁ፤ ወደፊት ስሜት እውነትን የሚመራበት ዘመን ይመጣል፣ ከዚያ ዘመን አላህ ይጠብቀን)[19]

ፍራቻ ያላት ነፍስ ባለቤቷን ወደ ወንጀል የምትገፋውን ነፍስ ከዝንባሌዋ ለመከልከል ዋና መሠረት ነው፡፡ የሰው ልጅ ያለ አላህ ፍራቻ ነፍሱን ከስሜት የሚገስጽበት አቅም ሊኖረው አይችልም፡፡

2. አላህን መፍራት ጠላኝ መሆኑ

﴿ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يَخْفَىٰ عَلَيْهِ شَىْءٌ فِى ٱلْأَرْضِ وَلَا فِى ٱلسَّمَآءِ ﴾ آل عمران: ٥

"አላህ በምድርም በሰማይም ምንም ነገር በርሱ ላይ አይሰወርም፡ ፡ "

(አል-ዒምራን: 5)

እንዲሁም አላህ (ሱ.ወ) ምንም አይነት ተግባር ይሁን ንግግር፣ በሌሊትም ይሁን በቀን ከርሱ አይደበቅም፤ አላህ እንዲህ ይላል፡-

[18](ቁርጡቢይ 19/208)
[19](ቁርጡቢይ 19/208)

﴿ سَوَآءٌ مِّنكُم مَّنْ أَسَرَّ ٱلْقَوْلَ وَمَن جَهَرَ بِهِۦ وَمَنْ هُوَ مُسْتَخْفٍۭ بِٱلَّيْلِ وَسَارِبٌۢ بِٱلنَّهَارِ ﴿١٠﴾ ﴾ الرعد: ١٠

"ከናንተ ወስጥ ድምጹን ዝቅ ያደረገ ሰው፣ በርሱ የጮኸም ሰው፣ እርሱ በሌሊት ተደባቂም፣ በቀን (ተገልጾ) ሂያጅም የሆነ ሰው እርሱ ዘንድ እኩል ነው" (አር-ረዕድ፡ 10)

ይህ ሁሉ ለኛ ወይም በኛ ላይ ሂሳብ ይደረጋል፤ አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ لِّلَّهِ مَا فِى ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِى ٱلْأَرْضِ ۗ وَإِن تُبْدُوا۟ مَا فِىٓ أَنفُسِكُمْ أَوْ تُخْفُوهُ يُحَاسِبْكُم بِهِ ٱللَّهُ ۖ فَيَغْفِرُ لِمَن يَشَآءُ وَيُعَذِّبُ مَن يَشَآءُ ۗ وَٱللَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَىْءٍ قَدِيرٌ ﴾ البقرة: ٢٨٤

"በሰማያት ወስጥና በምድርም ወስጥ ያለው ሁሉ የአላህ ነው፡ በነፍሶቻችሁ ወስጥ ያለውን ብትገልጹ ወይም ብትደብቁት አላህ በርሱ ይቆጣጠራችኋል፤ ለሚሸውም ሰው ይምራል የሚሸውንም ሰው ይቀጣል፤ አላህም በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው፡፡" (አል-በቀራህ: 284)

አንድ ሙስሊም በማንኛውም ተግባሩም ይሁን እንቅስቃሴው፣ ሥነ-ምግባሩም ይሁን እሳቤው ዘወትር አላህን ይፈራል፡፡ አላህ ድብቁንም ይሁን ግልጹን ሁሉ ተመልካች ለመሆኑ ጥልቅ እምነት አለው፡፡ ስለዚህም ማንኛውንም ሊተገብረው ያሰበውን ነገር አላህ ካዘዘውና ከከለከለው ነገር ጋር መጣጣሙን ያነፃፅራል፡፡ ሥራው ትክክለኛ ከሆነና የአላህን ፊት በኢኽላስ (ግባዊ ቅንነት) ተፈልጎበት ከሆነ ይተገብረዋል፡፡ በተቃራኒው በውስጡ ወንጀል ወይም የነፍስ ዝንባሌ ካለበት ደግሞ ይርቀዋል፡፡ ቁርአን ይህን አይነቱን ግንዛቤ በሚያንጸባርቁ አናቅፅ የተሞላ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿ يَعْلَمُ خَآئِنَةَ ٱلْأَعْيُنِ وَمَا تُخْفِى ٱلصُّدُورُ ﴾ غافر: ١٩

"አላህ የአይኖቸን ክዳት ልቦችም የሚደብቁትን ሁሉ ያውቃል፡፡" (ጋፊር፡ 19)

አላህ በሌላ የቁርአን አንቀጽ እንዲህ ይላል፡-

﴿ أَلَمْ يَعْلَم بِأَنَّ ٱللَّهَ يَرَىٰ ﴾ العلق: ١٤

"አላህ የሚያይ መሆኑን አያውቅምን?" (አል-ዐለቅ: 14)

በሱረቱል ሐዲድ ቁጥር 4 ላይ ደግሞ፡-

﴿ وَهُوَ مَعَكُمۡ أَيۡنَ مَا كُنتُمۡۚ وَٱللَّهُ بِمَا تَعۡمَلُونَ بَصِيرٞ ﴾ الحديد: ٤

"የትም ብትሆኑ ከእናንተ ጋር ነው፣ አላህም የምትሠሩትን ሁሉ ተመልካች ነው" (አል-ሐዲድ፡ 4) ይላል።

በአል-ቂያማህ ምዕራፍ ከአንቀጽ 14 እስከ 15 እንዲህ ይላል፡-

﴿ بَلِ ٱلۡإِنسَٰنُ عَلَىٰ نَفۡسِهِۦ بَصِيرَةٞ ١٤ ﴾ القيامة: ١٤ - ١٥

"በእርግጥም ሰው በነፍሱ ላይ አስረጅ ነው፡" (አል-ቂያማህ፡ 14)

(አካሎቹ ሁሉ ይመሰክሩበታል) ምክንያቶቹን ሁሉ ቢያመጣ እንኳ፤ (አይሰማም)። በሱረቱል በቀራህ አንቀጽ 235 ላይ፡-

﴿ وَٱعۡلَمُوٓاْ أَنَّ ٱللَّهَ يَعۡلَمُ مَا فِيٓ أَنفُسِكُمۡ فَٱحۡذَرُوهُۚ ﴾ البقرة: ٢٣٥

"አላህም በነፍሶቻችሁ ውስጥ ያለውን ነገር የሚያውቅ መሆኑን ዕወቁ፤ ተጠንቀቁትም፡" (አል-በቀራህ፡ 235)

በአር-ረዕድ ምዕራፍ አንቀጽ 33 ደግሞ እንዲህ ይላል፡-

﴿ أَفَمَنۡ هُوَ قَآئِمٌ عَلَىٰ كُلِّ نَفۡسِۭ بِمَا كَسَبَتۡ ﴾ الرعد: ٣٣

"እርሱ በነፍስ ሁሉ ላይ በሠራችው ሥራ ተጠባቂ የሆነው..." (አር-ረዕድ፡ 33)

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት አናቅጽ እንደሚያመላክቱት የአላህን ጌትነት የሚያምን ሰው ነፍስ አላህ (ሱ.ወ) በእርሷ ላይ ተቆጣጣሪ፣ ምስጢሯን አዋቂና ሥራዋን የሚከታተል መሆኑን አጥብቃ እውነት ትላለች። ስለሆነም የዚህች ነፍስ ባለቤት ነፍሱን እራስ በራሱ በንቁ ህሊናው ይቆጣጠራታል። ለመተግበር ያሰበችውን ንግግርም ይሁን ሥራ ሸሪዓው በቀጥታ አዞታል? ወይንስ ከቁርአንና ከሐዲስ የመነጨ ማስረጃ አለው? በማለት ንፅፅር ያደርጋል። ይህም ንፅፅር በሚባዳ ተግባራት ላይም ሆነ በሌላ የማህበራዊ ዘርፍ ድርጊት ላይ ሊሆን ይችላል። ተግባሩ ሸሪዓው የሚደግፈው መሆኑን ሕሊናው ካረጋገጠ በልቦናው የአላህን

ውዴታ ለማግኘት በማሰብ ለትግበራው ይጣደፋል። በሂደቱም (ስግደቴም፣ እርዴም፣ ሕይወቴም፣ ሞቴም የዓለማት ጌታ ለሆነው ለአላህ ነው) የሚለውን የቁርአን አንቀጽ ያስተነትናል።

ልቡ በአላህ ላይ የተንጠለጠለ፣ አካላቱ አላህን በማስታወስ ላይ የተንበረከከ ሙስሊም ግለሰብ በመጥፎ አዛኝ በሆነችው ነፍሱ ላይ የመፍረድ አቅም አለው። ስሜቱንም የመቆጣጠር ብቃት አለው። ስለሆነም ነፍሱን በራሱ ይቆጣጠራታል። በማንኛውም እንቅስቃሴውና ተግባሩ አላህን ይፈራል። ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ አል-በቀራህ ምዕራፍ ቁጥር 235 ላይ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَٱعۡلَمُوٓاْ أَنَّ ٱللَّهَ يَعۡلَمُ مَا فِيٓ أَنفُسِكُمۡ فَٱحۡذَرُوهُۚ ﴾البقرة: ٢٣٥

"አላህም በነፍሶቻችሁ ውስጥ ያለውን ነገር የሚያውቅ መኾኑን ዕወቁ፤ ተጠንቀቁትም ። " (አል-በቀራህ፡ 235)

እንደዚሁም በሱረቱል ሙልክ ቁጥር 12፡-

﴿ إِنَّ ٱلَّذِينَ يَخۡشَوۡنَ رَبَّهُم بِٱلۡغَيۡبِ لَهُم مَّغۡفِرَةٞ وَأَجۡرٞ كَبِيرٞ ﴾الملك: ١٢

"እነዚያ ጌታቸውን በሩቁ የሚፈሩ ለነርሱ ምሕረትና ታላቅ ምንዳ አላቸው" ይላል። (አል-ሙልክ፡ 12)

ሙስሊም ነገ የቂያማ እለት በአላህ ፊት ቆሞ ምርመራ እንደሚደረግ ያምናል...ስለሆነም ዛሬ ላይ አላህ የከለከለው ነገር ላይ ከመውደቅም ሆነ ከመቅረብ መጠበቅን መርጧል።

ሰይድ ቁጥብ (አላህ ይዘንለትና) እንዲህ ብሏል፡-"በጌታው ፊት መቆምን የሚፈራ ወደ ወንጀል አያመራም፣ በሰዋዊ ድክመቱ ምክንያት ወንጀል ላይ ቢወድቅ አንኳን በአላህ ፊት የመቆም ፍራቻው እንዲጸጸትና ምህረትን ፈጥኖ እንዲጠይቅ እንዲሁም ወደ አላህ እንዲመለስ ይገፋፋዋል። ይህም ዘወትር በተውበት ክልል ውስጥ እንዲኖር ያስችለዋል። ነፍስን ከስሜት የማቀብ ተግባር የአላህን ትእዛዝ ከመጠበቅ ረገድ ወሳኝ ነጥብ ነው። ስሜት ወሰንን ለማለፍ ከባድ ኃይል ነው። ለማንኛውም የድንበር ጥሰት፣ ለማንኛውም የወንጀል ድርጊትና የተንኮል ምንጭ መሠረቱ ስሜት ነው። ለሰው ልጅ በስሜት በኩል ከሚመጣበት ነገር ውጭ

ያለው ሁሉ ቀላል ነው፡፡ አላዋቂነትን ማከም ገር ሲሆን ከዕውቀት በኋላ በስሜት ምክንያት የመጣ ነገር ግን የነፍስ መጥፊያዋ ነው፡፡ ከዚህ ጥፋት ለመዳንም በጣም ከባድ ትግልና ረጅም ጊዜን ይጠይቃል፡፡ አላህን መፍራት ለዚህ አስከፊ ለሆነው የስሜት ግፊት በቂ የሆነ መጋረጃ ነው፡፡ ከአላህ ፍራቻ ውጭ ለስሜት መጋረጃ የሚደረግ መፍትሄ በቀላሉ ተሸናፊ ይሆናል፡፡"[20]

ስሜት አስከፊ ከመሆኑ የተነሳ አእምሮን ይሸፍናል፡፡ እስረኛ ያደርገዋል፡፡ እርሱን ለመጋፈጥ ከፍተኛ የሆነ ኃይል ይፈልጋል፡፡ ይህ ኃይልም በአላህ ፍራቻ ላይ የተረመኮዘ መሆን አለበት፡፡ ይህም የቂያማ እለት የሚደርስበትን ውርደት በመፍራትና በዱንያውም ሆነ በአኼራው እድለ-ቢስ ከመሆን በመስጋት ነው፡፡ እንደዚህ ነበር የአላህ መልካም ባሮች ራሳቸውንም ሆነ ተከታዮቻቸውን የአላህን ምህረቱንና እዝነቱን ከመከጀል ጎን ለጎን እርሱን በመፍራት ላይ ተርቢያ የሚያደርጉት!

ነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ) የአላህ መልእክተኛና በራእይ የታገዙ ሆነው ሳለ እንዲህ ይሉ ነበር፡- "እኔ ከማንኛችሁም በላይ አላህን ፈሪያችሁ ነኝ!" (ቡኻሪ ዘግበውታል)

- አላህን የሚፈራ ሰው ቁጣውን ይጠነቀቃል፣ ቅጣቱን ይፈራል፣ ከከለከለው ነገር ላይ ከመውደቅ ይቆጠባል፡፡

- አላህን የሚፈራ ከሰዎች ሁሉ ልቡ ንፁህ፣ ነፍሱ የጠራ፣ አይኑ የሚያነባና እጁ ለጋስ ይሆናል፡፡ መልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ በማለት ዱዓ ያደርጉ ነበር "አላህ ሆይ! እንባ ደም ከመሆኗ በፊት በፍራቻህ እንባን በማዝነብ ልብን የሚያከሙ የሆኑ አልቃሻ አይኖችን ስጠኝ »(ጠበራኒ ዘግበውታል)

3. ከነቢዩ ባልደረቦችና ከደጋግ የአላህ ባሮች ነፍስን የመቆጣጠር ምሳሌ

- **ፍዮል ጠባቂውና ዑመር ኢብኑል ኸጣብ**

አብዱላህ ኢብኑ ዲናር (ረ.ዐ) እንዲህ ብሏል፡-"ከዑመር ኢብኑል ኸጣብ ጋር ወደ መካ ወጣንና የሆነ መንገድ ላይ አረፍን፡፡ ከተራራ ላይ አንድ ፍየል ጠባቂ

[20](ፊዚላል)

ተንደርድሮ መጣ። ዑመርም አንተ እረኛ ሆይ! ከነኝህ ፍየሎች አንዷን ሸጥልኝ አሉት። እኔ አገልጋይ ነኝ አለ። ለአለቃህ ቀበሮ በላት በለው አሉት። እረኛውም ለአላህስ ምን ልለው ነው? አያየኝምን አለ። ዑመር አለቀሱ። ከዚያም ወደአለቃው ዘንድ ገሰገሱና እረኛውን ገዝተው ከባርነት ነፃ አደረጉት። ከዚያም በዚህች ንግግርህ በዱንያ ነፃ አውጥቸሃለሁ፣ በአኼራ ደግሞ ነፃ እንድታወጣህ እመኝልሃለሁ አሉት።

(ይህች ታሪክ ብዙ ቁምነገር አዝላለች። ከዚህም መካከል በአላህ መንገድ ላይ የታነፁ ሙስሊም ግለሰቦች ከሰዎች ማንንም አይፈሩም፣ ዱንያ አታታልላቸውም፣ ገንዘብ አያታልላቸውም። ለምን? ቢባል አላህ ዘንድ ያለው በላጭና ዘውታሪ በመሆኑ ነው። እነኝህ ሰዎች በእስልምና ትምህርት ቤት ተኮተኩቱ፤ ስለሆነም አላህን ፈሪዎችና ነገስታትን የማይፈሩ ለመሆን በቁ።)

- **ወተት ሻጯና ውሸቱ ኢብኑል ኸጣብ**

አስለም እንዳወሩት ዑመር አንድ ቀን በከተማዋ ያለውን ሁኔታ ለመከታተል በወጡበት አብሬያቸው ነበርኩ። በሌሊቱ ክፍለ ጊዜ ወደ አንድ ግድግዳ ተጠጉ...በዚህም ወቅት አንዲት ሴት ለልጇ “ተነሽና እዚያ ወተት ላይ ውሃ ቀላቅይበት!” ስትል ሰሙ ልጅቷም ለእናቷ “የሙእሚኖች መሪ ምን አዋጅ እንዳስተላለፉ አላወቅሽምን?” አለቻት። እናቷም “ምን ነበር ያወጀው ልጄ?” አለቻት። ወጣቷም አዋጅ ባዩን ወተት በውሃ እንዳይቀላቀል ብሎ እንዲያውጅ ነው ያስደረገው አለቻት። እናትም እያቄለች ልጄ ሆይ! ይልቁንስ ተነሽና ውሃ ቀላቅይበት፤ አሁን ያለሽው ዑመርም ሆነ ተጣሪው ከማያዩበት ነው አለቻት። ልጅቷም ተቆጥታ ለእናቷ አይሆንም እናቴ ! ውሃ ለመቀላቀል አልታዘዝሽም። ዑመር ሩቅ ሆኖ ባያየን የዑመር ጌታ ከእኛ ይርቃልን? አለቻት። ዑመር ሁሉንም ንግግር ሰሙ። ለአስለምም በሩን ምልከት አድርግበት፣ ቦታውንም በትክክል እወቅ አሉት።ከዚያም ሄዱና ሲነጋ አስለምን ሂድና ቦታውን ተመልከት አሉት። ተናጋሪዋ ማን እንደሆነችና የምትመልስላትስ ማን እንደነበረች፣ ባልስ አላት ወይ? የሚለውን አጣርተህ ተመለስ አሉት። እኔም ከቦታው መጣሁና ልጅቷም ሆነ እናቷ ባል እንደሌላቸው ነገርኳቸው። ዑመር ልጆቻቸውን ሰበሰቡና ከመካከላችሁ ሚስት የምድረው ማን አለ? አባታችሁ ሴት የሚፈልግ ቢሆን ኖሮ ይህችን ልጃገረድ

ማንም አይቀድመውም ነበር በማለት ጠየቁ፡፡ ከዓሲም ኢብኑ ዑመር በስተቀር ሁሉም ሚስት ስለነበራቸው ዓሲም አገቧት፡፡ እርሷም ዑመር ኢብኑ ዐብዱል ዐዚዝን (አላህ ሥራውን ይውደድለትና) ወለደች፡፡

- **የሸጁኹ፣ የልጁና የመጪቹ ታሪክ**

ወጣት ደረሳ የነበረው አንድ ሸይኽ ነበር ይባላል፡፡ ይህ ሰው ወጣቱን ደረሳ በደንብ ይንከባከበዋል፡፡ የሸይኹ ባልደረቦች የኾኑ ትልልቅ ሸማግሌዎች እኛ እያለን እንዴት ይህን ወጣት ልጅ ትንከባከባለህ? በማለት ይጠይቁታል፡፡ እርሱም ብዙ እርግቦች ተይዘው እንዲመጡለት አዘዘ፡፡ ከዚያም ለእያንዳንዳቸው አንድ አንድ እርግብና አንድ አንድ ቢላዋ ሰጣቸውና ማንም ከማያያቸሁ ቦታ ሄዳችሁ እርግባችሁን እረዱ አላቸው፡፡ ለወጣቱም እንደዚሁ ቀድሞ ሰጠውና ለነርሱ ያላቸውን ለርሱም አለው፡፡ ሁሉም የታረደ እርግባቸውን ይዘው ተመለሱ፡፡ ወጣቱ ግን ሳያርድ ተመለሰ፡፡ ሸይኹም ሌሎቹ እንዳረዱት አንተስ ለምን አላረድከውም አለው፡፡ ማንም የማያየኝ ቦታ አላገኘሁም፣ አላህ ሁሉም ቦታ ላይ እየተከታተለኝ አገኘሁት በማለት መለሰ፡፡ ሌሎቹም ይህችን ሙራቀባህ (የአላህ ክትትል) ከርሱ ተማሩ፤ እርሱንም በርግጥ ልትከበር ይገባሃል በማለት አሞገሱት፡፡

4. ነፍሱ ለአላህ ያላትን ፍሬቻና ለርሱ ያላትን ክትትል ሊመዝን

ወንድሜ ሆይ! አላህን በመፍራት ረገድ ምን ያህል ነህ? ማንኛውንም ሥራ ከመጀመርህ በፊት አንተ ክትትል ውስጥ መሆንህንና በሁሉም ነገር ምርመራ እንደምትደረግ አስታውስ! ቀጥሎ ካለው ሰንጠረዥ ካንተ ደረጃ ጋር የሚስማማውን ምረጥ፡-

ተ.ቁ	ተግባር	በጭራሽ (0)	አንዳንድ ጊዜ (1)	አልፎ አልፎ(2)	በአብዛኛው (3)	ሁልጊዜ (4)
1	ከነፍሴ ጋር ለብቻ በምሆንበት ሰዓት አላህ ያየኛል የሚለው ስሜት ያድርብኛል					
2	ከሥራዬ የትኛው ለአላህ መሆን እንደሚገባውና					

	የትኛው ለራሴ መሆን እንዳለበት አውቃለሁ					
3	በሥራዬ ከትትል እንደምደረግ አውቃለሁ፣ እንዲሁም ከመላእክት የሚከታተሉኝን አፍራለሁ					
4	አላህ እንደሚከታተለኝ ሳስብ ስራዬን አሳምራለሁ					
5	ለሌሎች ሰዎች ስለ-ሙራቀባና አላህን ስለመፍራት ትርጉም ግልፅ አደርጋለሁ					

ደረጃህ ጥሩ ሆኖ ካገኘኸው አላህን አመስግን፣ ከዚያ የተለየ ከሆነ ደግሞ ነፍስህ ለአላህ ካላት ፍራቻ አንፃር ገምግማት።

የመጠቀሻ ጥያቄዎች

1. ነፍስን የማስተካከያ መንገዶች ዘርዝር።
2. ነፍስን የማስተካከያ መንገዶች አብራራ።
3. አላህን መፍራት ሲባል ምን ማለት እንደሆነ ግለፅ።
4. አላህን መፍራት አስፈላጊ መሆኑን አብራራ።
5. ከሰሃቦችና ከመልካም ባሮች ስብዕና ነፍስን በመኮትኮት ዙሪያ ምሳሌዎችን ጥቀስ።
6. አላህን በመፍራትና ትእዛዙን በመጠባበቅ ዙሪያ ራስህን መዝን።
7. የአላህን ፍራቻ የሚገልፅ የሕይወት ተሞክሮህን ጥቀስ-ይህ ተሞክሮ ባንተ ላይ ምን ተፅእኖ እንዳሳደረብህ አብራራ።
8. አላህን በመፍራት ላይ የተመሰረተና ስነምግባርህን ለማስተካከል፣ ወይም ስህተትህን ለማረም ያስቻለህን በሕይወትህ የፈጸምከውን ተግባር ጥቀስ።

2- ነፍስን መመርመር

የትምህርቱ ዓላማ

1. ነፍስን ምርመራ ማድረግ ሲባል ምን እንደተፈለገ እንዲያብራራ ማስቻል
2. ነፍስን ምርመራ ማድረግ ወሳኝ መሆኑን እንዲያብራራ ማስቻል
3. ሰሃቦችና ደጋግ ባሮች ነፍሳቸውን እንደት ይመረምሩ አንደነበር ምሳሌ እንዲጠቅስ ማስቻል
4. ነፍሱን በመርመር ላይ ልምምድ እንዲያደርግ ማስቻል
5. ነፍሱን ምን ያህል እንደሚመረምራት እንዲገመግም ማስቻል

1. ነፍስን መመርመር ሲባል ምን እንደተፈለገ

ሙሓሰባ...ሂሳብ ወይም ምርመራ ከሚለው የተያዘ ሲሆን ስያሜውም የመጣው ትርፍን ከኪሳራ ለመለየት ነው[21]

ሙሐሰበተ-ነፍስ ሲባል፡- አንድ ግለሰብ ራሱን በራሱ ነፍሱን ምርመራ ማድረግ ማለት ነው፡፡ ይህም ተግባሩን፣ ሁኔታውን፣ ሥነ-ምግባሩንና እንቅስቃሴውን፣ በግልፅ የፈፀመውንም ሆነ በድብቅ የሠራውን አንድ በአንድ መመርመር ሲችል ነው፡፡ ይህ ምርመራው ሸሪዓው ከሚደነግገው አንፃር ተግባሩ ምን ላይ እንዳለ ለማወቅ ያስችለዋል፡፡ ለዚህም ራሱን በራሱ ይገመግማል፡፡ ተግባሩ ከሸሪአው አፈንግጦ ቢሆን እንኳን የማስተካከያ ጊዜው ሳያልፍበት፣ እድሜው ሳይቋጭ፣ አላህ (ሱ.ወ) ፊት ሳይቆም ለማስተካከል እድል አለው፡፡

ነፍሰን መመርመር የጥንቁቆች መንገድ ነው፣ የሙእሚኖችና የደጋግ ባሮች ሰንቅ ነው፣ አላህን የመፍራት ዋነኛው አሰኳል ነው፣ ሌሎችንም ወደ ዓለማት ጌታ አመላካች ነው[22]

---

[21](መሸሩዕ በርናሚጅ አል-ተርበዊይ ሊኢስላሒ ነፍስ -ዶ/ር አብዱል ሐይ አል-ገርማዊይ)።
[22](ሙሓሰበተ-ነፍስ በ ዶ/ር ሁሰይን ሸሃታ)

2. ነፍስን ምርጠው የማድረግ ጠቀሜነት

አላህ (ሱ.ወ) በተከበረው ቁርአኑ እንዲህ ይላል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱتَّقُواْ ٱللَّهَ وَلۡتَنظُرۡ نَفۡسٞ مَّا قَدَّمَتۡ لِغَدٖۖ ﴾الحشر: ١٨

"እናንተ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ አላህን ፍሩት፣ ነፍስም ለነገ ያስቀደመችውን ነገር ትመልከት፡ ፡ " (አል-ሐሽር: 18)

ይህ አንቀጽ ነፍስን መመርመር አስፈላጊ መሆኑን ያመላክታል፡፡ መልክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ቀደምት ሙስሊሞችን ራሳቸውን ምርመራ እንዲያደርጉ ሲያንጿቸው ነበር፡፡ የአኼራን የምርመራ ክፋት በሚገባ አስጠነቅቀዋቸዋል፡፡ እነኝህ ሰዎች አላህ በጥብቅ እንደሚከታተላቸው ተገንዝበዋል፡፡ በእለተ ቂያማ በሁሉም ነገር ላይ ምርመራ እንደሚደረግባቸው አውቀዋል፡፡ ከዚህ ከባድ ምርመራ ቀድመው በራሳቸው ላይ ያደረጉት ሂሳብና እውነተኛ ክትትል ካልሆነ በስተቀር ሊያድናቸው የሚችል ነገር እንደሌለ ተረድተዋል፡፡ ሂሳብ ከመደረጉ በፊት ራሱን ሂሳብ ያደረገ ሰው የቂያማ ዕለት ይቀልለታል፡፡ ሲጠየቅ መልሱ ይገለፅለታል፡፡ መመለሻውና መዘውተሪያው ያማረ ይሆናል፡፡ ራሱን ሂሳብ ያላደረገ ክስረቱ ይፀናል፡፡ የቂያማ ዕለት ለጥያቄ የሚቆምበት ይረዝማል፡፡ ዑባደት ኢብኑ ሳሚት(ረ.ዐ) እንደዘገቡት ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲመክሩት የመጣውን ሰው እንዲህ ሉሉት፡- *"አንድ ነገር ለማድረግ ስትፈልግ መጨረሻውን አስተንትን፣ ትክክለኛ ከሆነ ቀጥልበት፣ መጥፎ ከሆነ ደግም ከእርሱ ተከልከል፡፡"* ሸዳድ ኢብኑ አውስ (ረ.ዐ) እንዳወሩት ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ በማለት ተናገሩ፡- "ብልጥ ማለት ነፍሱን ያሸነፈና ከሞት በኋላ ላለው ሕይወቱ የሚሠራ ነው፣ ደካማ ማለት ደግሞ ነፍሱን ስሜቷን እንዲትከተል ካደረጋት በኋላ ከአላህ ዘንድ ምህረትን የሚመኝ ነው" (አህመድና ቲርሚዚይ ዘግበውታል)

(አዋቂ ማለት ሂሳብ ከመደረጉ በፊት አሁን ራሱን ምርመራ ያደረገ ነው፡፡ አሁን ላይ ነፍሱን ለረጅም ጊዜ ሂሳብ ያደረገ ከቂያማ ዕለት ሂሳብ ነፃ ይወጣል...፡፡ የሰው ልጅ እራሱን መመርመሩን ባበዛ ቁጥር ወንጀሉ ይቀልለታል፣ ጥሩ ሥራው ይበዛለታል፣ ራሱን ለማስተካከል የሚያደርገው እርምጃ ስኬታማ ይሆናል፡፡ ዑመር አላህ ሥራውን ይውደድለትና እንዲህ ይል ነበር፡- (ምርመራ ከመደረጋችሁ በፊት

እራሳችሁን መርምሩ፣ በሥራችሁ ከመመዘናችሁ በፊት ሥራችሁን መዝኑ፤ ለታላቁ ቀን እራሳችሁን አዘጋጁ፡- “በዚያን ቀን ከናንተ ተደባቂ (ነገሮች) የማይደበቁ ሲኾኑ ትቀርባላችሁ (አል-ሀቃህ: 18)”[23]

ሐሰን (አላህ ሥራቸውን ይውደድላቸውና) “ሙእሚን በነፍሱ ላይ ጠንካራ ነው፣ ነፍሱን ይመረምራል” ይሉ ነበር። መይሙን ኢብኑ መህራን እንደሚሉት “አንድ ባሪያ ከንግድ አጋሩ ጋር ከሚያደርገው መተሳሰብ የበረታ ነፍሱን እስካልተሳሰባት ድረስ ተቂይ(አላህን ፈሪ) ሊሆን አይችልም። ሁለት የንግድ ጓደኛሞች ከሥራ በኋላ ይተሳሰባሉ”

አላህን የምትፈራ ጥንቁቅና እርብትብት የሆነች ነፍስ ዋነኛ መለያዋ የእለት ተእለት ድብቁንም ይሁን ይፋ የሆነውን እንቅስቃሴዋንና ተግባሯን ምርመራ ማድረጓ ነው። ይህ ደግሞ ይህች ነፍስ ቁርአን ባሰመረው፣ መልክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ግልፅ ባደረጉትና ደጋግ ተከታዮችና ወዳጆቻቸው ባለፉበት ቀጥተኛ መንገድ ላይ በፅናት እየተጓዘች መሆኑን ለማረጋገጥ ይረዳል። ይህ ሲሆን ስህተት ላይ ብትወድቅና ከመንገዱ ብታፈነግጥ እንኳን በቀላሉ ምክንያቱን አውቃ በፍጥነት ወደ እውነታው ትመለሳለች። በዚህም እንዳትጠምና እድለቢስ እንዳትሆን ይጠብቃታል። አንድ ሙስሊም እስልምናው የተስተካከለ ነው ሊባል የሚችለው ነፍሱን ለመመርመር አቅም ሲኖረውና እንቅስቃሴውንም ሆነ ተግባሩን መቆጣጠር ሲችል ነው። ዐዋቂና ብልህ ማለት ነፍሱን የሚኮንንና ባጠፋች ጊዜ የሚወቅሳት ነው። ምክንያቱም በዚያ ምርመራው በከፋው ቀን ከአላህ (ሱ.ወ) ፊት ቀርቦ መጠየቅን ስለሚፈራ ነው።

አንድ ሙእሚን ነፍሱን ከመመርመርና በሰላሟም ይሁን በአደጋዋ ወቅት እርሷ ላይ ጫና ከመፍጠር ሊዘናጋ አይገባም። በእድሜው ውስጥ ያለችን እያንዳንዷን እስትንፋስ እንደ ዕንቁ ሊቆጥራት ይገባል። ምክንያቱም በዚህች እስትንፋስ ምናልባትም ፀጋው ለዘላለሙ የማያልቅ የሆነን ድልብ ሊገዛባት ይችላልና። ይህችን የሕይወት እስትንፋሱን ችላ ማለት ወይም ደግሞ ለጥፋት የሚዳርገውን መጥፎ ድርጊት መሸመት ትልቅ ኪሳራ ሲሆን የዚህ ስው ምድቡም

[23] (መሸሩዕ በርናሚጅ አል-ተርበዊይ ሊኢስላሒ ነፍሰ-ዶ/ር አብዱል ሐይ አል-ገርማዊይ)።

በጣም ቂላቂልና አእምሯቸው ደካማ የሆኑ የከፉ እድለቢሶች ጋር ይሆናል። ይህ ሰው መክሰሩን የሚያረጋግጠው ያኔ ገንዘብም ሆነ ልጅ በማይጠቅምበትና ታዛዥ የሆነች ቀልብ ብቻ አዋጭ በሆነችበት በከባዱ የጭንቅ እለት ነው።

(ሙስሊም በዱንያ ሳለ ለአኼራው የሚበጀውን ነገር ለመተግበር በሌሊትም ሆነ በቀን የሚለፋው እንዳለ ሆኖ በቅድሚያ ትልቅ ትኩረት የሚሰጠው አላህ ግደታ ባደረገበት ነገር ላይ ነው። ልክ አንድ ነጋዴ ለዋና ካፒታሉ ትልቅ ትኩረት እንደሚሰጠው ሁሉ። ወንጀሉንና ስህተቱን በንግዱ ላይ እንደሚገጥመው ኪሳራ ሊመለከት ይገባል። ለዚህም በመጨረሻው የቀኑ ክፍለ ጊዜው ራሱን ገለል አድርጎ በየቀኑ ነፍሱ ባደረገችው የቀን ተግባሯ ላይ ሂሳብ ማድረግ አለበት። በዚህ ምርመራው ግዴታ በሆኑት ተግባራት ላይ ጉድለት ካገኘባት ነፍሱን ይወቅሳታል፣ አጥብቆ ይኮንናታል፣ ከዚያም ወዲያውኑ እንድትስተካከል ያደርጋታል። ጉድለቱ በማካካሻ (ቀዷ) የሚከፈል ከሆነ ወዲያውኑ ቀዷ ይከፍላል፤ ካልሆነ ደግሞ ለዚያ ማካካሻ እንዲሆን ትርፍ ተግባራትን (ነዋፊል) በብዛት ይተገብራል። በነዋፊል ተግባሩ ላይ ክፍተት ካስተዋለ ጉድለቱን ይሞላና ለቀጣዩ በቁርጠኝነት ይሠራል። ክልክል የሆነውን ነገር በመፈፀም ኪሳራ ውስጥ መሆኑን ከተረዳ አላህን ምህረት ይጠይቃል፣ ይፀፀታል፣ ይመለሳል፣ ላጠፋው ጥፋት ምላሽ የሚሆን መልካም ተግባር ይሠራል።)[24]

እንግዲህ ነፍስን ሙሓሰባ ማድረግ የተፈለገው ለዚህ ነው።እርሷን ለማስተካከል፣ ሥርዓት ለማስያዝና ለማፅዳት አንዱ መንገድ ነውና!

3. ነፍስን ሙሓሰባ በማድረግ ፈገድ ከሰሐቦችና ከደጋግ ባሮች ምሳሌ

- ዑመር ሌሊቱ በጨለመ ጊዜ እግራቸውን በአለንጋ ይገርፉ ነበር፤ ነፍሳቸውንም ዛሬ ምን ስትሠሪ ዋልሽ? ይሏት ነበር፡-
- አነስ ኢብኑ ማሊክ (አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና) እንዲህ አሉ፡- ዑመር ኢብኑል ኸጧብን-አላህ ሥራውን ይውደድለትና-ሰምቸዋለሁ። አንድ ቀን ራቅ ወዳለ ቦታ በወጣበት ወቀት እኔም ተከትልኩት፤ ከዚያም የሆነ

[24](መንሀጀል ሙስሊም)

አጥር ውስጥ ገባ፤ በመካከላችን ግድግዳ ይከልለን ነበር፡፡ እንዲህ ሲል ሰማሁት፡- *“የሙእሚኖች መሪ የዑመር ኢብኑል ኸጧብ ነፍስ ሆይ! ጥፋትሽ ጥፋትሽ! በአላህ ይሁንብኝ ወይ አላህን ትፈሪያለሽ ካልሆነ ደግሞ ይቀጣሻል፡፡”*

- ቡህተሪ ኢብኑ ሐሪሣ እንዲህ አሉ፡- *ኣንድ* ቀን አንድ የአላህ ባሪያ ዘንድ ገባሁኝ፤ በወቅቱ ነፍሱን ሂሳብ ለማድረግ ሲል እጁን እሳት ውስጥ አስገብቷት አየሁኝ፤ ነፍሱን እየወቀሳትም በዚያው ሞተ”

- ኢብኑ ሶሚ ነፍሳቸውን በየቀኑ ሂሳብ ከሚያደርጉ ደጋግ ሰዎች አንዱ ነበሩ፡፡ አንድ ቀን እድሜያቸው 60 ዓመት እያለ ነፍሳቸውን ሂሳብ አደረጓት፡፡ እድሚያቸው ስንት ቀን እንደሆነ ሂሳብ አድርገው ሃያ አንድ ሺህ አምስት መቶ ቀናት መሆኑን ደረሱበት፡፡ ከዚያም እንዲህ በማለት ጮኹ፡- “ወይ ጥፋቴ! አምላኬን ሃያ አንድ ሺህ አምስት መቶ ወንጀል ይዤ ልገናኘው ነው? በእያንዳንዱ ቀን ደግሞስ አስር ሺህ ወንጀል ቢኖርብኝስ!! ከዚያም ራሳቸውን ስተው ወደቁና በዚያው ሞቱ፡፡

- ከታቢዒዮች አንዱ በሚባዳውና ወደ አላህ በመቃረብ ረገድ በየቀኑ ይጨምር ነበር፡፡ (ይህ ሰው ሱጁድ ላይ ባለበት ሰዓት ልክ የአጥር እንጨት ይመስላቸውና ወፎች በጀርባው ላይ አርፈው ሲተክትኩት ምንም አይንቀሳቀስም ነበር፡፡)[25] ይህ ባሪያ ከዚህ *ሥራውም ጋር* ዘወትር በፍራቻ ይዋጣል፡፡ በየእለቱ ነፍሱን ሂሳብ ያደርጋታል፡፡ (*የምናገረው ከምሠራው ጋር ላይገጥም ይችላልና እየዋሸሁ ነው ብየ እፈራለሁ* ይል ነበር፡፡)[26] በዚህ መልኩ ነፍሱን ሁል ጊዜ ሂሳብ በማድረግ ሚባዳውን ይጨምር ነበር፡፡ በዚህም ነፍሱ ከማፈንገጥና ከመገልበጥ እንድትጠበቅ አድርጓታል፡፡

እንግዲህ ሶሐባዎችና ደጋግ የአላህ ባሮች ነፍሳቸውን እንደዚህ ይመረምሯት ነበር፡፡ በዚያ በምርመራ ቀን ነጻ ለመውጣት በሉ እኛም የነርሱን ፈለግ እንከተል! ያ በዚያ *“መዝገብህን አንብብ! ዛሬ ባንተ ላይ ተቆጣጣሪነት በነፍስህ በቃ! “*(አል-ኢስራእ፡ 14) በሚባልበት ቀን

[25][ዙህዱል አህመድ 363]
[26][ሲይሩ አዕላሙ ኑብላእ 5/61]

4. ነፍሱን በመርመር ላይ ልምምድ እንዲያደርግ ማስቻል

ነፍስን የመመርመር አይነቶች የተለያዩ ናቸው፡፡ አንደኛው አይነት የተቆራረጠ የምርመራ ስልት ሲሆን ይህም ነፍስን ከረጅም ጊዜ በኋላ በየመሃሉ ሂሳብ ማድረግ ነው፡፡ ሌላኛው የነፍስ ምርመራ አይነት ደግም ከባባድ ጥፋቶችን ሲያስተውል ነፍሱን የመቅጣት ሂደት ነው፡፡ ሦስተኛውና የሚመረጠው የነፍስ ምርመራ አይነት ወዲያውኑ የሚደረግ ሙሓሰባ ነው፡፡ በዚህ ሂደት አንድ ሰው ነፍሱ ለሠራችው ስህተት በሙሉ ጊዜ ሳይሰጥ ምርመራ ያደርጋታል፡፡ ይህ አይነቱ ሙሓሰባ የነፍስን እንቅስቃሴ በንቃት በመከታተልና እርሷን በመውቀስ ካልተጀመረ ሊሳካ አይችልም፡፡ ምክንያቱም ነፍስ በባህሪዋ ተከራካሪና አላዋቂ ናትና፡፡

“የሕያ ኢብኑ ሙዓዝ በጣም ተከራካሪህ ማነው? ተብለው ሲጠየቁ ነፍሴ ናት፤ እርሷ ጀነትንና ዘላለማዊ ፀጋዎቿን በአንድ ሰዓት ስሜት ልሸጥ ብላ ትምማተናለች ብለው መለሱ፡፡” [27]

ይህ ከባዱ የነፍስ ጉትጎታ ነው፤ ለሰው ልጅ ከዱንያ ውጭ አሸብርቃ የምታሳይበት ስልት ነው፡፡ ስሜቱን አሰማምራ ታቀርብለታለች፣ እንዳሻው እንዲዘግን ታገራለታለች፣ ጥፋቱንም አሳንሳ ታሳየዋለች፡፡ ይህ በአንድ ሙእሚንና መጥፎን መራጭ በሆነችውና የጀነትን ጣዕም እርግፍ አድርጋ በምትረሳው ነፍሱ መካከል የሚደረግ ትግል ነው፡፡ እርሷም ጀነትን እንዲታወር ታደርገዋለች፣ ጠፊ የሆነውን የዱንያ ጥፍጥና አጉልታ ታሳየዋለች፡፡ እንግዲህ ይህች አይነቷ ነፍስ ናት ኢማም ያህያ ኢብኑ ሙዓዝን እንዲህ እንዲናገሩ ያደረገቻቸው፡፡ እርሱ ባይሆን ኖሮ ጀነትና ፀጋዋን በሰዓት ስሜት በቀላሉ በሸጠ ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ ኢማም ነፍሱን ለመመርመር በቅድሚያ እርሷን መከታተልና መውቀስ አስፈላጊ መሆኑን በትክክል ተገንዝቧል፡፡

ሁልጊዜም ንቁ መሆን

[27](ሲፈቱ ሰፍዋ 4/94)

(ሙስሊም ዘወትር ነፍሱን ሊከታተላት ይገባል፤ከቀጥተኛው መንገድ ልታስወጣው የምትችልበትን ምንም አይነት ሁናቴ ወይም በር አይከፍትላትም። ይህ ሙስሊም ራሱን አሳንሶ ይመለከታል። ከርሱ ትልቅ የሆነን ሰው ሲያይ እርሱ እኮ በኢማንና በመልካም ሥራ የቀደመኝ ምርጥ ሰው ነው ብሎ ያስባል። ከርሱ ታናሽ የሆነን ሰው ባየ ጊዜ ደግሞ እኔ እኮ ይህንን ሰው በወንጀልና በስህተት ቀዳሚው ነኝ፣ እርሱ ከኔ የተሻለ ነው ይላል። ወንድሞቹ ሲያከብሩትና ሲያልቁት ባየ ጊዜ ይኼ ለነርሱ የተሰጣቸው ፀጋ ነው ብሎ ሲያስብ ከነርሱ ክፍተት ባስተዋለ ጊዜ ደግሞ ይኽ በፈጸምኩት ወንጀል የመጣ ነው ብሎ ያምናል።)[28]

ነፍሱን በሁለመናዋ አካቧታል፣ የምትተነፍስበት እስትንፋስ አይሰጣትም፣ ልትላተመው የምትችልበትን እድል አይፈቅድላትም። በርግጥ ለሰው ልጅ ነፍስ እንደፈለገች የምትሆንበት ሰፊ የእንቅስቃሴ መድረክ አላት። ነገርግን ነፍሱን ዘወትር ነቅቶ የሚጠብቅ ሙእሚን ዘንድ ቦታ የላትም።

ነፍስን የመመርመር ተግባር በሚከተሉት አኳኋን ይካሄዳል፡-

1. የሙሓሰባ (ነፍስን የመመርመር) ጊዜን መወሰን። ይህም በእያንዳንዱ ቅፅበት ወይም ሰዓት አሊያም በቀኑ መጨረሻ ወይም በሌላ መልኩ ሊሆን ይችላል።
2. ግለሰቡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ያደረገውን ተግባርና እንቅስቃሴ መልሶ በማየት ምርመራውን ያካሂዳል (ለምርመራው አጋዥ የሚሆነው የመከታተያ ቅፅ ሊጠቀም ይችላል)።
3. ለጥሩ የምርመራ ውጤቶቹ አላህን(ሱ.ወ) ያመሰግናል።ይህንም ተግባር ሊያጎለብተውና ሊያከልበት ይተጋል። ለጉድለቶቹ ደግሞ ነፍሱን በመውቀስ ከዚያ ድርጊት ይቆጠባል፣ ነፍሱ ላይ በመበርታትም ያመለጠውን ያካክሳል።

የተግባር ልምምድ

- በዛሬዋ ሌሊት በመኝታ ክፍልህ ብቻህን በመሆን ለግማሽ ሰዓት ያህል መብራት አጥፍተህና በርህን ዘግተህ በእለቱ ባደረገችው ተግባራት ላይ ነፍስህን ሳትመረምር አትተኛ። ጥሩ ሆኖ ካገኘህ ለአላህ ምስጋና ሁለት ረከዓ ስገድ። መጥፎ ሆኖ ካገኘህ ደግሞ ወደ አላህ ተውበት አድርግ፣ ጥሩ ነገር ለመሥራትም በቁርጠኝነት ወስን።

5. ስንተ ነፍሳቸዉን ከሚጠይምዲ ሰዎች ነህን?

በሚከተሉት የመለያ ነጥቦች በመታገዝ አንድ ሰው ራሳቸውን በንቃት ከሚመረምሩት ሰዎች መደብ ነውን ወይንስ በእርሷ ላይ ከተዘናጉት የሚለውን መገምገም ይችላል፡፡ በዚህም የመመለሻ እድሉን ከማጣቱ በፊት ያመለጠውን እንዲያካክስ ይረዳዋል- ወንድም ሆይ! ከተከሰተ በኋላ መመለሻ እድል የሌለው ሂሳብ ከመምጣቱ በፊት አሁንም ከፊት ለፊትህ ነፍስህን ለማስተካከል ጊዜ አለህ፡-

(ካንተ ደረጃ ጋር የሚስማማውን ምረጥ)

ተ.ቁ	ተግባር	በጭራሽ (0)	አንዳንድ ጊዜ (1)	አልፎ አልፎ (2)	ባብዛሃኛው(3)	ሁልጊዜ (4)
1	ወደ መኝታ በሄድኩኝ ቁጥር ነፍሴ ዳግመኛ ላትመለስ እንደምትችል አስባለሁ					
2	ከእንቅልፌ በነቃሁ ቁጥር ጥሩ ነገር ለመሥራት አዲስ እድል እንደተሰጠኝ አስባለሁ					
3	አላህ ግደታ ያደረገብኝ ተግባር ሲያመልጠኝ ትልቅ ኪሳራ እንደከሰርኩ አስባለሁ					
4	ነፍሴ ከትናንቱ የተሻለ ጥሩ ነገር አለማድረጓን ሳስተውል ትልቅ ሀዘን ይሰማኛል					
5	በዚህች ሕይወት ውሰጥ ለተወሰነች ጊዜ ብቻ እንደምኖር ሳስብ ጭንቀት					

	ይሰማኛል					
6	ሞትና ሕይወት በሰው ልጅ ላይ እንደሚፈራረቁ ነፍሴን አስታውሳታለሁ					
7	በሶላቴ መጨረሻ ላይ ተግባሬን እፈትሻለሁ፣ ለጉድለቴም ምህረትን እጠይቃለሁ					

የመመዘኛ ጥያቄዎች

1. ነፍስን መመርመር ሲባል ምን እንደተፈለገ ግለፅ።
2. ነፍስን የመመርመር አስፈላጊነት አብራራ።
3. ሶሃባዎችና ደጋግ ባሮች ነፍስን በመርመር ዙሪያ ካላቸው ተሞክሮ ጥቀስ።
4. የሰው ልጅ ነፍሱን ለመመርመር እንዴት ሊለማመድ እንደሚችል አብራራ።
5. ነፍሱን ለመመርመር መማር ለሚፈልግ ሰው ልትመክረው የምትችላቸውን ተግባራዊ ጉዳዮች ጥቀስ።
6. የሕይወት ተሞክሮህን ጥቀስ ወይም ስሌሎች ራሳቸውን ምርመራ ስለሚያደርጉ ሰዎች የሰማኸውን አብራራ። ይህን ኣይነቱ ተግባር ባንተ ላይ ምን ተፅእኖ ፈጠረብህ?
7. አንተ በሁሉም ተግባራትህ ነፍስህን ትመረምራለህን? በየቀኑ መጨረሻ ዉሎህን በሚመለከት ከነፍስህ ጋር ሂሳብ ታደርጋለህን? መልስህ አዎ ካልሆነ በቀጣይ ምን ልታደርግ ወስነሃል?

3 - ወደ ኣላህ ተውበት ማድረግ

የትምህርቱ ዓላማ

1. ወደ አላህ የሚደረግ እውነተኛ ተውበት ምን እንደሆነ እንዲያብራራ ማስቻል
2. ወደ አላህ ተውበት ማድረግ ግደታ መሆኑን እንዲያብራራ ማስቻል
3. የተውበት መስፈርቶችን እንዲያብራራ ማስቻል
4. የተውበት ትሩፋቶችን እንዲያብራራ ማስቻል
5. ተውበት እንዴት ለአላህ እንደሚሆን እንዲያብራራ ማስቻል
6. ወደ አላህ ተውበት ከማድረግ ረገድ እራሱን እንዲገመግም ማስቻል

1. እውነተኛ ተውበት

ተውበት ማለት የሚከተሉትን ሦስት ነገራት አስተሳስሮ የያዘ መገለጫ መሆኑን ዕወቅ! እነርሱም፡- ዕውቀት፣ ሁናቴና ተግባር ናቸው፡፡

ዕውቀት፡- የወንጀልን አስከፊነትን ጠንቅቆ ማወቅ ሲሆን ይህም ወንጅል በአንድ ባያና በወዳጁ መካከል ግርዶሽ መሆኑን መረዳት ነው፡፡

ሁናቴ፡- ልቦና የሚወደውን እንዳጣ በተረዳ ጊዜ ህመም ይሰማዋል፡፡ ወዳጁን የሚያሳጣውን ተግባር በመፈፀሙ ምክንያት የሚሰማው የህመም ስሜት ጸጸት ይባላል፡፡

ተግባር፡- ይህ የህመም ስሜት በልቦና ላይ ሲበረታ አሁን መተግበር ስላለበት፣ ስላለፈውና ስለወደፊቱ የሚተገብራቸውን ተግባራት ያመነጫል፡-

አሁን ላይ፡- ወንጀሉ ቀጥሎ ከነበረ ማቆም፡፡

ለወደፊቱ፡- እስከ እድሜው ፍፃሜ ድርስ ይህንን ወንጀል በቁርጠኝነት ሊተው፡፡

ላለፈው፡- ያለፈውን መጥፎ ነገር በጥሩ ነገር ሊሸርና የወንጀሉ አይነት ከጥሩ ነገር መታቀብ ከነበረ ያቆመውንጥሩ ነገር በመቀጠል ሊያካክስ፡፡

ተውበት የሚለው ቃል ብዙ ጊዜ ጸጸትን ብቻ ለመግለፅ ጥቅም ላይ ሲውል ይስተዋላል፡፡ ለዚህ አይነቱ አገላለፅ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- “ጸጸት በራሱ ተውበት ነው” (ኢብኑ ማጃህ፣ ኢብኑ ሒባንና ሃኪም ዘግበውታል)፡፡ ስለዚህም ከልቦና የመነጨ ጸጸት ዉጤታማ የሆነ ከወንጀል መታቀብንና ቁርጠኛ የሆነ ውሳኔን ማስከተሉ አይቀሬ ነው፡፡)[29]

(ተውባህ ማለት ከወንጀሎች ሁሉ መራቅ፣ ላለፉት ወንጀሎችና ጉድለቶች መጸጸትና በቀሪው የእድሜ ዘመን ዳግም ወደ ወንጀል ላለመመለስ ቁርጠኛ ውሳኔ መወሰን ነው)[30]

2. ወደ አላህ ተዉበት ማድረግ ግዴታ መሆኑ

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ تُوبُوٓاْ إِلَى ٱللَّهِ تَوۡبَةٗ نَّصُوحًا عَسَىٰ رَبُّكُمۡ أَن يُكَفِّرَ عَنكُمۡ سَيِّـَٔاتِكُمۡ وَيُدۡخِلَكُمۡ جَنَّٰتٖ تَجۡرِي مِن تَحۡتِهَا ٱلۡأَنۡهَٰرُ ﴾التحريم: ٨

“እናንተ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ ንጹሕ የሆነችን ጸጸት በመጸጸት ወደ አላህ ተመለሱ፤ ጌታችሁ ከእናንተ ሃጢኣቶቻችሁን ሊሰርይላችሁ፡ ከሥሮቻቸው ወንዞች የሚሰብቸውንም ገነቶች ሊያስገባችሁ፡ ይከጅላልና፡ ፡ ” (አት-ተሕሪም:8)

በሌሎች የቁርአን አንቀጾች፡-

﴿ وَتُوبُوٓاْ إِلَى ٱللَّهِ جَمِيعًا أَيُّهَ ٱلۡمُؤۡمِنُونَ لَعَلَّكُمۡ تُفۡلِحُونَ ﴾النور: ٣١

“ምእመናኖች ሆይ ትድኑ ዘንድ ሁላችሁም በጸጸት ወደ አላህ ተመለሱ፡ ፡ ”

(አን-ኑር: 31)

﴿ وَمَن لَّمۡ يَتُبۡ فَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلظَّٰلِمُونَ ﴾الحجرات: ١١

“ወደ አላህ (ተጸጽቶ) የሚመለስ አነዚያ እነርሱ ከበደለኞች ናቸው”

(አል-ሑጁራት: 11)

[29][ኪታቡ ተውባህ -አል-ኢማም ጋዛሊ]
[30][መንሃጁል ሙስሊም]

﴿إِنَّ ٱللَّهَ يُحِبُّ ٱلتَّوَّٰبِينَ وَيُحِبُّ ٱلۡمُتَطَهِّرِينَ﴾ البقرة: ٢٢٢

"በእርግጥ አላህ ተጸፀት ወደ እርሱ ተመላሾችንና ተጥራሪዎችን ይወዳል" (አል-በቀራህ: 222)

የሚከተሉትን የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ንግግሮች እንመልከት፡-

- *"እናንተ ሰዎች ሆይ! ወደ አላህ ተመለሱ:: እኔ በቀን መቶ ጊዜ ተውበት አደረግጋለሁ::"* (ሙስሊም ዘግቦታል)
- *"ተውበት አድራጊ የአላህ ወዳጅ ነው:: ከወንጀል ተውበት የሚያደርግ ልክ ወንጀል እንደሌለበት ሰው ነው"* (ኢብኑ ማጃህ ከኢብኑ መስዑድ ዘግበውታል)

የእስልምና ሊቃውንት በሙሉ ተውበት ግደታ በመሆኑ ላይ ተስማምተውበታል:: ቁርጡቢ (አላህ ይዘንላቸውና) እንደሚሉት "ኡማው በሙሉ ተውበት በሙእሚኖች ላይ ግደታ መሆኑን የተስማማበት ጉዳይ ነው"[31] ኢብኑ ቁዳማህ አል-መቅዲስይ(አላህ ይዘንላቸውና) መንሃጁል ቃሲዲይን በምትባለው አጭር መጽሐፋቸው እንዳሰፈሩት "ሊቃውንት በስምምነት ተውበት ግደታ መሆኑን ያምናሉ::ምክንያቱም ወንጀል አጥፊና ከአላህ የሚያርቅ በመሆኑ ከእርሱ ፈጥኖ መሸሽ አስፈላጊ ስለሆነ ነው"

የሰው ልጅ ሲባል-ማንም ሳይቀር- ለስህተት የተጋለጠ ነው:: መልክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) እንደሚሉት፡-*"የአደም ልጅ በሙሉ ስህተትን ይሠራሉ:: ከእነርሱ በላጩ ሰው ተውበት አድራጊው ነው"* (ቱርሚዚ፣ ኢብኑ ማጃህና ሌሎችም ዘግበውታል)

3. ስተዉበት መስፈርቶች ስሱት

የእስልምና ሊቃውንት ከቁርአንና ከትክክለኛ ሐዲሶች በመነሳት ለተውበት መስፈርቶችን አስቀምጠዋል:: እነርሱም፡-

[31](ጃሚዑል አህካሙል ቁርአን 5/90)።

1. ለተፈፀመው ወንጀል ጸጸትሊኖር ይገባል፡፡ ነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ) “ጸጸት ተውበት ነው” ብለዋል፡፡ (አህመድና ሌሎቹም ዘግበውታል)
2. ወንጀሉን ማቆም፡፡
3. ወንጀሉን በድጋሚ ላይመለስበት በቁርጠኝነት ማቆም፡፡
4. ወንጀሉ በሰዎች ላይ ከሆነ በወንጀሉ ምክንያት የተያዘን የሰው ሀቅ መመለስ ወይም የሀቅ ባለቤቶቹን ይቅርታ መጠየቅ፡፡

ተውበት አድራጊ የፈፀመው ወንጀል በእርሱና በአላህ መካከል ከሆነ በወደቀበት ወንጀል ላይ ነፍሱን ሊመረምርና ሊፈትሽ ይገባል፡፡ እንደዚሁም ወንጀሉ በርሱና በሌላ ሰው መካከል በሆነውም ጉዳይ ሂሳብ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ የወንጀሉንም መጠን መለካት የግድ ነው፡፡ ለያንዳንዱ ለፈፀመው ወንጀል ተስማሚ የሆነ ጥሩ ነገር መፈለግና በወንጀሉ ልክ መልካም ነገሮችን መተግበር ያስፈልገዋል፡፡ እንዳውም መልካም ነገሩን በብዛት መጨመር አለበት፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

﴿وَأَقِمِ ٱلصَّلَوٰةَ طَرَفَيِ ٱلنَّهَارِ وَزُلَفٗا مِّنَ ٱلَّيۡلِۚ إِنَّ ٱلۡحَسَنَٰتِ يُذۡهِبۡنَ ٱلسَّيِّـَٔاتِۚ ذَٰلِكَ ذِكۡرَىٰ لِلذَّٰكِرِينَ ١١٤﴾ هود: ١١٤

“ሶላትንም በቀን ጫፎች ከሌሊትም ክፍሎች ፈጽም፡ መልካም ሥራዎች ጎጠኣቶችን ያስወግድሉና፡፡ ይህ ለተገሳፁት ግሳጼ ነው፡” (ሁድ፡ 114)

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- “ወንጀልን በመልካም ነገር አስከትል፤ ያብስልሃልና”

አንድ ተውበት አድራጊ ተውቡ ለአላህ ብቻ ጥርት ያለች ልትሆን ግድ ይለዋል፡፡ ወንጀሉን ለሌላ ምክንያት ብሎ ቢያቆም ወይም ለመፈፀም አቅም ቢያንሰው ከተውበት አይቆጠርለትም፡፡ የሚሰርቀው በማጣቱ ያልሰረቀ ሌባ ከተውበት አድራጊ አይቆጠርም፡፡ እንደዚሁም ሀኪሙ በጤንነቱ ላይ ጉዳት እንዳያደርስበት መጠጥ እንዳይጠጣ ስላስጠነቀቀው መጠጥን የተወ ሰው ተውበት አደረገ አይባልም፡፡

ተሙበት ኣድራጊዎች ኣሉት ደረጃዎች ኣሏቸው[32]

- **የተረጋጋች ነፍስ ባለቤት**፡- ይህ ሰው ተውበት ካደረገ በኋላ እስከ እድሜ ዘመኑ ቀጥ ብሎ ይፀናል፡፡ እድሜው በፈቀደለት ያመለጠውን ያካክሳል፡፡ ወደ ወንጀል ለመመለስ ነፍሱን አያናግራትም፡፡ ይህች አይነቷ ተውበት ንጹሕ ተውበት ትባላለች፡፡

- **የወቃሽ ነፍስ ባለቤት**፡- ይህ ሰው ተውበት ያደርጋል፣ በመሠረታዊ ታዛዥነት በፅናት መንገድ ላይ ይቀጥላል፡፡ ከባባድና ጸያፍ ነገሮችን ይታቀባል፡፡ ነገር ግን ባለው የቁርጠኝነት መላላት የተነሳ ሊያስወቅሰው የሚችል ጥፋት ላይ ይወድቃል፡፡ ይህ ሰው ጥፋቱን እንደገና ባስተዋለ ጊዜ ነፍሱን ይወቅሳታል፣ ይጸጸታል፣ ይቆጫል፡፡ ወደ ወንጅል የሚመሩትን ምክንያቶች ሊጠነቀቅ ቁርጠኝነቱን ያድሳል፡፡

- **የደካማ ነፍስ ባለቤት**፡- የዚህች ነፍስ ባለቤት ለተወሰነ ጊዜ ተውበት አድርጎ ለመቀጠል ይሞክራል፣ ከዚያም ስሜቱ ያሸንፈውና አስቦበትና አቅዶት ከወንጀሉ ይዘግናል፣ ከዚያም ይጸጸታል፣ አላህ ችሎታውን ቢሰጠው ከዚህ ተንኮል ሊያድነው እንደሚችል ያስባል፡፡ ነገር ግን ነፍሱ ታግራራለትና እንደገና ተውበቱ ይሰናከላል፣ እንደገናም ይጸጸታል፡፡

- **በመጥፎ አዛዥ ነፍስ ባለቤት**፡- ይህ ሰው ተውበት አድርጎ የፅናቱን መንገድ ከጀመረ በኋላ ነፍሱን ስለተውበት ሳያናግራት ከእንደገና ወንጀል ውስጥ ይዘፈቃል፡፡ ይህ ክፍል መጨረሻው እንዳይበላሽ አላህ ይጠብቀንና ያስፈራል፡፡

4. የተሙበት ትሩፋቶች

- ተውበት ወንጀልህን ታብስልሃለች

ነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-“ከወንጀል ተውበት የሚያደርግ ልክ ወንጀል እንደሌለበት ነው” [ኢብኑ ማጃህና ሌሎችም ዘግበውታል]

[32][ፊ ሪያዲል ጀናህ]

- ተውበት ወንጀልን ወደ መልካም ምንዳዎች ይቀይራል

አላህ (ሱ.ወ) አል-ፉርቃን ምዕራፍ አንቀጽ 70 ላይ እንዲህ ይላል፡-

﴿ إِلَّا مَن تَابَ وَءَامَنَ وَعَمِلَ عَمَلًا صَٰلِحًا فَأُوْلَٰٓئِكَ يُبَدِّلُ ٱللَّهُ سَيِّـَٔاتِهِمْ حَسَنَٰتٍ ۗ وَكَانَ ٱللَّهُ غَفُورًا رَّحِيمًا ﴿٧٠﴾ ﴾ الفرقان: ٧٠

"ተጸጽቶ የተመለሰና ያመነ፣ መልካምንም ሥራ የሠራ ሰው ብቻ ሲቀር እነዚያም አላህ መጥፎ ሥራዎቻቸውን በመልካም ሥራዎች ይለውጣል፤ አላህም እጅግ ማሓሪ አዛኝ ነው፡፡" (አል-ፉርቃን፡ 70)

- ተውበት ለሕይወት መረጋጋትና ለሪዝቅና ለሀይል መስፋት ምክንያት ነው፡-

"አላህ (ሱ.ወ) በሁድ ምዕራፍ አንቀጽ 3 ላይ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ وَأَنِ ٱسْتَغْفِرُوا۟ رَبَّكُمْ ثُمَّ تُوبُوٓا۟ إِلَيْهِ يُمَتِّعْكُم مَّتَٰعًا حَسَنًا إِلَىٰٓ أَجَلٍ مُّسَمًّى وَيُؤْتِ كُلَّ ذِى فَضْلٍ فَضْلَهُۥ ۖ وَإِن تَوَلَّوْا۟ فَإِنِّىٓ أَخَافُ عَلَيْكُمْ عَذَابَ يَوْمٍ كَبِيرٍ ﴿٣﴾ ﴾ هود: ٣

"ጌታችሁን ምህረትን ለምኑት፤ ከዚያም ወደርሱ ተመለሱ፤ እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ መልካምን መጥቀም ይጠቅማቸኋልና፡፡ የትሩፋትንም ባለቤት ሁሉ ችሮታውን (ምንዳውን) ይሰጠዋል፡፡" (ሁድ፡ 3)

በሌላ የቁርአን አንቀጽ በነቢዩላህ ኑህ (ዐ.ሰ) አንደበት እንዲህ ብሏል፡-

﴿ فَقُلْتُ ٱسْتَغْفِرُوا۟ رَبَّكُمْ إِنَّهُۥ كَانَ غَفَّارًا ﴿١٠﴾ يُرْسِلِ ٱلسَّمَآءَ عَلَيْكُم مِّدْرَارًا ﴿١١﴾ وَيُمْدِدْكُم بِأَمْوَٰلٍ وَبَنِينَ وَيَجْعَل لَّكُمْ جَنَّٰتٍ وَيَجْعَل لَّكُمْ أَنْهَٰرًا ﴿١٢﴾ ﴾ نوح: ١٠ - ١٢

"አልኳቸውም ጌታችሁን ምህረትን ለምኑት፣ እርሱ በጣም ማሓሪ ነውና፤ በናንተ ላይ ዝናብን ተከታታይ አድረጎ ያወርዳል፤ በገንዘቦችና በልጆቸም ይለግሳችኋል፤ ለናንተም መንዞችን ያደርግላችኋል፡፡" (ኑሕ፡ 10-12)

- ተውበት ላድራጊው ግለሰብ ቀልቡን ያፀዳለታል፡-

መልክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- *"አንድ ባሪያ ወንጀል ሲፈጽም በልቡ ላይ አንድ ጥቁር ነጥብ ያርፍበታል፡፡ ከወንጀሉ ከታቀበና ምህረትን ከጠየቀ*

ልቡ ይፀዳል፡፡ ወደ ወንጀሉ ከተመለሰ ጥቁረቱ ቀስበቀስ ሙሉ ልቡን ይሸፍነዋል፡፡ ይህ የተሸፈነ ልብ ዝንቡ የሚባለው ልብ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) በቁርአኑ የጠቀሰው፡-

﴿ كَلَّا بَلْ رَانَ عَلَىٰ قُلُوبِهِم مَّا كَانُوا يَكْسِبُونَ ﴾ المطففين: ١٤

"ይከልከል፤ ይልቁንም ይሠሩት የነበሩት ኃጢኣት በልቦቻቸው ላይ ደገ ደገ ባቸው" (አል-ሙጠፊፊን፡ 14)

- ተውበት ለዱንያም ለአኼራም የስኬት ምክንያት ይሆናል

የሚከተለው የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ይህንን ያመላክታል፡-

﴿ فَأَمَّا مَن تَابَ وَءَامَنَ وَعَمِلَ صَٰلِحًا فَعَسَىٰٓ أَن يَكُونَ مِنَ ٱلْمُفْلِحِينَ ﴾ القصص: ٦٧

"የተጸጸተና ያመነ ሰውማ ሚልካምንም የሠራ ከሚፎኑት ሊሆን ይከጀላል፡ ፡ " (አል-ቀሰስ: 67)

በሌላ የቁርአን አንቀጽም አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ إِلَّا مَن تَابَ وَءَامَنَ وَعَمِلَ صَٰلِحًا فَأُو۟لَٰٓئِكَ يَدْخُلُونَ ٱلْجَنَّةَ وَلَا يُظْلَمُونَ شَيْـًٔا ﴾ مريم: ٦٠

"ግን የተጸጸተና ያመነ፡ በጎንም ሥራ የሠራ ሰው እነዚህ ገነትን ይገባሉ አንዳችንም አይበደሉም፡ ፡ " (መርየም: 60)

5. እንዴት ተውበት ላድርግ?

- **ምንም ቀላል ቢሆን ወንጀልን አሳንሶ ከማየት ተጠንቀቅ**

ተውበት ለማድረግ የመጀመሪያው እርምጃ ትንሽም ይሁን ትልቅ ከወንጀል ወዲያውኑ መራቅ ነው፡፡ ምክንያቱም ትንንሽ ወንጀሎችን ተውበት ሳታደርግባቸው ከተጠራቀሙ ሊያጠፉህ ስለሚችሉ ነው፡፡ ነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- *"ወንጀልን አሳንሶ ከማየት ሊደራ እላችኋለሁ፡፡ ወንጀልን የሚያሳንስ ምሳሌው ወደ ሆነ ሸለቆ እንደወረዱ ህዝቦች ነው፡፡ ከነዚህም ሰዎች አንዱ አንድ ሸክም እንጨት ሲያመጣ፣ ሌላውም አንድ ሸክም እንጨት ሲያመጣ፣ በዚያ ማገዶ ዳቧቸውን*

ያበስሉበታል። ወንጀልን የሚያሳንሰ ሰው በተያዘ ጊዜ ያች ትንሽ ወንጀል ታጠፋዋለች።" (አህመድና ሌሎችም ዘግበውታል)። በሌላ ዘገባ፡- *"ወንጀልን ከማሳነስ አደራ እላችኋለሁ። እነዚህ ይጠራቀሙና ሰውየውን ያጠፉታል።"*

ውድ ወንድሜ የወንጀልን ትንሽነት አትመልከት፤ ይልቁንም ጥፋት የፈጸምክበትን (የአላህን) ታላቅነት ተመልከት። አብዛኛው ሰው አሳንሶየሚያቸው ወንጀሎች አሉ። ይህም በተደጋጋሚ ስለሚፈጸሙና ሰዎችም በግልጽ ሲተገብሩት ስለሚስተዋል ነው። ነገርግን እነዚህ ወንጀሎች በሙእሚኖችና በአላህ ዘንድ በጣም ከባድ ናቸው። በኢማም አህመድ ሙስነድ ላይ እንደተዘገበው አባ ሰዒድ አል-ኹድሪይ (አላህ ሥራቸውን ይውደድላቸውና) እንዲህ ብለዋል፡- "እናንተ ሥራን (ወንጀልን) ትሠሩና ከጸጉር የቀጠነ አድርጋችሁ ታዩታላችሁ። እኛ ግን እነኝህን ሥራዎች በአላህ መልክተኛ ዘመን አጥፊ ከሚባሉ ወንጀሎች ጎራ እንመድባቸው ነበር።" የሚከተለውን የመልክተኛውን (ሰ.ዐ.ወ) ንግግር አስተውል፡- *"አንድ ሰው፥ ጉዳይ ባላላት ንግግሩ የአላህ ቁጣ ያርፍበታል። በእርሷም ምክንያት ለሰባ ዓመት እሳት ውስጥ ይወረወራል።"*

- **ወንጀልን ግልፅ ከማውጣትና ያስፈም ቢሆን ስለው ከመናገር ተጠንቀቅ**

ይህምለሚከተለው የመልክተኛው (ሰ.ዐ.ወ)ንግግር ሲባል ነው፡- *"ሁሉም የእኔ ኡመት ይቅር ይባላል፤ ወንጀላቸውን ግልፅ ከሚያወጡት በስተቀር። ወንጀልን ግልፅ ከማውጣት መካከል ሰውየው በሌሊት ወንጀል ይፈፅምና አላህ (ሱ.ወ) ይሸሽግለታል፣ ከዚያም እገሌ ሆይ እኔ እኮ እንዲህ እንዲህ አይነት ጀብዱ ሠራሁ በማለት ያወራል፤ ጌታው ሸሽጎለት ያነጋል እርሱ ደግሞ ሲነጋ የአላህን ሚርዶሽ ይገፋል።"* (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታ)። ወንጀልን ይፋ ማድረግ በራሱ እንደ ወንጀል የሚቆጠርበት አንዱ ምክንያት ወንጀልን ግልፅ ማድረጉ ለሌሎች ሰዎች ቀላልና እንዲሁም አሳንሰው እንዲያዩት ስለሚያግዝ ነው። እንዲሁም ወንጀሉ በሰዎች መካከል እንዲስፋፋ ይረዳል። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿ إِنَّ ٱلَّذِينَ يُحِبُّونَ أَن تَشِيعَ ٱلۡفَٰحِشَةُ فِي ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَهُمۡ عَذَابٌ أَلِيمٞ فِي ٱلدُّنۡيَا وَٱلۡأٓخِرَةِۚ وَٱللَّهُ يَعۡلَمُ وَأَنتُمۡ لَا تَعۡلَمُونَ ﴾ النور: ١٩

"እነዚያ መጥፎ ወሬ በአማኞች ዘንድ እንዲትስፋፋ የሚወዱ ለነርሱ በቅርቢቱም በሚጪሻይቱም ዓለም አሳሚ ቅጣት አላቸው፡ ፡ አላህም ያውቃል እናንተ ግን አታውቁም ፡ ፡" (አን-ኑር፡ 19)

ይህ ማለት ግን ወንጀላቸውን ለማንም ሰው አልተናገሩምና ብቻቸውን በሚገለሉበት ወቅት ከወንጀላቸው ይዘናጉ ማለት እንዳልሆነ ግንዛቤ ሊኖር ይገባል። ይህን በተመለከተ መልክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ በማለት አስጠንቅቀዋል፡- *"ከኡመቴ ህዝቦችን አውቃለሁ፤ የቂያማ ዕለት ተራራ የሚያክልና የሚያብረቀርቅ መልካም ሥራ ይዘው ይመጣሉ። አላህ ግን ባዶ ብናኝ ያደርገዋል። በእርግጥ እነኚህ ሰዎች የናንተው ወንድሞችና የሥጋ ዘመዶቻችሁ ናቸው። እናንተ በሌሊት ኢባዳ እንደምታደርጉት እነርሱም ያደርጋሉ። ነገር ግን ብቻቸውን በሚሆኑበት ወቅት አላህ እርም ያደረገውን ድንበር ይጥሳሉ።"* (ኢብኑ ማጃህ ዘግበውታል) ስለዚህም ወንጀልን ይፋ ከማውጣት ተቆጠብ! ለብቻህ በምትሆንበት ወቅት ወንጀልን ከመዝገንም ተተንቀቅ! አላህ የምንደብቀውንም ሆነ ግልፅ የምናወጣውን አዋቂ ነው። አላህ በሁሉም ነገር አዋቂ ነው።

- **እኔንም እንተንም ሰላህ ደዘንልንና ተጡበትን ከማዘግየትና ጊዜ ከመስጠት ተጠንቀቅ**

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَأَنِيبُوٓاْ إِلَىٰ رَبِّكُمۡ وَأَسۡلِمُواْ لَهُۥ مِن قَبۡلِ أَن يَأۡتِيَكُمُ ٱلۡعَذَابُ ثُمَّ لَا تُنصَرُونَ ﴾ الزمر: ٥٤

"ቅጣቱም ወደናንተ ከማማጣቱና ከዚያም የማረዱ ከመኾናችሁ በፊት ወደ ጌታችሁ (በመጸጸት) ተመለሱ፤ ለርሱም ታዘዙ። ፡ ፡" (አዝ-ዙመር: 54)

ሞት መቼ እንደሚደርስ አታውቅምና፤ በዚያን ጊዜም ተውበት ጥቅም የለውም። ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዳሉት፡- *"አላህ (ሱ.ወ) የአንድን ባሪያ ተውበት ጣዕረ-ሞት ላይ እስካልደረሰ ድረስ ይቀበላል።"* (አህመድና ቱርሚዚ ዘግበውታል)። ከማንኛውም ወንጀል ወደ አላህ ለመመለስ ተቻኮል፤ አታዘግይ። ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- *"ከአላህ ባሪያ የለም፥ ወንጀልን ከፈፀመ በኋላ ውዱእ አድርጎና ንፅህናውን አሳምሮ፣ ሁለት ረከዓ የሚሰግድና ከዚያም ለዚያ ወንጀል አላህን ምህረት የሚጠይቅ። አላህ ለርሱ ምህረትን ቢለግሰው እንጅ።"* (አህመድና ሌሎችም ዘግበውታል)

- **በመንጀል ላይ ከመዘሙተር ተጠንቀቅ**

በአል-ዒምራን ምዕራፍ አንቀጽ 135 አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَٱلَّذِينَ إِذَا فَعَلُواْ فَٰحِشَةً أَوۡ ظَلَمُوٓاْ أَنفُسَهُمۡ ذَكَرُواْ ٱللَّهَ فَٱسۡتَغۡفَرُواْ لِذُنُوبِهِمۡ وَمَن يَغۡفِرُ ٱلذُّنُوبَ إِلَّا ٱللَّهُ وَلَمۡ يُصِرُّواْ عَلَىٰ مَا فَعَلُواْ وَهُمۡ يَعۡلَمُونَ ﴾ آل عمران: ١٣٥

"ለነዚያም መጥፎ ሥራን ለሠሩ ወይም ነፍሶቻቸውን በበደሉ ጊዜ አላህን የሚያስታውሰና ለኃጢኣቶቻቸው ምሕረትን የሚጠይቁ ለኾኑት ከአላህም ሌላ ኃጢኣቶችን የሚሞር አንድም የለ፣ (በስህተት) በሠሩትም ላይ እነርሱ የሚወቁሲኾኑ የሚዘወትሩ ለኾኑት (ተደግሳለች)። ፡ ፡" (አል-ዒምራን፡ 135)

- **ከአላህ እዝነት ተስፋ ከመቁረጥ ተጠንቀቅ**

እውነተኛ የሆነው አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

﴿ قَالَ وَمَن يَقْنَطُ مِن رَّحْمَةِ رَبِّهِۦٓ إِلَّا ٱلضَّآلُّونَ ﴾الحجر: ٥٦

"ከጠሞሞችም በስተቀር ከጌታው እዝነት ተስፋን የሞቹርጥ ማነ አለ" (አል-ሒጅር: 56) በሌላ አንቀጽ፡-

﴿ قُلْ يَٰعِبَادِيَ ٱلَّذِينَ أَسْرَفُوا۟ عَلَىٰٓ أَنفُسِهِمْ لَا تَقْنَطُوا۟ مِن رَّحْمَةِ ٱللَّهِ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ يَغْفِرُ ٱلذُّنُوبَ جَمِيعًا ۚ إِنَّهُۥ هُوَ ٱلْغَفُورُ ٱلرَّحِيمُ ﴾الزمر: ٥٣

"በላቸው-እናንተ በነፍሶቻችሁ ላይ ድንበር ያለፋችሁ ባሮቼ ሆይ! ከአላህ እዝነት ተስፋ አትቁረጡ፤ አላህ ኃጢአቶችን በሞላ ይምራልና፡፡ እነሆ እርሱ መሓሪው አዛኙ ነውና፡፡" (አዝ-ዙመር: 53)

- **ወንጀልን በመልካም ነገር ስስከተል (መልካም ነገር ወንጀልን) ታብሳታለችና**

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

﴿ إِنَّ ٱلْحَسَنَٰتِ يُذْهِبْنَ ٱلسَّيِّـَٔاتِ ۚ ﴾هود: ١١٤

"መልካም ነገራት ወንጀሎችን ያስወግዳሉ፡፡" (ሁድ፡ 114)

﴿ إِلَّا مَن تَابَ وَءَامَنَ وَعَمِلَ عَمَلًا صَٰلِحًا فَأُو۟لَٰٓئِكَ يُبَدِّلُ ٱللَّهُ سَيِّـَٔاتِهِمْ حَسَنَٰتٍ ۗ وَكَانَ ٱللَّهُ غَفُورًا رَّحِيمًا ﴾الفرقان: ٧٠

"ተጸጽቶ የተመለሰና ያመነ፣ መልካምንም ሥራ የሠራ ሰው ብቻ ሲቀር እነዚያም አላህ መጥፎ ሥራዎቻቸውን በመልካም ሥራዎች ይለወጣል፤ አላህም እጅግ መሓሪ አዛኝ ነው፡፡" (አል-ፉርቃን፡ 70)

ኢማሙ ሙስሊም ትክክለኛ ነው ባሉት በሐዲስል ቁድስ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- *"ወደ እኔ ሰንዝርን የቀረበኝን አንድ ክንድ ያክል እቀርበዋለሁ፣ አንድ ክንድ የቀረበኝን በእጥፍ እቀርበዋለሁ፣ እየተራመደ ወደ እኔ የሚመጣን በሶምሶሟ እቀርበዋለሁ፡፡"* ኢማም ኢብኑ ተይሚያህ (አላህ ይዘንላቸውና) እንዲህ ብለዋል፡- "ብልህ ማለት ወንጀሉን የሚያብስለትን መልካም ሥራ ከመሥራት

የማይወገድ ነው።።"የአዛኞች ሁሉ አዛኝ በሆነው አላህ ላይ ጥሩ ጥርጣሬ ይኑርህ፣ ወደ አላህ ተውበት በማድረግ ላይ ቀጥል፣ ከእርሱ በስተቀር ሌላ መጠጊያ የሌለ መሆኑን አውቀህ ከልብህ ምህረትን ጠይቅ፣ ጥሩ ነገርን በመሥራት ላይ ተሸቀዳደም፣ ጥሩ ነገር እንድትሠራ የሚረዱህን መልካም ባሮቹን ተጎዳኝ፣ የተጠሉ ተግባራትን እንዲትሠራ ከሚያቃልሉልህ መጥፎ ጓደኞች ጋር አትጎዳኝ፣ በማንኛውም ሁኔታ አላህን (ሱ.ወ) በማስታወስ ላይ ዘውትር-ምክንያቱም አላህን መዘከር ሸይጧንን ለማባረር የሚያግዝህ ትልቅ መሳሪያ ነውና።። እንደዚሁም ወንጀልን የሚያብሱ ተግባራትን ትተገብር ዘንድአይነታቸውን ለማወቅልትሮጥ ይገባል፤ ከፊሎቹን እንደሚከተለው ዘርዝረናል፡-

- **ሙዱእ አሚልቶ ማድረግና ወደ መስጊድ መሄድ**

መልክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) "አላህ ኃጢአትን የሚያብስበትንና ደረጃን ከፍ የሚያደርግበትን ነገር ላመላክታችሁን? አሉ።። ሰሐባዎችም እንዴታ ንገሩን እንጅ አንቱ አላህ መልክተኛ አሉ።። ነቢዩም (ሰ.ዐ.ወ) አሉ፡- *"በከባድ ወቅት (በብርድ ወይ በዝናብ ወይ በህመም ወዘተ.) ዉዱእን አሟልቶ ማድረግ፣ ወደ መስጊድ እርምጃን ማብዛትና አንዱ ሶላት አልፎ ሌላ ሶላት እስከሚመጣ መጠባበቅ፤ እነኝህ መከታ ናቸው! እነኝህ መከታ ናቸው! እነኝህ መከታ ናቸው!"*

- **የዐረፋና የዐሹራን ቀን መፃም**

መልክተኛውም (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-"የዓረፋን ቀን መፆም ያለፈውን የአንድ ዓመትና የወደፊቱን አንድ ዓመት ወንጀል ያሰርዛል ብዬ ወደ አላህ አስባለሁ፣ የአሹራን ቀን መፆም እንደዚሁ የወደፊቱን አንድ ዓመት ወንጀል ያሰርያል ብየ ወደ አላህ አስባለሁ" (ቱርሚዚ ዘግበውታል)

- **የረመዳንን ወር በሚባዳ ማሳለፍ**

መልክተኛውም (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- "የረመዳንን ወር ከአላህ ምንዳ አገኛለሁ ብሎ አምኖና አስቦ በሚባዳ ያሳለፈ ያለፈው ወንጀሉ ይማርለታል" (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)

- **ንጹህ የሆነ ሐጅ**

መልክተኛውም (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-“ሐጅ አድርጎ ከፀያፍ ድርጊትና ከአመፅ የተቆጠበ ልክ እናቱ እንደወለችው ቀን ሆኖ ይመለሳል” (ምንም ወንጀል ሳይኖርበት ለማለት ነው) (ቡኻሪ ዘግበውታል)

- **ሰላምታን ማብዛትና መልካምን መናገር**

መልክተኛውም (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-“ምህረትን ከሚያስገኙ ነገሮች ሰላምታን ማብዛትና መልካምን መናገር ነው” (ኸራኢጥ ዘግበውታል፤ አልባኒ ትክክል ነው ብለዋል)

- **አምስት ወቅት ሶላቶችንና ጁመዓን መጠበቅና የረመዳንን ወር መፃም**

መልክተኛውም (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-*“አምስት ወቅት ሶላቶች፣ ጁመዓ እሰከ ጁመዓ፣ ረመዳን እሰከ ረመዳን ከባባድ ወንጀሎችን እሰከራቁ ድረስ በመካከላቸው ያለን ወንጀል ያብሳሉ::”* (ሙስሊም ዘግበውታል)

- **ዚክር ማድረግ ወንጀልን ያብሳል**

መልክተኛውም (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- *“ምግብን የተመገበና ከዚያም፣ ይህንን ምግብ ያለ እኔ ብልሃትና ኃይል ለመገበኝና ለለገሰኝ አላህ ምስጋና ይገባው በማለት ያወደሰ ሰው ያለፈው ወንጀሉ ይማርለታል::”* (አት-ቲርሚዚ ዘግበውታል):: በሌላ ሐዲስ፡- *“ይህንን ልብስ ያለ እኔ ብልሀትና ኃይል ላለበሰኝና ለለገሰኝ አላህ ምስጋና ይገባው በማለት ያወደሰ ሰው ያለፈው ወንጀሉ ይማርለታል::”* (አቡ ዳውድ ዘግበውታል):: ስለሆነም ብዙዎቹ የቀንና የሌሊት ውዳሴዎች፣ የጧትና የማታ አዝካሮች እንዲሁም ሌሎች የጥሩ ነገር በሮች በሙሉ ሊያመልጡን አይገባም፤ አላህ እርሱ ብቸኛ ረዳት ነው::

የተግባር ልምምድ

1. ነፍስህ ከተረጋጋች ነፍስ ምድብ እንዲትሆን አላህን ለምን።
2. ሁለት ረከዐህ ስገድ፤ ከዚያም ለፈጸምከው ወንጀል አላህን ምህረትን ጠይቅ።
3. ወደ የትኛውም ወንጀል ወይም ጉድለት ላትመለስ አሁኑኑ በቁርጠኝነት ወስን፤ ከዚያም አላህ እንዲያግዝህ ለምነው።
4. ምርጡ የምህረት ዱዓ የሚል ስያሜ የተሰጠውን አዝካር ሁልጊዜም አዘውትር፡-

“አላህ ሆይ አንተ ጌታዬ ነህ፣ ካንተ በስተቀር አምላክ የለም፣ እኔን ፈጠርክ፡ እኔም ባሪያህ ነኝ፣ አቅሜ በፈቀደ በቃልኪዳንህና በማስጠንቀቂያህ ዘውትሬያለሁ፣ ከሠራሁት መጥፎ ነገር ባንተ እጠበቃለሁ፣ በእኔ ላይ ያፈሰስከው ፀጋ ያስወተውተኛል፣ እንዲሁም የፈጸምኩት ወንጀል ያስጮኸኛል። ምህረትህን ለግሰኝ በእርግጥ ከአንተ በስተቀር ወንጀልን ይቅር ባይ የለምና”

6. ወደ አላህ ተውበት በማድረግ ዙሪያ ነፍሱን ሲገመግም

በሚከተሉት የመገምገሚያ ነጥቦች በመታገዝ ወደ አላህ ተውበት ከማድረግ አኳያ እራስህን ገምግም። እንዴት ተውበት ላድርግ በሚለው ክፍል ከተጠቀሱት ነጥቦች በግምገማ ነጥቡቹ ላይ ልትጨምር ትችላለህ። ከነዚህ በመነሳት ደረጃህን

ለካ፣ ሁኔታህን መላልሰህ ገምግም፣ ክፍተቶችህን ለይተህ አስቀምጥ፤ ከስህተተኞች መልካም ናቸው:: የሚባሉት ቶሎ ተውበት አድራጊዎች ናቸውና::

ተ.ቁ	ተግባር	በጭራሽ (0)	አንዳንድ ጊዜ (1)	አልፎ አልፎ(2)	ባብዛሃኛው (3)	ሁልጊዜ (4)
1	ወንጀል በእኔና በአላህ መካከል ያለውን ግንኙነት እንደሚያርቅ ይሰማኛል					
2	በግልፅ ጉዳት የሚያመጣ ወንጀል ስፈፅም ነፍሴ ትወቅሰኛለች					
3	ነፍሴ ወደ ወንጀል በድጋሜ እንዳትመጣ የሚያግዙኝን ዘዴዎች እጠቀማለሁ					
4	ወንጀል ላይ አልዘወትርም፤ በፍጥነት ወደ አላህ እመለሳለሁ					
5	ወንጀል ባልፈፅም ብዬ ሁሌም እመኛለሁ					
6	የተውት መስፈርቶችን ለሚሟላት ጥረት አደርጋለሁ					
7	በየቀኑ ተውበትና ኢስቲግፋርን መደጋገም የዘወትር ተግባሬ ነው					
8	የቀኑን በቀን የሌሊቱን በሌሊት ተውበት ለማድረግ ጥረት አደርጋለሁ					
9	ወንጀልን ባስታወስኩት ቅጽበት ወዲያውኑ አቆማለሁ					
10	እስከ እድሜዬ መጨረሻ ወንጀልን ለመተው ቁርጠኛ ውሳኔ አለኝ					
11	ያለፈው ወንጀል ለፈጠረው ተፅእኖ ማካካሻ እተገብራለሁ ወይም ያለፈኝን እሠራለሁ					

የመጨረሻ ጥያቄዎች

1. እውነተኛ ተውበት ምን እንደሆነ አብራራ፡፡
2. ወደ አላህ ተውበት ማድረግ ግዴታ ስለመሆኑ አብራራ፡፡
3. የተውበት መስፈርቶችን አብራራ፡፡
4. ወደ አላህ ተውበት ማድረግ ያሉትን ትሩፋቶች ዘርዝር፡፡
5. ወደ አላህ ተውበት ማድረግ እንዴት እንደሆነ አብራራ፡፡
6. ወደ አላህ ተውበት በማድረግ ዙሪያ እራስህን ገምግም፡፡

1. ሞትን ማስታወስ

የትምህርቱ ዓላማ

1. ሞትን የማስታወስ አስፈላጊነት እንዲያብራራ ማስቻል፡፡
2. ለሞት ዝግጅት የሚያግዙ ነገሮችን እንዲያብራራ ማስቻል፡፡
3. ሞትን እንዲያስታውስ የሚረዱትን ተግባራዊ ከንዋኔዎች እንዲያስታውስ ማስቻል፡፡

ነፍስን ለማፅዳት ከሚያግዙ መንገዶች መካከል ታላቁ ሞትን ማስታወስና ለእሱ ዝግጅት ማድረግ ነው፡፡ የሞት መልአክ ከበሩ አፋፍ ላይ የተጣደ መሆኑን የሚያስተነትን ከእርሱ ጋር ለመጓዝ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ ወደ ጀነት ወይም ወደ እሳት፡፡ ከዱንያ በኋላ ያለው አገር ጀነት ወይም እሳት ነው፡፡ ሞት ምንም የማይቀር ሁሉም ሰው የሚጎነጨው ፅዋና እውነታ ነው፡፡ እውነተኛ የሆነው አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

﴿ وَجَآءَتۡ سَكۡرَةُ ٱلۡمَوۡتِ بِٱلۡحَقِّۖ ذَٰلِكَ مَا كُنتَ مِنۡهُ تَحِيدُ ١٩ وَنُفِخَ فِي ٱلصُّورِۚ ذَٰلِكَ يَوۡمُ ٱلۡوَعِيدِ ٢٠ وَجَآءَتۡ كُلُّ نَفۡسٖ مَّعَهَا سَآئِقٞ وَشَهِيدٞ ٢١ لَّقَدۡ كُنتَ فِي غَفۡلَةٖ مِّنۡ هَٰذَا فَكَشَفۡنَا عَنكَ غِطَآءَكَ فَبَصَرُكَ ٱلۡيَوۡمَ حَدِيدٞ ٢٢ ﴾ ق: ١٩ - ٢٢

"የሞትም ሚከራ እውነቱን ነገር ታመጣለች፤ (ሰው ሆይ) –ይህ ያ ስትሸሸው የነበርከው ነው (ይባላል)። በቀንድም ወደጥ ይነፋል ያ (ቀን) የዛቻው (ሚፈጸሚ) ቀን ነው። ነፍስም ሁሉ ከርሷ ጋር ነጂና ሚከሪ ያለባት ኾና ትመጣለች። ከዚህ ነገር በእርግጥ በዝንጋቴ ወደጥ ነበርክ፤ ሺፋንህንም ካንተ ላይ ገለጥንልህ፤ ስለዚህ ዛሬ ዓይንህ ስለታም ነው (ይባላል)።" (ቃፍ: 19-22)

የቅርቢቱ ዓለም የሥራ አገር ስትሆን የመጨረሻው ዓለም ደግሞ የምርመራ አገር ነው። ስለሆነም ወንድም ሆይ! ለመመለሻህ ተሰነቅ፣ ጊዜው ሳያልፍ ስንቅህንም አብዛ፡-

﴿ وَأَنفِقُواْ مِن مَّا رَزَقۡنَٰكُم مِّن قَبۡلِ أَن يَأۡتِيَ أَحَدَكُمُ ٱلۡمَوۡتُ فَيَقُولَ رَبِّ لَوۡلَآ أَخَّرۡتَنِيٓ إِلَىٰٓ أَجَلٖ قَرِيبٖ فَأَصَّدَّقَ وَأَكُن مِّنَ ٱلصَّٰلِحِينَ ﴾ المنافقون: ١٠

"አንዳችሁን ሞት ሳይመጣውና –ጌታየ ሆይ እንዲመጻወትና ከደጋጎቹም ሰዎች እንዲሆን ጥቂት ጊዜ ብታቆየኝ ኖሮ እመኛለሁ ከሚለቱ በፊት ከሰጠናችሁ ሲሳይ ለግሱ።" (አል-ሙናፊቁን: 10)

አስጠንቃቂ ብልጭታዎች[33]

ዘያሪህ (ሞት) ከመምጣቱ በፊት ወዳንተ እየደረሰ መሆኑንና የእድሜ ቀጠሮህ እየቀረበህ መሆኑን አስጠንቃቂ መልእክቶችን (ቴሌግራም) በእርግጥ ልኮልሃል። ልትቀበለው ተዘጋጅተሃልን?... የመምጫ ቅደመ-መልእክቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

1. ህመም

ሙሐመድ ኢብኑ ዋሲዕ ለሞት የዳረገውን ህመም ታሞ እያለ ሰዎች ሊጠይቁት ገቡ። እርሱም እንዲህ አላቸው፡-ወንድሞቼ ሆይ...ወንድሞቼ ሆይ...

[33](ዛኢዱል አኺር-ዶ/ር ኻሊድ አቡ ሻዲ)

እባካችሁን አድምጡኝ አላህን መመለስን ጠየቅነው ለእናንተ ሰጣችሁ እኔን ከለከለኝ...ነፍሳችሁን ኪሳራ ውስጥ አታስገቡ!

አብዱልመሊክ ኢብኑ መርዋን ለሞት የዳረገውን ህመም በታመመ ጊዜ 'ቀን በቀን የሚበቃኝን ሥርቼ በነበር! አላህን በመታዘዝ ለፍቼ በነበር!' እያለ እጁን ከራሱ ጋር እያጋጨ ነፍሱን ይኮንናት ነበር። ይህ የእርሱ ሁኔታ ለአቢ ሃዝም ተነገራቸውና እንዲህ አሉ፡-"ሊሞቱ ሲሉ እኛ ያለንበትን እንዲመኙ ላደረጋቸው አላህ ምስጋና ይገባው! እኛ ግን ልንሞት ስንል እነርሱ ያሉበትን አንመኝም።"

ወንድም ሆይ...ሞቱን ያራቀ፣ ምኞቱን ያስረዘመና ቀብሩን የረሳ የሀሰን አል-በስሪን ምክር ያንብብ፡-"ሰው በድንገት ባይሞት አንኳን በድንገት ይታመማል፣ አላህን ፍሩ፣ የጌታችሁን ድንገተኛ ትእዛዝ ተጠንቀቁ።"

ሀኪም በህክምናው ቢወርድ ቢወጣ
ወዳጅ አያድንም ቀጠሮው ከመጣ
ሀኪሙ ምን ሆኗል ምነው አቅም አጣ
ባዳነው በሽታ ሰው ታሞ ሲመጣ
በፊት ያዳነውን ማዳን ተስኖት
ይሄው ተዳረገ ሰውየው ለሞት
ሀኪሙም አልዳነ ታካሚም አልቀረ
መድሃኒት ሻጩም ገዥም ተጨመረ

2. ሽበት

ሽበት ፀጉርህን ሳይቀይረው በርትተህ ሥራ፤ እርሱ ከተቀየረ ጭንቀትህ ይቀንሳል፣ ጉልበትህ ይርዳል፣ ፍላጎትህ ይደክማል፣ ችሎታህ አይጠቅምም፣ ስለ ጥሩ ተግባራት ምንዳ ሐዲስ ትሰማለህ፣ ልትሠራው ትመኛለህ ነገርግን አትችልም። ነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ) እንደመከሩህ ወጣትነትህን ከማጣትህ በፊት ተጠቀምበት።

ሐሰን አል-በስሪ (አላህ ይዘንላቸውና) ሽማግሌዎችን እንዲህ በማለት አባነኗቸው፡- “እናንተ ሽማግሌዎች ሆይ! አዝመራ ከደረሰ ምን ይጠብቀዋል?” አሏቸው፡፡ እነርሱም “መሰብሰብ” ብለው መለሱ፡፡ ወጣቶችን ደግሞ እንዲህ በማለት አባነኗቸው፡- “እናንተ ወጣቶች ሆይ አዝመራ ከመድረሱ በፊት ጥፋት ሊደርስበት ይችላል!”

3. ከሚመጹት መለዮት

ከሰለፎች አንዱ ከወንድሞቹ መካከል የአንዱ ሞት ደረሰው፡፡ እርሱም እንዲህ አለ፡- “እኛ ለአላህ ነን ወደ እርሱም ተመላሾች ነን...በአላህ እምላለሁ እኔ ራሴ እድለቢሱ ተወሳጅ (ሟች) የሆንኩኝ መሰለኝ፡፡” በዚህም ለሰውየው ጥንካሬንና ለጥሩ ነገር መልፋትን አላህ ጨመረለት፡፡

አንድ ሰው ወደ ፉደይል ኢብኑ ዒያድ ዘንድ መጣና ምከረኝ አላቸው፡፡ አባትህ ሞቷልን? አሉት አዎ አለ፡፡ በቃ ከእኔ ዘንድ ተነስ ከወላጁ ሞት በኋላ ሌላ ምክር የሚፈልግ ለእርሱ ምክር አትጠቅመውም፡፡

4. ዝምተኛው መካፊ (ቀብር)

ውድ ወንድሜ ሆይ...ስለ ቀብር ምክር ስንት ጊዜ ሰምተሃል? ስንት ጊዜስ ጎብኝተሃል? ቀብርህን አስበህ ታውቃለህ? ለእርሱ ጓደኛ የሚሆንህ ምን አዘጋጀህ? ቀብርን መጎብኘት አብዛ! አኼራን ያስታውስሃልና! መልክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- *“ቀብር መጎብኘትን ከልክያችሁ ነበር፡፡ አሁን ግን ዓዎጅ! ጎብኟት፡፡ እርሷ በእርግጥ ዓኼራን ታስታውሳችኋለች፡፡”* (ሐዲሱ ሶሂህ ነው)

ሞትን እንዴት ማስታወስ ይቻላል

- አንድ ሰው ሞትን ሊያስታውስ አይችልም በምላሱም፣ በልቦናውም በአካላቱም ሞትን እስካላስታወሰ ድረስ፡፡
- በእያንዳንዱ ሌሊት ለመኝታ ወደ ፍራሽህ ስትጠጋ ሞትን አስታውስ፣ የእንቅልፍ ጊዜ ዱዓንም እንዲህ በማለት አድርግ፡- *“አላህ ሆይ በሰምህ ሀያው*

እሆናለሁ፣በሰምህ እምታለሁ"፤ በነቃህም ጊዜ እንዲህ በል፡- *"ከገደለን በኋላ ህያው ላደረገን አላህ ምስጋና ይገባው፣ መቀስቀስም ወደ እርሱ ነው"*፡፡

- የታመመን፣ አደጋ የደረሰባቸውንና የአልጋ ቁራኛ የሆኑ የሆስፒታል በሽተኞችን መጠየቅ አብዛ፤ ሞትን ያስታውስሃል፡፡
- ቅርብ ዘመድህም ሆነ የምትወደው በሞተ ጊዜ ጀናዛው ላይ በአጠባና ከፈኑ ላይ ተሳተፍ፡፡
- ከፈንህን በሕይወት ሳለህ አዘጋጅ፤ ቀጠሮህ መቼ እንደሆነ አታውቅምና፡፡
- ሸሪዓዊ ወሲያህን አዘጋጅ፣ ቤተሰብህንም አሳውቅ፡፡
- ከጊዜህ ምንንም ያክል ቢሆን ከሞት በኋላ የምትጸጸትበት ነገር ላይ አታሳልፍ፤ ከሞትክ በኋላ በእርሱ ሂሳብ መደረግህ አይቀርምና፡፡
- በሰገድክ ጊዜ ይህች ሶላትህ የመጨረሻ ሶላትህ እንደሆነች አስበህ የመሰናበቻ ሶላትን ስገድ፡፡
- ዛሬ ከገንዘብህ ለግስ፤ ነገ ገንዘብህ ለወራሽ ከመከፋፈሉና አንተም በእርሱ ሂሳብ ከመደረግህ በፊት፡፡
- ጀናዛ መሸኘትን አብዛ፡፡

የመጨረሻ ጥያቄዎች

1. የሞትን ማስታወስአስፈላጊነት አብራራ፡፡
2. የሰው ልጅን ለሞት እነዲዘጋጅ ቀድመው የሚመጡ መልእክቶችን አብራራ፡፡
3. ሞትን ለማስታወስ የሚረዱ ተግባራዊ ክንዋኔዎችን ጥቀስ፡፡
4. ለሞት ለመዘጋጀት በግልህ የምትተገብራቸውን ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች አብራራ፡፡

5- ጹዓ

የትምህርቱ ዓላማ

1. የጹዓን አስፈላጊነትና ትሩፋቶቹን እንዲያብራራ ማስቻል፡፡
2. የጹዓ አደራረግ ሥርዓቶችን እንዲያስታውስ ማስቻል፡፡

1. የጹዓ ስለፈላጊነትና ትሩፋቶቹ

ጹዓ ነፍስን ለማፅዳት ከምንጠቀምባቸው መንገዶች ዋነኛው ነው፡፡ እንዲያውም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) *“ጹዓ ሷባዳ ነው”* በማለት ተናግረዋል፡፡ (አህመድ ዘግበውታል፣ አልባኒ ትክክል ነው ብለዋል)፡፡ ጹዓ ቀልብን ብርታትና መለዘብን የሚያስታጥቃት መሳሪያ ነው፡፡ ጹዓ የሰው ልጅ ፈጣሪውን ከሚያስታውስበት ክፍል ነው፡፡ ወደርሱ ይጠጋበታል፣ ሰዋዊ ደካማነቱን ይገልፅበታል፣ ከጎኑ ካለችውና በመጥፎ ከምታዘው ጠላቱ (ከነፍሱ) እንዲጠብቀው ይማፀንበታል፡፡

እስኪ አቡበክር አስ-ሲዲቅ (ረ.ዐ) ከንጹሁ ምንጭ ይህችን ነፍሳቸውን ለማጽዳት የሚያግዟቸውን መንገዶች ለመቅሰም የሚያደረጉትን ጥረት እንመልከት፤ አቡ ሁረይራ (ረ.ዐ) በዘገቡት ሐዲስ አቡ በክር ሲድቅ (ረ.ዐ) ለመልክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ በማለት ጠየቁ፡- “ሳነጋና ሳመሽ የምለው ነገር አመላክተኝ፡፡” ነቢዩም (ሰ.ዐ.ወ) አሉ፡-*“በል! አላህ ሆይ ድብቁንም ግልጹንም ዐዋቂ የሆንከው፣ የሰማይና የምድር ፈጣሪ፣ የሁሉ ነገር ጌታና ባለቤት የሆንክ፣ ካንተ በስተቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፣ ከነፍሴ ተንኮል ባንተ እጠበቃለሁ፣ ከሸይጧንም ተንኮል፣ ከአጋሮቹም፡፡”* (አህመድና ቲርሚዚ ዘግበውታል፣ አልባኒ ትክክል ነው ብለዋል)

በአቡ ራሺድ አል-ሀድራኒ ዘገባ የሚከተለው ጭማሪ አለ፡- *“በነፍሴ ላይ ወንጀልን ከመዝገን፣ በሙስሊም ላይ ተንኮሌን ከመሳብም (ባንተ እጠበቃለሁ)፡፡”* (አት-ቲርሚዚ ዘግበውታል)

ኢማም ኢብኑል ቀይም እንዲህ ብለዋል፡-“ይህ ሐዲስ ከተንኮል፣ ከመነሻውና ከመድረሻውም መጠበቅን አካቷል፡፡ የተንኮል ሁሉ ምንጭ ነፍስ ወይም ሸይጧን ነው፡፡ ጥፋቱም በተግባሪው ላይ ይደርሳል ወይም በሙስሊም ወንድሙ ላይ

ይሸጋገራል፡፡ ይህ ሐዲስ ሁለቱንም የተንኮል መነሻዎችና መድረሻቸውንም አካቷል፡፡”[34]

ይህች ወሲያ ከሰዎች ሁሉ አላህን ፈሪ ከሆኑት ከሰዎች ሁሉ ለሚወዱት የተደረገች ናት፡፡ ተመካሪውም ጧትና ማታ ዘውትረውባታል፡፡ ይህም ዱዓ ነፍስን ተርቢያ ለማድረግ በጣም አስፈላጊ መንገድ መሆኑን ያመላክታል፡፡

ነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ) ድንቅ ሶሃቦቻቸውን ነፍሳቸውን ተርቢያ ያደርጉ ዘንድ የመከሩበት ዱዓ ይህ ብቻ አይደለም፡፡ ይልቁንም በሐዲስ መጻህፍት ውስጥ የዱዓ አርእስትን የከፈተ ሁሉ ነፍስን ተርቢያ በማድረግ ዙሪያ ትልቅ ድልብ ያገኛል፡፡

ተውፊቅ ለማግኘት ቁልፉ መንገዶች

ኢማም ኢብኑል ቀይም እንደሚሉት “ተውፊቅ ማለት አላህ በነፍስህ ላይ ላፍታም ሳይተውህ ሲቀር ነው፡፡ ረሳህ የሚባለው ደግም ባንተና በነፍስህ መካከል ሲተውህ ነው፡፡ የሁሉም ጥሩ ነገር መሰረቱ ተውፊቅ ሲሆን እርሱም በአላህ እጅ እንጅ በሰው እጅ አይደለም፡፡ ቁልፉም ዱዓ፣ ወደ እርሱም ድህነቱን አውቆ መቅረብ፣ በእውነት ተናንሶ መጠጋት፣ መከጀልና በፍርሃት ወደእርሱ መመለስ ናቸው፡፡ አንድ ባሪያ እነኝህን ቁልፎች ከተሰጠ በእርግጥም አላህ የጥሩ ነገርን በር ሊከፍትለት ፈልጓል ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ከነዚህ ቁልፎች ከነፈገው የጥሩ ነገር በሮች ሁሉ ዝግ ይሆኑበታል”[35] ዱዓ የጥሩ ነገር ቁልፍ እንደሆነ ሁሉ ተከታዮቻቸውም ተውፊቅን ነፍስን ከማከሚያ መሠረቶች አንዱ መሠረት አድርገው ይይዙ ነበር፡፡ የአቡ ረዋድ ልጅ አላህ ይዘንላቸውና ስለ እነርሱ እንዳወሩት፡- “ጣውስና ባልደረቦቹ ዐስር ከሰገዱ በኋላ ማንንም ሳያናግሩ በዱዓ መማፀናቸውን ይቀጥሉ ነበር፡፡”[36]

እርስ በእርሳቸው ስለሚያደርጉት ምክክር

[34] (ፈይዱል ቀዲር -4/521)

[35](አል ፈዋኢድ 127-128 -አል-ነጋኢስ)።

[36](ሲፈቱ ሰፍዋ 2/288)

ታቢዒዮች አላህ ሥራቸውን ይውደድላቸውና እርስ በእርሳቸው በዚህ ነፍስን በማነፅ መሠረታዊ ጉዳይ ላይ ይመካከሩ ነበር። ታዋቂው የመካ ሙፍቲ ዐጣእ ኢብኑ አቢ ረባህ ስለ ባልደረባቸው ጣውስ ሲናገሩ "ዐጣእ ሆይ! በሩን ባንተ ላይ ለዘጋብህና በእርሷም ላይ ግርዶሽ ላደረገባት ጉዳይህን አታቅርብ። ነገርግን በሩን እስከ ቂያማ እለት ለከፈተልህ፣ ሁልጊዜ እንድትጠይቀው ላዘዘህና መልስ ሊሰጥህ ዋስትና ለገባልህ ጉዳይህን አቅርብ" በማለት ይመክረኝ ነበር።[37]

በርግጥ ያ ምርጥ ትውልድ ዱዓ ተቀባይነት የሚያገኝበትን መንገዶች ጠንቅቀው እንደሚያውቅ አያጠራጥርም። ከነዚህም መካከል ሐላልን መመገብ፣ ተቀባይነት ያላቸውን የዱዓ ወቅቶች መምረጥ፣ ውዳሴን ማስቀደም፣ ዝምድናን የሚቆርጥ ዱዓ አለማድረግ የሚሉት ይገኙበታል። ብዙዎቹ ያልታደሉትን የዱዓ ተቀባይነት ምስጢር ለእኛ ምልክት ይሆነን ዘንድ ታቢዒዮች አብራርተውልናል። በእርሱም እንመራበታለን፣ ከእርሱ በኋላም ምላሹ ቅርብ መሆኑን እንድናውቅ ወይም ተቀባይነት ካላገኘም መቀበል እንድንችል ይረዳናል። አንድ ሰው ታዋቂው የየመን ታቢዒይ ሀፊዝ ጣውስ ኪሳኒ ዘንድ በመምጣት "አላህን ለምንልን" አለው። "ልቤ ላይ ላንተ ዱዓ ማድረግ የሚያስችለኝ የአላህ ፍራቻ አላገኘሁም"[38] በዚህ መልሳቸው ለማለት የፈለጉት ሁለት ጉዳዮችን ነው። የመጀመሪያው ጠያቂው በራሱ መጠየቅን እንዲማርና በአላህና በባሪያው መካከል ግርዶሽ የሌለ መሆኑን እንዲያውቅ ነው። ሁለተኛው ደግሞ እርሳቸው ዘንድ ሰዎች በመምጣት ዱዓ እንዲያደርጉላቸው ስለጠየቁ ነፍሳቸው እንዳትታለል ተርቢያ ሊያደርጓት ስለፈለጉ ነው። እዚህም ጋር በንግግራቸው አልዋሹም፤ በርግጥም እውነተኛ የአላህ ፍራቻ ለተቀባይነት ወሳኝ መስፈርት ሲሆን ብዙ ሰዎች ለዱዓቸው ተቀባይነት ማጣት ምክንያት መሆኗን አይረዱም።

ታቢዒዩ ሣቢት አል-በናኒ ስለ አንድ የአላህ አገልጋይ ባሪያ ንግግር ሲናገሩ "እኔ ጌታዬ ልመናዬን ሲቀበለኝ አውቀዋለሁ!" አሉ። በንግግሩም በመገረም 'ጌታህ ሲቀበልህ ታውቃለህን?' አሉት። "አዎ!" አለ። 'እንዴት ታውቃለህ?' አሉት። "ልቤ ሲፈራ፣ ቆዳዬ ሲኮማተር፣ አይኔ እንባ ስታዘንብና ዱዓ ሲከፈትልኝ

[37](አስራሩል ኢስቲጃባህ)
[38](ሲየር አዕላሙ ነብላእ 5/42)

እንደተቀበለኝ አውቃለሁ" በማለት መለሰ። (ሲፈቱ ሰፍዋ 3/261)። ይህ ምስጢር ባጠቃላይ ዐጣእ ለዚያ ሰው ከመለሱለት መልስ ውስጥ ይካተታል። ከፊሎቹ መስፈርቶች ደግሞ የሙእሚኖች መሪ ዑመር ኢብኑል ኸጣብ (ረ.ዐ) የተናገሩትን ያረጋግጣል፡- "እኔ ዱዓዬ መልስ ስለማግኘቱ አልጨነቅም። ይልቁንስ ጭንቀቴ ዱዓ ስለማድረጌ ነው። ዱዓ ከተከፈተልኝ ተቀባይነቱ አብሮት እንደሚመጣ አውቃለሁ።"[39]

ከአስገራሚ ዱዓዎቻቸው

ጣውስና ሳቢት አል-በናኒ ባወሱት አላህን ጠንቅቆ የመፍራት ምስጢር ከማወቅ የተነሳ አላህ አስገራሚ ዱዓዎችን ይከፍትላቸዋል። ዘይኑል ዓቢዲይን ያደርጉት ከነበረው ዱዓ፡- "አላህ ሆይ! አይኖች በይፋ ሲያዩኝ ከማሳምረውና ከአይኖች ስሰወር ከማደረግው መጥፎ ነገር ባንተ እጠበቃለሁ። አላህ ሆይ! እኔ ሳጠፋ መልካም እንደምትውልልኝ ሁሉ ድንበር ስጥስም በእኔ ላይ እንድትመለስልኝ እጠይቅሃለሁ።"[40]

የበስራ አገር ታቢዒይ የነበሩት እውቁ ዛሂድ ጠለቅ ኢብኑ ሀቢብ ያደርጉት ከነበረው ዱዓ፡- "አላህ ሆይ! ካንተ የሚፈሩትን ሰዎች ዕውቀት፣ የአንተን ዓዋቂዎች ፍርሃት፣ ባንተ ተመኪዎችን የቂን፣ ባንተ የቂን ያላቸውን ሰዎች መመካት፣ ላንተ የሚተናነሱ ሰዎችን ተውበት፣ ወዳንተ ተመላሾችን መተናነስ፣ የታጋሾችህን ምስጋና፣ አንተ ዘንድ እድለኛ የሆኑትን መገናኘት እንድትለግሰኝ እጠይቅሃለሁ።"

ከነዚህ ሰዎች ዱዓ እያንዳንዱን ቃላት ብናስተነትን ከበስተጀርባ ትልቅ ዕውቀቶችንና ግልፅ አላህን የመፍራት ተግባራት መገብየት እንችላለን።

የመጨረሻ ጥያቄዎች

1. የዱዓን አስፈላጊነትናተሩፋት አብራራ።
2. የዱዓን ስርዓቶችን ጥቀስ።

[39](አል-ፈዋኢድ 127/128)
[40] (ሲየሩ አዕላሙ ነብላእ 4/396)

3. **የዱዓን ስርዓቶችን ምን ያህል እንደምትጠብቅ ራስህን ገምግም፡፡**

የመረጃ ምንጮች

1.	ፊዚላሊል ቁርአን	ሸሂድ ሰይድ ቁጥብ
2.	መንሃጁ ታቢዒይን ፊተርቢየቲ ነፍስ	ኡስታዝ አብዱልሃሚድ አል-በላሊ
3.	ኢህያእ ዑሉሙዲን	ኢማም አቡሃሚድ አል-ጋዛሊ
4.	ሙኽተሰር መንሀጁል ቃሲዲን	ኢማም ኢብኑ ቁዳመተ አል-መቀደሲ
5.	መንሀጁል ሙስሊም	ሸይኽ/ አቡበክር አል-ጀዛኢሪ
6.	ዛሂረቱል ደዕፊነፍሲ	ዶ/ር መጅዲ ሂላሊ
7.	አት-ተዝኪያ	ኡስታዝ ነቢል ሃሚድ አል-ሙዓዝ
8.	ሙሓሰበተነፍስ	ዶ/ር ሁሰይን ሸሃተሁ
9.	መሸሩዕ በርናሚጅ አል-ተርበዊይ ኢስላሚይሊኢስላሒነፍስ	ዶ/አበዱልሐይአል-ፈርማዊይ
10.	ረሳኢል (ደዕወቱና-ሙእተመርአል-ኻሚስ)	ኢማም ሸሂድ ሀሰን አል-በና
11.	ተፍሲሩል ቁርአኑል ዐዚም	አላመቱ ኢብኑ ከሲር
12.	አልጃሚዑል አህካሙል ቁርአን	አላመቱ ኢብኑ ከሲር
13.	ፈልነብደእ ቢአንፉሲና	ዶ/ መጅዲ ሂላሊ
14.	ሰይሩል አእላም አኑበላእ	ዘሀቢይ
15.	ሲፈቱ ሰፍዋ	ኢብኑል ጀውዚይ
16.	አል-ቢዳየቱ ወኒሃያ	አላመቱ ኢብኑ ከሲር

ምዕራፍ ሰባት

የእስልምና የዕውቀት ምንጭ

አጠቃላይ ዓላማ

*የመጀመሪያው አጠቃላይ ዓላማ፦*እስልምናን ከምንጮቹ (ከቁርአንና ከሱንና) ሊገነዘብ፣ ከዲን ምሁራን በሚያምንበት ምሁር ቃል በቃል ትምህርት በመውሰድ የመልእክተኛውን (ሰ.ዐ.ወ) ፈለግ ሊከተል፤

ዝርዝር ዓላማ

1. የእስልምናን የዕውቀት ምንጭ ግልፅ እንዲያደርግ ማስቻል።
2. እስልምናን ለመገንዘብ ከርሱ የተሻለ ዕውቀት ባለው ሰው መታገዝ ወሳኝ መሆኑንን እንዲያብራራ ማስቻል።
3. እስልምናን ከምንጩ ለማወቅ አላህን ፈሪና በእውቀቱ የተሻለ መሆኑን በሚያምንበት ሰው እንዲታገዝ ማስቻል።
4. በማንኛውም ሁኔታው የመልእክተኛውንና የቀደምት መልካም የአላህ ባሮች ፈለግ በተግባር እንዲከተል ማስቻል።
5. ምሉዕ የሆነ ሒባዳን እንዲተገብር ማስቻል።

የመጀመሪያው ዓላማ

የእስልምናን የዕውቀት ምንጭ ግልፅ ማድረግ

የትምህርቱ ዓላማ

1. እስልምናን ለመገንዘብ የመጀመሪያውን የዕውቀት ምንጭ ግልፅ ማድረግ
2. እስልምናን ለመገንዘብ የሁለተኛውን የዕውቀት ምንጭ ግልፅ ማድረግ

እስልምና ሃይማኖታዊ የመረጃ ምንጩ መለኮታዊ ራዕይ (ወሕይ) መሆኑ ከሌሎች ሃይማኖቶች ልዩ ያደርገዋል። ይህ እምነት በአላህ ብርሀን ተሞልቷል፤

﴿ وَكَذَٰلِكَ أَوۡحَيۡنَآ إِلَيۡكَ رُوحٗا مِّنۡ أَمۡرِنَاۚ مَا كُنتَ تَدۡرِي مَا ٱلۡكِتَٰبُ وَلَا ٱلۡإِيمَٰنُ وَلَٰكِن جَعَلۡنَٰهُ نُورٗا نَّهۡدِي بِهِۦ مَن نَّشَآءُ مِنۡ عِبَادِنَا ﴾ الشورى: ٥٢

"እንደዚሁም ወዳንተ ከትእዛዛችን ሲኾን መንፈስን (ቁርአንን) አወረድን፤ መጽሐፉም እምነቱም ምን እንደ ኾነ የምታውቅ አልነበርክም፡ ግን (መንፈሱን) ከባሮቻችን የምንሻውን ሰው በርሱ የምንመራበት ብርሃን አደረግነው...." (አሽ-ሹራ: 52)

መለኮታዊ ራዕይ (ወሕይ) አላህ በቁርአንና በሱንና ያወረደው ነው። በቁርአን የወረደው ማለት በቃልም በትርጉምም ከአላህ የወረደውን ሲሆን በሱንና የወረደው ማለት ደግሞ ቃል በቃል ሳይሆን በትርጉም ደረጃ ከአላህ የወረደውን ማለት ነው። የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- *"አጥብቃችሁ እስክያዛችሁት ድረስ ከኔ በኋላ በጭራሽ የማትሳሳቱበትን ነገር ትቼላችኋለሁ፤ የአላህን መጽሐፍ (ቁርአን) እና ሱናዬን (ፈለጌን)"*። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

﴿ وَأَطِيعُواْ ٱللَّهَ وَٱلرَّسُولَ لَعَلَّكُمۡ تُرۡحَمُونَ ﴾ آل عمران: ١٣٢

"ይታዘንላችሁም ዘንድ አላህንና መልእክተኛውን ታዘዙ" (አል-ዒምራን: 132)

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ أَطِيعُواْ ٱللَّهَ وَأَطِيعُواْ ٱلرَّسُولَ وَأُوْلِي ٱلۡأَمۡرِ مِنكُمۡۖ فَإِن تَنَٰزَعۡتُمۡ فِي شَيۡءٖ فَرُدُّوهُ إِلَى ٱللَّهِ وَٱلرَّسُولِ إِن كُنتُمۡ تُؤۡمِنُونَ بِٱللَّهِ وَٱلۡيَوۡمِ ٱلۡأٓخِرِۚ ذَٰلِكَ خَيۡرٞ وَأَحۡسَنُ تَأۡوِيلًا ﴾ النساء: ٥٩

"እናንተ ያመናችሁ ሆይ አላህን ተገዙ፣ መልእክተኛውንና ከናንተም የስልጣን ባለቤቶችን ታዘዙ፤ በማንኛውም ነገር ብትከራከሩ በአላህና በመጨረሻው ቀን የምታምኑ ብትኾኑ (የተከራከራችሁበትን ነገር) ወደ አላህና ወደ መልእክተኛው መልሱት፤ ይህ የተሻለ መጨረሻውም ያማረ ነው፡" (አን-ኒሳእ: 59)

﴿ وَمَن يُطِعِ ٱللَّهَ وَٱلرَّسُولَ فَأُوْلَٰٓئِكَ مَعَ ٱلَّذِينَ أَنۡعَمَ ٱللَّهُ عَلَيۡهِم مِّنَ ٱلنَّبِيِّـۧنَ وَٱلصِّدِّيقِينَ وَٱلشُّهَدَآءِ وَٱلصَّٰلِحِينَۚ وَحَسُنَ أُوْلَٰٓئِكَ رَفِيقٗا ﴾ النساء: ٦٩

"አላህንና መልእክተኛውንም የሚዘዝ ሰው ከነዚያ አላህ በነርሱ ላይ ከለገሰላቸው ከነቢያት፣ ከጻድቃንም፣ ከሰማእታትም፣ ከመልካሞቹ ጋር ይሆናሉ፡፡ የነዚያም ጓደኝነት አሚ" (አን-ኒሳእ: 69)

﴿ وَمَآ ءَاتَىٰكُمُ ٱلرَّسُولُ فَخُذُوهُ وَمَا نَهَىٰكُمْ عَنْهُ فَٱنتَهُوا۟ ﴾ الحشر: ٧

"...መልእክተኛው የሰጣቸሁን (ማንኛውንም) ነገር ያዙት ከርሱም የከለከላችሁን ነገር ተከልከሉ..." (አል-ሐሽር: 7)

﴿ مَّن يُطِعِ ٱلرَّسُولَ فَقَدْ أَطَاعَ ٱللَّهَ ۖ وَمَن تَوَلَّىٰ فَمَآ أَرْسَلْنَٰكَ عَلَيْهِمْ حَفِيظًا ﴾ النساء: ٨٠

"መልእክተኛውን የሚዘዝ ሰው በርግጥ አላህን ታዘዘ፡፡ ከትእዛዝም የሸሸ ሰው (አያሳስብህ)፤ በእነርሱ ላይ ጠባቂ አድርገን አልላክንህምና፡፡"

(አን-ኒሳእ: 80)

﴿ وَأَطِيعُوا۟ ٱللَّهَ وَأَطِيعُوا۟ ٱلرَّسُولَ وَٱحْذَرُوا۟ ۚ فَإِن تَوَلَّيْتُمْ فَٱعْلَمُوٓا۟ أَنَّمَا عَلَىٰ رَسُولِنَا ٱلْبَلَٰغُ ٱلْمُبِينُ ﴾

"አላህንም ተገዙ፤ መልእክተኛውንም ታዘዙ፤ ተጠንቀቁም፤ ብትሸሹም በመልእክተኛችን ላይ ያለበት ግልፅ ሙድረስ ብቻ መሆኑን እወቁ፡፡"

(አል-ማኢዳህ: 92)

ቁርአንና ሱንና በጋራ የእስልምና ድንጋጌዎችን ለማወቅም ሆነ ስለዐቂዳና ኢስላማዊ አተያዮች፣ ስለ ዒባዳ እና ህግጋት፣ ስለ ሥነ-ምግባርና አዳቦች እንዲሁም ስለ ተለያዩ የሕይወት ዘርፎች ለማስተማር ብቸኛ የመረጃ ምንጮች ናቸው፡፡ ለዚህም ነው በማንኛውም ሙስሊም ላይ ቁርአንና ሱንናን በትክክለኛ መልኩ መረዳት ግድ የሚሆንበት፡፡ ይህን ጉዳይ በሚከተሉት ክፍሎች የበለጠ ለማብራራት እንሞክራለን፡፡

1. እስልምናን ለመረዳት የመጀመሪያው የመረጃ ምንጭ (ቁርአን)

ቁርአን የአላህ ቃል ሲሆን ይህም ቃል ታማኝ በሆነው መልአክ (ጂብሪል) አማካኝነት ሙሐመድ ኢብን ዐብዱላህ ልብ ላይ በዐረብኛ ቋንቋ የሰፈረ፣ መልእክቱ እውነት የሆነ፣ ከዚህ በፊት ለተላኩ መልክተኞች መስካሪ፣ ለሰው ልጆች

የሕይወት መመሪያ፣ እርሱን በማንበብ ወደ ጌታቸው መቃረቢያ፣ በሁለት የመጽሐፍ ሽፋኖች መካከል ተመዝግቦ ያለ፣ በፋቲሐ ምዕራፍ ጀምሮ በአን-ናስ ምዕራፍ የሚጨርስ፣ ከትውልድ ትውልድ አስተማማኝ በሆነ መልኩ በጽሑፍና በንግግር ወደ እኛ የተላለፈ፣ ከማንኛውም አይነት ክለሳና ብረዛ የተጠበቀ፣ 'እኛው አውርደነዋል እኛም እንጠብቀዋለን' በማለት በአል-ሒጅር ምዕራፍ አንቀጽ 9 ላይ የተገለፀውን የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ያረጋገጠ ነው።

ቁርአን በቃላቱም ሆነ በይዘቱ ከአላህ (ሱ.ወ) የተወረደ መለኮታዊ ራእይ (ወሕይ) ነው።

﴿ وَإِنَّهُۥ لَتَنزِيلُ رَبِّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ١٩٢ نَزَلَ بِهِ ٱلرُّوحُ ٱلۡأَمِينُ ١٩٣ عَلَىٰ قَلۡبِكَ لِتَكُونَ مِنَ ٱلۡمُنذِرِينَ ١٩٤ بِلِسَانٍ عَرَبِيّٖ مُّبِينٖ ١٩٥ ﴾ الشعراء: ١٩٢ - ١٩٥

"እርሱም (ቁርአን) በእርግጥ ከዓለማት ጌታ የተወረደ ነው። እርሱን ታማኙ መንፈስ (ጅብሪል) አወረደው። ከአስፈራሪዎቹ (ነቢያት) ትሆን ዘንድ በልብህ ላይ (አወረደው)፣ ግልጽ በሆነ ዐረብኛ ቋንቋ።"

(አሽ-ሹዐራእ: 192-194)

መልክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ስለ ቁርአን እንዲህ ብለዋል፡-"(ቁርአን) በውስጡ ከበስተፊታችሁ የነበረን ዜና የያዘ፣ ከናንተ በኋላ ስለሚመጣው የሚናገር፣ በመካከላችሁ የሚፈርድ፣ ዛዛታ የሌለበትና እውነትን ከውሸት የሚለይ፣ በእርሱ የኮራን (የተወን) አላህ ረግሞታል፣ ከእርሱ ውጭ መቀናትን የፈለገን አላህ አጥምሞታል። ቁርአን የአላህ ጥብቅ ገመድ ነው፤ ግልፅ የሆነ የአላህ ብርሃን፣ የጥበበኛው (አላህ) ግሳፄና ቀጥተኛ ጎዳና፣ ስሜቶች (ወደ መጥፎ) የማይዘነበሉበት፣ ንግግሮች የማይቀላቀሉበት (ገር የሆነ)፣ አመለካከቶች የማይለያዩበት፣ የዕውቀት ባለቤቶች የማይጠግቡት፣ አላህን ፈሪዎች የማይሰለቹት፣ ጥፍጥናው ከመደጋገም ብዛት የማይሻር፣ ተአምራቱ የማያልቅ፣ አጋንንት እንደሰሙት *'አሰደናቂ የሆነን ቁርአን ሰማን፣ ወደ ቀጥተኛ መንገድ የሚመራ፤ በርሱም አመንን'* (አል-ጂን፡ 2) በማለት የተጣደፉለት፣ የያዘው ዕውቀት ሁሉን የቀደመ፣ በርሱ የተናገረን እውነተኛ የሚያደርግ፣ በርሱ የፈረደን ፍትሃዊነትን የሚያጎናፅፍ፣ በርሱ የሠራን የሚያስመነዳ፣ በርሱ ጥሪ ያደረገን ወደ ቀጥተኛው መንገድ የሚያስመራ ነው"

“ቲርሚዚ ከዘገቡት በከፊል የተወሰደ. ገፅ 149...ቁርጡቢም ጃሚዑል አህካም በሚለው ኪታባቸው ላይ ይህንኑ አመላክተዋል”

በርግጥ የብዙ ልዩ ባህሪያት ባለቤት የሆነውን የአላህን ኪታብ ማንስ ሊያካብበው ይችላል?

2. እስልምናን ለመረዳት ሁለተኛው የመረጃ ምንጭ (ሱንና)

ቁርአን እስልምናን ለመረዳት የመጀመሪያ ምንጭ ሲሆን የተቀደሰው ሱንና ደግሞ ሁለተኛው የሸሪዓ ምንጭ ነው፡፡ ይህንንም አላህ (ሱ.ወ) በነጅም ምዕራፍ አንቀጽ 3 እና 4 ላይ እንዲህ በማለት ያረጋግጣል፡-

﴿ وَمَا يَنطِقُ عَنِ ٱلۡهَوَىٰٓ ۝٣ إِنۡ هُوَ إِلَّا وَحۡيٞ يُوحَىٰ ۝٤ ﴾ النجم: ٣ - ٤

“ከልብ ወለድም አይናገርም እርሱ (ንግግሩ) የሚወረድ ራእይ እንጅ ሌላ አይደለም” (አን-ነጅም፡ 3-4)

﴿ وَمَآ ءَاتَىٰكُمُ ٱلرَّسُولُ فَخُذُوهُ وَمَا نَهَىٰكُمۡ عَنۡهُ فَٱنتَهُواْۚ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ ﴾ الحشر: ٧

“መልክተኛው የሰጣቸሁን (ማንኛውንም) ነገር ያዙት ከርሱም የከለከላችሁን ነገር ተከልከሉ” (አል-ሐሽር: 7)

ሱንና የመለኮታዊ ራእይ አካል ነው፡፡ ይህንን አስመልክቶ ሱዩጢ ሚቅዳም ኢብን መዕድ የክሪብን ጠቅሰው ትክክለኛ በሆነ ዘገባ እንዳወሩት የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- *“እዎጅ (እወቁ) እኔ ቁርአንንና ከርሱም ጋር የርሱን አምሳያ የሆነውን(ሱናን) ተሰጥቻለሁ!!”*

ሱንና ቁርአንን ለማብራራት ይረዳል፡-

﴿ وَأَنزَلۡنَآ إِلَيۡكَ ٱلذِّكۡرَ لِتُبَيِّنَ لِلنَّاسِ ﴾ النحل: ٤٤

“ለሰዎች ወደ እነርሱ የተወረደወን (ፍቺ) ትገልፅላቸው ዘንድ ዚክርን (ቁርአንን) ባንተ ላይ አወረድን፡፡” (አን-ነሕል: 44)

ሱንና፡ ንግግር፣ ተግባርም፣ ዉሳኔም ነዉ

ሱንና ምን እንደሆነ ለመረዳት እንድንችል የሚከተለውን ገለፃ እንመልከት፡፡ “ሱንና ፈለግና ታሪክ ነው፤ እርሱ ነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ)በንግግርም ይሁን በተግባር ያዘዙት ወይም የከለከሉት ወይም የፈቀዱት ወይም በተከበረው ቁርአን ያልተጠቀሰም ቢሆን ያረጋገጡት ነገር ነው፡፡ ለዚህም ነው በሸሪዓው ቁርአንና ሐዲስ ለማለት ኪታብና ሱንና ተብሎ የሚገለፀው፡፡”[41]

በሌላ ገለፃ ሱንና ማለት ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የተወሰደ ማንኛውም ንግግር ወይም ተግባር ወይም ማረጋገጫ ነው፡፡ ከንግግር ምሳሌ “ሥራ የሚለካው በሐሳብ (ኒይያ) ነው” በማለት የተናገሩትን፣ ከተግባር ምሳሌ ባልደረቦቻቸው ዒባዳንም ሆነ ሌሎች ጉዳዮችን አስመልክቶ ከርሳቸው የወሰዱትን፣ ማረጋገጥን አስመልክቶ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በበኒ ቁረይዛ ዘመቻ ወቅት የዐስርን ሰላት አስመልክቶ ባልደረቦቻቸው ያደረጉትን ኢጅቲሃድ ማረጋገጣቸውና ለኻሊድ ብኑ ወሊድ የእንሸላሊት ስጋ መብላት ክልክል እንዳልሆነ ያረጋገጡለትን መጥቀስ ይቻላል፡፡[42]

የሱንና ሸሪዓዊ ማስረጃነት

ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የተወሰደ ማንኛውም ንግግር ወይም ተግባር ወይም ማረጋገጫ፣ ንግግሩ ወይም ተግባሩ እንዲፈፀም አስበውበት እስከሆነ ድረስና ታማኝ ከሆነ ዘጋቢ በትክክለኛ መልኩ መዘገቡ የተረጋገጠ መሆኑ ከታወቀ ይህ ሐዲስ በሙስሊሞች ላይ ሸሪዓዊ ማስረጃ ተደርጎ መወሰድ እንደሚችልና ኢስላማዊ ህግጋትን መመራመር (ኢጅቲሃድ ማድረግ) ለሚችሉ ምሁራኖች እርሱን መነሻ በማድረግ አዳዲስ ህግጋትን ሊያወጡ እንደሚችሉ ሙስሊሞች ሁሉ ተስማምተውበታል፡፡ በሌላ አገላለጽ ከሱንና የተገኙ ድንጋጌዎች ከቁርአን ድንጋጌዎች ጋር በጋራ ተፈፃሚና ሊከተሏቸው ግዴታ የሆኑ ኢስላማዊ ህግጋት ናቸው፡፡[43]

---

[41]አን-ኒሃያ ፊ ገሪቢል ሐዲስ ወልአሠር 2/409
[42] አስ-ሲባዒይ፣ አሰ-ሱንናህ ወማከነቱሃ ፊ አት-ተሽሪይዕ አል-ኢስላሚይ፣ ገጽ 47
[43](ኢልሚል ኡሱል ፊቅህ)

ሱንና ከቁርአን ጋር ያለው ትስስር

1. ሸሪዓዊ ማስረጃነትን በተመለከተ ሱንና ከቁርአን በሁለተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ይህም ማለት አንድ ሙጅተሂድ ፍርድ ሊሰጥበት ላሰበው ጉዳይ ከቁርአን ግልፅ የሆነ ማስረጃ ካላጣ በስተቀር ቀድሞ ወደ ሱንና ማስረጃነት ሊሄድ አይገባም፡፡

2. ከሐዲስ የሚገኙ ድንጋጌዎች ከሚከተሉት ሦስት አይነት ሁኔታዎች ሊወጡ አይችሉም፡-

   - አንዳንድ ሐዲሶች በቁርአን ውስጥ የተጠቀሱ ትእዛዛትና ክልከላዎችን የሚደግፉ ሆነው ይገኛሉ፡፡ በዚህን ወቅት ሁለቱንም ማለትም ከነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ) የተገኙ ሱናዎችንና ከቁርአን የተገኙትን ማስረጃዎች እንደመረጃ በመጠቀም ፍርድ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ለምሳሌ ከሽርክ ስለመከልከል፣ ለወላጆች በጎ ስለመዋል፣ ከሐሰት ምስክርነት ስለመከልከልና ያለ ሐቅ ነፍስ ማጥፋት ክልክልነት በመሳሰሉ ጉዳዮች፣

   - ከፊሎቹ ሐዲሶች ደግሞ በቁርአን ውስጥ ጥቅል ሆኖ የመጣውን ነገር በዝርዝር ለማብራራት ወይም በቁርአን ውስጥ ልቅ የሆነን ነገር ውስን ለማድረግ (ለመገደብ) ወይም በቁርአን ውስጥ ለአጠቃላይ የተወሳውን ነገር ለተወሰነ ሁኔታ ብቻ እንዲውል ለማድረግ የመጡ ይሆናሉ፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ለየአላህ መልዕክተኛ(ሰ.ዐ.ወ) ቁርአንን ተገቢ በሆነ መልኩ በዝርዝር የማብራራት ችሎታ ችሯቸዋል፡-

﴿وَأَنزَلۡنَآ إِلَيۡكَ ٱلذِّكۡرَ لِتُبَيِّنَ لِلنَّاسِ﴾ النحل: ٤٤

"ለሰዎች ወደ እነርሱ የተወረደውን (ፍቺ) ትገልጽላቸው ዘንድ ዚክርን (ቁርአንን) ባንተ ላይ አወረድን፡፡" (አን-ነሕል: 44)

ለዚህ እንደምሳሌ ስለ ሶላት አሰጋገድ፣ ስለ ዘካ አወጣጥና ስለ ሐጅ ሥነ-ሥርዓት የሚያብራሩ ሐዲሶች ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ ቁርአን ሰላትን መስገድ ግዴታ እንደሆነ፣ ዘካ ማውጣት ግዴታ መሆኑንና የአላህን ቤት መጎብኘት ግዴታነት ይናገር እንጅ ስለ ሶላት የሩኩዕ ቁጥርም ይሁን ስለ ዘካ ስሌት ወይም ስለ ሐጅ ተግባራት በዝርዝር ያወሳው ነገር የለም፡፡ ነገር ግን የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተግባራዊና

ንግግራዊ ሱናዎች እነዚህን ጥቅል ጉዳዮች በዝርዝር አብራርተዋል፡፡ እንደዚሁም አላህ (ሱ.ወ) በቁርአን ውስጥ ግብይት የተፈቀደ መሆኑንና ወለድ(ሪባ) ደግሞ ክልክል መሆኑን ደንግጓል፡፡ ይሁን እንጂ ትክክለኛ የሆነው ግብይት የትኛው እንደሆነና ክልክል የሆነው የግብይት አይነት ምን እንደሚመስል በዝርዝር ያሳወቀን የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሱንና ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) የርሱ ስም ሳይወሳበት ሞቶ የተገኘ ነገር መብላት ክልክል መሆኑን በቁርአን ይገልፃል፡፡ ነገር ግን ይህ ክልከላ በባህር ውስጥ የሚኖሩ እንሰሳት ሆነው የሞቱትን እንደማያጠቃልል ያብራራልን የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሱንና ነው፡፡ እንደዚሁ ሌሎች ሱናዎችም በቁርአን ውስጥ ጥቅል፣ ልቅና አጠቃላይ የሆኑ ድንጋጌዎች በማብራራት የቁርአን ማሟያና ከእርሱ ጋር የተያያዙ ሆነው ይገኛሉ፡፡

- አንዳንድ ሐዲሶች ደግሞ በቁርአን ውስጥ በምንም መልኩ መረጃ ያልተጠቀሰበትን ጉዳይ የሚያወሱ ይሆናሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ሐዲሶቹ በራሳቸው ፅኑና የህግ ምንጭ ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ አንዲትን ሴት ከእናቷም ይሁን ከአባቷ እህት ጋር አብሮ ማግባት እንደማይፈቀድ፣ ከራንቻ ጥርስ ያላቸውን ማንኛውም የዱር እንሰሳትና ረጅም ጥፍር ያላቸውን አእዋፋት መብላት እንደማይፈቀድ፣ የሀር ልብስ መልበስና ለወንዶች ከወርቅ የተሠራ ቀለበት ማድረግ እንደማይፈቀድ፣ “በስጋ ዝምድናነት ክልክል የሆነ ሁሉ ለጥቢ ዝምድናም ክልክል እንደሚሆን”ና ሌሎችም በሱና ብቻ የተደነገጉ ጉዳዮች ምንጫቸው አላህ (ሱ.ወ) ለመልክተኛው የገለጸላቸው ወይም በራሳቸው ምርምር (ኢጅቲሃድ) ያደረጉት እንደሆነ ልንረዳ ይገባል፡፡

ከዚህ እንደምንገነዘበው በቁርአንና በሱና ድንጋጌዎች መካከል ምንም አይነት ልዩነትም ይሁን ተቃርኖ ሊኖር እንደማይችል ነው፡፡[44]

የሱናን ደረጃዎች (ሐላል-ሐራም-መንዱብ-ሙባህ-መክሩህ) በሚገባ ለመረዳት የሚቻለው ከታማኝ የሐዲስ ዘጋቢዎች መሆን ይኖርበታል፡፡ ኢማም ሸሂድ ሐሰን አል-በና በኡሱል አል-ዒሽሪን ላይ እንዳመላከቱት፡

[44] ዒልሙ ኡሱሉ-ል-ፊቅህ፣ ዶ/ር ዐብዱልወሃብ ኸላፍ

“የተከበረው ቁርአንና የተቀደሰው ሱና የእስልምናን ድንጋጌዎች ለመረዳት የሁሉም ሙስሊም የመረጃ ምንጮች ናቸው።ቁርአንን ምንም አይነት ጫናና መዛነፍ ሳይኖርበት በአረብኛ ቋንቋ ሥርዓት መሠረት መረዳት ሲቻል የተቀደሰውን ሱና ለመረዳት ደግሞ ወደ ታማኝ የሐዲስ ዘጋቢዎች መመለስ አስፈላጊ ነው።”

የመጨረሻ ጥያቄዎች

1. እስልምናን ለመገንዘብ የመጀመሪያው የመረጃ ምንጭ_____ሲሆን ሁለተኛው የመረጃ ምንጭ ደግሞ_____ነው።

2. ቁርአን _____ ሲሆን ሱና ደግሞ_____ ነው።

3. ሱና ምን እንደሆነ፣ ሸሪዓዊ ማስረጃነቱንና ከቁርአን ጋር ያለውን ትስስር አብራራ።

የሁለተኛው አጠቃላይ ዓላማ

እስልምናን ለመገንዘብ በዲን ፅሁቀት በተሻሉ ሰዎች መታገዝ እስፈላጊ ስለመሆኑ

ዝርዝር ዓላማ

1. ዑለማኦች በዲኑ ያላቸውን ደረጃና ብልጫ እንዲያብራራ ማስቻል።
2. የዕውቀትንና የመማር አስፈላጊነት እንዲያብራራ ማስቻል።

አላህ(ሱ.ወ) በየዘመናቱ ለነበሩ ህዝቦች ያወረደላቸውን መልእክት ሙሉ በሙሉ ይገነዘቡ ዘንድ የላከላቸው መልክተኞችም በህዝባቸው ቋንቋ ተናጋሪዎች አድርጎ መሆኑን ልናውቅ ይገባል፡-

﴿ وَمَآ أَرۡسَلۡنَا مِن رَّسُولٍ إِلَّا بِلِسَانِ قَوۡمِهِۦ لِيُبَيِّنَ لَهُمۡ ﴾ إبراهيم: ٤

"ከመልክተኛ ማንኛውንም ለነርሱ ያብራራላቸው ዘንድ በወገኖቹ ቋንቋ እንጅ በሌላ አልላክንም ፡ ፡" (አብራሂም: 4)

﴿ كَمَآ أَرۡسَلۡنَا فِيكُمۡ رَسُولٗا مِّنكُمۡ يَتۡلُواْ عَلَيۡكُمۡ ءَايَٰتِنَا وَيُزَكِّيكُمۡ وَيُعَلِّمُكُمُ ٱلۡكِتَٰبَ وَٱلۡحِكۡمَةَ وَيُعَلِّمُكُم مَّا لَمۡ تَكُونُواْ تَعۡلَمُونَ ﴾ البقرة: ١٥١

"በወለጣቹሁ ከናንተው የኾነን አንቀጾቻችንን የሚነብላችሁና የሚጠራችሁ መጽሐፍንና ጥበብንም የሚስተምራችሁ ታወቁት ያልነበራችሁትን ነገር የሚሳወቃችሁ የኾነን መልክተኛ እንደላክን (ጸጋን ሞላንላችሁ)" (አል-በቀራህ: 151)

አላህ (ሱ.ወ) በፍጡራኑ ላይ ያለውን ፍላጎት ለማብራራት የመጀመሪያው አስተማሪ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ነበሩ። የማያውቁትን ያስተምሯቸዋል፣ ያልገባቸውን በመጠየቅ ያስረዷቸዋል፣ ሲሳሳቱ ያስተካክሏቸዋል።" *(የአምልኮ) ተግባራቸሁን ከእኔ ያዙ።"*

ዓማር (ረ.ዐ) እንዳወሩት “አንድ ቀን ጀናባ ሆኜ ውሃ አጣሁኝ፡፡ ሜዳ ላይ ተንከባለልኩና ሰገድኩኝም፡፡ ይህም ተግባሬ ለነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተነገራቸው፡፡ እንዲህ ብታደርጉም አኮ ይበቃ፣ ነበር አሉኝና መዳፎቻቸውን መሬት ላይ አሳረፉ፣ ከዚያም አቧራውን በትንፋሻቸው አራገፉና ፊታቸውን ከዚያም መዳፎቻቸውን አበሱ” (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)

ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሌላ ሐዲስ ደግሞ ዓዲይ ኢብኑ ሓቲም እንዲህ አሉ፡-

﴿ حَتَّىٰ يَتَبَيَّنَ لَكُمُ ٱلۡخَيۡطُ ٱلۡأَبۡيَضُ مِنَ ٱلۡخَيۡطِ ٱلۡأَسۡوَدِ مِنَ ٱلۡفَجۡرِ ﴾ البقرة: ١٨٧

“ከነህ የኾነው ነጩ ክርም ከጥቁሩ ክር ለናንተም እስከሚለጽላችሁ ድረስ” (አል-በቀራህ፡ 127)

የሚለው የቁርአን አንቀጽ በወረደ ጊዜ አንድ ጥቁር ቋጠሮና አንድ ነጭ ቋጠሮ አዘጋጅቼ ትራሴ ሥር አስቀመጥኩኝ፣ ከዚያም በሌሊት መመልከት ጀመርኩ ነገር ግን ሊለይልኝ አልቻለም፡፡ በማለዳም ወደ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ ሄድኩኝና ነገርኳቸው፡፡ እንዲህም አሉኝ ‘ያ ማለት እኮ የሌሊቱን ጨለማነትና የቀኑን ብርሃንነት ለማመልከት ነው፡፡’

ከዚህም በላይ ነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ) አንድ ሰው ወደ እርሳቸው ካልሆነም ወደ አንድ ሌላ ዓሊም ዘንድ በመሄድ ዕውቀት ሳይቀስም በራሱ ስሜት ፈትዋ ሲሰጥ ካዩ ይቆጡ ነበር፤ ድርጊቱንም ይጠሉ ነበር፡፡ ጃቢር (ረ.ዐ) ባወሩት ሐዲስ ለጉዞ በወጣንበት ከመካከላችን አንዱ ሰው ከግመሉ ላይ ወድቆ ድንጋይ መታውና እራሱ ተፈነከተ፡፡ ከዚያም ኢህቲላም ሆነ (በህልሙ ግንኙነት ሲያደርግ አየ)፡፡ ከዚያም ጓደኞቹን ተየሙም በማድረግ (ሰውነቴን ከሙሉ ትጥበት እንድተው) ልታግራሩልኝ ይቻላልን? በማለት ጠየቃቸው፡፡ እነርሱም አንተ መታጠብ ስለምትችል ምንም አይነት ማግራራት ልናገኝልህ አንችልም አሉት፡፡ እርሱም ታጠበና በዚያው ምክንያት ሞተ፡፡ ወደ አላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) በተመለስን ጊዜ ይህ ጉዳይ ተነገራቸው፡፡ እርሳቸውም ‘ገደሉት! አላህ ይግደላቸው፤ ካላወቁ አይጠይቁም ነበርን? ላለማወቅ መድሃኒቱ መጠየቅ ነው፣ ተየሙም ማድረግ ይበቃው ነበር ወይም ደግሞ ቁስሉን በቁራጭ ጨርቅ በማሰር በውሃ ካበሰ በኋላ

የቀረውን ሰውነቱን መታጠብ ይችል ነበር።' አሉ። (አቡ ዳዉድ፣ ኢብን ማጃህና ዳረ ቁጥኒይ ዘግበውታል፣ ኢብኑ ሰኪን ሶሂህ ነው ብለዋል።)

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- *'ከእናንተ መካከል ፈትዋ ለመስጠት የሚቀድም እሳት ለመግባትም ቀዳሚ ነው።'*

ዕውቀትን የፈለገ ከዲኑ ታላላቅ መሪዎች (አኢማዎች) አንዱን ሊከተልና ከእርሱም ቃል በቃል ትምህርት ሊወስድ ይገባል። ይህን መንገድ ነው ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከርሳቸው በኋላ ለነበሩት ሰለፎች ያወረሱት፣ እነርሱም እንዲሁ ለተከታዮቻቸው፣ ተከታዮቻቸውም ለተከታዮቻቸው፣ አስከ ዕለተ ትንሳኤ ድረስ። ይህ ነው እንግድህ የማይቀየር የሆነውና ከአላህ ሱናዎች መካከል አንዱ መንገድ።

1. የዑለማዎች ደረጃና ብልጫቸው

ዑለማዎች የነቢያት ወራሽ ናቸው

ዑለማዎች ከአላህ መልዕክተኛ(ሰ.ዐ.ወ) በኋላ ወደ እስልምና በቀጣይነት የመጣራትን (ዳዕዋ ማድረግ)፣ ግልፅ የማድረግን፣ የማብራራትና እንዲሁም የማስተማርን ኃላፊነት የወረሱ ናቸው። የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- *"አላህ የተሻለ ነገርን የሻለት ሰው በዲን ጥልቅ ግንዛቤን ይቸረዋል፣ ዕውቀት ደግሞ በመማር ነው፣ ዓዋቂዎች የነብያት ወራሾች ናቸው። ነቢያት (የአላህ ሰለዋት በነርሱ ላይ ይውረድና) ዲናርንም ይሁን ዲርሃምን ኣያወርሱም፣ እነርሱ በርግጥ የሚያወርሱት ዕውቀትን ነው፣ ዕውቀትን የያዘ ትልቅ እድልንና ሙሉ የሆነ ነገርን ይዟል።"*

በማንኛውም ጉዳይ የአላህን (ሱ.ወ) ድንጋጌዎች ከቁርአንና ሐዲስ ለመረዳት መዳረሻችን ዑለማኦች ሊሆኑ ይገባል። አላህ (ሱ.ወ) እንዳዘዘውም

﴿فَسْـَٔلُوٓاْ أَهْلَ ٱلذِّكْرِ إِن كُنتُمْ لَا تَعْلَمُونَ ٧﴾ الأنبياء: ٧

"ከአንተም በፊት ወደ እነሱ የምናወርደላቸው የኾኑን ሰዎችን እንጂ ሌላን አላክንም፡ የሚዝወቁም ብትኾኑ የመጽሐፉን ባለቤቶች ጠይቁ፡፡" (አል-አንብያእ፡ 7)

የሚለውን በተግባር ልናውለው ግድ ይለናል። ሰሐባዎችም ባጠቃላይ ይህንን ጉዳይ ተግባራዊ በማድረግ በወቅቱ የነበረው ህብረተሰብ ያልገባውን ነገር ይጠይቃቸውና እነርሱም መልስ ይሰጡ ነበር። ጥያቄ በመጠየቁ ምክንያት አንድንም ሰው አይነቅፉም ነበር። አንድን ጉዳይ የማያውቅ ሰው አላህን ከሚፈሩ ሰዎች ነው ብሎ ካላሰበ በስተቀር በዘፈቀደ ማንኛውንም ተራ ሰው ስለ ዲን ጉዳይ መጠየቅ አይፈቀድለትም። በሀገሩ ውስጥ በዲን ጉዳይ ተመራማሪዎች (ሙጅተሂዶች) ካሉ ከነርሱ መካከል የፈለገውን ሰው መጠየቅ ይችላል። የትኛው ሰው የተሻለ ነው ብሎ እነርሱን ማበላለጥ አይጠበቅበትም።

ዑለማዎች የዲኑ ጠባቂዎች ናቸው

ዑለማኦች በየዘመናቱ የሽሪዓ ተሸካሚዎችና ከፅንፈኞች ፅንፍ፣ ከአፈንጋጮች ማፈንገጥ፣ ከአጥፊዎች ጥፋት፣ ከአመጸኞችና ከከሃድያን ትግል የዲኑ ተከላካዮች ናቸው።

ከኢብኑ ዑመር (ረ.ዐ) እንደተወራው የአላህ መልዕክተኛ(ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡

“አላህ ዕውቀትን ለሰዎች ከሰጣቸው በኋላ የሚያነሳው ከነርሱ መንጭቆ በመውሰድ አይደለም፤ነገር ግን ዕውቀትን የሚያነሳው ዑለማኦችን በማንሳት(በሞት) ነው። አንድ ዐሊም በጠፋ ቁጥር ከርሱ ጋር ያለው ዕውቀትም አብሮ ይጠፋል፣በዚህ ሂደት መጨረሻ ላይ [ዐሊሞቹ ሁሉ ጠፍተው] የአላዋቂዎች(ጃሂሎች) ቁንጮ የሆኑት ብቻ ይቀሩና ፈትዋ ሲጠየቁ ያለዕውቀት መልስ ይሰጣሉ፣ ራሳቸው ጠመው ሌላውንም ያጠማሉ።” (ቡኻሪና ሙስሊም ተስማምተውበታል፣ ቡኻሪ ዒልሙል ሐዲስ በሚለው ክፍል ቁጥር 98)

ዑለማኦች ለሁሉም የዕውቀት አይነት መሠረት የጣሉና ይህም መሠረት እንዳይናጋ የርሱ ጠባቂዎች ናቸው። ከነርሱ መካከል እንደ አቡ ሐኒፋ፣ አህመድ ኢብኑ ሀንበልና ሻፊዒይ ያሉት የፊቅህ ጥልቅ አዋቂዎች ሲሆኑ እነዚህ ታላላቅ ዑለማዎች ስለዒባዳ እና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ግንዛቤ መሠረት የጣሉ ናቸው። እንደ ኢብኑ ተይሚያና ኢብኑል ቀይም ያሉት ዑለማዎች ደግሞ በዘመኑ ከድንበር ያፈነገጡና ጽንፈኝነትን የሚያራምዱ የሱፍያና የባጢኒያ ቡድኖች በሰፊው

መከተዋል፡፡ በዘመናችን ከነበሩት ዑለማዎች መካከል እንደ ኢማም ሐሰን አል-በና፣ ሸይኽ አል-ጋዛሊ፣ ሸይኽ ሸዕራዊ እና ሸይኽ ቀረዳዊ ያሉት ደግሞ ሰዎች እስልምናን እንዴት መረዳት እንዳለባቸው በሰፊው ያብራሩና በዘመናችን የሰዎችን አስተሳሰብ ችግር ውስጥ እያስገባና አዕምሮን እየሸረሸረ ያለውን የቁሳዊነት (Materialism) አስተሳሰብ አቀንቃኞች በከፍተኛ ሁኔታ የተጋፈጡ ናቸው፡፡

ዑለማዎችን ማክበር ወደ አላህ ያቃርባል

ዑለማዎችን ማክበር ወደ አላህ ከሚቃረቡም ባሻገር ከሸሪዓ አንፃር በራሱ ግዴታ ነው፡፡ ኢማም ጠሐዊ እንደሚሉት “ቀደምት የሰለፍ ዑለማዎችንም ሆነ ከነርሱ በኋላ ያሉ መልካምና ደጋግ የፊቂህ አዋቂዎች በጥሩ እንጅ በመጥፎ ሊነሱ አይገባም፡፡ እነርሱን በመጥፎ የሚያነሳ በአማኞች መንገድ ላይ አይደለም፡፡”

አስተያየት ሰጭዎች እንደሚሉት በማንኛውም ሙስሊም ላይ አላህንና መልእክተኛውን እንደሚወድ ሁሉ በቀጣይነትም አማኞችን ሊወድ ይገባል፡፡ በቁርአን ውስጥ በተለየ ሁኔታ እንደተብራራው እነዚያ የነቢያት ወራሽ የሆኑትንና ህብረተሰቡን በየብስም ሆነ በባህር ውስጥ ከጨለማ ወደ ብርሀን በመምራት ረገድ የኮከብነትን ደረጃ አላህ (ሱ.ወ) የሰጣቸውን ዑለማዎች ማክበር ግዴታ ነው፡፡

ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ከመላካቸው በፊት ለነበሩት ህዝቦች ዑለማዎቻቸው ከነርሱ ውስጥ በጣም ተንኮለኞቹ የነበሩ ሲሆን ሙስሊሞች ግን ዑለማዎቻቸው ከነርሱ መካከል በጣም ምርጦቹ ናቸው፡፡ የሙስሊሙ ኡምማ መሪዎች የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ምትኮች ሲሆኑ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ከሞቱ በኋላም ፈለጋቸውን ህያው ያደረጉና “እነርሱ መልዕክተኛው የተላከበትን መልእክት ቀድሞ በማድረስና ግልፅ ያልሆነውን በማብራራት በኩል ፈጣን ከመሆናቸው አኳያ ትልቅ ደረጃና ክብር እንድንሰጥ በእኛ ላይ ግደታ ይሆንብናል፡፡ አላህ ሥራቸውን ይውደድላቸው፣ እነርሱንም ይውደዳቸው፡፡” የተባለላቸው ናቸው፡፡ (ኡሱሉል አቂዳ ሊኢብኒልዐሊል-ዒዚ ገጽ ከ197-198 የተወሰደ)

ሸሂድ ሐሰን አል-በና እንዲህ ብለዋል “ደጋጎችን መውደድ፣ ለታወቁ መልካም ተግባራቶቻቸው እነርሱን ማክበርና ማሞገስ ወደ አላህ (ሱ.ወ) ከሚያቃርቡ መንገዶች ነው።”

አህነፍ (አላህ ሥራቸውን ይውደድለቸውና) እንደሚሉት “በዕውቀት ላይ ያልተገነባ ክብር ወደ ውርደት ማዘንበሉ አይቀርም”። አሊ (አላህ ሥራቸውን ይውደድለቸውና) እንዳሉት ደግሞ “ዓሊም ከጂሚ፣ ከሌሊት ሰጋጅና ከታጋይ ይበልጣል። አንድ ዓሊም በሞተ ጊዜ ከኢስላም በእርሱ ተሸፍኖ የነበረው ቀዳዳ ክፍት ይሆናል። የርሱን ክፍተት ሊሞላ የሚችለው የእርሱ ተተኪ ካለ ብቻ ነው።”

ዕውቀት የሚደያዘው ከዕውቀቱ ልዩ ባለቤቶች ነው

የዲን ዑለማዎች በዲኑ ዘርፍ የቆሙ ዘቦች ናቸው። ከመካከላችን በዱንያው ዘርፍ የህክምና፣ የምህንድስና፣ የሂሳብ ሥራ ወይም የፋብሪካ፣ የግብርና፣ የዕደ ጥበብ ጉዳዮች ቢገጥሙት በዚህ ሙያ ልዩ ዕውቀት ወዳላቸው ባለሞያዎች ይሄዳል። የዲን ዕውቀትን መማር ስንፈልግ በሸሪዓ ዘርፍ ዕውቀት ወዳላቸው ባለሞያዎች የማንሄደው ለምንድን ነው? እራሳችንን ለእነርሱ አስገዝተን ዕውቀትንና ግንዛቤን ለምን አንፈልግም? አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

﴿فَسْـَٔلُوٓاْ أَهْلَ ٱلذِّكْرِ إِن كُنتُمْ لَا تَعْلَمُونَ﴾ الأنبياء: ٧

“የሚያውቁ ከሆናችሁ የዕወቀት ባለቤቶችን ጠይቁ።” (አንቢያእ: 7)

كما قال تعالى ﴿فَسْـَٔلْ بِهِۦ خَبِيرًا﴾ الفرقان: ٥٩

“በጉዳዩ ዐዋቂን ጠይቅ።” (ፉርቃን: 59)

﴿وَلَا يُنَبِّئُكَ مِثْلُ خَبِيرٍ﴾ فاطر: ١٤

“እንደ ወሰጠ ዐዋቂው ማንም አይነግርህም።” (ፋጢር: 14)

ዑለማዎች *“ሐላልም ግልጽ ነው፣ ሐራምም ግልጽ ነው፣ በሁለቱ መካከል ግን አሻሚ ጉዳዮች አሉ ከሰዎች ብዙዎቹ አያውቋቸውም...”* በሚለው የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ንግግር ውስጥ የተንጸባረቁ ናቸው። ኢብኑ ረጀብ አል-ሐንበሊ

እንደሚሉት “የዚህ ሀዲስ ትርጉም ሐላል ግልጽ የሆነ ጉዳይ ነው፡፡ በውስጡ አሻሚነት የለበትም፡፡ ሐራምም እንደዚሁ ግልጽ ነው፡፡ ነገር ግን በነዚህ ሁለት ጉዳዮች መካከል ለብዙ ሰው ሐላል ነው ወይንስ ሐራም? በሚል አሻሚ የሆኑ ነገሮች አሉ፡፡ በዕውቀቱ ጥልቅ ግንዛቤ ያላቸው ዑለማዎች እነዚህ ጉዳዮች አሻሚ አይሆኑባቸውም፡፡ ከየትኛው ክፍል እንደሆኑ በቀላሉ ይለይዩዋቸዋል፡፡”

ኢማም አን-ነወዊይ አንደሚሉት “አሻሚ የሆነ ጉዳይ ማለት ሐላል ይሁን ሐራም ግልጽ ያልሆነ ማለት ሲሆን ይህ ደግም ብዙ ሰው የማያውቀውና ምን እንደሚያስወስንም የማይረዱት የሆነ ነው፡፡ ዑለማዎች ግን ራሱን በቀጥታ በመረዳት (ነስ) ወይም ጉዳዩን ከቁርአንና ከሌላ ሐዲስ ጋር በማዛመድ (ቂያስ) ካልሆነም የጉዳዩን ከዚህ በፊት መከሰትና በቀጣይም የመኖሩን ሁኔታ በማጤን (ኢስቲስሓብ) ወይም በሌላ መልኩ የነገሩን ሁከም ያውቁታል፡፡”

ዕዉቀትን ከባለቤቱ የመውሰዱ ሁኔታ ከአደም ጀምሮ እስካሁን ድረስ በሁሉም ትውልዶች ዘንድ ሲተላለፍ የቆየ ተግባር ነው፡፡ በፋሪሲ ዘመን ከሊላና ዱምና በሚል መጽሀፍ ውስጥ የተወሳ ታሪክን እንጥቀስ፡- “አንድ ሰው ከሰዎች ንግግር ‘ዒልመል-ፈሲህ’ ወይም ጥልቅ ግንዛቤ የሚባለውን መማር ፈለገና በዚህ ዘርፍ የታወቀ ወደሆነ ጓደኛው ዘንድ በመምጣት እንዲያስተምረው ጠየቀው፡፡ ጓደኛውም ‘ፈሲህ’ የሆነች ንግግርን፣ አጠቃቀሟንና ምን አቅጣጫ እንደምታስይዝ በቢጫ ወረቀት ላይ ጽፎ ሰጠው፡፡ እርሱም ያችን ጽሑፍ ይዞ በመሄድ ደጋግሞ እያነበበ ሸመደዳት፡፡ ነገር ግን እርሷ ምን ማለት እንደሆነችና በውስጧ ያለውንም ትርጓሜዋን በቅጡ አልተረዳም፡፡ በዚህ ዘርፍ ሁሉንም ዕውቀት የጨበጠ መስሎ ተሰማው፡፡ ከዚያም አንድ ቀን ከ’ፈሲህ’ ዐዋቂዎች ጋር በአንድ ዝግጅት ላይ ተገኝቶ ዉይይት ማድረግ ጀመረ፡፡ ከንግግሩም አንድ ስህተትን ፈጸመ፡፡ ከፊሎቹ ዐዋቂዎች ‘አንተ በእርግጥ ተሳስተሃል፡፡ የንግግሩ ጭብጥ አንተ ባልከው መልኩ አይደለም’ አሉት፡፡ እርሱም ‘በቤቴ ውስጥ ያለችውን ቢጫዋን ወረቀት በደንብ አንብቤ ሳለ እንዴት ተሳስተሃል ትሉኛላችሁ?’ አላቸው፡፡ ይህች ንግግሩ በራሷ

እንደገና የመማር ግደታ እንዳለበት፣ ለአላዋቂነት የቀረበ መሆኑንና ከሥርአቱ የራቀ መሆኑን ታጎላለች"[45]

አቡ ሀሚድ አል-ጋዛሊ እንዲህ አሉ፡- "አላህ ሱብሐነሁ ወተዐላ በዐሊም ቀልብ ላይ የእርሱ መለዮ የሆነችን ዕውቀት ከፍቶለታል፡፡ እርሱ እንደ ግምጃ ቤት ነው፣ በነፍሱ ውስጥ እርሷን ጠባቂ ነው፡፡ ይህችን ዕውቀት ፈልጎ ለሚመጣ ከዚያች ቆንጥሮ እንዲሰጥ ተፈቅዶለታል፡፡ ለመሆኑ በአላህና በፍጡራኑ መካከል አማላጅ፣ ወደ እርሱ አቃራቢና ዘላለማዊ ወደ ሆነችው ገነት የሚያመራ ከሆነው (ከዕውቀት) በላይ ለአንድ ባሪያ ምን የላቀ ደረጃ ይኖረዋል?"

2. የዕውቀትና የመማር አስፈላጊነት

የዕውቀት ጠቢባን ስለ ዕውቀትና ስለ መማር አስፈላጊነት ብዙ ንግግሮች አሏቸው፡፡ ከፊሎቹን እንጠቅሳለን፡-

- ጥበበኛው ሉቅማን ለልጃቸው እንዲህ ሲሉ መክረዋል፡- "ልጄ ሆይ! ዑለማዎችን ተጠጋ፤ በጉልበትህ ተንበርከከህ ቅረባቸው፡፡ አላህ ሱብሐነሁ ወተዓላልክ ምድርን ከሰማይ በሚወርድ የዝናብ ጎርፍ ህያው እንደሚያደርግ ሁሉ፤ ልብን በጥበብ ብርሃን ህያው ያደርጋታል፡፡"
- ከዐሊሞች መካከል አንዱ እንዲህ ብሏል፡-"የዕውቀት መሠረቶች አምስት ናቸው፤ አስ፣ ዕውቀቱ በራሱ፣ መዳረሻ መንገዶቹና የመማር ማስተማር ሥርዓቱ ናቸው፡፡ እነዚህን መሠረቶች የያዘ በእርግጥ (ዕውቀትን) ሰብስቧል፡፡" አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

﴿ ٱقۡرَأۡ وَرَبُّكَ ٱلۡأَكۡرَمُ ٣ ٱلَّذِي عَلَّمَ بِٱلۡقَلَمِ ٤ عَلَّمَ ٱلۡإِنسَٰنَ مَا لَمۡ يَعۡلَمۡ ٥ ﴾ العلق3-5

"አንብብ፤ ጌታህ በጣም ቸር ሲሆን፤ ያ በብዕር ያስተማረ፤ ሰውን ያላወቀውን ሁሉ ያሳወቀ ሲሆን" (አል-ዐለቅ: 3-5)

[45] (ከሊላና ዱምና-አቡዱላህ ኢብኑ መቅፈህ)

እነዚህ አንቀጾች የዕውቀት መሰረቶችን ሰብስበዋል። አስ አላህ፣ የሰው ልጅ ሲሆን ትምህርቱ ደግሞ የሰው ልጅ ሊያውቀው የሚፈልገው ነገር ሁሉ ነው፤ መርፌ መሥራት እንኳን ቢሆን። የዕውቀቱ ማማኛ መንገድ ደግሞ ማንበብና ማዳመጥ ሲሆን የትምህርት መሣሪያዎቹ ደግሞ ብዕርና መጻህፍቱ ናቸው።

- አንድ ሌላ ዓሊም እንደተናገሩት "አስ መጽሐፉ ብቻ የሆነ ሰው ከሚሰራው መልካም ሥራ ይልቅ ስህተቱ ይበዛል።"
- ኢማም አል-በና እንዲህ ብለዋል "ማንኛውም በዲን ጉዳይ በራሱ ተገንዝቦ የመወሰን ደረጃ ላይ ያልደረሰ ሙስሊም ቅርንጫፋዊ በሆኑ ድንጋጌዎች ላይ ከኡማው ታላላቅ ዑለማዎች አንዱን ሊከተል ይገባል። ከዚሁ ጎን ለጎን ማስረጃዎቹን በራሱ መገንዘብ እንዲችል ጥረት ሊያደርግ ይገባል። በግንዛቤውም መሠረት ትክክለኛና በቂ ማስረጃ ያለውን ሊቀበልና በተጨማሪም ሰውየው ከዑለማዎች ጎራ የሚመደብ ከሆነ በዕውቀቱ ዙሪያ ያለበትን ጉድለት በራሱ ተገንዝቦ መወሰን እስከሚችልበት ደረጃ (ደረጀተ-ነዘር) ድረስ ሊያሟላ ግድ ይለዋል።"
- አቡ ዑስማን ነይሳቡሪይ እንዲህ ብለዋል፡-"አላህን መጎዳኘት በመልካም ሥነ-ምግባርና እርሱን ዘወትር በመፍራትና እርሱ እንደሚከታተለን በማወቅ ነው። ከአላህ መልዕክተኛ(ሰ.ዐ.ወ) ጋር ያለ ጉድኝት ሱናቸውን በመከተልና ግልጽ በሆነው ግንዛቤ ላይ በመዘውተር ነው። ከዑለማዎች ጋር የሚኖረን ጉድኝት ደግሞ ለእነርሱ ተገቢውን ክብር በመስጠትና በማገልገል ነው።"

ሠጠገድ ያስበት ክፍተት፡-

በአሁኑ ጊዜ ከዑለማዎች ጋር መቀማመጥ አስፈላጊ አይደለም የሚሉ አንዳንድ ሰዎች ብቅ ብለዋል። አንዳንድ ጊዜ ዑለማዎቹም ሰው ናቸው እኛም ሰው ነን የሚል ተራ ምክንያት ያቀርባሉ። በሆነ ጊዜ አንዱን "ከዐብዱረዛቅ ሄደህ አትሰማምን?" ሲባል "ከፈጣሪ መስማት የሚችል ሰው ከአብዱረዛቅ መስማት ምን ያስፈልገዋል?" በማለት መለሰ። ይህ ሰው በንግግሩ የፈለገው ዕውቀቱን በቀጥታ ከቁርአን አገኘዋለሁ ለማለት ነው።ይህና መሰል ንግግሮች አላዋቂነትና የሰይጣን

ንግግሮች ናቸው፡፡ እንደ አብዱረዛቅና መሰል የሐዲስ ዑለማዎች ባይኖሩ ኖሮ ይህንና ሌሎች የእስልምና ተግባራት በፍጹም ባልደረሱ ነበር፡፡[46]

ዑለማዎች በህዝብ ላይ መስካሪዎች ናቸው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) በርሱ ብቸኝነት (ተውሂድ) ጉዳይ የዕውቀት ባለቤቶችን ምስክር አድርጓቸዋል፡፡ ምስክርነታቸውንም ከእርሱ መስካሪነትና ቀጥሎም ከመላእክት መስካሪነት ጋር አቆራኝቶታል፡- *"አላህ ከእርሱ በስተቀር ሊገዙት የሚገባ ሌላ አምላክ እንደሌለ መስክሯል፣ መላእክቶቹም ከዚያም የዕውቀት ባለቤቶችም መስክረዋል፤ በትክክለኛ ውሳኔ ላይ የቆመ፡ ከርሱ በስተቀር ሊገዙት የሚገባ አምላክ የለም፣ እርሱ አሸናፊና ጥበበኛ ነው።"* (አል-ዒምራን 18)

የዕውቀት ጠቀሜታ፡-

የዑለማዎችና የዲን ታጋዮችን ታሪክ እንዲሁም በዲኑ የጥልቅ ዕውቀት ባለቤትና የፈጣሪን ቅን አገልጋዮች ፈለግ ደጋግሞ የሚቃኝ ሰው እነርሱን ሞዴል አድርጎ እንዲይዝ ነፍሱ ትንተገተዋለች፣ በተግባራቸው ለመመሳሰል ደፋ ቀና እንዲል ውስጡ ያስገደድዋል፣ አላህ ፈቅዶለት የእነርሱን ደረጃ ለመድረስ ይጣጣራል፡፡ ኢማሙ ጁነይድ "ሒካያ (ትረካ) ከአላህ ሠራዊቶች አንዱ ነው፤ ልቦችን በኃይል ያነለብታል፡፡" ሲሉ ለዚህ ማስረጃ አለህን? ብለው ጠየቋቸው፡፡ እርሳቸውም አዎ አላህ በቁርአኑ እንዲህ ብሏል፡-

﴿نَّقُصُّ عَلَيْكَ مِنْ أَنبَاءِ الرُّسُلِ مَا نُثَبِّتُ بِهِ فُؤَادَكَ﴾ هود: ١٢٠

"ከመልክተኞቹም ዜናዎች (ተፈላጊወን)፡፡ ሁሉንም ልብህን በርሱ የምናረካበትን እንተርክልሃለን..." (ሁድ፡ 120)

ስለሆነም ውድ ወንድሜ ሆይ! የዑለማዎችን፣ የፉቀሃዎችን፣ የሙጅተሂዶችን ታሪክ ለማንበብ ተጣደፍ፤ በታጋሽነታቸው፣ በፅናታቸውና በጥብቅነታቸው እነርሱን ሞደል አድርገህ ለመኖር ጥረት አድርግ!!

[46](ተዝሂብ መዳሪክ ሳሊኪን -መንዚለቱል ዒልም)

እንደነርሱም ባትሆኑ እስኪ እነርሱን ምሰሉ

እጅጉን ይሻላልና በወንድ መመሰሉ

የመዝጊያ ጥያቄዎች

1. እስልምናን በመገንዘብ እረገድ ካንተ በተሻለ ሰው የመታገዝን አስፈላጊነት አብራራ።
2. ዑለማዎች ያለቸውን ደረጃና ክብር አስረዳ።
3. የዕውቀትንና የመማርን አስፈላጊነት አስረዳ።
4. በዕውቀትና በተቅዋ ባለቤቶች እስልምናን ለማወቅ ምን ያክል እንደታገዝክ አብራራ። በምንስ ጉዳይ?

የሦስተኛው አጠቃላይ ዓላማ

እስልምናን ከምንጩ ለማወቅ አላህን ፈሪና በእውቀቱ የተሻለ መሆኑን በሚያምንበት ሰው እንዲታገዝ ማስቻል

ዝርዝር ዓላማ

1. አላህን ፈሪና በእውቀቱ የተሻለ መሆኑን የምናምንበት ሰው ባህሪያት እንዲያብራራ ማስቻል።
2. ከተማሪ የሚፈለጉ ባህሪያትን እንዲገልፅ ማስቻል።
3. እነዚህን ተፈላጊ የተማሪ ባህሪያት በራሱ ላይ ምን ያህል ተግባራዊ ማድረጉን እንዲመዝን ማስቻል።

እስልምና የመከተል ሃይማኖት ነው

በእርግጥ ለመጀመሪያው የእስልምና ትውልድ መልክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) በተግባር የሚታዩ ሞደል ነበሩ። እስልምናን በቃላትም ሆነ በተግባር በማስተዋወቅ ረገድ ከባድ ተፅዕኖ አሳድረዋል። ትውልዱም መልክተኛውን ሞዴል አድርገው ተገቢ መከተልን ያዙ፣ በትንሹም በትልቁም ጉዳይ ፈለጋቸውን የሙጥኝ አሉ። በሚባዳ ጉዳይም ይሁን በማህበራዊ ዉሎ የአበላል፣ የአጠጣጥ፣ የአስተኛኘት፣ የአለባበስና ሌሎችንም የዕለት ከዕለት ስርዓት ሳይቀር የሙጭኝ ብለው ከእርሳቸው ወረሱ።

መልክተኛው(ሰ.ዐ.ወ) ጥሩ የሆኑ ነገሮችን ሁሉ ለሙስሊሞች በማመላከትና ችግር የሚያመጡ መጥፎ ነገሮችን በሙሉ እንዲታቀቡ በማድረግ በከፍተኛ ሁኔታ የማስተማር ኃላፊነታቸውን ተወጡ። የዚህም የማሰልጠን ድካማቸው ዉጤት የመጀመሪያውን የሙስሊም ብርቅዬ ትውልድ ገንብተው አምሳያ የማይገኝለት ሞዴል ትውልድ እንዲሆን አስቻሉት። የዚህ ምርጥ የመልክተኛው ባልደረቦች መልካም ስብዕናም ከትውልድ ትውልድ እየተላለፈ ይኸውና እኛ ጋር ደርሷል። በአላህ ፈቃድ እኛም ለቀጣይ ትውልድ ልናወርስ ግድ ይለናል።

በርግጥ የመልክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ባልደረቦች በእርሳቸው የመመራትንና የመከተልን ትርጉም በጥልቅ ተገንዝበዋል። በወቅቱ ለመልክተኛው ሁሉም ጆሯቸውን ይሰጡ ነበር፣ አይናቸውም እያንዳንዱን ድርጊታቸውን ይከታተላል። ማንኛውንም የንግግርም ይሁን የተግባር ፈለጋቸውን፣ ሌሎች ሠርተውት እርሳቸው ያፀደቁትንም ጭምር በሙሉ የማወቅ ከፍተኛ ጉጉት ነበራቸው። ከዚያም አጥብቀው ተከተሉ፣ በዚያውም ላይ ፀኑ፣ ይህንን ፈለግ ጠብቀውም ለቀጣዩ ትውልድ እኛ ጋር እስከሚደርስ ድረስ በሚገባ አሸጋገሩ። ለነገሩ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባልደረቦች መልክተኛው የዲኑን አጠቃላይ ገፅታዎችና አስፈላጊ ነገሮች በተግባር ቁመው እያስተማሯቸው እንዴትስ ላይከተሏቸው ይችላሉ? ይህ ትምህርት ደግሞ አላህ (ሱ.ወ) እንዲሆን በፈለገው ቃልኪዳኑና በወሕይ (ራእይ) መልክ ወደ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የወረደው ነው። ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የበለጠ በዚህ ዲን ጉዳይ ዐዋቂም ሆነ ጥልቅ ግንዛቤ ያለው አንድም ሰው የለም። ስለሆነም አላህንና የመጨረሻውን ቀን የፈለገ ሰው፣ ማንኛውም በእስልምና ላይ ያለበትን ግደታ በተገቢው ሁኔታ ማስተማርም ሆነ በተግባር መወጣት የፈለገ ሰው መልክተኛውን ያለምንም ማቅማማት ሊከተል ግድ ይሆንበታል።

እስልምናን በማወቅ ረገድ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባልደረቦች ዲናቸውን ለማወቅ ያደረጉትን ጥረት ያህል ልንራመድ ይገባል። እነርሱ መልክተኛውን በመከተል እንደዘወተሩ ሁሉ እኛም በዲኑና ለአላህ ባለው ፍራቻ የምንተማመንበትን ሰው ኢስላም ካሉት ታላለቅ ዑለማዎችና የዘመናት ችግር ያልበገራቸው ከሆኑት መካከል ሊኖረን ይገባል። የጥሩ ነገር ምሳሌዎች በሆኑ የአላህ ባሮች ውስጥ በመግባት ሕይወታችንን ለመምራት ልንታገዝ ግድ ይለናል። እንደዚሁም ከመጥፎ ሥራ ባለቤቶች መራቅ ይኖርብናል። በዚህ ረገድ ከሚያነሳሱን የቁርአን አንቀፆች መካከል የሚከተሉትን እናገኛለን፡-

﴿ أُوْلَٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ هَدَى ٱللَّهُۖ فَبِهُدَىٰهُمُ ٱقۡتَدِهۡۗ ﴾ الأنعام: ٩٠

"እነዚህ (ነቢያት) እነዚያ አላህ የመራቸው ናቸው መንገዳቸውንም ተከተል፡፡" (አል-አንዓም: 90)

﴿ لَقَدۡ كَانَ لَكُمۡ فِيهِمۡ أُسۡوَةٌ حَسَنَةٞ لِّمَن كَانَ يَرۡجُواْ ٱللَّهَ وَٱلۡيَوۡمَ ٱلۡأٓخِرَۚ وَمَن يَتَوَلَّ فَإِنَّ ٱللَّهَ هُوَ ٱلۡغَنِيُّ ٱلۡحَمِيدُ ﴾

"ለናንተ አላህንና የሚጨሻወን ቀን ለሚፈራ ሰው በነርሱ ሚልካም ሞተል አላችሁ የሚዞርም ሰው (ራሱን ይጎዳል) አላህ ተብቃቂው ምስጉኑ እርሱ ብቻ ነውና" (አል-ሙምተሒነህ: 6)

ቁርአን ከመጥፎ ሥራ ባለቤቶች መራቅ እንዳለብን በሚከተሉት አንቀጾች ያብራራልናል፡-

﴿ وَيَوْمَ يَعَضُّ ٱلظَّالِمُ عَلَىٰ يَدَيْهِ يَقُولُ يَٰلَيْتَنِي ٱتَّخَذْتُ مَعَ ٱلرَّسُولِ سَبِيلًا ﴿٢٧﴾ يَٰوَيْلَتَىٰ لَيْتَنِي لَمْ أَتَّخِذْ فُلَانًا خَلِيلًا ﴿٢٨﴾ لَّقَدْ أَضَلَّنِي عَنِ ٱلذِّكْرِ بَعْدَ إِذْ جَآءَنِي ۗ وَكَانَ ٱلشَّيْطَٰنُ لِلْإِنسَٰنِ خَذُولًا ﴿٢٩﴾ ﴾

"በዳይም – ከሚልከተኛው ጋር ቀጥተኛ መንገድ ይገ በኸነ ዋ! ምኞቴ እያለ (በጸጸት) ሀለት አጆቹን የሚከስበትን ቀን አስታውስ፡፡ ዋ! ጥፋቴ እገሌን ወዳጅ አድርጌ ባልያዝኩ ኖሮ እሞኝለሁ፡ (የእምነት ቃልን) ከመጣልኝ በኋላ ከሚከታወስ በእርግጥ አሳሳተኝ (ይላል) ሰይጣንም ለሰው አጋላጭ ነው፡፡" (አል-ፉርቃን: 27-29)

﴿ وَقَدْ نَزَّلَ عَلَيْكُمْ فِي ٱلْكِتَٰبِ أَنْ إِذَا سَمِعْتُمْ ءَايَٰتِ ٱللَّهِ يُكْفَرُ بِهَا وَيُسْتَهْزَأُ بِهَا فَلَا تَقْعُدُوا۟ مَعَهُمْ حَتَّىٰ يَخُوضُوا۟ فِى حَدِيثٍ غَيْرِهِۦٓ ۚ إِنَّكُمْ إِذًا مِّثْلُهُمْ ۗ إِنَّ ٱللَّهَ جَامِعُ ٱلْمُنَٰفِقِينَ وَٱلْكَٰفِرِينَ فِى جَهَنَّمَ جَمِيعًا ﴾

"በእናንተም ላይ በጽሑፍ ወስጥ የአላህን አንቀጾች በርሷ ሲካድባትና በርሷም ሲለገጥባት በሰማችሁ ጊዜ በሌላ ወሬ ወስጥ እስከሚቡ ድረስ ከእነሱ ጋር አትቀማጦሟትን በእርግጥ አወረደ፡፡ እናንተ ያን ጊዜ ብጠያቸው ናችሁና አላህ ሚፍቃንንና ከሓዲዎችን በሚሰበገሀነም ወስጥ ሰብሳቢ ነውና፡፡" (አን-ኒሳእ: 140)

በዚህ ግንዛቤ ዙሪያ መልክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) በሐዲስ ጥሩ መልእክቶችን አስተላልፈዋል፡፡ አቡሙሳ አል-አሽዐሪይ (አላህ ሥራቸውን ይውደድላቸውና) ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰምተው እንዳወሩት ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፡- *"ከመልካም ሰው መቀማመጥና ከመጥፎ ሰው መቀማመጥ ምሳሌው ልክ ሽቶ ኪያዘና ወናፍ ኪያዘ ጋር እንደሚቀመጥ ሰው ነው፡፡ ሽቶ የያዘው ሰው ጋር ከተቀመጥክ ወይ ከሽቶው*

ሰጦታ ያበረክትልሃል ወይም ልትገዛው ትችላለህ ካልሆነም በቆይታህ ጥሩ ሽታ ታሸታለህ። በተቃራኒው ወናፍ ኪየዘው ሰው ጋር ከተቀመጥክ ደግም በእሳቱ ፍንጣሪ ጨርቅህ ሊቃጠል ይችላል ካልሆነም መጥፎ ሽታ ይሸትሃል።" (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)

ከዚህ በመቀጠል ትልቁ ጥያቄ የሚሆነው በዚህ ዘመን ስለ እስልምና ግንዛቤ ለማገኘት ከማን ጋር እንቀማመጥ የሚለው ነው?

ይህ ጉዳይ የበለጠ ግልፅ ሆኖ በቅኑ መንገድ መራመድ እንድትችል እነዚያን መልካም ሰዎች ከሌሎቹ የሚለዩባቸውን የሥነ-ምግባርና መገለጫ ባህሪያት ጠንቅቀህ ማወቅን ያሻል። መገለጫ ባህሪያቸውን ባስተዋልክ ጊዜ ባለቤቶቿን ልትቆራኛቸው ይገባል። ምክንያቱም ቁስ በመንፈስ ላይ በነገሰበት በአሁኑ ዘመን እንደነዚህ አይነት ብርቅዬ ሰዎችን ማግኘት አዳጋች ነውና!

እነኝህ ባህሪያት የሚከተሉት ናቸው፡-

1. ለአላህ ባላቸው ፍራቻ (ተቅዋ) እና በሰውቀታቸው ልንተማመንባቸው የሚገቡ ሰዎች

- **አኼራን ከዱንያቸው ያስበልጣሉ**

የዕውቀት ባለቤቶች አኼራን ከዱንያ እንደሚያስበልጡ አላህ በቁርአኑ ሲገልጽ፡-

﴿ فَخَرَجَ عَلَىٰ قَوْمِهِۦ فِى زِينَتِهِۦ ۖ قَالَ ٱلَّذِينَ يُرِيدُونَ ٱلْحَيَوٰةَ ٱلدُّنْيَا يَٰلَيْتَ لَنَا مِثْلَ مَآ أُوتِىَ قَٰرُونُ إِنَّهُۥ لَذُو حَظٍّ عَظِيمٍ ﴿٧٩﴾ وَقَالَ ٱلَّذِينَ أُوتُوا۟ ٱلْعِلْمَ وَيْلَكُمْ ثَوَابُ ٱللَّهِ خَيْرٌ لِّمَنْ ءَامَنَ وَعَمِلَ صَٰلِحًا وَلَا يُلَقَّىٰهَآ إِلَّا ٱلصَّٰبِرُونَ ﴿٨٠﴾ ﴾ القصص: ٧٩ - ٨٠

"በሕዝቡም ላይ በጌጡ ወጣ፡ እነዚያ ቅርቢቱን ሕይወት የሚፈልጉት ወይ ምኞታችን ቃሩን የተሰጠው ብጤ ምነው ለኛ በኖረን፣ እርሱ የታላቅ እድል ባለቤት ነውና አሉ፡፡ እነዚያም እውቀትን የተሰጠት፡ –ወዮላችሁ የአላህ ምንዳ ለአመነ ሰው፣ መልካምንም ለሠራ

በላጭ ነው፣ ታጋሾችም እንጅ ሌላው ሰው አያገኛትም አሉ። ” (አል-ቀሰስ፡ 79-80)

ጃቢር (አላህ ሥራቸውን ይውደድላቸውና) እንዳወሩት ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- *“ከአምስት ነገር ወደ አምስት ነገር የሚጠራችሁ ካልሆነ በስተቀር ከማንኛውም ዓሊም ጋር አትቀመጡ፡- ከጥርጣሬ ወደ እርግጠኝነት፣ ከይዩልኝ ሥራ ወደ ኢኽላስ (ለአላህ ወደ ማጥራት)፣ ከማይቆረጥ ፍላጎት ወደ ዙህድ (ለውቆ ፍላጎትን መግታት)፣ ከኩራት ወደ መተናነስ፣ ከጠላትነት ወደ መካሪነት።።”* (አቡ-ነዒም አል-ሀሊያህ ላይ እንዲሁም ኢብንጀውዚይ መውዱኣት ላይ ዘግበውታል።)

ስለ ሐሰን አል-በስሪ (አላህ ሥራቸውን ይውደድላቸውና) እንደተወራው በአንድ ወቅት ከመማክርታቸው ሲነሱ አንድ ከኹራሳን የመጣ ሰው 5 ሺህ ዲርሃምና አስር ከሐር የተዘጋጁ ለስላሳ አልባሳት በቦርሳ ተሸክሞ በመጠጋት “ያ አባ ሰዒድ ሆይ ይህች ለወጭ የምትሆን ስጦታ ናት፤ ይህች ደግሞ ልብስ ናት አላቸው። እርሳቸውም እንዲህ በማለት መለሱለት፡- አላህ ይቅር ይበልህ ገንዘብህንም ልብስህንም ለራስህ ያዝ። እኛ ከርሱ ጉዳይ የለንም። እንደ እኔ እንደዚህ አይነት መጅሊስ ላይ ተቀምጦ ከሰዎች የዚህ አይነቱን የሚቀበል ከሆነ የቂያማ እለት አላህን ሲገናኝ አላውቅህም ይባላል።”[47]

አቡሁረይራ (አላህ ሥራቸውን ይውደድላቸውና) እንዳወሩት ነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- *“የአላህን ውዴታ ፈልጎ ከሚያስተምር ዓሊም ዘንድ በውሰጡ የዱንያ ጥቅም ለማግኘት አስቦ የሚማር ሰው የቂያማ ዕለት የጀነትን ሽታ አያገኝም።።”*

እነኝህ ሰዎች ዘንድ አኼራ ትልቅ መሠረት እንደሆነችና በዙሪያቸው ያለውን ነገር ሁሉ ከእርሷ አንፃር እንደሚመለከቱ አስተዋልከን? ገንዘብንም በሚመለከት ከርሱ ይልቅ ከአላህ የሚከፈላቸውን ምንዳ ያስበልጣሉ፤ በሁሉም ነገራቸው እንደዚህ ናቸው።

[47](ኢሕያኡ ዑሉሙዲን)

- **ተግባራቸው ከንግግራቸው አይቃረንም**

ከመለያ ባህሪያቸው አንዱ ተግባራቸው ከንግግራቸው የማይቃረን መሆኑ ነው። እንዳውም ቀድመው ያልተገበሩትን ሌሎች እንዲሠሩ አያዙም። አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ أَتَأۡمُرُونَ ٱلنَّاسَ بِٱلۡبِرِّ وَتَنسَوۡنَ أَنفُسَكُمۡ وَأَنتُمۡ تَتۡلُونَ ٱلۡكِتَٰبَۚ أَفَلَا تَعۡقِلُونَ ٤٤ ﴾

"እናንተ መጽሐፍን የምታነቡ ሆናችሁ ሰዎችን በበጎ ሥራ ታዛላችሁን? ነፍሶቻችሁንም ትረሳላችሁን? (የሥራችሁን መጥፎነት) አታውቁምን?" (አል-በቀራህ፡ 44)

﴿ كَبُرَ مَقۡتًا عِندَ ٱللَّهِ أَن تَقُولُواْ مَا لَا تَفۡعَلُونَ ﴾ الصف: ٣

"የማትሠሩትን ነገር መናገራችሁ አላህ ዘንድ ማከፋቱ ተለቀ፡ ፡" (አስ-ሰፍ፡ 2)

በሹዐይብ (ረ.ዐ)ታሪክ ውስጥ አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ وَمَآ أُرِيدُ أَنۡ أُخَالِفَكُمۡ إِلَىٰ مَآ أَنۡهَىٰكُمۡ عَنۡهُۚ ﴾هود: ٨٨

"...ወደ ከለከልኳችሁም ነገር ልለያችሁ (እናንተን ከልከዬ እኔ ልሠራው) አልሻም ፡ ፡" (ሁድ: 88)

ሙዓዝ ከመልክተኛው (አላህ ሥራቸውን ይውደድላቸውና) ሰምተው እንዳወሩት እንዲህ ብለዋል *"ማወቅ የፈለጋችሁትን ሁሉ ተማሩ፤ ነገር ግን እስካልሠራችሁበት ድረስ አላህ አይመነዳችሁም።"* (ደራሚይ ሙዓዝ ላይ ተንተርሰው በትክክለኛ ሰነድ ዘግበውታል።)

አላህና መልክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) እንዳብራሩት ዕውቀት ላይ የተመሠረተ ተግባር የትክክለኛነቱና አላህን የመፍራቱ (ተቅዋ) ማሰረጃ ነው። እንደዚሁም የአንድ ዓሊም ተግባር ከንግግሩ መጋጨት የንፍቅና ምልክት ነው። ኢብኑ ሲማክ አላህ ይዘንላቸውና እንደተናገሩት፡- "ስንት ሰዎች አሉ አላህን እንዲያስታውሱ ሌሎችን የሚመክሩ ነገር ግን አላህን የረሱ፣ አላህን ስለመፍራት የሚያስተምሩ ነገር ግን አላህን የሚዳፈሩ፣ ሌሎች ወደ አላህ እንዲቀርቡ የሚጎተጉቱ ነገር ግን ከአላህ

የራቁ፣ ወደ አላህ ተጣሪዎች ነገር ግን ከአላህ የሚሸሹ፣ የአላህን መጽሐፍ የሚያነቡ ነገር ግን ከአላህ አንቀፆች ያፈነገጡ”

ሐሰን አል-በስሪ አላህ ሥራቸውን ይውደድላቸው እንዲህ ብለዋል፡- “የፈለጋችሁትን ተማሩ በአላህ ይሁንብኝ ባወቃችሁት ነገር እስካልሠራችሁበት አላህ አይመነዳችሁም። ቂላቂሎች ጭንቀታቸው ማነብነብ ነው። ዓሊሞች ደግሞ ጭንቀታቸው ያወቁትን በተግባር መጠበቅ ነው።”

አዎ! በርግጥም በዘመናችን ተናጋሪ ዓሊም እንዳሸን ነው፤ ሰዎችን ይገስፃሉ እነርሱ ግን አይገሰፁም፣ ወደ አላህ ያመላክታሉ ነገር ግን ለአላህ አይሠሩም። ስለሆነም ወንድም ሆይ! አደራህን ከዚህ አይነቱ ጋር ከመቀመጥ እራቅ፤ ልክ ኢብኑ መስዑድ አላህ ሥራቸውን ይውደድላቸውና እንዳሉት “ዕውቀት በማነብነብ ብዛት አይደለም፣ ዕውቀት ማለት ፍራቻ ነው”

መልክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) *“ሸይጧን ምናልባትም በዕውቀት ሊያታልላችሁ ይችላል”* አሉ። ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? ተባሉ። ነቢዩም (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ አሉ *“ዕውቀትን ፈልግ፤ ነገር ግን እሰምታውቅ ድረስ አትሥራ፥ ይላል! ሰውየው ምንም ሳይሠራ በሞት እሰከሚለይ ድረስ፥ ዕውቀትን ፈልግ ሳታውቀው ግን አትሥራ፥ እያለ ከመወትወት አይወገድም።”* (ከአነስ ሐዲስ ጃሚዕ ላይ የተዘገበ)

• ከቅንጦት የፁቁ ናቸው

አኼራን ከሚያስበልጡ ዑለማዎች ባህሪ አንዱ ባመጋገብ፣ ባጠጣጥ፣ በአለባበስ፣ በዕቃዎቻቸውና በመኖሪያቸው ወደ ቅንጦት አለመዘንበላቸው ነው። እንዳውም በሁሉም ነገራቸው መቆጠብን የሚመርጡና በዚህም አላህ ይዘንላቸውና ቀደምት ሰለፎችን ለመመሳሰል የሚጥሩ፣ ከላይ በተጠቀሱት ነገሮች ሁሉ በትንሹ የሚብቃቁ ናቸው።

በርግጥ ማጌጥ በራሱ ክልክል ሆኖ አይደለም። ነገር ግን በዚህ ጉዳይ ከመጠን በላይ መስመጥ ሁልጊዜም ያንን ሁናቴ የመፈለግና ከርሱ ለመላቀቅ እስከ መቸገር ስለሚያደርስ ነው። ጌጣጌጥን ማዘውተር ባብዛሃኛው ወንጀልን ለመዳፈር ምክንያት ከመሆን አይዘልም፣ ሙገሳን መፈለግ፣ ሌሎችን መከታተል፣ ልታይ

ባይነትና ለመሳሰሉት አደገኛ ነገሮች ስለሚዳርግ በቁርጠኝነት መራቅ ያስፈልጋል። ብዙ ዓሊሞች ባመጋገባቸውና በአጋጊያጣቸው መጠን ባለፉ ቁጥር ባለስልጣናት በቀላሉ ጥገኛ ያደርጓቸዋል፤ ከዚያም እነርሱ የሚፈልጉትን እንጅ ሌላን መናገር አይችሉም፣ እነርሱ ከሚከለክሉት ውጭ ሌላ ነገርን የመከልከል አቅም የላቸውም። እንደነዚህ አይነቶቹ ገና ጉሮሯቸው በባለስልጣናት እንዳይዘጋ በመፍራት ወጣቱ ትውልድ ሱናን እንዳይተገብር ይከለክላሉ፣ ዲንን ይዋጋሉ። ቅንጦታቸው በፈጠረው አበሳ ከእነርሱ ላይ ይጣበቃሉ፣ አላህ ይጠብቀን!

• ከሹመትና ከስልጣን ይርቃሉ

እስልምናን እንድናውቅ እንዲያግዙን የምንፈልጋቸው ሰዎች ከስልጣን ጥማት የራቁ ሊሆኑ ይገባል። ከስልጣን የመሸሻ ቀዳዳ እስካላቸው ድረስ አገኘን ብለው በቀጥታ አይገቡበትም። ምክንያቱም ከነገስታት ጋር መቀላቀል የእነርሱን ውደታ ለመፈለግና ልባቸውን ለመግዛት ሲባል ፈተና ውስጥ መግባቱ አይቀሬ ነው።

ሑዘይፋ እንዲህ በማለት አስጠነቀቁ፡-“ከፈተና ቦታ አደራችሁን! (የፈተና ቦታ) ምንድን ናት? ሲባሉ የባለስልጣናት በሮች፣ አንደኛችሁ ባለስልጣኑ ጋር ይገባና ውሸቱን እውነት ነው ብሎ ያረጋግጥለታል፣ እርሱ ያልሆነውን ሆነ ብሎ ያወራል።”

ባንድ ወቅት ዑመር ኢብኑ አብዱል አዚዝ አላህ ይዘንላቸውና ለሐሰን እንዲህ በማለት ደብዳቤ ፃፉለት፡- “በአላህ (ሱ.ወ) ጉዳይ ሊያማክሩኝ የሚችሉ ሰዎችን አመላክተኝ!” ሐሰንም እንዲህ ብለው ጻፉለት፡- “የዲን ባለቤቶች እንደሆነ አይፈልጉህም፣ የዱንያን ሰዎች ደግሞ አንተ አትፈልጋቸውም፣ በክትትል አደራህን ክብራቸውን አሳልፈው በክህደት እንዳያቆሽሹት።”

• ለነፍሳቸው ታጋዩና ለጌታቸው ትእዛዝ ተጠባቂ ናቸው

ከአኼራ ዑለማዎች ባህሪያት መካከል ቀልባቸውን ለማወቅ ብዙ ትኩረት መስጠት፣ የአኼራን መንገዶች ማወቅ፣ እውነተኛ ፍላጎት መኖርና ይህንንም ከነፍሳቸው ጋር ብዙ በመታገልና ትእዛዛትን በመጠበቅ በተግባር መግለፅ ይገኙበታል። እነኝህ ሰዎች የአላህን ትእዛዛት መጠበቅ የዘወትር ጭንቀታቸው

ነው፣ ውዴታውን ለማግኘት ሁልጊዜም ይጥራሉ፣ ቀልባቸውን ሰብስበው በፀዳ አስተሳሰብና ወደ አላህ ብቻ በመዘንበል ከእርሱ ጋር የተሳሰሩ ናቸው። አንተ ከእነኚህ አይነት ሰዎች ጋር ስትቀመጥ አላህን እንድትወድ ያደርጉሃል፣ ወደ እርሱ ያመላክቱሃል፣ ሥራህን በሙሉ ለርሱ ብቻ እንድታጠራ ያስታውሱሃል፣ አላህን በማስታወስ ላይ ያግዙሃል፤ እነኚህ ከዋና መለያ ባህሪያታቸው ናቸው።

• በአላህ ላይ ባላቸው እርግጠኝነት (የቂን) በብርቱ የታገዙ ናቸው

እርግጠኝነት የዲን ዋና ካፒታል ነው። መልክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) *"የቂን እምነትን በሙሉ ያካትታል"* ብለዋል። (ከኢብኑ መስዑድ ሐዲስ በይሀቂይ ዘግበውታል)። እነኚህ ሰዎች መልክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) "የቂንን ተማሩ!" በማለት ለተናገሩት ጉዳይ ትኩረት ይሰጣሉ። (አቡ ነዒም ሙርሰል በማለት ዘግበውታል)። ትርጉሙም የቂን ባዮች ጋር ተቀማመጡ፣ ከእነርሱም ስለ የቂን ተማሩ፣ የእነርሱ የቂን እንደጨመረ ሁሉ የእናንተም የቂናችሁ እንዲጨምር ፈለጋቸውን ተከተሉ፤ የቂን ያለበት ትንሽ ሥራ የቂን ከሌለበት ብዙ ሥራ ይበልጣል የሚል ነው፤ እነኚህ ሰዎች በአላህ ላይ ባላቸው የቂን ከውርደት በቀላሉ ሲያመልጡና ፈተናን በድል ሲወጡ ታያቸዋለህ።

ሉቅማን (ዐ.ሰ) ለልጃቸው ከሰጡት ምክር "ልጄ ሆይ ሥራ ያለ የቂን አይሆንም፣ አንድ ሰው ሥራን አይሠራም በየቂኑ ልክ ቢሆን እንጅ፣ ሥራውም አይቀንስም የቂኑ ላይ በቀነሰው ልክ ቢሆን እንጅ" የሚለው ይገኝበታል። ስለሆነም ወንድም ሆይ ይህንን ትምህርት አኼራን ከሚፈልጉ ሰዎች እንጅ ከሌላ እንደማታገኘው ዕወቅ።

• መፈጋጋትና ክብር ይስተዋልባቸዋል

መረጋጋትና ክብር መለያ ባህሪዎቻቸው ናቸው። ራሳቸውን ሰበር አድርገው በረጋ መንፈስና በዝምታ ድባብ ተውጠው ታያቸዋለህ። ለአላህ ያላቸው ፍራቻ ባጠቃላይ ገፅታቸው፣ ባለባበሳቸው፣ ባረማመዳቸው፣ በእንቅስቃሴያቸው፣ ባኗኗራቸው፣ ባነጋገራቸውና በዝምታቸው ይንፀባረቃል። ሰዎች ወደ እነርሱ በተመለከቱ ጊዜ አላህን ለማስታወስ ይገደዳሉ፣ ገፅታቸው የተግባራቸው ማስረጃ ነው። በርግጥ እንደዚህ ተብሏል "አላህ ለአንድ ባሪያው ከመረጋጋት ከሆነች

የፍራቻ ልብስ የበለጠ የተዋበ ልብስ አያለብሰውም፣ እርሷ የነቢያት ልብስ ናት፣ የደጋግ ባሮችና የዑለማዎች መለዮ ናት።።"

ለመናገር መጣደፍና ማንቧረቅ፣ ሳቅ ውስጥ መዘፈቅ፣በእንቅስቃሴም ሆነ በንግግር መንቦጥረር፤ እነዚህ ሁሉ ባጠቃላይ ከኩራት የሚመነጩ ጠባሳዎችና የአላህን ከባድ ቅጣትና ብርቱ አያያዝ ከመዘንጋት የሚመጡ ናቸው።። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿إِنَّمَا يَخۡشَى ٱللَّهَ مِنۡ عِبَادِهِ ٱلۡعُلَمَٰٓؤُاْ﴾ فاطر: ٢٨

"አላህን የሚፈሩት ዐለሞች (የበለጠ የሚወቁት) ናቸው።" (ፋጢር: 28)

መልክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ከነማን ጋር ብንቀማመጥ ይሻላለል ተብለው ለተጠየቁት ሲመልሱ፡-"እነዚያ በዓይን በታዩ ጊዜ አላህ የሚታወስባቸው የሆኑትን!"

ዕወቅ! ያ አንተ ባየኸው ጊዜ እርሱን ማየትህ አላህን እንድታስታውስ ካደረገህ የዚህን ሰው ጓደኝነት አዘውትር፣ ሌላ ተለዋጭ አትፈልግ፣ ለእርሱ ተናነስለት፣ እርሱ ዘንድ ያለውን ዕውቀት ማውጣት እንድትችል ለስላሳ ጎኑን ሁንለት።።

- **በዲን ላይ ፈጠራን አይቀበሉም**

ከአኼራ ዑለማዎች ባህሪያት መካከል በዲን ዙሪያ በሚደረጉ ፈጠራዎች (ቢድዓ) ላይ መላው ህዝብ ቢስማማበት እንኳን እነርሱ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረጋቸው ነው።። የከፊል ሶሐባዎችን (አላህ ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸውና) ስም እየጠሩ በሚደረጉ በቃላት የተሸጎደጎዱ ፈጠራዎችም አይታለሉም።። እንዳውም የሶሐቦቹን ሁናቴ፣ ታሪክ፣ ሥራቸውንና ትልቅ ጉዳያቸው ምን እንደነበር ለመፈተሽ ይጣደፋሉ፤ ወቅፍ የተደረጉ ንብረቶችን ያስተዳድር ነበርን? የየቲምን ገንዘብ ይበላ ነበርን? ነገስታትን ተቀላቅሎ ከነርሱ ጋር ይሞዳሞድ ነበርን? ወይስ አላህን በመፍራት፣ በትካዜ፣ በሀሳብ፣ ነፍሱን በመታገል፣ የአላህንን ትእዛዝት በመጠበቅ፣ ትንሹንም ትልቁንም ወንጀል በመራቅ፣ የስሜትና የ ሸይጧንን ድብቅ ተንኮል ተገንዝቦ በመታገል ላይ ነበርን? የመሳሰሉትንና ሌሎችንም የቀልብ ፅዱነት መለኪያ ዕውቀቶችን በመጠቀም ይመረምራሉ።።

ዐሊ (አላህ ሥራቸውን ይውደድላቸውና) “ከእኛ በላጫችን ዲኑን የተከተለው ነው!” ይሉ ነበር። ስለሆነም ወንድሜ ሆይ! መልክተኛውን (ሰ.ዐ.ወ) ተከታይ የሆነውን በመከተል ተጣደፍ። በሁሉም ሁኔታው ተከተለው፤ በንግግሩ፣ በሥራው፣ ወደ አላህ በሚቃረብበት ነገር። ይህ ሰው በዲን ላይ ከሚደረጉ ፈጠራዎች ይርቃል። ለምን ቢባል ማንኛውም ፈጠራ ሁሉ ቢድዓ ነው፣ ማንኛውም ቢድዓ ጥመት ነው፣ የጥመት መዳረሻው ደግሞ እሳት ውስጥ ነው።

ከላይ የተጠቀሱት ስምንት ምልክቶች ከአኼራ ዑለማዎች መለያ ባህሪያት የተወሰዱ ናቸው። ወንድም ሆይ! እንዚህ አይነቶቹን ዓሊሞች ተቆራኝ፣ ይህን አይነቱን ያማረ ጉድኝት አጥብቅ፣ በዚህም መልካም ባህሪያትን ትወርሳለህ። ዱንያ ከማታሞኛቸውና በአላህ ላይ ማታለል ከማያታልላቸው እንዲያደረገን አላህን እንለምናለን።

2. ከተማሪ ባህሪያት

አንድ ተማሪ ከላይ በተወሱት ዑለማዎች መሃል ተስማምቶ እንዲኖር የሚያስችሉት ልዩ ባህሪያት ሊኖሩት ግድ ይላል፡-

- **ሙተናነስ**

ዑመር ኢብን አል-ኸጣብ (አላህ ሥራቸውን ይውደድላቸውና) እንዲህ አሉ፡- “ከርሱ የምትማሩበት ከሆነው ሰው ተናነሱ፣ ከእናንተ የሚማርም ለናንተ ይተናነስ፣ ራሳቸውን ከሚክቡ ዑለማዎች አትሁኑ፣ ዕውቀታችሁም በድንቁርናችሁ ላይ አይመሥረት።”

ተማሪ በዕውቀት ላይ አይኮራም፣ በአስም ላይ የበላይ አይሆንም፣ እንዲውም ጉዳዩን በዝርዝር ከፍቶ ልጓሙን ይለቅለታል፣ የሚሰጠውን ምክር ልክ ለአንድ ምንም ለማያውቅ በሽተኛ በጣም ብልህና አዋቂ የሆነ ሐኪም እንደሚሰጠው ምክር አስቦ በቅንነት ዝቅ ብሎ ይቀበላል። ሸዕቢይ እንዳሉት፡- “ዘይድ ኢብኑ ሳቢት በሆነ ጀናዛ ላይ ሰገደ፣ በቅሎውን እንዲጋልባት ወደርሱ አስጠጋሁለት። ኢብኑ ዐባስ መጣና እርካቡን ያዘለት፣ ዘይድም የነቢዩ የአጎት ልጅ ሆይ ተው ይህ ላንተ አይገባም አለ። ኢብን ዐባስም ለዑለማዎችና ለታላቆቻችን እንደዚህ

እንድናደርግ ነው የታዘዝነው አለ። ዘይድ ኢብኑ ሳቢትም እጁን ሳመውና ለነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ) ቤተሰቦች እንዲህ እንድናደርግ ነው እኛም የተዛዝነው አለው።"
(ኢህያእ ዑሉሙዲን፣ ክፍል አንድ)

• ሐቅ ሳይ ለመድረስ ከሙስጥ የመነጨ ፍላጎት

አንድ ተማሪ ዕውቀትን ለማግኘት ፍላጎት ሊኖረው ግድ ይላል። ሲማርም የአላህን ፊት ብቻ ፈልጎ መሆን አለበት። መልክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- *"የአላህን ውዴታ ፈልጎ ከሚያስተምር ዓሊም ዘንድ በውስጡ የዱንያ ጥቅም ለማግኘት አስቦ የሚማር ሰው የቂያማ ዕለት የጀነትን ሽታ አያገኝም።"* (አቡ ዳውድ ዘግበውታል)። ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በሌላ ሐዲሳቸው እንዲህ ብለዋል፡- *"ሥራ የሚለካው በኒያ (ፍላጎት) ነው። ሁሉም ሰው የነየተው አለው።"* (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)

አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ أَمَّنْ هُوَ قَٰنِتٌ ءَانَآءَ ٱلَّيْلِ سَاجِدًا وَقَآئِمًا يَحْذَرُ ٱلْءَاخِرَةَ وَيَرْجُوا۟ رَحْمَةَ رَبِّهِۦ ۗ قُلْ هَلْ يَسْتَوِى ٱلَّذِينَ يَعْلَمُونَ وَٱلَّذِينَ لَا يَعْلَمُونَ ۗ إِنَّمَا يَتَذَكَّرُ أُو۟لُوا۟ ٱلْأَلْبَٰبِ ﴾ الزمر: ٩

"እርሱ የሚጨሻይቱን ዓለም (ቅጥ) የሚፈራ የጌታውንም ችሮታ የሚጅል ሲኾን በሌሊት ሰዓቶች ሰጋጅና ቋሚ ሆኖ ለጌታው የሚዛ ሰው (እንደ ተሰፋ ቢሱ ከሓዲ ነውን? በለው፣ እነዚያ የሚውቁትና እነዚያ የሚውቁት ይስተካከላሉን? በላቸው፤ የሚነዘቡት የአእምሮ ባለቤቶች ናቸው።"
(አዝ-ዙመር: 9)

• <u>ትሕትና</u> ሊያከብር ይገባል

አንድ ተማሪ የሚያስተምረው ሸይኽ ሊያከብር ይገባል። ጥያቄ በማብዛት ችክ አይልም፣ ንግግሩንም አያቋርጠውም፣ ሸይኹ ሲናገር እርሱ ጆሮ ይሰጣል፣ አይኑ ወደ ሌላ አይቃብዝም፣ ሸይኹ ከመቀመጫው ሲነሳ ጨርቁን ይዞ አይጎትተውም። ነቀፌታም አያሳየውም። ሸይኹን ልክ እንደ ንፉስ መጠለያ አድርጎ

ይይዛል፣ ለሸይኹ ከባድ የመሆን ስሜት አይታይበትም፣ ንግግሩን አይገድበውም፤ የሸይኹን ንግግር ይቀበለዋል፣ አይከራከረውም።

- **በግለሰብ ሳይሆን በመርህ ሊመሩ**

አንድ ተማሪ ከላይ ለአስ የሚሰጠው ክብር እንደተጠበቀ ሆኖ ነገር ግን ታማኝነቱ ለግለሰቡ ሳይሆን ለአላህና ለመልክተኛው፣ እንዲሁም ለኢስላማዊ መርሆ ሊሆን ይገባል። ኢማም አል-በና እንደሚሉት፡- "ማንኛውም ሰው ከንግግሩ ሊያዝለት ወይም ሊተውም ይችላል፤ ፍፁም የሆኑት የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ንግግር ሲቀር።" (ረሳኢል ሪሳለቱ አት-ተዓሊም)

ዑመር ኢብን አል-ኸጣብ እንዲህ ብለዋል፡- "የአንድ ዓሊም መንሸራተት ብዙ ሰዎችን ያንሸራትታል።" ስለዚህ ታማኝነትህን ለግለሰብ ሳይሆን ለአላህ በማድረግ ከመንሸራተት እራስህን ጠብቅ!

3. ከአስ የወረሰውን ባህሪ በተግባር ማዋሉን ሊገመግም

ከአስ የወረሰውን ባህሪ በተግባር ማዋሉን ለመገምገም የሚረዱ መለኪያዎች፡-

ተ.ቁ.	የባህሪያት	ሁልጊዜ (ከ75% በላይ)	በከፊል (ከ50 % - 75 %)	አልፎ አልፎ (ከ50% ከታች)
1	ለአስተማሪዬ እተናነሳለሁ			
2	ከዕውቀት አልኮራም			
3	የሚሰጠኝን ምክር በጉጉት እቀበላለሁ			
4	አስተማሪዬን አከብራለሁ፣ አልቃለሁ			
5	አስተማሪዬን በጥያቄ አልጨቀጭቅም			
6	አስተማሪዬን ከንግግሩ አላቋርጥም			
7	አስተማሪዬ ሲናገር ጆሮ እሰጠዋለሁ			
8	አስተማሪየ ሲናገር አይኔ አይ,ቃብዝም			
9	ለአስተማሪዬ ከባድ ሆኜ አልታይም			

10	አስተማሪዬን አልከራከርም			
11	በዕውቀቴ የአላህን ፊት እከጅላለሁ			
12	ምን ጊዜም በዕውቀቴ እውነትን እፈልጋለሁ			
13	ግለሰብን ሳይሆን መርህን እከተላለሁ			
14	የሚጠቅመኝን ነገር አስተማሪየን ከመጠየቅ አላፍርም			

ከላይ የተቀመጡትን መለኪያዎች በመገምገም ከአስ የወረሳቸውን ባህሪያት ምን ያክል በተግባር እንዳዋላቸው ይረዳል፤ በውጤቱ ጥሩ ካገኘ አላህን ያመሰግናል፣ በዚሁም ለመቀጠል ይጣደፋል። በውጤቱ ዝቅተኛ ከሆነ ያሉበትን ክፍተቶች ለማከም እርሱ በሚያምንበትና አላህን ፈሪ እንዲሁም አዋቂ ከሆነ ሰው ትምህርት ሊቀስም ይገባል።

የመጠዘኛ ጥያቄዎች

1. በዕውቀትና በተቅዋው ልትተማመንበት የሚገባ ሰው ባህሪያት አስረዳ።
2. በዕውቀትና በተቅዋው የምትተማመንበት ሰው አግኝተሃልን? በምንስ ጉዳይ?
3. የተማሪ ወሳኝ ባህሪያትን አስረዳ።
4. የተማሪ ባህሪያትን ምን ያክል እንዳሟላህ አስረዳ። መስተካከል ያለበት ክፍተት ካስተዋልክም ምክንያቱን ግለፅ።
5. በመልክተኛውና በደጋግ ሰለፎች መመራት እንዴት እንደሆነ አብራራ።
6. “የሰው ልጅ የሥራው ትክክለኛነት የሚለካው በእስልምናው ሲዘወትርና የአላህን መመሪያ በሕይወቱ ተግባራዊ ሲያደርግ እንጅ እርሱ ዘንድ ባለው ዕውቀት ልክ አይደለም” ይህንን አብራራ።
7. በበልክተኛውና በደጋግ ሰለፎች መከተልን ምን ያክል ተግባራዊ እንደዳደረግክ እራስህን ገንግም። በተለይም ያሉብህን ድክመቶች፣ ምክንያቶቹንና የማከሚያ መንገዶቹን በመዘርዘር።

የስፈተኛው ስጠቃላይ ዓላማ

የመልዕክተኛውንና (ሰ.ዐ.ወ) የቀደምት መልካም ሰለፎችን ፈለግ በማንኛውም ሁኔታው ተግባራዊ እንዲያደርግ ማስቻል

ዝርዝር ዓላማ

1. በዕውቀትና በተግባር መካከል ያለውን ትስስር እንዲያብራራ ማስቻል
2. የመልክተኛውንና (ሰ.ዐ.ወ) የቀደምት መልካም ሰለፎችን ፈለግ በማንኛውም ሁኔታው እንዴት እንደሚተገብር እንዲያብራራ ማስቻል
3. በመልክተኛውና (ሰ.ዐ.ወ) እና በመልካም ሰለፎች ፈለግ ምን ያክል እየተመራ እንደሆነ እራሱን እንዲገመግም ማስቻል

1. በዕውቀትና በተግባር መካከል ያለው ትስስር

እስልምና የሕይወት መመሪያ ብቻ ሳይሆን በተግባር ሊፈፀም የሚገባውም መመሪያም ነው። የእስልምና መሠረቶች ያለተግባር ሊሟሉ አይችሉም። እምነትም ሙሉ ሊሆን አይችልም ልቦና እውነት ያለውንና አንደበት ያረጋገጠውን አካላት በተግባር እስካላረጋጡት ድረስ።

አንድ ጉዳይ በሥራና በተግባር ሳይፈፀም በዕውቀት ደረጃ ብቻ ከቀረ ለባለቤቱ ፈተናና መጥፊያው ይሆንበታል። ነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ) ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ አስጠንቅቀዋል። ለዚህም ያ ያወቀውን በሥራ የማይተገብር፣ ንግግሩና ተግባሩ የሚቃረኑ የሆነን ሰው የመጨረሻ ውጤት እንደሚከተለው አብራርተዋል፡- *“የቂያማ አለት አንድ ሰው ተይዞ ይመጣና ወደ እሳት ይወረወራል፣ አንጀቱ ይዘረገፍና ልክ አህያ በእሥሩ እንደሚዞረው እርሱም በአንጀቱ ተተብትቦ ይዞራል። የእሳት ሰዎች ይሰበሰቡና እገሌ ሆይ! ምን ሁነህ ነው አንተ በመልካም ታዝ፣ ከመጥፎም ትከለክል አልነበረምን? ይሉታል። እርሱም አዎ! በጥሩ አዛችሁ ነበር፤*

ግን እኔ አልተገብረውም። ከመጥፎም እከለክላችሁ ነበር፤ ግን እኔ ያን መጥፎ ሥራ እሠራ ነበር ይላቸዋል።" (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል፣ ሙስሊም የዘገቡት ከኡሳማህ ኢብኑ ዘይድ ነው)

አቡ ሁረይራ (አላህ ሥራቸውን ይውደድላቸውና) እንደዘገቡት ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- *"የመጀመሪያ እሳት የምትንቀለቀልበት ሦስት ሓይነት ሰዎች ላይ ነው። ከነርሱ አንዱ የሆነው ያ ዕውቀትን ተምሮ ያስተማረ፣ ቁርአንን የቀራና ጥቅሙን የተረዳና ያስረዳ ሰው ይመጣል፤ አላህም ምን ሠራህም ይለዋል። እርሱም ዕውቀትን ተማርኩ ሌሎችንም አስተማርኩ፣ ቁርአንንም ላንተ ብዬ ቀራሁኝ ይላል፤ አላህም ዋሸተሃል! አንተ የተማርከው እርሱ ቃሪእ ነው እንድትባል ነው። እርሱንም (በዱንያ) ተብለሃል ይለዋል፣ ከዚያም አላህ በፊቱ እየተንተተ ወደ እሳት እንዲወረወር ያዝና በዚህ ሁኔታ ይገባታል።"* (ሙስሊምና ነሳኢይ ዘግበውታል)

የሰው ልጅ የሥራው ትክክለኛነት የሚለካው በእስልምናው ሲዘወትርና የአላህን መመሪያ በሕይወቱ ተግባራዊ ሲያደርግ እንጅ እርሱ ዘንድ ባለው ዕውቀት ልክ አይደለም። ይህ ቢሆንማ ከሙስሊሞች የተሻለ እስልምናን የተማሩ ነገር ግን ምንም ያልተጠቀሙበት ስንትና ስንት ኦሬንታሊስቶች ነበሩ። ወደ አላህ ውዴታ መዳረሻ መንገዱ መልካም ተግባርና ለእርሱ የተሟላ ዒባዳ መፈጸም እንጅ ሌላ ሊሆን አይችልም።

ቃል-በቃል የትምህርት አቀባበል ዘዴ

የሶሐቦች የትምህርት አቀባበል ዘዴ ቃል በቃል (ተለቂይ) ሲሆን ይህም በቀላሉ ወደ ተግባር ለመለወጥ አመች ዘዴ ነው። ሰይዳችን ዑመር እንዲህ ብለዋል፡- "ከመልእክተኛው ጋር ሳለን አስር አንቀጾች ሲወርዱ አንቀጾቹን ለመሐፈዝ ሁላችንም እንጣደፍ ነበር፣ ከዚው ወዲያውኑ ተግባራዊ እናደርጋቸው ነበር። ዕውቀትና ተግባርን አንድ ላይ ነው የተማርነው።" በሌላ ዘገባ "ወደ ቤታችን ሄደን ልጆቻችንና ባለቤቶቻችንን እናስተምር ነበር" ብለዋል። ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በዚህ መልክ ባልደረቦቻቸውን በተርቢያ ይኮተኩቷቸውም ነበር። ቂያማ ሞች ናት? ብሎ አንዱ ሲጠይቃቸው ለእርሷ ምን አዘጋጅተሃል? ነበር ያሉት።

2. በመልክተኛውና (ሰ.ዐ.ወ) በመልካም ሰዎች መመራት

እስልምናን ለመተግበር ቀዳሚ ሞዴሎቻችን መልክተኛው (ሰ.ዐ.ወ)፣ የተከበሩት ሶሐባዎችና ደጋግ ሰለፎች ናቸው። መልክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) በአካል የሚንቀሳቀሱ ህያው ቁርአን ነበሩ። እመት ዓኢሻ (አላህ ሥራዋን ይውደድላትና) ስለ መልክተኛው ስትጠየቅ እንዲህ ነበር ያለችው *"ሥነ-ምግባራቸው ቁርአን ነው!"*

ባልደረቦቻቸውም በእስልምና ላይ የነበራቸው ዘውታሪነትና የተግባር እንቅስቃሴ ህያው ምሳሌ ናቸው። እነርሱ እስልምናን በመልክተኛው እጅ የተማሩና በተግባርም የታነፁ ናቸው፤ ስለሆነም "እነርሱ በምድር ላይ የሚራመዱ ቁርአን ነበሩ!" የሚለው አባባል በትክክል ይገልፃቸዋል። ከዚያም የዚያ ኡመት ተከታይ የነበሩት ደጋግ ሰለፎች የነርሱን የመማርና የመተግበር ሥርዓት በትክክል የወረሱ በመሆናቸው በእርግጥም ምርጥ ተከታዮች ናቸው፡- *"ምርጥ ተከታዮቼ በእኔ ዘመን ያሉት ናቸው፣ ከዚያም የእነርሱ ተተኪዎች፣ ከዚያም የእነርሱ ተተኪዎች!"*

አለህ (ሱ.ወ) የእኛ መመሪያችን መልክተኛው(ሰ.ዐ.ወ) እንዲሆኑ አዟል፡-

﴿ لَّقَدۡ كَانَ لَكُمۡ فِي رَسُولِ ٱللَّهِ أُسۡوَةٌ حَسَنَةٞ لِّمَن كَانَ يَرۡجُواْ ٱللَّهَ وَٱلۡيَوۡمَ ٱلۡأٓخِرَ وَذَكَرَ ٱللَّهَ كَثِيرٗا ﴾

"ለናንተ አላህንና የሚጨሻወን ቀን የሚጅል ለሆነ ሰው አላህንም በብዙ ሊያወሳ በአላህ መልክተኛ መልካም መከተል አላቸው" (አል-አህዛብ: 21)

﴿ وَمَآ ءَاتَىٰكُمُ ٱلرَّسُولُ فَخُذُوهُ وَمَا نَهَىٰكُمۡ عَنۡهُ فَٱنتَهُواْۚ ﴾ الحشر: ٧

"መልክተኛወም የሰጣቸሁን ማንኛወንም ነገር ያዙት፡ ከርሱም የከለከላችሁን ነገር ተከልከሉ..." (አል-ሐሸር: 7)

﴿ قُلۡ إِن كُنتُمۡ تُحِبُّونَ ٱللَّهَ فَٱتَّبِعُونِي يُحۡبِبۡكُمُ ٱللَّهُ وَيَغۡفِرۡ لَكُمۡ ذُنُوبَكُمۡۗ وَٱللَّهُ غَفُورٞ رَّحِيمٞ ﴾

"በላቸው፡ – አላህን የምትወዱ እንደኾናችሁ ተከተሉኝ አላህ ይወዳችኋልና ኃጢያቶቻችሁንም ለናንተ ይምራልና አላህም መሓሪ አዘኝ ነወና፡፡"

(አል-ዒምራን: 31)

መልክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) የሶሃቦቻቸውን ፈለግ እንዲንከተል መክረውናል፡-

"በሱናዬ ላይ አደራ እላችኋለሁ፤ ከዚያም ቅኑን መንገድ የተመሩ የሆኑትን ተተኪዎቸን እንድትከተሉ!"

3. በመልክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) እና በመልካም ሰለፎች ፈለግ ምን ያክል እየተመሩ እንደሆነ እራሱን እንዲገመግም ማስቻል

ውድ ወንድሜ ሆይ፡-ያ አንተ በማንኛውም ሁኔታህ መልክተኛውንና ደጋግ ሰለፎች ለመከተል የምትሮጠው፤ ራስህን በነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ) እንደገና እንድትገመግም አደራ እልሃለሁ፣ ከዚያም ሕይወትህ በሙሉ በደስታ የተረጋጋች ትሆንልሃለች፡-

- በሥነ-ምግባርህም ሆነ በማንኛውም ጉዳይህ የአላህን ህግጋት ለማወቅ ወደ ቁርአን (በተቅዋውና በዕውቀቱ በምትተማመንበት ሰው በመታገዝ) ትመለሳለህን?
- በሥራህና በንግግርህ ዙሪያ የመልክተኛውን ተግባር ታገናዝባለህን?
- በሚባዳህና በሥነ-ምግባርህ መልክተኛውን ትከተላለህን?
- በማህበራዊ ውሎህ መልክተኛውን ትከተላለህን?
- በተቅዋውና በዕውቀቱ የምትተማመንበትን ሰው ሀሳብ ካንተ ስሜትና ሃሳብ ቢቃረን አንኳ ትቀበለዋለህን?
- ባንተ ላይ ቢሆንና ቢመርህ እንኳን ሀቅን ትቀበላለህን?
- የሆነ ጉዳይ ሲገጥምህ ሐቅን ለማግኘት ትጥራለህን? ወይስ ሐቅን ረግጠህም ቢሆን ለራስህ ብቻ መውጫ ቀዳዳ ትፈልጋለህ?

እነዚህንና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች በእውነት በመመለስ በመልክተኛውና በደጋግ ሰለፎች መከተል እንዳለህ ራስህን መገምገም ትችላለህ። ክፍተቶችህንም በዝርዝር ትለያለህ። በዚህ ተግባርህ ምናልባትም አላህ ወደ ሐቅ ይመራህና በዚያውም ላይ ሊያፀናህ ይከጀላል።

መልክተኛውን በመከተል ዙሪያ በየግል የተደረጉ ጥረቶችን፣ ለአላህ ባለው ፍራቻና ዕውቀት የሚተማመንባቸውን ሰዎች በመጠየቅ የተደረጉ ሙከራዎችን አንስቶ መወያየት ይቻላል።

የመጠዘኛ ጥያቄዎች

1. በመልክተኛውና በደጋግ ሰለፎች መመራት እንዴት እንደሆነ አብራራ።
2. "የሰው ልጅ የሥራው ትክክለኛነት የሚለካው በእስልምናው ሲዘወትርና የአላህን መመሪያ በሕይወቱ ተግባራዊ ሲያደርግ እንጅ እርሱ ዘንድ ባለው ዕውቀት ልክ አይደለም" ይህንን አብራራ።
3. በመልክተኛውና በደጋግ ሰለፎች መከተልን ምን ያክል ተግባራዊ እንደዳደረግክ በተለይ ያሉብህን ድክመቶች፣ ምክንያቶቹንና የማከሚያ መንገዶቹን በመዘርዘር እራስህን ገምግም።

የመረጃ ምንጮች

መንሃጅ አል-ሙእሚን ፊ ሸርሕ ኡሱል አል-ዒሽሪን - ሸይህ ወሸሊ

አል-ወጂይዝ ፊ ኡሱል አል-ፊቅህ - ዶ/ር አብዱል ከሪም ዘይዳን

አት-ተህዚብ መዳሪጅ አስ-ሳሊኪን - አል-ኢማም ኢብን አል-ቀይም

ጃሚዕ አል-ዑሉም ወአል-ሂከም - ኢማም ኢብኑ ረጀብ አል-ሀንበሊይ

ዐውን አል-መብዑድ ፊይ ሸርሕ መትን አቢ ዳውድ ኢብኑ ጠይብ ሙሐመድ

ኡሱል አል-ዐቂዳህኡስታዝዐብዱል - ሙንዒም ሷሊሕ አል-ኢዚይ

አል ቁድወቱ ዐላ ጠሪይቅ አል-ደዕዋህ - ኡስታዝ ሙስጠፋ መሸኹር

ኢህያእ ዑሉሙዲን-ባብ አል-ዒልም - አል-ኢማም አል-ጋዛሊ

አዝ-ዙህድ - ኡስታዝ ኢብን አል-ሙባረክ